በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

የ2015/2016 ኦዲት ዓመት

የፌዴራል ዋና ኦዲተር ሪፖርት

አጠቃላይ ዘገባ

ጥራዝ 2

ሰኔ / 2016

አዲስ አበባ

ማውጫ

ገጽ

- መግቢያ……………………………………………………………………………… 3
- የ2015/2016 ኦዲት ዓመት ሥራዎች ዕቅድና አፈጻጸም………………………… 7
- የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሣቦች…. 7
- የክዋኔ እና የአካባቢያዊ ኦዲት ዋና ዋና ግኝቶች እና የማሻሻያ
  ሃሳቦች…………………………………………………………………………. 56
- የድጋፍና ድጎማ ኦዲት ዳይሬክቶሬት የ2015/ 2016 ኦዲት ዘመን የዕቅድ
  ክንውን እና ዋና ዋና ኝቶች……………………………………………….. 237
- ልዩ ኦዲት ………………………………………………………………… 250
- የሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን የ2015 በጀት ዓመት የሥራ
  ክንውን………………………………………………………………………. 251
- አባሪዎች………………………………………………………………….… 283

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

በ2015/2016 የኦዲት ዓመት የተከናወኑ ኦዲቶች

ዓመታዊ ሪፖርት እና የመ/ቤቱ እቅድ አፈጻጸም

1. መግቢያ

የዋና ኦዲተር መ/ቤት መንግስት የሀገሪቱን ኢኮኖሚ በሚገባ ለመምራትና ለማስተዳደር የሚያስፈልገውን አስተማማኝ መረጃ ለማግኘትና በፌዴራል መንግስት መዋቅር ስር ባሉ መ/ቤቶች ውስጥ ተጠያቂነት ግልፅነትና መልካም አስተዳደር ለማስፈን አስተዋጽኦ ስለሚያደርግ በኢፌዴሪ ህገ-መንግሥት አንቀጽ 55/1 እና አንቀጽ 101/4 መሠረት በአዋጅ ቁጥር 982/2008 (1146/2011 እንደተሻሻለው) የሚከተሉት ዓላማዎች ለማሳካት እንደገና እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡

- የፌዴራል መንግሥት እቅዶችና በጀት በሚገባ ለመምራትና ለማስተዳደር የሚያስፈልገውን አስተማማኝ መረጃ ለማግኘት የሚረዳ የኦዲት ሥርዓትን ማጠናከር፣
- የፌዴራል መንግሥት ገንዘብና ንብረት በወጡት ህጎችና ደንቦች መሠረት መሰብሰቡን መጠበቁን እና በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን ማረጋገጥ እና የደረሰበትን ውጤት ለምክር ቤት ሪፖርት ማቅረብ፣
- የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች እና ድርጅቶች ላይ የፋይናንስ፣ የክዋኔ፣ የአካባቢ ጥበቃ፣ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፣ የቁጥጥር ኦዲቶች፣ ልዩ ኦዲቶችና ሌሎች ኦዲቶችን ማካሄድ፣
- አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የሂሳብ አያያዝና የኦዲት ሙያ እንዲያድግና እንዲጠናከር ጥረት ማድረግ፣
- በሂሳብ አያያዝና በኦዲት ሙያ ላይ ለተሰማሩት የክልልና የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች ሙያዊ ዕገዛና ምክር መስጠት፣

- የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች ሂሳብ የሚመረመርበት የኦዲት ደረጃ (ስታንዳርድ) ማውጣትና ተግባራዊ መሆኑን መከታተል፣

ናቸው፡፡

1.1. የመ/ቤቱ ስልጣንና ተግባር

ከላይ የተገለጹትን ዓላማዎች ለማስፈጸም እንዲችል የተሰጡት ሥልጣን፣ ተግባርና ኃላፊነቶች ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችንና ድርጅቶችን ሂሳብ ኦዲት ያደርጋል፣ ያስደርጋል፤
- የፌዴራል መንግሥት መስሪያ መ/ቤቶችና ድርጅቶችን የእንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ስርዓት አጠቃቀምና አስተዳደር ኦዲት ያደርጋል፣ ያስደርጋል፣
- የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች ያስገኙት ውጤት ሕጉን የተከተለ፣ ኢኮኖሚያዊ በሆነ አሠራር የተፈጸመ መሆኑን፤ተፈላጊውን ግብ መምታቱን ለማረጋገጥ እንደአስፈላጊነቱ የክዋኔ ኦዲት ያደርጋል፣ ያስደርጋል፤
- የመንግሥትንና የሕዝብን ጥቅም ለማስጠበቅ ሲባል የግል ወይም የሕዝባዊ ድርጅቶችን ኦዲት ያደርጋል ፤ ያስደርጋል፣
- በፌዴራል መንግሥቱ መ/ቤቶችና ድርጅቶች የተለገሱ እርዳታዎችን ወይም ስጦታዎችን እንዲሁም ብድርን ኦዲት ያደርጋል፤ ያስደርጋል፣
- በዚህ መሰረት ያከናከነውን የኦዲት ውጤት እንደነገሩ ሁኔታ ለመ/ቤቱ ወይም ለድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ያሳውቃል፡፡ የፌዴራል ዋና ኦዲተሩ ውጤት ወንጀል መፈጸሙን የሚያሳይ ሆኖ ሲገኝ ለሚመለከተው አካል ወዲያውኑ ያሳውቃል፡፡
- ጉዳዩ ከሚመለከታቸው መሥሪያ ቤቶች ጋር በመመካከር የሂሣብና የንብረት ኦዲት ስርዓትና ደረጃን የሚመለከቱ መመሪያዎችን ያወጣል፤

- አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የማናቸውም የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤት የውስጥ ኦዲተሮች የመ/ቤታቸውን ሂሳብና ንብረት በመመርመር ውጤቱን እንዲገልጹለት ሊያድረግ ይችላል፤

- ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር እንዳአስፈላጊነቱ ለውስጥ ኦዲተሮች ስልጠና ይሰጣል፤

- አንድ ሂሳብ ወንጀል ባለበት ሁኔታና ታማኝነት በጎደለው አኳኃን መያዙን ለማመን ምክንያት ያለው እንደሆነ፤ ይህን ሂሳብ የሚመለከቱ ጽሑፎች፤ መዘክሮች፤መዝገቦች ሰነዶችና ሌሎች ተያያዥ ነት ያላቸው መረጃዎች ላይ ያሸጋል፤

- የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ስለገንዘብ አያያዝ፤አጠባበቅ፤ የሂሳብ አያያዝና ንብረት አስተዳደር በሚያዘጋጀው መመሪያዎች ላይ አስፈለጊውን ምክር ይሰጣል፤

- ከሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸው ጋር የፌዴራልና ክልል መ/ቤቶች ጋር በመተባበር የኦዲትና የሂሣብ አያያዝ ሙያ ትክክለኛውን ፈር ይዞ እንዲዳብር ጥረት ያደርጋል፤

- የፌዴራል መንግስት ለክልል መንግስታት የሚሰጠውን የበጀት ድጋፍ እና ልዩ ድጎማዎችን ኦዲት ያደርጋል፡ ያስደርጋል።

- ከክልል የኦዲት መ/ቤቶች እና ቁጥጥር ቢሮዎች ጋር የኦዲት ተግባር የሚዳብርበትን ሁኔታ በተመለከተ የቅርብ የስራ ግንኙነትና ትብብር ያደርጋል።

የሚሉት ናቸው፡፡

1.2. <u>የሪፖርቱ ዓላማ</u>

ሪፖርቱ መ/ቤቱን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 (1146/2011 እንደተሸሻለው) በአንቀጽ 13/1 እስከ 4 መሠረት በ2015/2016 የኦዲት ዓመት ባከናወናቸው ኦዲቶች የታዩ ዋና ዋና ግኝቶች፣ በምክር ቤቱ ለ2015 በጀት ዓመት የተፈቀደው በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉንና ተፈላጊውን ውጤት ማስገኘቱን

ለማረጋገጥና በሪፖርቱ በቀረበው መረጃ መሠረት ተገቢውን ውሣኔ ለመስጠት እንዲያስችለው፤ እንዲሁም መ/ቤታችን በአዋጅ የተሰጠውን ኃላፊነትና ተግባር በተሻለና በተጠናከረ ሁኔታ ለመፈጸም ባደረገው የሥራ እንቅስቃሴ የ2015/2016 የኦዲት ዓመት እቅድ አፈፃፀም ለማመልከት ነው፡፡

በሪፖርቱ ውስጥ የተሰጡ አስተያየቶችና የመደምደሚያ ሃሳቦች መሰረት ያደረጉት የፌደራል መንግስት መ/ቤቶችን የ2015 በጀት ዓመት ሒሳብ ኦዲት፤ የክዋኔ ኦዲቶች፣ የኢትዮጵያ መንግስት እና የዓለም ባንክ ባደረጉት ስምምነት መሠረት የፍትሃዊነት መሠረታዊ አገልግሎት ለሁሉ ዓቀፍ የዕድገት ተጠቃሚነት ፕሮግራም (Enhancing Shared Prosperity through Equitable Service-ESPES) የተከታታይ እና የማረጋገጫ ኦዲት ሲሆን፣ የመንግሥት ልማት ድርጅቶችን በተመለከተ በሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽንና በሌሎች የሙያው ፈቃድ በተሰጣቸው የተፈቀደላቸው የኦዲት ድርጅቶች ኦዲት ተደርገው የተገኘውን ውጤት እና በመ/ቤታችን የተከናወኑ የልዩ ኦዲት ሥራዎችን ነው፡፡

የኦዲት ሪፖርቱ የኦዲቱ ሥራ ከተጠናቀቀ በኋላ ከመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ጋር በሚደረግ የመውጫ ስብሰባ ላይ የተነሱ ሃሣቦችን ያካተተ፣ ለእያንዳንዱ ኦዲት ተደራጊና ተቆጣጣሪ መ/ቤት እየተላከ፣ በአዋጅ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ መልስ የሰጡትን ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶችንና ድርጅቶችን መልስ እና አስተያየት ያገናዘበ ነው፡፡ ኦዲቱ የተካሄደው በአብዛኛው የተለመደውን የአልፎ አልፎ ወይም የናሙና ኦዲት ስልት በመከተል፤ እንዲሁም እንደ ኦዲቱ አስፈላጊነት እና ብዛት ሁኔታ እየታየ በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው የዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን መሰረት በማድረግ ሲሆን ለኦዲቱ መሰረት የሆኑት የመንግሥት ሂሣብ አያያዝ ስርዓት መሠረት በማድረግ እና በኦዲት ተደራጊ የመንግሥት መ/ቤቶችና የልማት ድርጅቶች ያቀረቧቸው የሂሣብ መዛግብት እና ሰነዶች፤ እንዲሁም የሂሣብ መግለጫዎችና ማብራሪያዎች ናቸው፡፡

በዚህ ሪፖርት መ/ቤታችን ባለው የሰው ኃይልና በተመደበለት በጀት በ2015/2016 የኦዲት ዓመት ያከናወናቸው ሥራዎች በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ተለይተው ቀርበዋል፡፡ በመጀመሪያው የ2015/2016 የኦዲት ዓመት የመ/ቤቱ ኦዲት ዕቅድና

አፈፃፀም፣ ዋና ዋና የድጋፍ ስራዎች ክንውን ሪፖርት፣ መ/ቤቱን ያጋጠሙ ችግሮችና አጭር ማጠቃለያ ቀርቧል።

ሁለተኛው የ2015 በጀት ዓመት ሂሳብ የኦዲት ሥራን በተመለከተ የቀረበው ሪፖርት የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የፋይናንስና የሕጋዊነት ኦዲት ዋና ዋና ግኝቶች እና የክዋኔና የአካባቢ ኦዲት ፣ እንዲሁም የኢትዮጵያ መንግስት እና የዓለም ባንክ ባደረጉት ስምምነት መሠረት የፍትሃዊነት መሠረታዊ አገልግሎት ለሁሉ ዓቀፍ የዕድገት ተጠቃሚነት ፕሮግራም (Enhancing Shared Prosperity through Equitable Service-ESPES) የተከታታይ እና የማረጋገጫ ኦዲት) የተከታታይ እና የማረጋገጫ ኦዲት የማረጋገጥ ሥራዎች የተከናወኑ እና በገንዘብ ሚኒስቴር ደረጃ ተጠቃሎ የተዘጋጀውን የፕሮግራሙን ሂሳብ ኦዲት ውጤት ያጠቃልላል፡፡

ሦስተኛው ደግሞ የሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን የሥራ እንቅስቃሴ እና በኮርፖሬሽኑና በግል ኦዲት ድርጅቶች የተከናወኑ የመንግስት ልማት ድርጅቶችና በመንግስት እና በልማት አጋር ድርጅቶች ትብብር የሚተገበሩ ፕሮጀክቶች የኦዲት ውጤትን የሚመለከት ነው፡፡

2. የ2015/2016 ኦዲት ዓመት ሥራዎች ዕቅድና አፈጻጸም

2.1 የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት ዕቅድና ክንውን

1. በ2015 በጀት አመት በመ/ቤቱ አደረጃጀት መሠረት የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችን ኦዲት የሚያደርጉ ስድስት ኦዲት ዳይሬክቶሬቶች፣ የክልሎች ድጋፍና ድጎማ ሂሳብ ኦዲት የሚያደርግ አንድ ዳይሬክቶሬት እና በ1 የልዩ ኦዲት ዳይሬክቶሬት በአጠቃላይ በ8 ዳይሬክቶሬት የተዋቀረ ሲሆን፣ ከካቲት /2015 እስከ ጥር 30/2016 ድረስ በ2015 በጀት ዓመት ሂሳብ አቅራቢ ከነበሩት 173 የፌዴራል መንግሥት ባለበጀት መ/ቤቶች መካከል 162 መ/ቤቶችን እና 58 ቅርንጫፎች በመስሪያቤታችን የተቀሩትን 11ቹን ደግሞ በሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን ኦዲት በማስደረግ የኦዲት ሽፋኑን 100% ለማስቀጠል ታቅዶ የነበረ ቢሆንም 10 መ/ቤቶች እና 4 ቅርንጫፎች በጸጥታ ምክንያት ኦዲቱ ተጀምሮ የተቋረጠ ሲሆን 1 መ/ቤት ቢሮ ባለማቅረቡ አፈጻጸሙም የ151 መ/ቤቶች፣ አንድ የተጠቃለለ የመንግስት ሂሳብ እና 54 ቅርንጫፎች ኦዲት ተጠናቆ ሪፖርቱ ወጪ

የተደረገ ሲሆን ባጠቃላይ የመንግሰት ሂሳብ ኦዲትን ጨምሮ 94.44% መፈጸም ተችሏል።

የኦዲት ሪፖርቶቹም ከግኝታቸው ባህርይ አንፃር የተሰጡት የኦዲት አስተያየት ከ2013 እና 2014 በጀት ሂሳብ ኦዲት ከተሰጠው የኦዲት አስተያየት ጋር በማነፃፀር እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

መግለጫ /የተሰጠው የኦዲት አስተያየት/	**ኦዲት የተደረጉ ሂሳቦች ብዛት**		
	2013	2014	2015
ነቀፌታ የሌለበት አስተያየት	51	72	79
ከጥቂት ጉድለቶች በስተቀር በአጠቃላይ አጥጋቢ ሆነው የተገኙ	73	65	50
አስተያየት ለመስጠት ያልተቻለባቸው መ/ቤቶች	8	6	15
የጎላ ችግር ያለባቸው ሆነው በመገኘታቸው ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት የተሰጠባቸው	39	20	7
በፀጥታ እና በሌሎች ምክንያቶች ኦዲቱ ያልተሰራ	4	1/3*	10
የመውጫ ስብሳባ ያልተካሄደባቸውና ለስራ አመራር ሪፖርት ምላሽ ያልሰጡ በመሆኑ በዚህ ሪፖርት ያልተካተቱ	2		
ሂሳባቸውን በወቅቱ ስላልዘጉ ኦዲት ያልተደረጉ	1		
ቢሮ ባለመስጠት ኦዲት ያልተደረጉ	1		1
ድምር	**179**	**164/3***	**162**

*-ቅ/ጽ/ቤት

2.2 የመንግሥት ልማት ድርጅቶች፣ ፕሮጀክቶችና የእርዳታ ሂሣቦች ላይ የተከናወነው የፋይናንስ ኦዲት

በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና በግል ኦዲት ድርጅቶች የተከናወኑ እስከ የካቲት 30/2016 ዓ.ም ሪፖርታቸው ለመ/ቤታችን የቀረቡ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችና በሽርክና የተቋቋሙ ድርጅቶች ሪፖርት በቁጥር 47 (የተለያዩ ዓመታት በጀት ዓመት ሪፖርትን በመቁጠር) እንዲሁም በኢትዮጵያ መንግሥትና በልማት አጋር ድርጅቶች የጋራ ትብብር የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ሂሳብ ኦዲት 107 በድምሩ 105 (ይህ ቁጥር በበጀት ዓመቱ የሁለት እና ከዚያ በላይ በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት የተደረገ ድርጅቶች ወይም ፕሮጀክቶች እያንዳንዱን ሪፖርት በመቁጠር የተወሰዱ) ናቸው፡፡

ለመ/ቤታችን ከደረሱን የመንግስት የልማት ድርጅቶች የኦዲት ሪፖርቶች በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሠረት ሲተነተን አጥጋቢ ሆነው በመገኘታቸው ነቀፌታ የሌለበት (Unqualified Opinion) አስተያየት የተሰጠባቸው 26፣ ከጥቂት ጉድለቶች ወይም ስህተቶች በስተቀር በአጠቃላይ አጥጋቢ ቢሆንም ነቀፌታ ያለበት (Qualified Opinion) አስተያየት የተሰጠባቸው 13፣ አቋም ለመውሰድ የማይቻል በመሆኑ አስተያየት ያልተሰጠባቸው (Disclaimer Opinion) 5 እና ተቀይነት የሚያሳጣ የኦዲት አስተያየት የተሰጣቸው (Adverse opinion) 3፣ ሲሆን የፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች ኦዲቶች በኦዲት አስተያየት ሲተነተን አጥጋቢ ሆነው በመገኘታቸው ነቀፌታ የሌለበት (Unqualified Opinion) አስተያየት የተሰጠባቸው 80፣ ከጥቂት ጉድለቶች ወይም ስህተቶች በስተቀር በአጠቃላይ አጥጋቢ ቢሆንም ነቀፌታ ያለበት (Qualified Opinion) አስተያየት የተሰጠባቸው 19፣ አቋም ለመውሰድ የማይቻል በመሆኑ አስተያየት ያልተሰጠባቸው (Disclaimer Opinion) 3 እና ተቀይነት የሚያሳጣ የኦዲት አስተያየት የተሰጣቸው (Adverse opinion) 3 ናቸው፡፡

የክዋኔ ኦዲትን በተመለከተ

መ/ቤታችን የፋይናንስና የሕጋዊነት (Regularity) ኦዲቱን ሽፋንና ጥራት በከፍተኛ ደረጃ በማሳደግ በሂደት ትኩረቱን በክዋኔ ኦዲት ላይ የማድረግ አቅጣጫን ለመከተል በተወሰነው መሰረት በመንግሥት መ/ቤቶች የተቀረፁ ኘሮግራሞችና ኘሮጀክቶች የተመደበላቸውን በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ ማዋላቸውን እና የታለመላቸውን ዓላማና ግብ በብቃትና ስኬታማ በሆነ መንገድ መምታታቸውን ለማረጋገጥ የክዋኔ ኦዲት ይከናወናል፡፡ በዚሁ

መሠረት በ2015/2016 የኦዲት ዓመት (Audit Calendar) በአራቱም ክዋኔ ኦዲት ዳይሬክቶሬቶች ከየካቲት/2015 እስከ ጥር 30/2016 የሚጠናቀቁ 32 አዳዲስ ኦዲቶችንና 12 ክትትል ኦዲት በድምሩ 44 ኦዲቶችን ለማከናወን በዕቅድ ተይዞ ነበር፡፡ ዓመታዊ አፈጻጸሙም 32 አዳዲስ ኦዲቶችና 11 ክትትል ኦዲቶችን በድምሩ 43 ኦዲት የክዋኔና የአካባቢ ኦዲቶች የተሰሩ ሲሆን አንድ የክትትል ኦዲት በሰው ሃይል እጥረት ምክንያት ያልተሰራ በመሆኑ አፈፃፀሙ ከእቅድ አንፃር በመቶኛ 97.72% መፈጸም ተችሏል፡፡ ከእነዚህም መካከል 8 አዳዲስ እና 3 ክትትል ኦዲት አካባቢ ኦዲቶች ናቸው፡፡

በተጨማሪም በዘላቂ ልማት ግብ የክዋኔ ኦዲት ላይ የሠራተኞችን አቅም ለመገንባትና ክህሎታቸውን ለማዳበር ከአሜሪካ ዋና ኦዲተር የልቀት ማዕከል እና ከAFROSAI-E ጋር በጋራ በመሥራት ከፆታ እኩልነት ጋር በተያያዘ የሴቶችና ህጻናትን በሚመለከት የተገቡ ዓለምአቀፍ ውሎች ተፈጻሚነትን የክዋኔ ኦዲት ተከናውኗል፡፡ በመሆኑም በውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር የከተሞች የመጠጥ ውኃ አቅርቦትና ተደራሽነት ላይ፣ የከተሞች ፍሳሽ አገልግሎት፣ የአደጋ ሥጋት መልሶ መቋቋም፣ የመድሃኒት አቅርቦት እና ስርጭት ወዘተ ሥራዎች ተሰርተዋል፡፡

በኢንፎርሜሽን ሲስተም ሰርቪስ ኦዲት ማኑዋልና የስራ ወረቀቶች ላይ ግምገማዎችን የማከናወንና ወቅቱን ተከትለው ሊሻሻሉ የሚገባቸውን አካባቢዎች የመለየት ስራዎችን በማሻሻል 1 የኢንፎርሜሽን ሲስተም ኦዲት ለማድረግ ታቅዶ አንድ ኦዲት በጅማ ዩኒቨርስቲ ላይ ማካናወን ተችሏል፡፡

አጠቃላይ የመንግሥት ገቢና ወጪ ሂሣብ ኦዲት

በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 982/2008 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ከገንዘብ ሚኒስቴር በተላከው የ2015 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት አጠቃላይ የገቢና የወጪ ዝርዝር መግለጫ ላይ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ገቢና ወጪ፣ ሀብትና ዕዳ እንዲሁም የመንግሥት ገንዘብ ነክ የሆኑ መረጃዎችን ኦዲት በማድረግ ሪፖርቱ ለሚመለከታቸው አካላት ተልኳል፡፡

የ'ESPES ፕሮጀክት የተከታታይ ኦዲቶች በተመለከተ

የኢትዮጵያ መንግሥትና የዓለም ባንክ ባደረጉት ስምምነት መሠረት የፍትሃዊነት መሠረታዊ አገልግሎት ለሁሉ ዓቀፍ የዕድገት ተጠቃሚነት ፕሮግራም (Enhancing Shared Prosperity through Equitable Service-ESPES) የተከታታይ እና የማረጋገጫ ኦዲት ሲሆን፣ የተከታታይ ኦዲት በየሩብ ዓመቱ፣ የማረጋገጫ ኦዲት ደግሞ በገንዘብ ሚኒስቴር በተጠየቀ ጊዜ እየተከናወነ በስምምነቱ መሠረት ሪፖርቱ ለገንዘብ ሚኒስቴር እና ለዓለም ባንክ በወቅቱ እንዲደርስ ተደርጓል፡፡ ይህ ኦዲት የሚሸፍናቸው ሴክተሮች የመሠረታዊ አገልግሎት አቅራቢ የሆኑትን በወረዳና በክልል ደረጃ የሚገኙ የጤና፣ የትምህርት፣ የግብርናና ተፈጥሮ ሀብት፣ የንጹህ ውሃ አቅርቦት እና የገጠር መንገድ ሴክቶሮችን ነው፡፡

ስለሆነም የፍትሃዊነት መሠረታዊ አገልግሎት ለሁሉ ዓቀፍ የዕድገት ተጠቃሚነት ፕሮግራም (Enhancing Shared Prosperity through Equitable Service-ESPES) የተከታታይ እና የማረጋገጫ ኦዲት ዋና ትኩረት በእነዚህ መሠረታዊ አገልግሎት አቅራቢ መ/ቤቶች (በወረዳና በክልል ደረጃ) የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ላይ በመሆኑ፣ እየተጠቃለለ የሚላከው ኦዲት ሪፖርት ግኝቶች የሚያተኩረው በገንዘብ መጠን (quantitative amount) ላይ ሳይሆን በዓይነት ላይ (Qualitative) ነው፡፡

የመሠረታዊ አገልግሎቶች ማስከበር በፕሮጀክት ተከታታይ ኦዲትን በተመለከተም በበጀት ዓመቱ 313 የተከታታይ፣ 23 የማረጋገጫ (Verification) እና 1 ዓመታዊ ማጠቃለያ ጠቅላላ ድምር 337 ኦዲቶችን ለመሥራት የታቀደ ሲሆን በበጀት ዓመቱ አፈጻጸሙም 320 የተከታታይ ኦዲት፣ 24 የማረጋገጫ (Verification) እና 1 ዓመታዊ ማጠቃለያ ጠቅላላ ድምር 345 (102.37%) ኦዲቶችን ማከናወን ተችሏል፡፡

የኦዲት ጥራትና ሌሎች የኦዲት ሥራዎች

በመ/ቤታችን የሚከናወኑ ኦዲቶች ደረጃቸውንና ጥራታቸውን ጠብቆ እንዲሠሩ የእቅዳችን አንዱ የትኩረት አቅጣጫ ሲሆን የኦዲት ጥራት የሥራ ክፍልም ይህንኑ መሠረት በማድረግ የቅድመ እና የድህረ ኦዲት ቁጥጥር ሥራዎችን ለማከናወን አቅዷል፡፡ በዚህም መሠረት የኦዲት አገልግሎት፣ ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የአሰራር ሂደት፣ የላቀ መሪነት እና የላቀ መልካም ግንኙነትና ቅንጅት ያለው ተቋም ለማድረግ የታቀዱት

ስትራቴጅክ ዓላማዎች ስኬታማ እንዲሆኑ ኦዲቱ በISSAI እና በAFROSAI-E Regularity Audit Manual (RAM) መሰረት መከናወኑን ማረጋገጥ ነው፡፡

በመሆኑም የጥራት ማረጋገጥ ክለሳ ሥራን በተለያዩ የኦዲት ደረጃዎች /Audit phases/ ያሉትን የቅድመ ኦዲት /Pre engagement audit/፣ የመ/ቤቱን አጠቃላይ ሁኔታዎች መረዳት /Understanding the entity & materiality የሥጋት ዳሰሳና ምላሽ ሥራ (Risk Assessments and Response on Progress)፣ በተሰሩ በእያንዳንዱ የኦዲት ደረጃ የቅድመ እና ድህረ ኦዲት ጥራት ቁጥጥር ሥራን ለማጠናከር እና ለመተግበር ከ6 የፋይናንሻል ኦዲት ዳይሬክቶሬቶች በ15 የኦዲት ፋይሎች ላይ የቅድመ ሪፖርት የጥራት ክለሳ እና ክትትል (Follow Up) ለማድረግ ታቅዶ (ፕሪኢንጌጅመንት፣ የመ/ቤቱን አጠቃላይ ሁኔታ መረዳት እና የስጋት ደሰሳና ምላሽ ስራ) ላይ የ14 መ/ቤቶች የጥራት ክለሳ ማጠናቀቅ የተቻለ ሲሆን፤ በሌላ በኩል ደግሞ ከ6 የፋይናንሻል ኦዲት ዳይሬክቶሬቶች 6 የኦዲት ፋይሎች ላይ የድህረ ሪፖርት የጥራት ክለሳ እና ክትትል ስራዎች ተከናውኗል፡፡

የተጠናቀቁ የኦዲት የሥራ ወረቀቶች በስታንዳርዱ መሰረት ተዘጋጅተውና ተደራጅተው በተቀመጠው የጊዜ ሠሌዳ መቅረባቸውን/መቀመጣቸውን ክትትል ለማድረግ ታቅዶ በ2014/2015 የኦዲት ሪፖርቶች እና የ2015/2016 የኦዲት በጀት ዓመት የስራ ወረቀቶች በስታንዳርዱ መሠረት መሰራታቸውን የማረጋገጥ ስራ ተሰርቷል፡፡ በተጨማሪም በ 10 የክልል ዋና አደተር መ/ቤቶችና እና በ2 የከተማ አስተዳር ዋና ኦዲተሮች የተቋም የጥራት ክለሳ በማካሄድ በተለይ በIndependence and Legal Framework ላይ ዳሰሳ ተሰርቷል።

እያንዳንዱ የኦዲት ዳይሬክቶሬት ለጥራት ክፍተቶች የድርጊት መርሃ ግብርና የማስተካከያ ሪፖርቶችን በዓመት ሁለት ጊዜ የሥራ ወረቀቶቹን በመገምግም ማስተካከያ እንዲያደርጉ የግምገማ ሪፖርት ማድረግ ተችሏል፡፡

የመ/ቤታችን ዋና ዋና የድጋፍ ዘርፍ አፈጻጸም

የለውጥና የመልካም አስተዳደር ሥራዎችን በተመለከተ

የሰራተኛውን የስራ አፈፃፀም በተሻለ መለካት የሚችል የአፈፃፀም የስራ አመራር መሳሪያዎች (Performance Management & Appraisal) ተዘጋጅቷል በተጨማሪም የተቋሙ ስትራቴጂያዊ የትኩረት አቅጣጫዎች ውጤታማነት ለመለካት እንዲያስችል የአፈፃፀም አመልካቾች (key Performance Indicators) ተዘጋጅቶ ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል፡፡ የሠራተኛዉ አፈፃፀም በየ6 ወሩ ሀምሌና ጥር ወር ላይ እየተሞላ ለደረጃ ዕድገት እና ለትምህርና ሥልጠና ዉድድር በሚደረግበት ወቅት በማወዳደሪያነት እንዲይዝ ተደርጓል ከእያንዳንዱ ዳይሬክቶሬት የተሻለ አፈጻጸም ያላቸው ሠራተኞች ተመርጠዉ ዕውቅናና ማበረታቻ ሰርትፍኬት እንድያገኙ ተደርጓል፡፡

በሌላ በኩል ከየካቲት/2015 እስከ ጥር/2016 በበጀት ዓመቱ ውስጥ የተለያዩ አገልግሎት ለማግኘት ወደ መ/ቤታችን የመጡ ወንድ 290 ሴት 121 በድምሩ 411 አገልግሎት ያገኙ ሲሆኑ ሁሉም እንግዶች በአግባቡ ከመ/ቤቱ የተለያዩ አገልግሎቶችን በማግኘት የተስተናገዱ ናቸው፡፡

2.2. የሥነ-ምግባር ሥራዎችን በተመለከተ

ከሠራተኞች ሥነ ምግባር አንጻር የINTOSAI እና የመ/ቤቱ ሠራተኞች የሥነ-ምግባር መመሪያና መርሆዎችን ከመተግበር አንጻር ኦዲተሮች በየቡድናቸው የሥነ-ምግባር መግለጫዎችን (Code of ethics Declaration)፣ የኦዲተሮች መሠረታዊ ሥራ ስምምነት (Team Agreements)፣ የኦዲት አድራጊውን እና የኦዲት ተደራጊውን መሥሪያ ቤት ሥራ አመራር ግዴታና ኃላፊነት መግለጫ (Engagement Letter) እና በተለያዩ ቡድኖች ውስጥ እያንዳንዱ ኦዲተር ባለው የትምህርት ደረጃ፣ የሥራ ልምድና በተሰጠው ደረጃ መሠረት ሊሰራ የሚችለውን ሥራ የቡድኑ አባላት የሥራ ክፍፍል (competence matrix) እንዲሞላ ተደርጓል፡፡

የመ/ቤቱንም ሥነ ምግባር እና የስጋት ተጋላጭነት ለመቀነስ በመስክ ጭምር የክትትል (supervision) ሥራ በተከታታይነት በማከናወን የስነምግባር ችግሮችን ለመለየት መረጃ በማሰባሰብ የዳሰሳ ስራ ተሰርቷል፡፡

አዳዲስ ለተቀጠሩ 56 ሰራተኞች በሰራተኞች ስነምግባርና የሙያ ስነ ምግባር ዙሪያ ግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና የተሰጠ ሲሆን፣ ለአምስት ተከታታይ ቀናት የሙስና ስጋት ጥናት አስፈላጊነት፣ የሀብት ምዝገባ አዋጅ፣ የሙስና ወንጀል ለመደንገግ የወጣ አዋጅ፣ የሙስና ጥቆማ መረጃ አያያዝና አለማቀፍና አገር አቀፍ የፀረ-ሙስና ስምምነት አፈጻጸም ዙሪያ ለሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ በመ/ቤቱ የጥቆማ መቀበያ ሳጥን፤ የኢሜል አድራሻ ስርዓቱ ተዘርግቶ ጥቆማ ያላቸው አካላት የተዘረጋውን ስርዓት በመጠቀም ጥቆማ እንዲያቀርቡ ሁኔታዎች ተመቻችቷል፡፡

2.3 ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች (Crosscutting issues) በተመለከተ

በፋይናንስ እና ህጋዊነት እንዲሁም በክዋኔ ኦዲቶች ለሴቶች፤ ወጣቶች፣ ለአካል ጉዳተኞችና ለአረጋውያን ወዘተ በህግ የተጠበቁ መብቶች ተጠቃሚነትና የአገልግሎት ተደራሽነት በተመለከተ ሁሉም የሥራ ክፍሎች የሥርዓተ ፆታ ጉዳይን የዕቅዳቸው አካል አድርገው እንዲያቅዱና በኦዲቱ ትኩረት ሰጥተዉ እንዲያዩት ተደርጓል ፡፡

ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን የመ/ቤታችንን ሴት ሠራተኞች ተጠቃሚ ለማድረግ በተደረገው ጥረት በግማሽ ክፍያ በማስተርስ፣ በዲግሪ፣ ሙያ እና ቴክኒክ ደረጃዎች 54 ሴቶች የትምርት ዕድል ያገኙ ሲሆን ለ40 ሴት ሠራተኞች የንግድ ክህሎት፣ የስራ ፈጠራና ስርዓተ-ፆታ በሚሉ ርዕሶች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

በመ/ቤቱ የህፃናት ልጆች ማቆያ አገልግሎት በማዘጋጀት እና 2 ተንከባካቢ ነርሶችን በመቅጠር 12 ሕፃናት (7 ወንድና 5 ሴት) የቀን እንክብካቤ ማቆያ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

የገና በዓልን ምክንያት በማድረግ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 9 ነዋሪ ለሆኑ 30 አካል ጉዳተኞችና 80 አረጋዊያን የአልባሳት ስጦታ ተበርክቷል፡፡

የ2016 ዓ.ም አዲስ ዓመት በዓልን ምክንያት በማድረግ 75 ለሚሆኑ የመ/ቤቱ ሠራተኞች ከሰራተኛው የመዝናኛ ክበብ በተገኘ ገቢ የብር 187,500 ድጋፍ ተደርጓል፡፡

ሴቶችን አመራርነት ደረጃ ከማምጣትና ከማብቃት አንጻር በማኔጅመት ደረጃ 62 ማናጅሜንት አባላት ውስጥ 20 (32%) የሚሆኑት ሴቶች እንዲሆኑ በማድረግ ድርሻውን

ከፍ የማድረግ ሥራ የተሰራ ሲሆን በWomen in leadership፣ ሥርዓተ ጾታ ማካተት፣ የሥራ ፈጠራ፣ ቁጠባና የህይወት ክህሎት ሥልጠናዎችንም እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

በሌላ በኩል በዚህ ዓመትም ዓለም አቀፍ የሴቶችና የፀረ-ጾታ ጥቃት፣ የአካል ጉዳተኞች፣ ወጣቶችና የህፃናት ቀን እንደሁም የኤች አይ. ቪ. ኤድስ ቀናት በተለያዩ ትምህርታዊና የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት ተከብሯል፡፡ በተጨማሪም በየ 2 ወሩ በመደበኛነት የሚካሄደው የመ/ቤቱ ሴት ሠራተኞች የልምድ መለዋወጫ መድረክ አሁንም ቀጥሎ በመካሄድ ላይ የሚገኝ ሲሆን፣በ 119 ሴት ሠራተኞች የእናት ገንዘብ ቁጠባና የብድር አገልግሎት ህጋዊ ሰዉነት እንዲያገኝ እና እንዲቋቋም በማድረግ የካፒታል መጠኑ 529,722.61 የደረሰ ሲሆን ከዚህም ሴት ሠራተኞች አባላት የብድር አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡

የስራ አካባቢን ምቹ ከማድረግ አንጻር የሠራተኞች ክበብ በተመጣጣኝ ዋጋ የምግብ አገልግሎት ለሰራተኞች ሁሌም እንደሚደረገዉ በዚህ አመትም አገልግሎቱ እየቀረበ ሲሆን የመሠረታዊ ሸቀጣ ሸቀጦችን እና ሌሎችንም ግብዓቶች በተመጣጣኝ ዋጋ ለሠራተኛዉ በማቅረብ የኑሮ ዉድነቱን ጫና ለማገዝ ጥረት ተደርጓል፡፡

ሁሌ እንደሚደረገዉ በዚህ አመትም የመስክ የሥራ ድልድል ሲደረግ ለሴት ኦዲተሮች ቅድሚያ በመስጠትና ምቹ የሆነ የሥራ ቦታ ምደባ እንዲያገኙ በማድረግ በስራ ስምሪት ድልድል ወቅት ቅድሚያ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

2.4. የአቅም ግንባታ ሥራዎችን በተመለከተ

ለኦዲት ስራም ሆነ ለሌሎች ስራዎች ቀጣይነት ያለዉ ስልጠና መስጠት መሰረታዊ ጉዳይ በመሆኑ በመስሪያቤታችን ራሱን የቻለ የሥልጠና ተቋም ለመገንባት በስትራቴጅክ ዕቅድ ተይዞ ቅድመ ሁኔታዎችን እያመቻቸን እንገኛለን፡፡ ነገር ግን ይህ ተግባራዊ እስኪሆን ድረስ በተቋሙ የተዘጋጁ 5 የሚሆኑ የስልጠና ክፍሎችን በማደራጀት ስልጠና እየሰጠን ብንቆይም ህንጻዉ በእድሳት ላይ ስለሆነ ባቅራቢያችን ከሚገኙ ተቋማት አዳራሾችን በመጠቀም እና በተለያየ ቦታዎች ስልጠናዎችን እየሰጠን የምንገኝ ሲሆን በእድሳት ላይ ባለዉ ህንጻ ቀድሞ ከነበረዉ ተጨማሪ 2 የስልጠና ክፍሎችን እንዲኖሩት በማድረግ በቅርቡ ተጠናቆ ስራ የሚጀምር ይሆናል፡፡

መ/ቤታችን አሁን ያለዉን የስልጠና ማዕከል ለማሳደግ Concept note በማዘጋጀት ለአሜሪካ ጂ.ኤ.ኦ (GAO) አስተያየት እንዲሰጡ እና ሌሎች አስፈላጊ ቴክኒካል ድጋፎችን ማድረግ እንዲችሉ የተላከ ሲሆን ይህን አህጉራዊ ተቋም ለመገንባት የክልሎች ተሳትፎ አስፈላጊ በመሆኑ ሁሉም የክልል ዋና ኦዲተሮችን በማሳተፍ ኢንስቲትዩቱን ለማቋቋም የሚያስፈልጉ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ በጋራ መድረክ ውይይት በማድረግ ይህን የሚያስተባብሩ ኮሚቴ አባላት በክልሎች እንዲመረጥ ተደርጎ ሥራው በሂደት ላይ ይገኛል፡፡

በመ/ቤቱ በ2016 ዓ.ም 30 ለድጋፍ ዘርፍ እና 39 ለኦዲት ዘርፍ በድምሩ 69 ዓይነት የሥልጠና ፍላጎቶችን በመለየት በማኔጅመንት በማጸደቅ የሥልጠና ካላንደር እንዲዘጋጅ ተደርጓል፤ በፀደቀው ካላንደር መሰረትም ስልጠናዎች ተሰጥተዋል፡፡

በዚህም መሰረት ለ6 ሠራተኞች የውጭ አገር ሥልጠና በተለያዩ ርዕሶች፣ በፋይናንስና ህጋዊነት ዘርፍ ለ352 ሠራተኞች፣ በክዋኔ እና አከባቢ ኦዲት 68 ሠራተኞች፣ በድጋፍ ዘርፍ 69 እና ለባለድርሻ አካላትና ክልል ዋና ኦዲተሮች ደግሞ 791 ሠራተኞች አቅም ግንባታ ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡

በሌላ በኩል 10 ሠራተኞች የኤሲሲኤ (ACCA) ትምህርት እድል በዚህ አመት ያገኙ ሲሆን በትምህርት ላይ ላሉ 20 PESAI-P ትምህርት ለሚማሩ ተማሪዎች ድጋፍና ክትትል ተደርጓል። ከዚህ 2 ሰራተኞች ያጠናቀቁ እና 18 በመማር ሂደት ላይ ናቸዉ፡፡

እንዲሁም በቀጣይ ወደ ትምህርት የሚገቡ 26 ሰራተኞች የሁለተኛ ዲግሪ ለመማር የመግቢያ ፈተና እንዲወስዱ የተደረገ ሲሆን በተጨማሪም 10 ሰራተኞች IDI (INTOSAI Development Initiative) በሚሰጠዉ Professional Education for SAI-P (PESAI-P) የአንድ ዓመት ትምህርት በኦን ላይን (online) ለመማር ተመርጠው ለሚያስተምረዉ ተቋም እንዲላክ ተደርጓል፡፡

እንዲሁም ለሌሎች አካላት አቅም ግንባታ ድጋፍ ከማድረግ አንጻር ለ7 ክልል ዋና ኦዲተር መ/ቤቶች፣ለ10 ኦዲት ተደራጊ ሚ/ር መ/ቤቶች ፣ በተጨማሪም ለፌዴራል ፖሊስ ወንጀል ምርመራ መምሪያ እና አቃቤ ህግ እና ለመንግስት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት የተለያዩ የአቅም ግንባታ ሥልጠና እና የግንዛቤ ማስጨበጫዎች ተሰቷል፡፡

የኦዲት ባለድርሻ አካላት የጋራ መድረክ እና መረጃዎችን ተደራሽ ማድረግን በተመለከተ

ከባለድርሻ አካላት ጋር የግንኙነት መስመሮችን (Communication Channel) ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመፍጠር እና ለማሻሻል (ከአዲስ ዘመን ጋዜጣ፣ ከኢትዮጵያ ብሮድካስቲን ኮርፖሬሽን የቴሌቪዥን ጣቢያ የአዲስ ገበያ እንግዳ፣ ከኤፍ.ኤም.107.8 ሬዲዮ ጣቢያ እና በአዲስ አበባ አይሲቲ ፓርክ በተካሄደ የችግኝ ተከላ ስነስርዓት ላይ ከተለያዩ ሚዲያ አካላት ጋር ለቃለ መጠይቅ ከጋዜጠኞች ጋር ግንኙነት መፍጠር) የግንኙነት ሥራዎች ተሰርቷል፡፡

በበጀት ዓመቱ በድምሩ 128 ዜናዎችን እና መረጃ እና ግንዛቤ ማስጨበጫ መልዕክቶችን በመ/ቤቱ የፌስ ቡክ ገጽ፣ የተለያዩ ተቋማዊ መድረኮችንና ሁነቶችን የሚመለከቱ በድምሩ 74 ዜናዎችን በተቋሙ ድረገጽ እና 48 በዲዛይን የተሰሩ ዜናዎች በአውትሉክ ለሠራተኞች የማሰራጨት ስራ ተሰርቷል፡፡

መ/ቤታችን ከባለድርሻ አካላት ጋር በየጊዜው የሚያካሂዳቸው ምክክሮች ለኦዲቱ ስራ መሠረታዊ ግብአት የሚያስገኙ መሆናቸውን በማመን በበጀት ዓመቱ የፌዴራል፣ የክልል፣ የከተማ አስተዳደር ዋና ኦዲተር መ/ቤቶች እንዲሁም የቋሚ ኮሚቴ አባላትና ሌሎች ባለድርሻ አካላት የተሳተፉበት 1 መደበኛ ዓመታዊ የምክክር ጉባኤና ዋና ኦዲተር መ/ቤቶቹን ብቻ ያሳተፈ 1 ሌላ ልዩ ጉባኤ ተካሂዷል፡፡

በበጀት ዓመቱ የቋሚ ኮሚቴውና ሌሎች ባለድርሻ አካላት በተሳተፉባቸው 36 ያህል የይፋዊ ህዝባዊ መድረኮችና በምክር ቤቱ በተካሄደ 1 የኦዲት ባለድርሻ አካላት ፎረም መድረክ ላይ የተሳተፍን ሲሆን ከቋሚ ኮሚቴው አባላት ጋር በጋራ የተቀናጁ 5 የመስክ ምልከታዎችንም ተከናውኗል፡፡

በኦዲት ግኝቶች መሰረት ውጤታማ የተጠያቂነትና የግልጸኝነት አሠራርን ለማጠናከር እና በዚሁ ላይ ለስራችን ተገቢ ከሆኑ ባለድርሻ አካላት ጋር ሊኖር የሚገባውን ቅንጅታዊ ስራ ውጤታማ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ሲሆን ቀደም ሲል ከሌሎች ተቋማት ጋር ካደረግናቸው በተጨማሪ በበጀት ዓመቱ ከፌዴራል የስነ ምግባርና ጸረ ሙስና ኮሚሽን ጋር መረጃን መለዋወጥ የሚያስችል የቅንጅታዊ ስራ የመግባቢያ ስምምነት (MOU)

ተፈራርመናል፤ ወደፊትም ከሌሎች ተገቢ አካላት ጋር ይህንኑ የቅንጅታዊ አሠራር ስምምነት ሂደት አጠናክረን እንቀጥላለን፡፡

አዲስ የምክር ቤት አባላትን፣ የቋሚ ኮሚቴ አባላትን፣ የኦዲት ኮሚሽንና ሌሎች አካላትን በኦዲት አሰራር ላይ ግንዛቤ ለማስጨበጥ በታቀደው መሰረት በመ/ቤታችን እየተከናወነ ባለው በክዋኔ ኦዲት ተቀባይነት በሚያሳጣና አስተያየት መስጠት ባልተቻለባቸው ኦዲቶች ሪፖርቶች ላይ ለመንግሥት ወጪ አስተዳዳር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት፣ የኦዲት ኮሚሽንና ሌሎች አካላትን በኦዲት አሰራር ላይ ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥልጠናዎች ተሰጥቷል፡፡

ከክልልና ከፌዴራል ከተሞች አስተዳደር ዋና ኦዲተር መ/ቤቶች ጋር የሰራናቸው የተቀናጁ አሠራሮችም ለበጀት ዓመቱ የኦዲት ስራ አፈጻጸማችን ጉልህ ድርሻ ነበራቸው፡፡ በዚህም መሠረት የክልልና የከተማ አስተዳደር ዋና ኦዲተር መ/ቤቶች ቁልፍ የስራችን አጋዥ መሆናቸውን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት እና በመላው ሀገሪቱ የሚከናወኑ ኦዲቶች ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁና ወጥ እንዲሆኑ ለማስቻል መ/ቤቱ ከሌሎች ዓለም አቀፍ የኦዲትና ሌሎች ተዛማጅ ተቋማት ያገኛቸውን ተሞክሮዎችና ልምዶች በመቀመር ለክልሎቹ ተከታታይ የአቅም ግንባታ ድጋፎችን እየሰጠና የልምድ ልውውጥ ተግባራትን ማካናወን ተችሏል፡፡

በተለይም የጊዜና የሀብት ብክነት ሲያስከትል የቆየውን የኦዲት ድግግሞሽ አሠራር ለማስቀረት ከክልሎች ጋር በተደረገ የጋራ ምክክር የነጠላ ኦዲት አዋጅና ማስፈጸሚያ መመሪያ ከወጣ ወዲህ የክልልና የከተማ አስተዳደር ዋና ኦዲተር መ/ቤቶች የነጠላ ኦዲትን በስራ ላይ እንዲያውሉና በመላው ሀገሪቱ ወጥ የሆኑ የኦዲት አሠራሮችን እንዲተገበሩ ለማድረግ እንዲቻል ቀደም ሲል ከተሰጡት በተጨማሪ በበጀት ዓመቱ በነጠላ ኦዲት ትግበራ ላይ 2 ስልጠናዎች መስጠት ተችሏል፡፡ በዚህም በበጀት ዓመቱ በድምሩ 4 የሚሆኑት ክልሎች በሙከራ ደረጃ የነጠላ ኦዲቱን ለመተግበር የቻሉ ሲሆን ውጤታማነቱንም በጋራ ባደረግናቸው መገምገሚያ መድረኮች ማረጋገጥ በመቻሉ በቀጣይ ትግበራው በሁሉም ክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች እንዲፈጸም በዓመታዊ የጋራ የምክክር ጉባኤያችን አቅጣጫ ተቀምጦና አስፈላጊ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች ተሰርተው ክልሎቹ ትግበራውን ጀምረዋል፡፡

ከዚህም ባሻገር በበጀት ዓመቱ ታትመው በመሰራጨት ላይ የሚገኙ በድምሩ 2800 ያህል ከ2011 እስከ 2014 በጀት ዓመት ዓመታዊ የኦዲት ሪፖርቶችን ጨምሮ ጠቃሚ የመ/ቤቱን መረጃዎች የያዙ የህትመት ውጤቶችን ለተቋማትና ሌሎች አካላት የማሰራጨት ስራ እየተሰራ ሲሆን ተቋማዊ የውስጥ መረጃ ልውውጥ አሠራርን በማጠናከር በመ/ቤቱ የአውት ሉክ እና በቴሌግራም ቻናል በርካታ የእርስ በእርስ የመረጃ ልውውጦችን ማድረግ ተችሏል፡፡ ተቋሙን ከማስተዋወቅ አንጻር የቡክሌት ህትመት ከ2011 እስከ 2014 ዓ/ም ድረስ ታትሞ ለለፌዴራል መ/ቤቶች እንዲሁም ለመንግሥት ወጪ አስተዳደር ቋሚ ኮሚቴ ጭምር ተሰራጭቷል፡፡

2.6. ምቹ የሥራ አካባቢ ከመፍጠር አንጻር

የተቋሙ ውጤታማ የተሽከርካሪ አጠቃቀምን ለማስተዳደር እና ለመቆጣጠር የስምሪት አገልግሎት አሰጣጥና ነዳጅ አጠቃቀም መመሪያ በማዘጋጀትና የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት አስተያየት እንዲሰጡበት በማድረግ ተሽከርካሪዎች በቶታል አቢስኒያ የካርድ እና በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ የነዳጅ ግዢ እየተከናወነ አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙ ሲሆን የመስክ ተሽከርካሪዎች ደግሞ የቴሌ ብር ወይም የሲ.ቢ.ኢ. ብር አገልግሎት ደረሰኝ ብቻ ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማድረግ የተቻለ ሲሆን፣ በተቋሙ ዘመናዊ የአውቶሜሽን ሥርዓት ለመዘርጋት ጥናት እየተደረገ እና እየተጠናቀቀ ይገኛል በመሆኑም በቅርቡ የተማከለ አውቶሜሽን ስርዓት የሚዘረጋ ይሆናል፡፡

የመ/ቤታችንን የስራ አካባቢ የተሻለና የቢሮ ቅርጹንም መ/ቤቱ ከደረሰበት ዘመናዊ አሠራር ጋር የተሳለጠ እንዲሁም ደረጃውን የጠበቀ ለማድረግ በፕሮጀክት ዕቅድ ተይዞ በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ላይ ከፌዴራል ቤቶች ኮርፖሬሽን ጋር በተደረገ ህጋዊ የስራ ውል መሰረት የህንጻ እድሳት ስራ እየተከናወነ ይገኛል፡፡ በአሁን ሰዓት ከፊሉ የህንጻው ክፍል እድሳት ተጠናቆ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፤ የዚህ ህንጻ እድሳት ቀሪ ስራና የቢሮ መገልገያ ቁሳቁስ በአዲስ የሚሟላት ስራዎች በመጪዎቹ ጥቂት ወራት ውስጥ እንደሚጠናቀቁ ይጠበቃል፡፡

የመ/ቤቱ የሰው ሀብት ሁኔታ

ለመ/ቤቱ በመዋቅር የተፈቀደው የሰው ኃይል የኦዲት ባለሙያ 669፣ የድጋፍ ሰጪ ሠራተኛ 344 በድምሩ 1013 ሲሆን፡፡ ስራዉ ሲጀመር የነበረዉ የሰዉ ሃይል 489

ኦዲተሮችና 197 የድጋፍ ሰጪ በድምሩ 686 ሠራተኞች በሥራ ላይ ነበሩ፡፡ በኦዲት ዓመቱ ውስጥ 12 ሰራተኞች ለድጋፍ ዘርፍ እና 29 ለኦዲት ዘርፍ በድምሩ 41 ሠራተኞች ተቀጥረዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ከስራ የለቀቁት በገዛ ፈቃዳቸዉ ከኦዲት 39፣ ከድጋፍ 3 በጡረታ ደግሞ 6 ሰራተኞች ባጠቃላይ 48 ሰራተኞች በተለያየ ምክንያት መ/ቤቱን ለቀዋል፡፡

በመሆኑም በኦዲት ዓመቱ መጨረሻ በመ/ቤቱ 482 የኦዲት ባለሙያዎች (323 ወንድ እና 159 ሴት)፣ 197 የድጋፍ ሰጪ (88 ወንዶችና 109 ሴቶች) ሠራተኞች በአጠቃላይ 679 ሠራተኞች በሥራ ላይ ይገኛሉ፡፡ ክፍት የሥራ መደቦችን ለማሟላት በየወቅቱ ከፍተኛ ጥረት የሚደረግ ቢሆንም ባለው የሠራተኛ ፍልሰት እና በተለይ የስራ ባህሪው በአብዛኛው በመስክ አመቺ ባልሆኑ አከባቢዎች ጭምር የሚከናወን በመሆኑ የውሎ አበል ማናስ ምክንያት ሰራተኛው ተቋቁሞ መስራት በመቸገሩ ችግሩን ማስወገድ አልተቻለም፡፡

የ2015 በጀት ዓመት የበጀት አጠቃቀም

ለ2015 በጀት ዓመት በመ/ቤታችን ሊከናወኑ ለታቀዱት ሥራዎች ማከናወኛ መደበኛ በጀት ብር 160,523,312.38 የተፈቀደ ሲሆን ለዓመቱ ከተፈቀደው በጀት ውስጥ ብር 159,133,964.97 (99.13%) መጠቀም ተችሏል፡፡ አፈፃፀሙም የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሰየማቸው ገለልተኛ ኦዲተሮች ኦዲት በመከናወን ላይ የሚገኝ ሲሆን እንደተጠናቀቀ ለም/ቤቱ የሚላክ ይሆናል፡፡

የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አጠቃቀም በተመለከተ

የመ/ቤቱ ሥራዎች በቴክኖሎጂ በማስደገፍ የኦዲት አሠራር የሚያዘምኑና የመ/ቤቱን የመረጃ ስርዓቶች ተመጋጋቢ እንዲሆኑ የሚያደርጉ ከፍተኛ ወጪ የወጣበትን የዳታ ማዕከል መነሻ በማድረግ የመ/ቤቱን ሥራ ከማቀላጠፍ፣ ወረቀት አልባ ተቋም ለማድረግና ወጪን ከመቆጠብ አንጻር (Application Portal) ሥርዓቶች በመዘርጋት የሰው ሃብት (HRMS)፣ ግንኙነት ስርዓቶች IP Telephony፣ IPTV System፣ የቁጥጥር ስርዓቶች IP Surveillance System፣ Time Attendance System፣ ኮርፖሬት ኢሜል (Corporate E-Mail)፣ ድረ-ገፅ (Website)፣ የኢንተርኔትና ወረዳኔት አገልግሎት ክትትል፣ አገልግሎት አሰጣጥ አስተዳደር ስርዓት (Helpdesk Management System)፣ የኦዲት አስተያየት መከታተያ ስርአት (ARTS) ትግበራ፣ የተቀናጀ ፋይናንስ አስተዳደር ስርዓት (IFMIS)

ትግበራን ወደ ሲስተም እንዲገቡ በማድረግ፣ መከታተልና የመ/ቤቱን የአሰራር ሁኔታን በእድሳቱ ምክንያት መቆራረጥ ቢኖርም በቴክኖሎጂ እንዲደገፍ ተደርጓል፡፡

የአይቲ መሠረተ ልማት አውታሮች (Network Equipment's, Servers, Storages, IT Security Equipment's etc.) ውጤታማነትን ለመገምገም በታቀደው መሠረት የመ/ቤቱ ኔትዎርክና ሲስተሞች ደህንነት የተጠበቀ ሆኖ እንዲቀጥል ክትትል ከማድረግ አንፃር ሁሉም ሰርቨሮች ላይ የተጫነው አንቲ-ቫይረስ በትክክል መስራቱ ክትትል በማድረግ ሊፈጠር የሚችለዉን አንቲቫይረስ በመጫን የደህንነት ስጋት መቋቋም የሚያስችል ሥራ ተሰርቷል፡፡ እንዲሁም የ11 የኔትወርክ መረጃ መረብ የመገልገያ መሳሪያዎችን ደህንነትና አገልግሎታቸው ቀጣይነቱን አጠናክሮ እንድቀጥል በአዲስ መልክ የመከታተል ስራዎች እና ከፋይናንሽያልና ህጋዊነት ኦዲቶች የቴክኖሎጂ ትግበራዎች፣ ከክዋኔ የፕሮጀክት ኦዲት ላይ በቀረቡ የቴክኖሎጂ ትግበራዎችን ላይ የቴክኒካል ድጋፍ በማድረግ አቅም የማሳደግ ስራዎች ተሰርቷል፡፡

መ/ቤቱ ለሚያከናዉናቸው ኦዲቶች የሚያወጣውን ማንኛውንም ወጪ በመቀነስ የኤሌክትሮንክስ የክፍያና ግዥ ዘዴን በማዘመን የወረቀት አልባ የሥራ ግንኙነቶች በሁሉም ዳይሬክቶሬቶች ተግባረዊ የተደረገ ሲሆን የዳሰሳ ጥናት መጠይቅ በኦላይን ሰርቨይ (online survey) በማድረግ የወረቀት ብክነትን ለመቀነስ ተችሏል፡፡

በተጨማሪም የኦዲቱን ሥራ ለማገዝና የኦዲቱን ሥራ እንዲያቀላጥፉ 4 የተለያዩ የአይቲ ሲስተሞችን በመለየት ፕሮጀክት የመንደፍ ስራ የተከናወነ ስሆን የተለያዩ የICT መገልገያ መሳሪያዎች (ፕሪንተር፣ ላፕቶፕና ዴስክ ቶፕ ኮሚፒዩተሮች እና ሌሎች) ጥገና መስራት ተችሏል፡፡

2.11 ያጋጠሙ ችግሮና የተወሰዱ እርምጃዎች

በአፈጻጸም ወቅት መ/ቤቱን ካጋጠሙት ችግሮች መካከል አብዛኛዎች ባለፈዉ አመትም የነበሩ አሁንም የቀጠሉ ሲሆን ዋና ዋናዎቹ

የቀናጀ የፋይናንስ አስተዳደር የመረጃ ሥርዓት (IFMIS) ፣ eGP እና የገቢዎችና ጉምሩክ የሲስተም መቆራረጥ እንዲሁም በፀጥታ ምክንያት ሥራዎችን በታቀደው ዕቅድ መሠረት ማጠናቀቅ አለመቻል፣

በቢሮ ዕድሳት ምክንያት ማስረጃ ማቅረብ ባለመቻሉ ኦዲት ኦዲት ያልተደረገ መ/ቤት መኖሩ፣

የመ/ቤት ኃላፊዎች በመውጫ ስብሰባ ወቅት አለመገኘትና የኦዲት ጊዜውን ማጓተት እንዲሁም ከመውጫ ስብሰባ በኋላ በርካታ ዶክመንቶች አሉን በማለት ለማጣራት ተጨማሪ ጊዜ በመውሰዱ ኦዲቱ በወቅቱ እንዳይጠናቀቅ ማድረጉ፣

ለኦዲት ተደራጊዎች ለሚላኩ የኦዲት የስራ ወረቀቶች እና ረቂቅ ሪፖርቶች በወቅቱ ምላሽ አለመስጠት፣

የሂሳብ ሪፖርቶችን በወቅቱ ዘግቶ አለማቅረብ፣ የሥራ ቢሮና የሂሳብ ዶክሜንቶች በተቀመጠ ጊዜ ገደብ ዉስጥ ተዘጋጅቶ ለኦዲት ሥራ አለማድረስ፣ ለሥራ የሚያስፈልጉ በወቅቱ ማቅረብ አለመቻል፣

ካለው የኑሮ ውድነት ጋር ተያይዞ ለመ/ቤቱ ሠራተኞች ከመ/ቤቱ ተጠንቶ የቀረበው የውሎ አበል በኦዲት ኮሚሽኑ አስተያየት ተሰጥቶበት ለም/ቤቱ ቀርቦ እንዲም በም/ቤቱ የፕላን፣ በጀት እና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ይሁንታ አግኝቶ በዚሁ መሰረትም በፓርላማ ጽ/ቤት በኩል ለገ/ሚር ቢላክም እስካሁን ምላሽ የተሰጠበት ሁኔታ ባለመኖሩ በመ/ቤቱ ሠራተኞች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ከመድረሱም በላይ ከፍተኛ ልምድ ያላቸዉ የባለሙያ ፍልሰት እያስከተለ የሚገኝ ስለሆነ የተከበረው ምክር ቤት ትኩረት እንዲሰጥበት በአክብሮት እጠይቃለሁ፡፡

ከላይ የተጠቀሱትን ችግሮች ከሚመለከታቸዉ የስራ ሃላፊዎች ጋር በመነጋገር ለመፍታት ጥረት ተደርግዋል። በተጨማሪም ያልተፈቱ ችግሮች ቢኖሩም ችግሩን በመቋቋም ስራዎቻችንን በአቀድነው መሰረት ጥሩ በሚባል አፈፃፀም ማጠናቀቅ ተችሏል፡፡ የሰራተኛ የውሎ አበል በተመለከተ ሰራተኛው ሥጋት ያለበት አከባቢዎች በመስራት በ300 ብር ቁርስ፣ ምሳ፣ እራት እና አልጋ ሸፍነህ ሥራ መባሉ በሠራተኛው ላይ አሉታዊ ስሜት የፈጠረ በመሆኑ የዚህን መስሪያ ቤ/ት ጥያቄ መመለስ ትንሽ ሰጥቶ ብዙ የሚተረፍበት በመሆኑ የተከበረዉ ም/ቤት ጉዳዩን በአንክሮ አይቶ ምላሽ እንዲሰጠበት በአክብሮት እጠይቃለሁ፡፡

በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሆነው ሀላፊነታቸውን የተወጡትን ሰራተኞች በም/ቤቱ ፊት ላመሰግናቸው እወዳለሁ፡፡

3. የ2016/17 የኦዲት በጀት ዓመት ዕቅድ

የመ/ቤቱ ከየካቲት 2014/15 ዓ.ም እስከ ጥር 2017/18 ዓ.ም ያለው የ3 ዓመት የሚተገበር ስትራቴጅክ ዕቅድ ተዘጋጅቷል፡፡ በዚህም መሠረት በ2015 በጀት ዓመት በጀት ከተመደበላቸው 183 የፌዴራል መ/ቤቶች እንዲሁም 54 ቅርንጫፎች ውስጥ ቀደም እንዳሉት ዓመታት 14 የሚሆኑት ሂሳባቸው በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኦዲት እንደሚደረጉ ታሳቢ ተደርጎ የተቀሩትን 169 መ/ቤቶች 54 ቅርንጫፎች በመ/ቤታችን ኦዲት በማድረግ የፋይናንስና የሕጋዊነት ኦዲት ሽፋኑን 100% ለማድረስ ታቅዷል፡፡ እንደዚሁም 32 አዳዲስ የክዋኔ ኦዲቶችን እና 8 ክትትል ኦዲቶችን እንዲሁም 2 የኢንፎርሜሽን ሲስተም ሰርቪስ ኦዲት በድምሩ የ42 ኦዲቶች ሪፖርቶችን ለማውጣት ታቅዷል፡፡ በተጨማሪም በ359 የመሠረታዊ አገልግሎት ተጠቃሚ በሆኑ ወረዳዎችና የሴክተር ቢሮዎች 368 የተከታታይ ኦዲት በየሩብ ዓመቱ ለማከናወን፣ 13 የማረጋገጥ ስራዎች (Verifications)፣ አንድ ፕሮግራም አቀፍ ኦዲት በገንዘብ ሚኒስቴር ደረጃ እና 13 የዓመታዊ ግብዓት በድምሩ 395 ኦዲቶችን ለማካሄድ በእቅድ ተይዟል፡፡ እንዲሁም 26 የፋይናንስና ህጋዊናት እንዲሁም 4 የክዋኔ ኦዲት በድምሩ 30 የኦዲት ፋይሎች የጥራት ደረጃ በሌላም በኩል የመንግሥት የተጠቃለለ ገቢና ወጪ ሂሳብ እና 12 ልዩ ኦዲቶችን ሠርቶ ለማጠናቀቅ ታስቧል፡፡

4. ማጠቃለያ

የ2015 በጀት አመት ሂሳብ ላይ የተካሄደዉ የፋይናንስ እና ህጋዊነት ኦዲት በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እንደሚሰሩ የታቀዱትን ጨምሮ በወቅታዊ ሁኔታ ከተቋረጡት 11 መ/ቤች እና 4 ቅርንጫፎች በስተቀር በተቀሩት የፌደራል ባለበጀት መ/ቤቶች ኦዲቱ ተከናዉኗል፡፡ አፈጻጸሙም 94..44% ሆኗል።

በሌላ በኩልም የክዋኔ ኦዲትን እቅድ አፈጻጸምን በተመለከተ 32 አዲስ ፣ 12 የክትትል ኦዲት በድምሩ 44 ለመስራት ታቅዶ የ32 አዳዲስ ኦዲት እና 11 የክትትል ኦዲት በድምሩ የ43 የክዋኔ ኦዲት ሪፖርቶች ወጪ ተደርጓል። አፈጻጸሙ 97.72% ሆኗል፡፡አንድ የክትትል ኦዲት በሰዉ ሃይል ምክንያት ስራዉን መስራት አልተቻለም።

የልዩ ኦዲት እቅድ አፈጻጸምን በተመለከተ በእቅድ የተያዘዉ 11 ሲሆን በበጀት አመቱ 26 ጥያቄዎች የቀረቡ በመሆኑ ሌሎች የኦዲት የስራ ክፍሎች በተጨማሪ እንዲሰሩ በማድረግ አፈጻጸሙ 23 ሆኗል። የተሰራዉ ልዩ ኦዲትም ለጠየቀዉ አካል እንዲደርስ ተደርጓል።

የኢትዮጵያ መንግስት እና የአለም ባንክ ባደረጉት ስምምነት መሰረት የፍትሃዊነት መሰረታዊ አገልግሎት ለሁሉ አቀፍ የእድገት ተጠቃሚነት ፕሮግራምን የተከታታይ እና የማረጋገጫ ኦዲት የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ከሆኑ ክልል ወረዳዎች 337 ለመስራት ታቅዶ 345 መስራት ተችሏል። አፈጻጸሙም 102.37% ሆኗል፡፡

የ2015 በጀት አመት የኦዲት ዉጤት ሲታይ ነቀፌታ የሌበት 79፣ ከጥቂት ጉድለቶች በስተቀር አጥጋቢ ሆነዉ የተገኙ 50፣ አሰተያየት መስጠት ያልተቻለባቸዉ እና የጎላ ችግር ያለባቸዉ ሆኖ በመገኘታቸዉ ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት የተሰጣቸዉ 22 አጠቃላይ ዉጤቱ ሲታይ ነቀፌታ የሌለበት ከጥቂት ጉድሎቶች በስተቀር ባጠቃላይ አጥጋቢ ሆነዉ የተገኙ እና ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት የሚያሳጣ አስተያየት የተሰጠባቸዉ የተወሰነ መሻሻል ያልታየበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

3. የ2015 በጀት ዓመት ሂሣብ ሕጋዊነት ኦዲት ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሣቦች

በዚህ ክፍል የሚነሱ ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶች አብዛኞቹ ባለፉት ዓመታት ሪፖርታችን ደጋግመን ያቀረብናቸው ቢሆንም፣ በርካታ ጉድለት የታየባቸው መ/ቤቶች በመኖራቸው የሚመለከታቸው አካላት እንዲወስዱ አሁንም ደግመን ለማቅረብ አስፈላጊና ግዴታ ሆኖ በመገኘቱና በጉዳዩ ላይ ተገቢ ትኩረት እንዲሰጠው ለመግለጽ እንወዳለን፡፡

I. ኦዲት በተደረጉ መ/ቤቶች የተገኙ ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶች

ኦዲት በተደረጉ መ/ቤቶች የተገኙት የጥሬ ገንዘብና ሌሎች የአሰራርና የአፈፃፀም ጉድለቶች በየኦዲት ተልዕኮ ቡድኖች ስር በተደራጁ የኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች አንጻር የታዩት ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶችና የተሰጡት ማሻሻያ ሀሳቦች ተጠቃለው ከዚህ በታች ቀርቧል፡፡

1. የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያያዝ ድክመቶች

የጥሬ ገንዘብ ጉድለት

ኦዲት በተደረጉ መሥሪያ ቤቶች የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር ሥርዓት በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 3/2003 እና በፌደራል መንግሥት የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ2 መ/ቤቶች ብር 383,238.48 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ- 2/1 ተመልክቷል/

በጉድለት የታየው የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ እንዲተካ ለየመ/ቤቶቹ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

- የገንዘብ ሚኒስቴር ባስተላለፈው መመሪያ መሰረት ከብር 5,000.00 ብር በላይ የሆኑ ወጪዎች መከፈል ያለባቸው በቼክ/ በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ በመጠቀም ወደ ባለመብቱ የባንክ ሂሳብ በማስተላለፍ መሆን እንዳለበት በግልጽ ተመልክቷል፡፡ በዚህ መሰረት ኦዲት ሲደረግ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ብር 149,846,00 በቼክ/ በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ በመጠቀም ወደ ባለመብቱ የባንክ ሂሳብ በማስተላለፍ መፈጸም ሲገባቸው በግዥ ሰራተኞች ሥም ቼክ እየተዘጋጀ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ ታውቋል፡፡ ዝርዝሩ አባሪ 2/1 ሀ ተመልክቷል፡፡
- በቤተመንግሥት አስተዳደር በድምሩ ብር 190,579.77 በካዝና ከተፈቀደው በላይ ተቀምጦ ተገኝቷል ፡፡ ዝርዝሩ አባሪ 2/1 ለ ተመልክቷል፡፡
- የቤተ-መንግስት አስተዳደር በድምር ብር 642,587.41 የተሰበሰበው ገንዘብ በወቅቱ ወደ ባንክ ገቢ የማይሆን መሆኑ በኦዲት ተረጋግቷል፡፡ ዝርዝሩ አባሪ 2/1 ሐ ተመልክቷል፡፡
- የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ሚኒስቴር ባወጣው የፌደራል መንግስት የሂሰብ አያያዝ መመሪያ መሰረት በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ማለትም በሰኔ

30/2015 በጀት ዓመት እያንዳንዱ ሂሳብ መደብ በመደበኛ ሁኔታ የሚታወቅበትን ሚዛን የጠበቀ ለመሆኑ ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡-

መደበኛ ሚዛኑ ያልጠበቀ የተጣራ ሀብት ክሬዲት መያዝ ሲገባው በሂሳብ ሪፖርት ላይ በዴቢት ተመዝግቦ የሚታይበት በገቢዎች ሚኒስቴር ሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት ብር 80,702,549.07 ስለመኖሩ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ዝርዝሩ በአባሪ 2/2 ተመልክቷል፡፡

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ከ2006 ዓ.ም ጀምሮ ረጅም ዓመታት ፈሰስ ሳይደረግ በባንክ ውስጥ የተጠራቀመ የገቢ ሂሳብ ምክንያቱ የማይታወቅ ብር **110,444.01** የሚታይ መሆኑ በኦዲት ወቅት ታውቋል፡፡ ዝርዝሩ በአባሪ 2/2 ለ ተመልክቷል፡፡

በ1 መ/ቤት በድምር 226,243.88 የፕሮጀክት ስራቸው ተጠናቆ የባንክ ሂሳባቸው ያልተዘጋ የፕሮጀክት ባንክ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡ እንዲሁም በአንድ ሌላ መ/ቤት ደግሞ በግንባታ ሂሳብ ላይ ጥሬ ገንዘብ የምዝገባ ስህተት በብልጫ የተመዘገበ ብር 13,401,497.56፣ ያልተከፈለ ጥሬ ገንዘብ ብር 2,807,684.81 እና የሂሳብ ማስተካከያ ያልተሰራለት የግሬስ ፔሬድ ሂሳብ ብር 4,185,776.49 በኦዲቱ ተገኝቷል፡፡ ዝርዝሩ በአባሪ 2/3 ሀ እና ለ ተመልክቷል፡፡

መ/ቤቶች መንግሥት የዘረጋውን የክፍያ ሥርዓት እንዲተገብሩ እንዲሁም የገንዘብ ዝውውሩን ለመቆጣጠር መንግሥት ያወጣው መመሪያ ተግባራዊ እንዲሆን ተገቢው ቁጥጥርና ክትትል ማድረግ እንዳለባቸው ፣እንቅስቃሴ የሌላቸው የፕሮጀክት ሂሳቦች በሌጀር ሚዛን ላይ የሚታዩ ቋሚ ሂሳቦች ማለትም የሳጥንና የባንክ የጥሬ ገንዘብ ሂሳቦች ሚዛናቸውን ትክክለኛነታቸውን በተገቢው መንገድ በማጣራት በተደረሰው ውጤት መሰረት እና በፕሮጀክቶቹ የውል ስምምነት መሰረት ሂሳቡን በትክክል ተዘግቶ ሪፖርት መደረግ እንዳለበትና ለወደፊቱ የዚህ አይነት አሰራር እንዳይከሰት ተገቢውን ቁጥጥርና ክትትል መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

2. የተሰብሳቢ ሂሳብ

2.1 በደንቡ መሰረት በወቅቱ ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብ

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እስከ 35 እንዲሁም በፌዴራል የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 መሰረት ለውሎ አበልና ለመጓጓዣ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ሰራተኛው ሥራውን አጠናቆ ከተመለሰ በኋላ በሰባት ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበት ያዛል፡፡ ይሁንና በ124 መ/ቤቶች በጠቅላላው ብር 14,119,173,104.23 በወቅቱ ያልተወራረደ (ያልተሰበሰበ) ተሰብሳቢ ሂሳብ መኖሩ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፡-

የገቢዎችና ጉምሩክ መ/ቤቶች	ብር	34,932,377.61
የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	"	1,100,725,598.39
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	1,992,899,328.99
የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	2,410,782,443.36
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	"	8,171,141,833.28
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	408,691,522.60
ጠ/ድምር	ብር	14,119,173,104.23

ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ የተገኘ ሲሆን፣ የተሰብሳቢ ሂሳቡ ዕድሜ በቆይታ ጊዜው ሲተነተን፤ ከአንድ ወር በላይ እስከ አንድ ዓመት ብር 1,193,674,117.88፣ ከአንድ ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት ብር 10,957,913,180.42 ፣ ከአምስት ዓመት በላይ እስከ አሥር ዓመት ብር 1,722,681,309.82 እና ከአሥር ዓመት በላይ ብር 139,093,398.22 ሲሆን፤ ቀሪው ሂሳብ ብር 105,801,097.89 በቆይታ ጊዜው ያልተተነተነ ነው፡፡ (አባሪ 3/1 ተመልክቷል)

ውዝፍ ተሰብሳቢ ሒሳብ ከተገኘባቸው ተቋማት መካከል ከፍተኛውን ድርሻ የያዙት ጤና ሚኒስቴር ብር 6,005,511,975.43፣ የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር ብር 1,159,744,050፣ የትምህርት ሚኒስቴር ብር 1,012,583,714፣ በፌዴራል መንግስት ህንፃዎች ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ብር 970,941,401፣ የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም የህክምና ኮሌጅ ብር 756,353,005.5፣ የጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ ብር

433,597,818.5፣ የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ብር 286,886,896.20፣ የአደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን ብር 272,499,071.2፣ የመንግስት ግዥ አገልግሎት ብር 265,228,072.78፣ የፌዴራል ፖሊስ ኮምሽን ብር 250,766,953.97 እና የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ብር 218,363,536.2 ዋና ዋናዎች ናቸው፡፡

በ4 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 514,525,280.43 በወቅቱ ያልተወራረደ ውዝፍ ተሰብሳቢ የፕሮጀክት ሂሳብ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ 30020ዘ/2 ተመልክቷል፡፡/

የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 8 /4 ፊደል መ የተሰብሳቢ ሂሳብ በቂ ማስረጃ ሲቀርብበት ብቻ በተሰብሳቢ ሂሳብነት መያዝ ያለበት ሆኖ የተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት እንዳይፈጠር ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ ይሁንና በ15 መ/ቤቶች በጠቅላላው ብር 363,101,215.10 ማስረጃ ባለመቅረቡ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋጥ አልተቻለም፡፡

የተሰብሳቢ ሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ካልተቻለው መ/ቤቶች መካከል የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጅ ሚኒስቴር ብር 253,373,189.31፣ የመንግስት ግዥ አገልግሎት 39,163,790.17 እና የጤና ሚኒስቴር 28,002,059.43 ከፍተኛውን ድርሻ ይዘዋል፡፡ (አባሪ 3/3 ተመልክቷል)።

በመሆኑም ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳቢን በወቅቱ አለመወራረድ ለመንግሥት ገንዘብ መባከን በር የሚከፍት ስለሆነ በአስቸኳይ መወራረድ እንዳለበት፣ ለረጅም ዓመታት ሳይሰበሰቡ የተገኙት ሂሣቦች እንዲወራረዱ አስፈላጊው ክትትል እንዲደረግ፤ ሊሰበሰቡ በማይችሉት ላይ በመንግሥት መመሪያ መሠረት ከመዝገብ እንዲሰረዙ እንዲደረግ በላክናቸው ሪፖርቶች አሳስበናል፡፡

2.3 በተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ የታዩ ሌሎች ችግሮች

ከተለመደው የተሰብሳቢ ሂሳብ ሚዛን የተለዬ ክሬዲት ባላንስ (Abnormal balance) የሚታይባቸው፣ በ3 መ/ቤቶች ብር 3,443,374.21 መሆኑ፣

በተሰብሳቢ ሂሳብ መያዝ ሲገባው በወጪ የተመዘገበ በ4 መ/ቤቶች ብር 7,016,570.32 መሆኑ፤ በ4 መ/ቤቶች የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ ብር 7,016,570.32 በተሰብሳቢ መያዝ

ሲገባው በወጪ ተመዝግቦ መገኘቱ፣ በሁለት መ/ቤቶች በድምሩ ብር 292,579,579.73 የሂሳብ መደቡን ያልጠበቀ ተሰብሳቢ ሂሳብ መገኘቱ፣ በሁለት መ/ቤቶች ከግንባታ ክፍያዎች ያልተቀነሰ (ተመላሽ ያልተደረገ) የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ ብር 17,482,830.27 መገ፤ በአንድ መ/ቤት ደግሞ ተቀጽላ ሌጀር ያልተከፈተለት ተሰብሳቢ ሂሳብ/ተቀጽላ ሌጀር የሌለው በመሆኑ ከማን እንደሚሰበሰብ የማይታወቅ / ብር 1,136,040.83 መገኘቱ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ (አባሪ ¾ ተመልክቷል፡፡)

በመሆኑም ያልተሰበሰቡት ሂሳቦች በመንግሥት የፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት በወቅቱ እንዲወራረዱ/እንዲሰበሰቡ፣ ማስረጃ ያልቀረበላቸውም ሂሳብ ማስረጃ እንዲቀርብላቸውና ያልተለመደ ሚዛን የሚያሳዩ ተሰብሳቢ ሂሳቦችም ተጣርተው አስፈላጊው ማስተካከያ እንዲደረግላቸው፣ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት ለየመሥሪያ ቤቶቹ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3. የገቢ ሂሳብ

3.1 በገቢ ግብር፤ ቀረጥና ታክስ እንዲሁም በሌሎች ገቢ ለመሰብሰብ በሚደነግጉ አዋጆች ደንብና መመሪያዎች መሰረት ሳይሰበሰብ የተገኘ ሂሳብ

የገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶችና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ እንዲሁም በሌሎች ገቢ መሰብሰብን በሚፈቅዱ አዋጆች መሠረት የመንግሥትን ገቢ የሰበሰቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

የገቢዎች ሚኒስቴር ስር ባሉ 9 ቅ/ጽ/ቤቶች የአክስዮን ትርፍ ድርሻ የገቢ ግብር ብር 5,147,319.06 እና ንግድ ትርፍ ግብር ብር 220,311,281.08 በድምሩ ብር 225,458,600.14፣ እንዲሁም በሌሎች 6 መ/ቤቶች እና 3 ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ 14,613,015.45 ንግድ ትርፍ ግብር፣ የገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ /VAT/፤ ቅድመ ግብር (withholding tax) እና የአክስዮን ትርፍ ድርሻ ገቢ ለመሰብሰብ በሚያስገድዱ አዋጆችና ደንቦች መሠረት ያልተሰበሰበ ሂሳብ ተገኝቷ፤ል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ-4/3 ተመልክቷል/

ገቢ ለመሰብሰብ በሚፈቅዱ አዋጆች መሠረት ያልተሰበሰበው ሂሳብ በዘርፍ ሲጠቃለል፡-

የገቢዎችና ጉምሩክ መ/ቤቶች	ብር	12,391.8
የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	"	2,721,571.33
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	11,879,052.32
ጠ/ድምር	ብር	14,613,015.45

በአዋጁ ደንብና መመሪያው መሠረት ገቢ ካልሰበሰቡት መ/ቤቶች መካከል፣ በገቢዎች ሚኒስቴር የመካከለኛ ግብር ከፋዮች ብር 99,161,281.58፣ ሃዋሳ ገቢዎች ቅ/ጽ/ቤት 71,270,654.47፣ አዳማ ገቢዎች ቅ/ጽ/ቤት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በመሆኑም ያልተሰበሰበው የሀገር ውስጥ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ ወለድና መቀጫን በመጨመር ከአስመጪዎችና ግብር ከፋዮች መሰብሰብ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

ከገቢ አሰባሰብ አንፃር የሚከተሉት ሌሎች የኦዲት ግኝቶች ተገኝተዋል፡

ለከፍተኛ ትምህርት ወደ ውጪ ሀገር ተልከው በገቡት ውል መሰረት ባለመፈጸማቸው ተመላሽ/ገቢ ያልተደረገ ሂሳብ በ3 መ/ቤቶች ብር 8,136,001.98 መገኘቱ፣

በቫውቸር ሥርዓት ከቀረጥ ነጻ ገብተው በጊዜ ገደቡ ምርት ላይ ስለመዋሉና ምርቱም ለውጭ ገበያ የቀረበ ስለመሆኑ ማስረጃ ያልቀረበለት በመሆኑ አስቀድሞ በቫውቸር የተመዘገበው የቀረጥና ታክስ እንዲሰበሰብ ያልተደረገ በአንድ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ብር 13,596,147.01 መገኘቱ፣

በቅ/ጽ/ቤቶች በኩል ወደ ሀገር የገባው ዕቃ ቀረጥና ታክሱ የተሰላ ቢሆንም ክፍያ ሳይፈጸምበት የቆየ (assessed but not paid) በ2 ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ብር 297,075.06 መገኘቱ፣

በአንድ መ/ቤት የሚመለከተው አካል ሳይፈቅድ ከስፖንሰር ድርጅቶች የተሰበሰበ ገንዘብ ብር 8,693,749.27 መገኘቱ፣

የገቢ ደረሰኝ ያልተዘጋጀለት ወይም ያልቀረበለት የገቢ ሂሳብ በ1 መ/ቤት 1,708,998 መገኘቱ፣

ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ (ዝርዝሩን ከአባሪ 4/4-4/9 ተመልክቷል)

በመሆኑም መ/ቤቶች ለወደፊቱ የመንግሥት ገቢ ህግና ደንብ በሚፈቅደው መሠረት መሰብሰብ እንዳለባቸው፣ በተለያዩ ምክንያቶች ያልተሰበሰበውም ገቢ እንዲሰበሰብ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.2 ያልተሰበሰበ ውዝፍ የገቢ ሂሣብ

ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶችና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በወጣው ሕግና ደንብ መሠረት የመንግሥት ገቢ በአግባቡና በወቅቱ መሰብሰባቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

በ9 የገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶችና በ10 የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች በታክስ ኦዲት/በድህረ እቃ አወጣጥ ኦዲት ውሳኔ መሰረት/ያልተሰበሰበ ውዝፍ የገቢ ሂሣብ በድምሩ ብር 4,491,040,372.61 በኦዲቱ ተገኝቷል፡፡ (ዝርዝሩ አባሪ 4/1 ተመልክተል)

ስለሆነም ለወደፊቱ የገቢ አሰባሰቡ ደንብና መመሪያ ተጠብቆ እንዲሰራ እንዲሁም በተመለከቱት የአሰራርና የአፈጻጸም ድክመቶች ላይ ተገቢው እርምጃ እንዲወስዱ ለመ/ቤቶቹ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

በ3 የገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች በግብር ከፋዮች ወይም በአስመጪዎች ቅሬታ/አቤቱታ የቀረበበት የግብር ወይም የቀረጥና ታክስ ዕዳ አስፈላጊው ውሳኔ ሳይሰጥበት የቆየ ዕዳ በድምሩ ብር 410,440,931.1 በኦዲቱ ተገኝቷል፡፡ (አባሪ 4/2 ተመልክቷል)

ውዝፍ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ እና የአገር ውስጥ ግብር እና ታክስ በወቅቱ ካልሰበሰቡ መ/ቤቶች መካከል ውዝፍ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ እና የአገር ውስጥ ግብር እና ታክስ በወቅቱ ካልሰበሰቡ መ/ቤቶች በገቢዎች ሚኒስቴር መካከለኛ ቁ. 1 ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ብር 964,956,028.91፣ ሰሜን ምዕራብ አዲስ አበባ ገቢዎች ቅ/ጽ/ቤት ብር 135,926,265.24 ፣ ምዕራብ አዲስ አበባ ገቢዎች ቅ/ጽ/ቤት 79,744,389.82፣ ምስራቅ አዲስ አበባ ገቢዎች ቅ/ጽ/ቤት 72,754,393.40 እና ጂማ ገቢዎች ቅ/ጽ/ቤት 67,486,115.39 እና የጉምሩክ ኮሚሽን የቃሊቲ ቅ/ጽ/ቤት ብር 2,280,162,351.67፣ አዳማ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት 254,652,942.43 ጂግጂጋ ቅ/ጽ/ቤት ብር 246,330,900.06፣ ሞጆ

ቅ/ጽ/ቤት 162,359,936.94 እና ድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት ብር 119,959,763.52 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በመሆኑም የሚሰበሰበው ገቢ መንግስት ለሚያከናውናቸው የኢኮኖሚ ልማት፣ ማህበራዊ አገልግሎቶች መስፋፋትና መሠረተ-ልማት ዝርጋታ ፕሮጀክቶች፣ እንዲሁም ሀገሪቱ የልማት ዕቅድ መሳካት ወሳኝ ሚና የሚኖረው በመሆኑ፣ ለገቢ አሰባሰቡ ትኩረት ተሰጥቶ የመንግሥት ህግና ደንብ ተከብሮ እንዲሠራ፣ ያልተሰበሰበውም ውዝፍ ገቢ እንዲሰበሰብ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

3.4 ያልተሰበሰበ የጉዳት ካሳ

በፌዴራል መንግስት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 27/4 ሀ እና ለ መሰረት አቅራቢው ሳይፈጽም በቀረው የውል መጠን ላይ ውል ሰጪ የመንግስት መ/ቤቶች በየቀኑ 0.1% ወይም 1/1000ኛ ከውሉ ዋጋ 10% ሳይበልጥ ሊሰበስቡ እንደሚገባ ይደነግጋል፡፡ በዚህ መሰረት መ/ቤቶች በገቡት ውል መሰረት ባልፈፀሙት አቅራቢዎች ወይም አገልግሎት ሰጭዎች ላይ በመመሪያው መሰረት ተገቢውን እርምጃ የወሰዱ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በ7 መ/ቤቶች እና 4 ቅ/ጽ/ቤቶች ያልተሰበሰበ የጉዳት ካሳ ብር 1,017,192.80 ብር ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ 4/14 ለ ተመልክቷል/

በመሆኑም መ/ቤቶች በተቀመጠው መመሪያና ውል መሰረት ያልሰበሰቡትን ገቢና የጉዳት ካሳ እንዲሰበሰቡ እና ለወደፊቱም መመሪያው በሚጠይቀው መሰረት እንዲፈጽሙ አሳስበናል፡፡

3.5 ማስረጃ ባለመሟላቱ ምክንያት የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ

የተሰበሰበውን ገቢ ሂሳብ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ2 መ/ቤቶች ከተለያዩ የገቢ ማመንጫ የተሰበሰበው ገቢ ብር 910,656.04 እና በ7 የገቢዎችና ጉምሩክ መ/ቤት ቅ/ጽ/ቤት ብር 289,819,699.74 በድምሩ ብር 290,730,355.78 የገቢ ሂሳቡን ትክክለኛነት በኦዲት ማረጋገጥ አልተቻለም። እንዲሁም በአንድ መ/ቤት በዶላር 1,374,914 ዩ ኤስ ዶላር የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ /ዝርዝሩ አባሪ-4/10 ተመልክቷል/

ስለሆነም ማንኛውም ገቢ ማስረጃ ሳይሟላ በገቢ መመዝገቡ ተገቢ ስላልሆነ፣ የገቢ ማስረጃዎች በትክክል ተደራጅተው እንዲያዙና ተገቢው ማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.6 በገቢ ያልተመዘገበና በገቢ ሂሳብ ሪፖርት ያልተካተተ የገቢ ሂሳብ

በበጀት ዓመቱ የተሰበሰበው ገቢ በትክክል ተመዝግቦና በሂሣብ ሪፖርታቸው ተካቶ ለገንዘብ ሚኒስቴር መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ2 መ/ቤቶች ብር 86,881,039.48 የገቢ ሂሳብ ያልመዘገቡና በገቢ ሂሳብ ሪፖርት ያላካተቱ መሆኑ በኦዲቱ ተገኝቷል፡፡ በአባሪ-4/12 ተመልክቷል/

የተሰበሰበን ገቢ በሪፖርት አለማካተት በመ/ቤቶች የሚዘጋጁ የሂሳብ መግለጫዎች ትክክለኛውን የገቢ ሂሳብ እንቅስቃሴ የማያሳይና የመንግስት አጠቃላይ ገቢ ትክክለኛውን ገጽታ እንዳያሳይ ያደርጋል፡፡

በተጨማሪም በ2 መ/ቤቶች በእለቱ ተሰብስቦ ወደ ባንክ ያልገባ የገቢ ሂሳብ ብር 6,254,795.15 ተገኝቷል፡፡

እንዲሁም በ8 መ/ቤቶች በመንግስት የጸደቀ የማስከፈያ የዋጋ ተመን /ታሪፍ ሳይኖር የተሰበሰበ ገቢ ብር 187,189,294.74፣

በጉምሩክ ኮሚሽን 10 ቅ/ጽ/ቤቶች በቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ላይ መካተት ያለባቸው ወጪዎች ባለመካታተቸው ያልተሰበሰበሰ ቀረጥና ታክስ ብር 255,138,107.83 መገኘቱ፣

በጉምሩክ ኮሚሽን 8 ቅ/ጽ/ቤቶች በቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ላይ መካተት ያለባቸው የኢንሹራንስ ወጪዎች ባለመካተታቸው ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ ብር 118,188,418.62 መገኘቱ፣

በጉምሩክ ኮሚሽን 4 ቅ/ጽ/ቤቶች ክፍያ በተፈጸመበት ቀን ባለው የምንዛሬ ምጣኔ መሰረት ባለመሰራቱ ያልተሰበሰበሰ ቀረጥና ታክስ ብር 1,004,072.13 መገኘቱ፣

በጉምሩክ ኮሚሽን 3 ቅ/ጽ/ቤቶች የግብይት ዋጋ ከጉምሩክ የግብይት ዋጋ ጋር ሲነጻጸር ልዩነት በመኖሩ ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ ብር 104,644,448.95 መገኘቱ፣ አባሪ 4/12 ሀ፣ 4/15 ከሀ-ሰ ተመልክቷል፡፡

በመሆኑም መ/ቤቶች የሚሰበስቧቸውን የገቢ ሂሳብ በትክክል በመመዝገብና በሂሳብ መግለጫዎችም በማካተት ለገንዘብ ሚ/ር ሪፖርት ሊያደርጉ እንዲሁም የገቢ አሰባሰቡ ደንብና መመሪያ ተጠብቆ እንዲሰራ እንዲሁም የተጠቀሱት የአሰራርና የአፈጻጸም ድክመቶች ላይ ተገቢውን እርምጃ መውሰድ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

3.7 በገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች የታዩ ልዩ ልዩ የገቢ አሰባሰብና የአሠራር

የመንግስት ገቢ በአግባቡ መሰብሰቡንና የተዘረጋው የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት በአግባቡ መተግበሩን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የታዩት ዋና ዋና ድክመቶች ቀጥለው ቀርበዋል፡፡

- በ6 መ/ቤቶች በገቡት የውል ግዴታ መሰረት ትምህርታቸውን ጨርሰው ወደ ሥራ ገበታቸው ባልተመለሱ መምህራን ላይ በገቡት ውል መሰረት እርምጃ ያልተወሰደ ስለመሆኑ ብር 14,263,345.98 መገኘቱ፤ (ዝርዝሩ አባሪ 4/6 ተመልክቷል)
- ዓመታዊ የንግድ ትርፍ ግብር፤የተጨማሪ እሴት ታክስ፤ኤክሳይስ ታክስና ተርንኦቨር ታክስ በወቅቱ ያላሳወቁ ድርጅቶች ቫት/ቲኦቲ ያላስታወቁ ብዛት 284 እና ንግድ ትርፍ ያላስታወቁ ብዛት 122 በድምሩ 406 በኦዲቱ መገኘታቸው፣ ዝርዝሩ በአባሪ 4/11 ተመልክቷል
- በሁለት መ/ቤቶች የሂሳብ መደቡን ሳይጠብቅ በገቢ ተመዝግቦ የተገኘ ሂሳብ ብር 137,504,239.86፣ /ዝርዝሩን በአባሪ 4/14 ተመልክቷል፡፡/
- ያልተሰበሰበ የማህበራዊ ልማት ቀረጥ ብር 110,890,720.22 መገኘቱ፣
- በ1 መ/ቤት ቦሎና ቀረጥ ሳይከፈል ባልተሟላ ማስረጃ የተፈፀመ የተሽከርካሪ ሽያጭ ገቢ ብር 14,487,711.44 ተገኝቷል፡፡ ዝርዝሩ በአባሪ 10/1 ረ ተመልክቷል፡፡
- በአንድ መ/ቤት ተቀናሽ ያልተደረገ የሥራ ግብር ብር 26,521,701.84 መኖሩ፣
- በሁለት መ/ቤቶች የገቢ ሂሳብ ዕቅድና ክንውን ችግር መኖሩ

➢ በሁለት መ/ቤቶች የገቢ ዕቅድ በዝርዝር ያልተዘጋጀ መሆኑ፡፡

ታውቋል፡፡/ዝርዝሩን በአባሪ 4/5 ሐ ሸ፣ ቀ ተመልክቷል/

ስለሆነም ለወደፊቱ የገቢ አሰባሰቡ ደንብና መመሪያ ተጠብቆ እንዲሰራ እንዲሁም ከላይ የተመለከቱት የአሰራርና የአፈጻጸም ድክመቶች ላይ ተገቢውን እርምጃ እንዲወስዱ አሳስበናል፡፡

4. የወጪ ሂሳብ

4.1 ማስረጃ ሳይኖር በወጪ የተመዘገበና ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ያልተቻለ ወጪ ሂሳብ

በወጪ የተመዘገቡ ክፍያዎች ህጋዊ ማስረጃ የቀረበላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ11 መ/ቤቶች ብር 43,545,036.91 ማስረጃ ሣይኖረው በወጪ ሂሳብ የተመዘገበና ማስረጃዎቹ ለኦዲት ባለመቅረባቸው ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ያልተቻለ ወጪ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ- 5/2 ሀ ተመልክቷል/

ሂሳቡም በዘርፍ ሲጠቃለል፡-

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	"	17,544,125.03
ገቢዎችና ጉምሩክ መ/ቤቶች		2,445,750
የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	5,703,029.6
የልማትና ማሕበራዊ መ/ቤቶች	"	38,790.00
ንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች		17,813,342.28
በድምሩ	ብር	43,545,036.91

ማስረጃዎቹ ለኦዲት ባለመቅረባቸው ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ያልተቻለ ወጪ ሂሳብ ከተገኘባቸው መ/ቤቶች የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ብር 17,474,125.03፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን ብር 8,794,834.49፣ የመንገድ ደህንነትና መድን ፈንድ አገልግሎት ብር 8,746,697.81 የሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ብር 4,406,764.6፣ የኢትዮጵያ አካል ድጋፍ አገልግሎት ብር 3,325,475.00 ዋና ዋናዎቹ ናቸው::

ተገቢው ማስረጃ ሳይቀርብ ገንዘብ ወጪ ማድረግ የመንግስትን ገንዘብ ለብክነት የሚዳርግ በመሆኑ ባለጥቅሞቹ ገንዘቡ የደረሳቸው ለመሆኑ ተገቢው ማስረጃ እንዲቀርብ፣ ለወደፊቱም ማስረጃዎች ወዲያውኑ እንዲቀርቡ ቢደረግ ሊያጋጥም የሚችልን ስጋትና አላስፈላጊ ወጪን ለማስቀረት ስለሚያስችል ማንኛውም ወጪ ከመመዝገቡ በፊት ተገቢው ማስረጃ መቅረቡን በማረጋገጥ እንዲመዘገብ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.2 የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ክፍያ

በወጪ ለተመዘገቡ ሂሳቦች የተሟላ ማስረጃ መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ48 መ/ቤቶች የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ ብር 44,540,734.65 በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ- 5/1 ተመልክቷል/

ሂሳቡም በዘርፍ ሲጠቃለል፡-

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	7,722,647.08
ገቢዎችና ጉምሩክ መ/ቤቶች		981,500
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	"	17,465,026.87
ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	10,804,694.62
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	7,566,866.08
በድምሩ	ብር	44,540,734.65

ሆኖ ተገኝቷል።

ባልተሟላ ማስረጃ ወጪን ከመዘገቡት መ/ቤቶች መካከል ማዕድን ሚኒስቴር ብር 5,719,611.76፣ ጅግጂጋ ዩኒቨርሲቲ ብር 5,716,485.82፣ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ብር 4,677,134.45፣ የገንዘብ ሚኒስቴር፣ 3,034,625.64፣ በሥና ክህሎት ሚኒስቴር ገዋኔ የግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅ ብር 2,455,915.5፣ የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ኢንስቲትዩት ብር 2,185,589.00፣ የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ብር 1,956,014.99፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴያትር ብር 1,718,205 እና የኢትዮጵ የአካል ድጋፍ አገልግሎት ብር 1,713,089.61 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ ዝርዝሩ በአባሪ 5/1 ተመልክቷል፡፡

ለክፍያዎች የወጪ ማስረጃ የማይቀርብላቸው ከሆነ የሂሳቡን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ካለማስቻሉም በተጨማሪ የወጪ የሂሳቡን ተዓማኒነት ሊያሳጣ የሚችል በመሆኑ የወጪ ማስረጃ ላልቀረበላቸው ክፍያዎች የወጪ ማስረጃ እንዲቀርብላቸው፤ የወጪ ማስረጃ የማይቀርብላቸው ከሆነ ደግሞ ገንዘቡ ተመላሽ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

4.3 ደንብና መመሪያ ውጪ አላግባብ የተፈፀሙ ወጪ ክፍያዎች

ክፍያዎቹ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ደንብና መመሪያዎች መሠረት የተፈጸሙ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ30 መ/ቤቶች 16,407,985.47 ከደንብና መመሪያ ውጭ ያለአግባብ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ-5/3 ተመልክቷል/ ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በ11 መ/ቤቶች ያለሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ደረሰኝ የተፈጸመ ክፍያ ብር 37,367,913.29 በኦዲቱ ተገኝቷል፡፡ ዝርዝሩ በአባሪ 5/16 ተመልክቷል፡፡

ደንብና መመሪያ ያልተከተለ ወጪ ሂሳብ በዘርፍ ሲጠቃለል፡-

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	3,852,206.43
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	5,564,901.29
ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	1,880,779.32
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	"	512,769.22
ንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች		4,597,329.21
በድምሩ	ብር	16,407,985.47

ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከደንብና መመሪያ ውጪ አለአግባብ ክፍያ ከፈጸሙ መ/ቤቶች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ብር 3,001,220፣ የመንግስት ኮምንኬሽን አገልግሎት ብር 2,889,321.58፣ ኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ 2,442,200 ፣የመደወላቡ ዩኒቨርሲቲ ብር 1,156,500.00፣ ማሪታይም ባለስልጣን ብር 1,023,138.90 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

መሥሪያ ቤቶች የሚፈጽሟቸው ክፍያዎች በመንግሥት የወጡ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን ካልተከተሉ ለመንግሥት ገንዘብ አለአግባብ መውጣት ምክንያት ሊሆን ከመቻሉም በተጨማሪ ክፍያውን ተዓማኒነት ሊያሳጣው እና በውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱ ላይ

ክፍተት ሊፈጥር ይችላል፡፡ ስለሆነም መሥሪያ ቤቶች በመንግሥት የወጡ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን ተከትለው ክፍያ መፈጸም እንዳለባቸው እና አለአግባብ የተፈጸሙ ክፍያዎችም ተመላሽ መደረግ እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

4.4 በመስሪያ ቤቱ ለሌሉና ከስራ ለተሰናበቱ ሰራተኞች የተከፈለ ደመወዝ፣

የፌደራል የመንግሥት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 1 'ሀ' ለደመወዝ ዝግጅት የሚከተሉት መረጃዎች መሟላት አለባቸው በሚለው ውስጥ የመሥሪያ ቤቱ የሥራ ክፍሎች የክፍሉ ሠራተኞች በሥራ ላይ መሆናቸውን ለማረጋገጥ በዚህ መመሪያ መሠረት መፈፀሙን ለማረጋገጥ የደመወዝ ክፍያ ኦዲት ሲደረግ፡-

በ16 መ/ቤቶች በመስሪያ ቤቱ ለሌሉና ከስራ ለተሰናበቱ ሰራተኞች የተከፈለ ደመወዝ ብር 485,183.59 ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

ክፍያዎች መመሪያን ተከትለው እንዲፈፀሙ ተገቢው ክትትል ሊደረግ እንደሚገባ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡ / ዝርዝሩ በአባሪ 5/4 ተመላክቷል/

4.5 በሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ባልተፈቀደ የኮንትራት ሠራተኞች በመቅጠር የተፈጸመ ክፍያ

በመ/ቤቶች የሚፈፀመው ቅጥር በሰቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ደንብና መመሪያ መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሰደረግ፣

በ10 መ/ቤቶች ብር 42,748,121.67 በሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ያልተፈቀደ የኮንትራት ሠራተኞች በመቅጠር የተፈጸመ ክፍያ ተገኝቷል፡፡/ ዝርዝሩ በአባሪ 5/5 ተመላክቷል/

የኮንትራት ሠራተኞች ለመቅጠር አስገዳጅ የሆኑ የስራ ክፍሎች ተለይተው ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን በማስፈቀድ መሆን እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.6 በመንግስት የተፈቀደ የክፍያ መመሪያና የክፍያ ተመን ሳይኖር የተፈጸሙ ክፍያዎች፣

በመ/ቤቶች የሚፈጸሙ ክፍያዎች በመንግስት የተፈቀደ የክፍያ መመሪያና የክፍያ ተመን መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- በ6 መ/ቤቶች እና በገኒዎችና ጉምሩክ

መ/ቤቶች ስር በሚገኙ 9 ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 66,727,252.62 አላግባብ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ / ዝርዝሩ በአባሪ 5/6 ተመላክቷል/

ማንኛውንም ክፍያ ሲያከናውን ደንብና መመሪያን መሰረት ያደረገ ሊሆን እንደሚገባና የክፍያ ተመን ላልወጣላቸው ክፍያዎች የሚመለከተው አካል የክፍያ ተመን እንዲያወጣላቸው ሊደረግ እንደሚገባ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.7 አላግባብ የተከፈለ የግብር መቀጫ፣የፍርድ ቤት ትዕዛዝ በወቅቱ ባለመከፈሉ ምክንያት አላግባብ የተከፈለ ቅጣት፣

በ8 መ/ቤቶች ብር 16,346,989.68 አላግባብ የተከፈለ የግብር መቀጫ፣የፍርድ ቤት ትዕዛዝ በወቅቱ ባለመከፈሉ ምክንያት አላግባብ የተከፈለ የወለድ ቅጣት ተገኝቷል፡፡ በጅግጅጋ ጉምሩክ ቅ/ፅ/ቤት አላግባብ የተወረሰ ተሽከርካሪን ለባለቤቱ እንዲመልስ በፍርድ ቤት የተሰጠው ጊዜ ገደብ በማለፉ ፍርድ ቤቱ የተሽከርካሪውን ግምታዊ ዋጋ እንዲያቀርብለት ለጉምሩክ ኮሚሽን ዋና መ/ቤት በጠየቀው መሰረት በአዲስ ተሽከርካሪ ከፍተኛ ዋጋ ቀረጥና ታክስን ጨምሮ ዋጋ በመስጠቱ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ብር 10,070,064.95 ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ፣ / ዝርዝሩ በአባሪ 5/8 ተመላክቷል/

በ1 መ/ቤት በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ (TR) ላይ ሁለት ጊዜ የተመዘገበ ወጪ ብር 734,284.94 ፣

በ8 መ/ቤቶችና በ1 ቅ/ጽ/ቤት ብር 3,497,114,515.14 እና 7 የኦዲት ፋይሎች ለኦዲት ከተመረጡት ሰነዶች ውስጥ ለኦዲት ያልቀረቡ በመሆኑ የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፡፡ / ዝርዝሩ በአባሪ 5/11 ተመላክቷል/

በ1 መ/ቤት በቁጥር 55 ደንብና መመሪያን ያልተከተለ ምደባ የተፈፀመ መሆኑ፣ በሌላ አንድ መ/ቤት ደግሞ በዕቅዱ መሰረት መሰራት ሲኖርበት ለትርፍ ሰዓት የተከፈለ ብር 346,545.81 መሆኑ፣ አባሪ 5/13 እና 5/14 ተመልክቷል፡፡

ወጪዎች አፈፃፀም የመንግስት ገንዘብ ክፍያ ደንብና መመሪያን መሰረት ያደረገ ሊሆን እንደሚገባ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.8 በብልጫ አላግባብ የተከፈለ ወጪ

በወጪ የተመዘገቡት ሂሳቦች በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እና ደንብ መሰረት በአግባቡ የተፈጸሙ፣ እንዲሁም መ/ቤቶቹ ላገኙት አገልግሎት የተፈጸመ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡- በ32 መ/ቤቶች እና በ9 ቅ/ጽ/ቤቶች ለተለያዩ ግንባታና ግዢዎች ብር 4,968,408.26 እና ለውሎ አበልና ሌሎች ክፍያዎች ብር 57,683,793.41 በድምር ብር 62,652,201.67 በብልጫ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-5/17 ተመልክቷል/

በመሆኑም መ/ቤቶች የፋይናንስ ስርዓቱንና የወጡትን ደንብና መመሪያዎች ተከትሎ መፈጸም እንደሚገባቸው፣ በብልጫ የተከፈለውም ገንዘብ ለመንግስት ካዝና ተመላሽ እንዲሆን አስፈላጊው እርምጃእንዲወሰድ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

4.9 ከሥራ ተቋራጮች የሚፈለግ ያልተወራረደ ቅድሚያ ክፍያ፣

ለግንባታ ስራዎች የተፈቀደው በጀት ለታቀደለት ዓላማ መዋሉን እንዲሁም ለተቋራጮቹ የሚሰጡ ማናቸውም ቅድሚያ ክፍያዎች በሚቀርበው የተቋራጮች ክፍያ ላይ ለቅድመ ክፍያ በተቀመጠው ፐርሰንት ልክ ተቀናሽ እየተደረገ ለመንግስት ተመላሽ መደረግ እንደሚኖርበት የፋይናንስ ህጉ ይደነግጋል፡፡ በዚህ መሰረት መፈፀሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

በ 2 መቤቶች ለቅድሚያ ክፍያ የተከፈለ በድምሩ ብር 133,555,459.90 ከተቋራጮች ተመላሽ ተደርጎ ለመንግስት ገቢ ያልተደረገ እንዲሁም በ1 መ/ቤት ውል ከተቋረጠ በኋላ ተመላሽ ያልተደረገ ብር 15,411,224.99 በድምሩ ብር 148,966,684.89 በኦዲት ወቅት ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-5/18 ተመልክቷል/

የተከፈለው የቅድሚያ ክፍያ የመንግስት ገንዘብ ተመላሽ ተደርጎ ለመንግስት ፈሰስ መደረግ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.10 የግዥ አዋጅ ደንብና መመሪያ ያልተከተሉ ግዥዎች

የዕቃና አገልግሎት ግዥዎች በመንግሥት ደንብና መመሪያ መሠረት የተፈጸመ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡- በ73 መ/ቤቶችና በ15 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 2,573,435,682.25

የመንግሥትን የግዢ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ያልተከተለ ግዢ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ- 5/20 ተመልክቷል፡፡/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	320,446,681.80
ገቢ.ዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን	"	192,9594,963
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	"	157,438,256.7
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	49,074,744.72
ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	58,650,294.43
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	58,230,741.3
በድምር	ብር	2,573,435,682.25

ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ካልተከተሉት የግዥ አዋጅ ደንብና መመሪያዎች፡- ያለጨረታ በቀጥታ ግዥ በመፈጸም ብር 2,219,952,785.14፣ መስፈርቱ ሳይሟላ በውስን ጨረታ የተገዛ ብር 108,781,488.62 ፣ ግልጽ ጨረታ መውጣት ሲገባው በዋጋ ማወዳደሪያ የተፈጸመ ግዥ ብር 96,187,579.93 ፣ የዋጋ ማወዳደሪያ ሳይሰበሰብ በቀጥታ የተፈጸመ ግዥ ብር 13,840,367.55 እና ሌሎች የግዥ ሂደት ያልተከተሉ ብር 134,673,461.01 ናቸው፡፡ ከግዥ አዋጅ፤ ደንብና መመሪያዎች ውጭ ግዥ ከፈጸሙ መ/ቤቶች መካከል፡-

ገቢ.ዎች ሚኒስቴር ዋናው መ/ቤት ብር 1,845,081,624.67፣ የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት ብር 91,059,356.22፣ የውሀና ኢነርጂ ሚኒስቴር ብር 65,505,288.81፣ የፌዴራል ፖሊስ ኮምሽን ብር 62,911,764.97፣ የኢትዮጵያ ፖሊስ ዩኒቨርሲቲ ብር 57,185,359.91፣ ቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲ ብር 37,430,081.28፣ ምዕራብ አ አዲስ አበባ ገቢ.ዎች ቅ/ፅ/ቤት ብር 30,909,250.85፣ የኢትዮጵያ የአካል ድጋፍ አገልግሎት ብር 23,179,483.60፣ የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ኢንስቲትዩት ብር 20,724,803.5 እና ጉምሩክ ኮሚሽን ድሬዳዋ ቅርንጫፍ ብር 20,388,811.7 ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

ከዚሁ በተጨማሪ የተገዙት ዕቃዎችና የተሰጠው አገልግሎት በናሙናው መሠረት ገቢ. ለመሆኑና አገልግሎት ለመሰጠቱ የቴክኒክ ኮሚቴ/ በባለሙያ ሳይረጋገጥ በ14 መ/ቤቶች

የብር 96,429,644.41 ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ ተረጋግጧል። /ዝርዝሩ በአባሪ 5/21 ተመልክቷል፡፡/

በሌላ በኩል ከሚያዝያ በኋላ በቀሩት ሁለት ወራት ውስጥ ፣ የግዥው አንገብጋቢነትና የበላይ ኃላፊ ሳይፈቅድ ግዥዎች መፈፀማቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ6 መ/ቤቶችና በ1 ቅ/ጽ/ቤት የብር 32,771,637.95 ግዥዎች ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡ ዝርዝሩ በአባሪ 5/16 ተመልክቷል፡፡

ከመንግስት መመሪያ ውጪ ግዥ መፈፀም ጥራቱን ላልጠበቀ ዕቃ ወይም ግንባታና ለአላስፈላጊ ወጪ ሊዳርግ ስለሚችል መንግስት ሊያገኝ የሚገባውን ጥቅም የሚያሳጣ ነው፡፡

በመሆኑም ለወደፊቱ ግዥዎች ሲፈፀሙ መንግሥት ባወጣው የግዥ ደንብና መመሪያ መሠረት መፈጸም እንደሚገባ ያሳሰብን ሲሆን፣ የመንግስትን አዋጅ በማያከብሩ የመ/ቤቶች የስራ ኃላፊዎች ላይም ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል፡፡

4.11 የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልተዘጋጀለት

በበጀት ዓመቱ የተገዛ እቃ ወደ ንብረት ክፍል ገቢ የተደረገና የንብረት ገቢ ደረሰኝም የተቆጠረለት መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡- በ9 መ/ቤቶች በብር 2,196,501.19 ተገዙ ተብሎ በወጪ ለተመዘገበ ሂሳብ ንብረቱ ገቢ ለመደረጉ ማስረጃ ሳይቀርብ ሂሳቡን በወጪ የመዘገቡ መ/ቤቶች እና በ2 መ/ቤቶች ደግሞ ብር 58,653,155.12 ቀረጥ ተከፍሎባቸው ንብረቶቹ ገቢ ለመሆናቸው ማስረጃ ሳይቀርብላቸው ሂሳቡ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡/ በአባሪ 5/22 ሀ እና ለ ተመልክቷል/

ንብረቶቹ ለመደረጋቸው ማስረጃ ሳይቀርብ ሂሳቡ በወጪ የተመዘገበው በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	"	743,913.00
አቅን ግንባታ መ/ቤቶች	"	931,089.25
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	521,498.94
በድምሩ	ብር	2,196,501.19

ለዕቃና ንብረት ግዥ ለወጣው ገንዘብ ዕቃው ገቢ ለመደረጉ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሳይቀርብ በወጪ መመዝገቡ መንግስት ላወጣው ወጪ ተመጣጠኝ አገልግሎት ስለመግኘቱ ማረጋገጥ የማይቻል ሲሆን የተገዛው ንብረት ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል።

በመሆኑም መ/ቤቶች በዚህ መልኩ ወጪ ለሆነው ሂሳብ ንብረቱ ገቢ ለመሆኑ በማረጋገጥ የንብረት ገቢ ደረሰኝ እንዲያዘጋጁና ለተከፈለውም የቀረጥ ሂሳብ ምዝገባ ከማከናወናቸው በፊት ቀረጡን የከፈሉላቸው ድርጅቶች ቀረጥ የተከፈለባቸውን ንብረቶች ገቢ ለማድረጋቸው ማረጋገጥ እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

4.12 በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ የተመዘገበ የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ

በበጀት ዓመቱ በመንግሥት መ/ቤቶች በወጪ የተመዘገበው ሂሳብ ደንብና መመሪያ መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- በ4 መ/ቤቶች ለልዩ ልዩ ኮንትራታዊ አገልግሎቶች ክፍያ በድምሩ ብር 6,751,884.15 በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-5/27 ተመልክቷል/

የቅድሚያ ክፍያን በወጪ የመዘገቡ መ/ቤቶች፡- የፌዴራሉ ሪፐብሊካን ጥበቃ ኃይል ብር 2,217,300.00 ፣ የቤተ-መንግስት አስተዳደር ብር 705,985.25 ፣ የሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ብር 3,202,966.00 እና የፌዴራል ማረሚያ ቤት ኮሚሽን ብር 625,632.90 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ቅድሚያ ክፍያዎች በተሰበሳቢ ሂሳብነት ተይዘው ሥራው መሰራቱ ሲረጋገጥና ተገቢው ማስረጃ ሲሟላ ብቻ በወጪነት መመዝገብ አለባቸው፡፡ የግንባታ ክፍያዎችም በሚከፈሉበት ጊዜም ቀደም ሲል የተሰጠው ቅድሚያ ክፍያ እየተጣራ በሕጉ መሰረት ከእያንዳንዱ የክፍያ የምስክር ወረቀት ተቀንሶ ለመንግሥት ተመላሽ ሊሆን ይገባል፡፡

በመሆኑም የመንግሥት ሂሳብ አያያዝ በሚያዘው መሠረት አስፈላጊውን ማስተካከያ በማድረግ፣ ቅድሚያ ክፍያው ሥራው ተጠናቆ በቂ ማስረጃ እስከሚቀርብበት ድረስ በተሰብሳቢ ሂሳብ እንዲመዘገብ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

4.13 የሂሳብ መደቡን ሳይጠብቅ በወጪ ተመዝግቦ የተገኘ ሂሳብ

የወጪ ሂሣቦች የሚመዘገቡት የገ/ኢ/ት/ሚ/ር ነሐሴ 1999 ዓ.ም ባወጣው ደንብ መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- በ71 መ/ቤቶች እና በ7 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 293,470,433.15 የወጪ ሂሣብ መደባቸውን ሳይጠብቁ ተመዝግበው ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ- 5/25 ተመልክቷል/

ሂሳቡም በዘርፍ ሲጠቃለል፡-

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	"	47,185,246.29
ገቢዎችና ጉምሩክ መ/ቤቶች		7,570,847.33
ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	56,442,824.95
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	38,349,758.27
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	"	129,731,502.40
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	14,190,253.91
በድምር	ብር	293,470,433.15

የወጪ ሂሣብ መደብ ሳይጠብቁ ወጪ ከመዘገቡ መ/ቤቶች መካከል፡-

አማኑኤል የአዕምሮ እስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ብር 108,749,200.18፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ብር 27,190,058.66፣ የስፔስ ሳይንስና ጂኦስፓሻል ኢንስቲትዩት ብር 25,065,959.85፣ ኢሚግሬሽን እና ዜግነት አገልግሎት ብር 11,778,519.00 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

የሂሣብ መደቡን ጠብቆ ወጪ አለመመዝገብ የበጀት አጠቃቀም ላይ ተፅዕኖ በመፍጠር ከበጀት በላይ ወይም በታች መጠቀምን ከማስከተሉም በላይ የሂሳብ ሪፖርቱን ትክክለኛነትም ያዛባል፡፡

በመሆኑም ሂሣቦቹ በተገቢው የወጪ ሂሣብ መደብ እንዲመዘገቡና ለወደፊትም ተመሣሣይ የአሠራር ግድፈት እንዳይፈፀም ጥንቃቄ እንዲደረግ አሳስበናል፡፡

4.14 የበጀት ዓመቱን ያልጠበቀ የወጪ ሂሳብ

በወጪ የተመዘገቡ ሂሳቦች በበጀት ዓመቱ ለተገኙ አገልግሎቶች ብቻ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- በ21 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 4,4894,644.74 የወጪ ሒሳብ መደባቸውን ሳይጠብቁ ተመዝግቦ ተገኝጣል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ- 5/24 ተመልክቷል/

ሂሳቡም በዘርፍ ሲጠቃለል፤

የፋይናንስን ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	8,445,860.71
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች		30,072,138.92
ልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	"	128,340.95
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	6,248,304.16
በድምሩ	ብር	44,894,644.74

የበጀት ዓመቱን ያልጠበቀ የወጪ ሂሳብ የበጀት ዓመቱ የበጀት አፈፃፀም በትክክል እንዳይታይ ሊያደርግ ይችላል፡፡

በመሆኑም ለወደፊቱ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ማዕቀፍ መሰረት በበጀት ዓመቱ ለተገኘ አገልግሎት ወጪውም በተገኘበት በጀት ዓመት ሊመዘገብ እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.15 በአግባቡ ያልተመዘገበ የወጪ ሂሳብ

የወጪ ሂሳብ በፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሠረት በአግባቡ መፈጸሙንና በትክክል መመዘገቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡ በ1 መ/ቤት ብር 56,178,158.97 የወጪ ሂሳብ በድጋሚ የተመዘገበ መሆኑ፤ በ2 መ/ቤት ብር 721,743.72 የወጪ ሂሳብ በብልጫ የተመዘገበ መሆኑ፣ በ2 መ/ቤቶች ብር 7,815,207.57 በማነስ የተመዘገበ እና በ2 መ/ቤቶች ብር 1,222,117.91 የወጪ ሂሳብ ያልተመዘገበ መሆኑ፤ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡ ዝርዝሩ በአባሪ 5/23 ተመልክቷል፡፡

ለሂሳቦቹ ተገቢ የሂሳብ ማስተካከያ መስራት እንደሚገባ አሳስበናል፡፡ ለወደፊቱም ክፍያዎች በመንግስት መመሪያ መሠረት እንዲፈጸሙና በትክክል እንዲመዘገቡ በየጊዜው ተገቢ ቁጥጥር ማድረግ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

4.16 በወጪ አፈፃፀም ላይ በተለያዩ መ/ቤቶች የታዩ ሌሎች ችግሮች

በ1 መ/ቤት አላግባብ በወጪ የተመዘገበ የግንባታ መያዣ ተመላሽ ክፍያ ብር 44,755,532.47 መገኘቱ፣

በ2 መ/ቤቶች በአማካሪ መሐንዲስ የክፍያ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሳይቀርብ የተፈጸመ ክፍያ ብር 170,394,448.47 መከፈሉ፣

በ1 መ/ቤት መመሪያው ከሚፈቅደው በላይ ለስራ ተቋራጭ የተሰጠ የስራ ለውጥ ትዕዛዝ ብር 16,618,007.30 መገኘቱ፣

በ1 መ/ቤትና በ2 የገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽቤቶች በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ የተወራረደና በወጪ የተመዘገበ 3,255,857.08 መገኘቱ፣

በ2 መ/ቤቶች አግባብ ባለው ባለሥልጣንና ቦርድ ሳይፈቀድ የተፈጸመ ክፍያ ብር 430,560.00 ክፍያ መፈፀሙ፣ (አባሪ 5/26 ተመልክቷል)

በ4 መ/ቤቶች በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ የተመዘገበ የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ ብር 6,751,884.15 መገኘቱ፣

በ2 መ/ቤቶች በሚመለከተው አካል ያልጸደቀ ወጪ ሂሳብ ብር 924,505.86 መገኘቱ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ ዝርዝሩ በአባሪ 5/28 ስር ሀ-ከ ተመልክቷል፡፡

በ1 መ/ቤት የቀን ሰራኞችን እንደ ኮንትራት ሰራኛ በመቅጠርና በማሰራት የተፈጸመ ክፍያ ብር 13,520,250.17 መገኘቱ፣ (ዝርዝሩ አባሪ 10/1 ሀ ተመልክቷል)

በተጨማሪም የሚከተሉት ከወጪ ጋር የተያያዙ ዋና ዋና ግኝቶች ታይተዋል፡፡

በመ/ቤቱ ኃላፊ ያልተፈቀደ የትርፍ ሰዓት ክፍያ በ2 መ/ቤቶች ብር 530,102.75 መገኘቱ፣

በ1 መ/ቤት የስራ ዝርዝር መግለጫ (Bill of quantity) ሳይቀርብ ለቢሮ እድሳት ወጪ የሆነ ብር 7,300,000.02 መገኘቱ፣

በ2 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 279,915.90 መመሪያን ያልተከተለ ክፍያ ተፈፅሞ ተገኝቷል፡

ወጪዎች መንግስት ባወጣቸው ድንብና መመሪያዎች እንዲፈፀሙ እንዲሁም የምዝገባ ማስተካከያ የሚያስፈልጋቸው ከላይ የተጠቀሱ የክፍያ ችግሮችም አስፈላጊው ማስተካከያ እንዲደረግባቸው በላክንላቸው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

5 የተከፋይ ሂሣብ

5.1 በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሣብ

በገንዘብ ሚኒስቴር መመሪያ መሠረት በበጀት ዓመቱ በተከፋይ ሂሣብ የተያዙት ሂሣቦች በተገቢው ጊዜ ውስጥ መከፈላቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-በ81 መ/ቤቶችና በ14 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 1,052,366,599.87 በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-6/1 ተመልክቷል/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፡-

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን	ብር	559,128,479.90
የገቢዎችና ጉምሩክ መ/ቤቶች	"	7,390,605.16
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	79,473,085.21
የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	85,536339.55
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	104,047,903.47
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	"	216,790,186.6
ድምር	ብር	1,052,366,599.87

በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ተገኝቷል፡፡

የተከፋይ ሂሳቡ በዕድሜ ቆይታ ጊዜው ሲተነተን፡- ከአንድ ወር በላይ እስከ አንድ ዓመት ብር 226,938,553.05፣ ከአንድ ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት ብር 5,089,75,623.31፣ ከአምስት ዓመት በላይ እስከ አሥር ዓመት ብር 29,599,360.42 እና

ከአሥር ዓመት በላይ ብር 284,952,444.76 ሲሆን፤ ቀሪው ሂሳብ ብር 1,900,618.33 የቆይታ ጊዜው በግልጽ ያልተለየ ሂሳብ ነው፡፡

እንዲሁም በ4 መ/ቤቶች ደግሞ ከአንድ ወር በላይ እስከ አንድ ዓመት ብር 12,443,978.09 ፣ ከአንድ ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት ብር 104,60,115.82፣ ከአምስት ዓመት በላይ እስከ አሥር ዓመት ብር 1,090,309.21 በድምሩ ብር 23,994,403.12 የፕሮጀክት ተከፋይ ሂሳብ በኦዲቱ ታይቷል፡፡ /ዝዝሩ በአባሪ-6/2 ተመልክቷል/፡፡

በወቅቱ ያልተከፈለ ሂሳብ ከታየባቸው መ/ቤቶች፡-

የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ብር 268,067,702.92፣ የመንግስት ግዥ አገልግሎት ብር 194,872,813.34፣ የኢትዮጵያ ጤና መድህን አገልግሎት ብር 90,066,409 ፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ብር 77,496,027.43፣ የግብርና ሚኒስቴር ብር 6,788,0451.11 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በመሆኑም መ/ቤቶች በወቅቱ ያልተከፈለውን ተከፋይ ሂሳብ ለሚመለከተው አካል የፋይናንስ ሕጉን ተከትለው ትክክለኛ የመ/ቤቱ ዕዳ መሆኑን በማጣራ እንዲከፍሉ አሳስበናል፡

5.2 በተከፋይ ሂሳብ አያያዝ የታዩ ሌሎች ድክመቶች

መደበኛ ባልሆነ የሂሳብ ሚዛን (ዴብት) የሚታይ በ3 መ/ቤቶች ብር 3,636,445.73 መኖሩ፣

በ2 መ/ቤቶች ያለአግባብ የተመዘገበ የተከፋይ ሂሳብ ብር 23,027,175.36፣

ተቀጽላ ሌጀር ያልተዘጋጀለት በ1 መ/ቤት ብር 84,820,262.99 ተገኝቷል፡፡

በ1 መ/ቤት በገቢ መታየት የነበረበት በተከፋይ ሂሳብ የያዘ መ/ቤት ብር 457,643,809.64 መገኘቱ

በ1 መ/ቤት በውጪ መታየት የነበረበት በተከፋይ ሂሳብ የሚታ ፕሮጀክት ሂሳብ ብር 64,846,538.71 መኖሩ፣

በ1 መ/ቤት የፕሮጀክት ወጪን ከመደበኛ ሂሳብ ጋር 5054 በተከፋይ ሂሳብ የያዘ መ/ቤት ብር 144,455,549.86

በ1 መ/ቤት ያልተመዘገበ የግንባታ መያዣ (Retention) ተከፋይ ሂሳብ ብር 9,025,910.00 ያልያዘ

በ1 መ/ቤት የግንባታ ሥራ የጥራት ዋስትና መያዣ (Retention) ሳይቀነስ የተፈጸመ ክፍያ ብር 966,197.34 መኖሩ

ባለመብቱ ማንና ለማን እንደሚከፈል ያልታወቀ በ14 መ/ቤቶች ብር 1,754,048,466.57 መኖሩ፣

ከተከፋይ ሂሳብ ተቀናሽ ያልተደረገ ተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 649,497.42፣ ቅድሚያ ክፍያ ብር 554,459.57፣ የመዋዣ ሂሳብ ብር 413,054.68፣ የስራ ግብር ብር 84,600.00፣

(ዊይዝሆልድ ታክስ) ብር 32,883.06 በሌላ በኩል ደግሞ በብልጫ የተቀነሰ የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 5,118.44 መገኘቱ፣ ዝርዝሩ በአባሪ 6/3 ሀ-ተ ተመልክቷል፡፡

በተከፋይ ሂሳብ አያያዝ ላይ ከላይ የተዘረዘሩ ችግሮችን ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ እንዲሁም ምዝገባዎች ትክክለኛውን የሂሳብ ሚዛን ተጠብቆ መከናወን እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

6. የበጀት አጠቃቀም

ኦዲት በተደረጉት መ/ቤቶች የተፈቀደላቸው በጀትና በሥራ ላይ ያዋሉት ሂሳብ ሲነፃፀር ከበጀት በላይ ወጪ የተደረገና በርካታ ያልተሠራበት በጀት የተገኘ ሲሆን እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

6.1 በበጀት ኮዱ ከተደለደለው በጀት በላይ የወጣ

የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ መሠረት ሥራ ላይ ማዋላቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡- በ20 መ/ቤቶች በልዩ ልዩ የሂሳብ መደቦች በደንቡ መሠረት ሳያስፈቅዱ ከተደለደለው በጀት በላይ ወጪ የሆነ ሂሳብ ከመደበኛ በጀት ብር 524,796,213.55፣ ከውስጥ ገቢ ብር 288,998,079.52 እና ከካፒታል በጀት ብር

489,429,895.62 በድምሩ ብር 1,303,224,188.69 ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ 7/1 ተመልክቷል፡፡/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፡-

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች		112,746,859.27
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	92,137,714.58
የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	1,050,380,663
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች		19,355,851.11
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	28,603,101.15
ጠ/ድምር	ብር	1,303,224,188.69

ከበጀት በላይ ወጪ ካደረጉ መ/ቤቶች፡- የሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ብር 322,547,520.3፣ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እና ተጠሪ ተቋማቱ ብር 267,930,274.6፣ የጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ ብር 173,212,241.4፣ የወለጋ ዩኒቨርሲቲ ብር 128,153,771.3፣ የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ብር 109,533,570.54፣ ዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ ብር 91,376,175.48፣ የአምቦ ዩኒቨርስቲ ብር 83,386,864.29 እና የአርባምንጭ ዩኒቨርሲቲ 75,107,915.65 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ከዚህ በተጨማሪም በ2 መ/ቤቶች ብር 9,741,854.73 በጀት ስለመኖሩ ሳይረጋገጥ ወይም ሳይፈቀድ የተፈፀሙ ክፍያዎች /ዝርዝሩ በአባሪ- 7/2 ተመልክቷል/

መ/ቤቶች በበጀት እቅድ ዝግጅትና አጠቃቀም ወቅት ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊያደረግ እንደሚገባ እና የበጀት እጥረት ካጋጠመም በበጀት ሕጉ መሰረት የበጀት ዝውውር መጠየቅ እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

6.2 ያልተሰራበት በጀት

መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ መሠረት ሥራ ላይ ማዋላቸውና በጀታቸውንም በአግባቡ መጠቀመቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በየሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት ከ10% በላይ ያልተጠቀሙበትን ብቻ በመውሰድ በ101 መ/ቤቶች መደበኛ በጀት ብር 5,357,361,315.89፣ የውስጥ ገቢ ብር 207,644,481.79

እና ካፒታል ብር 13,725,126,257.26 በድምሩ ብር 19,290,132,054.94 ያልተሰራበት በጀት ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩም በአባሪ-7/1 ተመልክቷል፡፡/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፡-

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	10,249,945,604.40
ገቢዎችና ጉምሩክ መ/ቤቶች	"	648,789,176.6
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	"	4,215,004,662
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	609,738,799.7
ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	2,855,149,467
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	711,504,346
ጠ/ድምር	ብር	19,290,132,054.94

ለልዩ ልዩ የሂሳብ መደቦች ከተደለደለው በጀት ላይ ሳይሰራበት ከተገኘባቸው መ/ቤቶች መካከል፡- የገንዘብ ሚኒስቴር ብር 8,018,899,476.47፣ ጤና ሚኒስቴር ብር 1,993,400,893፣ የግብርና ሚኒስቴር ብር 1,202,273,994፣ የፌዴራል ፖሊስ ኮምሽን ብር 818,498,803.75፣ የወለጋ ዩኒቨርሲቲ ብር 727,839,708.8፣ ትምህርት ሚኒስቴር ብር 724,283,117.7፣ የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ብር 613,657,992.1፣ ጉምሩክ ኮሚሽን ብር 531,634,478.4፣ የጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ ብር 449,507,901፣ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እና ተጠሪ ተቋማቱ ብር 398,128,357.8 ፣ ትራንስፖርትና ሎጀስቲክ ሚኒስቴር ብር 346,223,039.46 ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

በጀት ከተፈቀደ በኋላ አለመጠቀም የታቀዱ ሥራዎች ሳይከናወኑ ሊቀሩና መ/ቤቱም ዓላማውን እንዳያሳካ ሊያደርግ ስለሚችል፣ ለወደፊቱ በበጀት ዝግጅትና አጠቃቀም ላይ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ለሚመለከታቸው መ/ቤቶች በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

7. የንብረት አያያዝና አጠባበቅ

7.1 የቋሚ የዕቃና ንብረት አስተዳደር ድክመቶች

መ/ቤቶች የመንግሥትን ንብረት በደንቡ መሠረት መዝግበው ቁጥጥር የሚያደርጉ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት የአሰራር ድክመቶች መኖራቸውን በኦዲታችን ወቅት ተረጋግጧል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ 8/1 ሀ እስከ ደ ተመልክቷል፡፡/

ንብረት አስተዳደር

የግኝት መግለጫ	መ/ቤቶች	ቅ/ጽ/ቤቶች
ለቋሚ ዕቃዎች የተሟላ መለያ ቁጥር ያልሰጡ	15	1
ዓመታዊ ቆጠራ ያደረጉ ቢሆንም ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር ትክክለኛነቱን ያላረጋገጡ	9	4
ዓመታዊ የቋሚና አላቂ ዕቃዎች ቆጠራ ያላደረጉ	14	
ቋሚና አላቂ ዕቃዎች መዝገብ/ስቶር ካርድ/ ያላቋቋሙ ወይም የተሟላ ምዝገባ ያላከናወኑ	6	3
የአላቂ የስቶክ መቆጣጠሪያ ቢን ካርድ ያላዘጋጁ መ/ቤቱች	21	2
አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ያለአገልግሎት የተቀመጡ ንብረቶች የተገኙባቸው	44	3
አገልግሎት መስጠት የማይችሉ የተለያዩ ንብረቶች በመንግስት መመሪያ መሰረት ሳይወደጉ የተገኙባቸው	56	8
ተያያዥነት ያላቸው የንብረት አስተዳደር ስራዎች በአንድ ሰራተኛ ብቻ የሚከናወንባቸው	15	
በየስራ ክፍሉ ለተሰጡ የቋሚ እቃዎች መቆጣጠሪያ ካርድ (User Card) ያላዘጋጁ መ/ቤቶች	10	2
የንብረት ክፍል ሰራተኞች ሲቀያየሩ ያስረከቡት ንብረት ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት ያልተረጋገጠ		
የንብረት ጥበቃ ላይ ተመድበው ተያዥ/ዋስትና ያላቀረቡ ሰራተኞች	1	
በተወረሱና በእንጥልጥል ላይ ያሉ ንብረቶች አያያዝ ችግር የሚታይባቸውና ዓመታዊ ቆጠራ ያልተደረገ/32 ተሽከርካሪዎችናሌሎች የተለያዩ ዕቃዎች/		6
የለቀቁ ሰራተኞች ሲጠቀሙባቸው የነበሩ ንብረቶች ወደ ግምጃ ቤት ተመላሽ አለማድረጋቸው (በርካታ ንብረቶች በገንዘብ ያልተገለፁ እና ሌሎች በዋጋ የተቀመጡ ብር 5,789,078.63	15	3

ይገኙበታል)		
በእርዳታና በስጦታ ለተገኙ ዕቃዎቸ ዋጋ ያልተመኑ መ/ቤቶች	1	2
አገልግሎት የሚሰጡና የማይሰጡ ዕቃዎች ተለይተው የማይቀመጡ መሆኑ		6
ጊዜው ያለፈበት መድሃኒትና የተለያዩ ኬሚካሎችን በአግባቡ ያላስወገዱ መ/ቤቶች	15	1

(ዝርዝሩ በአባሪ 8/1 ከሀ እስከ የ ተመልክቷል)

መንግሥት ለቋሚና አላቂ ዕቃዎች ግዥ በየዓመቱ የሚያወጣው ወጪ ከፍተኛ ቢሆንም በብዙ መ/ቤቶች የሚታየው ንብረት አስተዳደር አጥጋቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህም ምክንያት በእነዚህ መ/ቤቶች የተዘረጋው የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ደካማ በመሆኑ ዕቃና ንብረት ለምዝበራና ብክነት የመጋለጥ እድሉ ከፍተኛ ነው፡፡

አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ንብረቶች ያለአገልግሎት በየንብረት ክፍሉ ተከማችተው እያለ የተመሳሳይ ንብረቶች ግዥ የሚፈጽሙ መ/ቤቶችም መኖራቸው በኦዲታችን ወቅት ታይቷል። የእነዚህ የተለያዩ የንብረት አያያዝ ችግሮች የሚታዩባቸው በእያንዳንዱ የኦዲት ሪፖርት በዝርዝር እና ዋና ዋናዎቹም በየዘርፉ የንብረት አያያዝና አስተዳደር የታዩ ሌሎች የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ድክመቶች በሚል ተገልጿል።

በመሆኑም መ/ቤቶቹ የመንግሥትን ንብረት ለምዝበራና ብክነት እንዳይጋለጥ ተገቢውን ምዝገባና ቁጥጥር እንዲያደርጉ፤ አገልግሎት መስጠት የማይችሉትንና ጊዜ ያለፈባቸው መድኃኒቶችና ኬሚካሎች በመንግስት የንብረት አስተዳደር መመሪያ መሰረትና በጥንቃቄ እንዲያስወግዱ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

7.2 ተሽከርካሪ

የተሽከርካሪ አጠቃቀምና አያያዝን በተመለከተ በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

የተሽከርካሪ አጠቃቀምና አያያዝ

የግኝት መግለጫ	የተሽከርካሪዎች ብዛት		
	የመ/ቤቶች/ቅ*	መኪና	ሞተር ብስክሌቶች/**
ሊብሬ ያልቀረበላቸው	13/3*	85	11/6**
በብልሽት ምክንያት ያለአገልግሎት የቆሙ	37/4*	473	27/65**
የሰሌዳ ቁጥር የሌላቸው	2/2*	5	11
የባሌቤትነት መታወቂያ ደብተራቸው በሌሎች መ/ቤቶችና ድርጅቶች ስም የሆነ	21/4*	188	20
የሞተር ቁጥር የሌላቸው	1	5	4
የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር በተሽከርካሪዎቹ ላይ በተመለከተው የሻንሲ ቁጥር መካከል ልዩነት ያለው	1	8	
የነዳጅ መቆጣጠሪያቸው /ጌጅ/ የማይሰራ	9	85	4
የተሽከርካሪ ፋይል የሌላቸው / የማያደረጁ	10/1*	89	4
ሊብሬው ብቻ ኖሮ ተሽከርካሪው በአካል የሌለ	1/1*	1	4

ቅ*- ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ** ሌሎች- ሎቤድ፣ ትራክተር የቁፋሮ ማሽን፣ ኮምፕሬሰር… መኖራቸው ታውቋል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ- 8/2 ከሀ እስከ ፐ ተመልክቷል/

በመሆኑም መ/ቤቶቹ በሁኔታው ላይ የእርምት እርምጃ መውሰድ እንዳለባቸው በመግለጽ በብልሽት ምክንያት ቆመው የሚገኙ ተሽከርካሪዎች ተጠግነው አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ፣ የማያገለግሉት ደግሞ በመንግሥት ንብረት አስተዳዳር መመሪያ መሠረት እንዲሸጡ/እንዲወገዱ፣ ሊብሬ እና ሰሌዳ ቁጥር የሌላቸው እንዲወጣላቸው አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል፡፡

8. ባለፉት ዓመታት ኦዲት ሪፖርት በተሰጡ የማሻሻያ ሃሳቦች መሠረት እርምጃ አወሳሰድን በተመለከተ

በመ/ቤታችን ማቋቋሚያ አዋጅ አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ 3 እና 4 መሠረት ኦዲት ተደራጊዎች በፌዴራል ዋና ኦዲተሩ በተላኩ የኦዲት ሪፖርቶች የተገለጹ ግኝቶች ላይ በአሥራ አምስት ቀን ውስጥ እርምጃ የመውሰድ ግዴታ እንዳለባቸውና ለመውሰድ ካልቻሉም ምክንያቱን በመግለፅ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ማሳወቅ እንዳለባቸው ይታወቃል፡፡

በ2014 በጀት ዓመት እና ቀደም ባሉት ዓመታት መ/ቤታችን በላካቸው የኦዲት ሪፖርቶች መሠረት እርምጃ የተወሰደ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ90 መ/ቤቶች በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ተመላሽ እንዲደረግ ተብሎ አስተያየት ከተሰጠበት ሒሳብ ብር 443,023,846.91 እና 23,230.43 የአሜሪካ ዶላር ውስጥ ብር 394,805,880.56 እና 23,230.43 የአሜሪካ ዶላር እርምጃ ያልተወሰደበት ቀሪ ሂሳብ መሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን፣ ብር 48,217,965.67 ተመላሽ መደረጉን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በሌላ በኩል በገቢዎች ሚኒስቴር በሚገኙ 9 ቅ/ጽ/ቤቶች እና በጉምሩክ ኮሚሽን ስር በሚገኙ 11 ቅ/ጽ/ቤቶች በገቢ አሰባሰብ ዙሪያ ብር **18,397,938,661.00** እርምጃ እንዳልተወሰደ ታውቋል፡፡

2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ማሻሻያ ሀሳብ ላይ እርምጃ አወሳሰድ የተሟለላ ማስረጃ ሰነድ መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡ በ17 መ/ቤቶችና በ4 ቅ/ጽ/ቤቶች የሰነድ ማስረጃ እንዲቀርብ አስተያት ከተሰጠው ብር 5,061,185,100.80 ውስጥ ብር 508,157,756.13 የሰነድ ማስረጃ የቀረበለት ሲሆን ብር 4,553,027,344.67 ደግሞ የሰነድ ማስረጃ ያልቀረበለት መሆኑን ማረጋገጥ ተችላል፡፡ ዝርዝሩ በአባሪ 9/1ለ ተመልክቷል፡፡

በመሆኑም መሥሪያ ቤቶች በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት የማስተካከያ እርምጃ የማይወሰዱ ከሆነ ለውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱ መዳከም፣ ለመንግሥት ገንዘብና ንብረት መባከን እና አለአግባብ መውጣት ምክንያት ሊሆን ስለሚችል፣ በተሰጡ የማሻሻያ ሃሳቦች መሰረት አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወሰዱ፣ ለወደፊቱም በኦዲት ሪፖርት በሚሰጡት የማሻሻያ ሃሳቦች መሰረት እርምጃ ለመወሰዱ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

4. <u>የክዋኔ እና የአካባቢያዊ ኦዲት ዋና ዋና ግኝቶች እና የማሻሻያ ሃሳቦች</u>

በክዋኔ ኦዲቱ የታዩ ዋና ዋና ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡ እነርሱም፡-

5. <u>የልማትና ማህበራዊ አገልግሎቶች ክዋኔ ኦዲት የ2015-16 ኦዲት አመት የተከናወኑ ኦዲቶች ማጠቃለያ ዘገባ</u>

- **በኢትዮጵያ ሎተሪ አገልግሎት በፍቃድ ለሚሰሩ ለሌሎች አካላት የዕድል ሎተሪ እንዲያጫውቱ የሚደረግበት የፍቃድ አሰጣጥ እና ገቢ አሰባሰብ ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት**

1. **በአዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀፅ 107 (2) የተቋሙን አደረጃጀት እንዲሁም ስልጣንና ተግባራት የሚደነግግ ሌላ ህግ መውጣቱን በተመለከተ፡-**

2. በአዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀፅ 107 (2) የተቋሙን አደረጃጀት እንዲሁም ስልጣንና ተግባራት የሚደነግግ ሌላ ህግ ሊወጣ እና ባለቤቱ በትክክል ታውቆ ሥራው በአግባቡ ሊመራ ይገባል፡፡
3. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በአዋጅ ቁጥር 160/2001 አንቀጽ 6(4) በፍቃድ የዕድል ሎተሪ ጨዋታን ለሚያጫውቱ አካላት ፍቃድ የመስጠት እና የመቆጣጠር ስልጣንና ተግባር ለአገልግሎቱ ተሰጥቶ የነበረ ሲሆን በአዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀጽ 27 ቀ፣ በ፣ ተ መሰረት ለገቢዎች ሚኒስቴር የተሰጠው ቢሆንም አገልግሎቱ ከገቢዎች ሚኒስቴር ጋር በመሆን በአዋጁ የተሰጣቸውን አሁናዊ ኃላፊነት ለማስተግበር የየተቋማቸውን አደረጃጀትና ስልጣንና ተግባር የሚደነግግ ረቂቅ ህግ እንዲወጣ እና በሚመለከተው አካል እንዲጸድቅ በማቅረብ ለገቢዎች ሚኒስቴር ስራውን ያላስረከበ መሆኑ፣

4. **አገልግሎቱ የዕድል ሎተሪ ጨዋታዎች የሚመሩበት ደንብና መመሪያዎች መጽደቃቸው እና ወቅታዊ መደረጋቸውን በተመለከተ፡**

5. አገልግሎቱ የዕድል ጨዋታዎች የሚመሩበት ደንብና መመሪያዎች ሊያዘጋጅ፣ በሚመለከተው አካል እንዲጸድቁ ሊያደርግ እንዲሁም ወቅታዊ ሁኔታዎችን ተከትለው እንዲሻሻሉ ሊያደርግ ይገባል፡፡

6. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡
   - የኮንቬንሽን ቢንጎ መመሪያ (በ2002 ዓ.ም) እና የፕሮሞሽን ውድድር እና የቶምቦላ ወይም ራፍል መመሪያ (በ2005 ዓ.ም) ከአስር አመት በላይ ያገለገሉ ቢሆንም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ወቅታዊ ሁኔታዎችን ተከትለው እንዲሻሻሉ ያልተደረገ መሆኑ፤
   - ያልተሻሻሉ መመሪያዎችም ለአሰራርም አስቸጋሪ ሁኔታዎችን እየፈጠሩ መሆኑ ለምሳሌ የኮንቬንሽናል ቢንጎ መመሪያው ላይ በተቀመጠው ቀን እድሳት ያላደሰ ብር 500 ቅጣት በመክፈል ማደስ እንደሚችል የሚገልጽ በመሆኑ ምንም ያህል ጊዜ አሳልፈው ቢመጡ 500 ብር ብቻ ተቀጥተው እንደሚቀጥሉ እና ፍቃድ ለማገድ/ለመሰረዝ/ አገልግሎቱ የተቸገረ መሆኑ፤

7. **የዕድል ሎተሪ ጨዋታን ለማጫወት የሚያስችል የፍቃድ አሰጣጥን በተመለከተ፡-**

8. አገልግሎቱ ማንኛውም በፈቃድ የሚሰሩ የዕድል ሎተሪ ጨዋታዎችን ለማጫወት ፍቃድ የሚጠይቁ አመልካቾች ያቀረቡትን ማስረጃዎች በመመሪያው መሰረት የተሟሉ እና ትክክለኛ ስለመሆናቸው በማረጋገጥ ማስረጃዎች ካሟሉ በኋላ አገልግሎቱ የፈቃድ ሰርተፊኬት አዘጋጅቶ፣ አስፈርሞና ማህተም አድርጎ ሊሰጥ ይገባል፡፡

9. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡-
   - አገልግሎቱ ከኢትዮጵያ ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት ጋር በመሆን በኢትዮጵያ ውስጥ የስፖርት ውርርድ አሰራሮችን እና ውጤቶችን

መገምገም(Assessing the Practices and Effects of Sport Betting in Ethiopia) በሚል እ.ኤ.አ June 2021 የተጠና ጥናት ያለ ሲሆን በተጠናው ጥናት ግኝቶች መሰረት፡

- እ.ኤ.አ በ2021 ከነበሩ በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች የሚገኙ ከአገልግሎቱ ፍቃድ ከወሰዱ 42 የስፖርት ውርርድ አጫዋቾች ውስጥ በ15ቱ አጫዋቾች ማጫወቻ ቦታ በመገኘትና ማጫወቻ ቦታዎቹ ጋር ላገኛቸው 343 ተጫዋቾች ናሙና በመውሰድ ጥናቱን ያከናወነ ሲሆን የካፒታል ጋዜጣ እ.ኤ.አ በ2019 ባወጣው 1 ሚሊየን የስፖርት ውርርድ ጨዋታ ተጫዋቾች መኖራቸውን በሚገልፀው መረጃ መሰረት ጥናቱም ይህን ቁጥር እንደሚወክል የተገለፀ ሲሆን፡

- በናሙና በታዩ የስፖርት ውርርድ ተጫዋቾች እድሜያቸው ከ19-30 የሚሆኑ ወጣቶች 57.5% መሆናቸው፣ ዕድሜያቸው 31-40 የሆኑት 28.9% ሲሆኑ እድሜያቸው ከ41-50 የሚሆኑት 1.3% መሆናቸውን የሚገልጽ ሲሆን ይህም አብዛኛው በተማሪና ሰራተኛ እድሜ ክልል የሚገኙ ግለሰቦች በብዛት የሚጫወቱ መሆኑን የሚያሳይ መሆኑ፤
- የጨዋታ ድግግሞሽ በሚታይበት ጊዜ 29.6% የሚሆኑት አንዳንዴ የሚጫወቱ፣ 24.8% የሆኑት በሳምንት አንዳንድ ጊዜ የሚጫወቱ፣ 24.1% የሆኑት ሁል ጊዜ የሚጫወቱ፣ 8% የሆኑት በሳምንት አንድ ጊዜ የሚጫወቱ፣ 6.8% የሆኑት በቀን አንድ ጊዜ የሚጫወቱ፣ 6.8% የተወሰነ ጊዜ በሳምንት የሚጫወቱ ሲሆን ይህም የጨዋታው ሱስ ተጋላጭነታቸውን የሚያመላክት መሆኑ፤
- ለስፖርት ውርርዱ የሚወጡ ወጪዎችን በሚመለከት 39.5% እስከ 5% የወር ገቢያቸውን የሚያወጡ፣ 24.3% ከ5-15% የወር ገቢያቸውን የሚያወጡ፣ 15.6% ከ16-30% የወር ገቢያቸውን የሚያወጡ፣ 10.8% ከ31-50% የወር ገቢያቸውን የሚያወጡ፣ 9.9% ከ50% በላይ የወር ገቢያቸውን የሚያወጡ መሆኑን የተገለፀ መሆኑ፤
- 37.2% የሚኑ ተጫዋቾች ከእለት ወደ እለት የጨዋታ ፍላጎታቸው በከፍተኛ ሁኔታ መጨመሩን የገለፁ መሆኑ፤ የስፖርታዊ ውርርዶች እንደ ሱስ የመሆን ሁኔታ ያላቸው መሆኑን 41.1% የሚያምኑ፣

14.1% ገለልተኛ ሀሳብ የሰጡ እና 44.4% የማያምኑ ሲሆኑ ተጫዋቾች የስፖርት ውርርዶች ሱስ የመሆን ከፍተኛ እድል እንዳላቸው እያወቁ ከጨዋታው መገለል እንዳልቻሉ የሚያሳይ መሆኑ፤

- በጥናቱ ከታዩ ተጫዋቾች 22.6% የሚሆኑት የስፖርት ውርርድ ጨዋታዎች ያላቸውን ጠቃሚ ነገር ያሳጣቸው መሆኑን የገለፁ ሲሆን ጥናቱ ይወክላል ባለው 1 ሚሊየን ተጫዋች እንኳን ቢሰላ 226,000 (ሁለት መቶ ሀያ ስድስት ሺህ) ሰው በስፖርት ውርርድ ምክንያት አስፈላጊ ነገሮችን ያጣ መሆኑን የሚያሳይና አሁን ካለው የስፖርት አወዳዳሪ ቤቶች ብዛት አንፃር እና ተጫዋቾች ብዛት ቢታሰብ ቁጥሩ በጣም ከፍተኛ መሆኑን ለመገመት የሚያስችል መሆኑ፤
- በኢትዮጵያ የስፖርት ውርርድን የሚመራው ህግ ገቢን ከማግኘት አንፃር የበለጠ ትኩረት የሰጠ ቢሆንም እንደ ታዳጊና ወጣቶች ያሉ የህብረተሰብ ክፍሎችን ከመጠበቅና ወንጀልን ከመከላከል አንፃር ማህበረሰቡ ላይ የሚያሳድሩትን ተፅንዖች በተመለከተ ትኩረት ያልሰጠ መሆኑን እንዲሁም የስፖርት ውርርድ ጨዋታዎች ሱስ የሚያስይዙ እና ቁማር ጨዋታዎች መሆናቸውን በተገቢው መልኩ ከግንዛቤ ያልተወሰደ መሆኑን የሚገልፅ መሆኑ፤
- ስፖርት ውርርድ እንደ ሱስና ቁማር በሚሆንበት ጊዜ የተለያዩ የህብረተሰብ ጤና ስጋት ተደርጎ የሚወሰድ እንዲሁም የስነልቦና ጫናዎችን፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖዎችን የሚያስከትል ሲሆን ለማሳያም ግትርነት፣ እረፍት ማጣት፣ ከፍተኛ የጭንቀት ስሜት መሰማትና ይህንን ስሜትም ለመቋቋም ቁማርን እንደ መፍትሄ መጠቀም፣ ቁማር ላይ እራስን መቆጣጠር አለመቻል፣ የሚጫወቱበትን ገንዘብ ለማግኘት ወይም የቁማር እዳቸውን ለመክፈል ስርቆት ወንጀል መፈፀም፣ ያላቸውን ገቢ በጨዋታው አጥፍተው ቤተሰብ ማስራብ፣ ፍቺ (የቤተሰብ መበተን ብሎም ሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ለጎዳና ተዳዳሪነት መዳረግ)፣ ማህበራዊ መገለል፣ በስራ ላይ ያሉ ችግሮች እና የቤተሰብ ግንኙነቶችን ማበላሸት፣

ሲብስም እራስን ማጥፋት ወይም የሌላን ሰው ህይወት ማጥፋት ችግሮች እንደሚያስከትል፤

የሚገልፅ መሆኑ፤

10. **አገልግሎቱ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመደገፍ ፈቃድ በማውጣት የዕድል ሎተሪ ጨዋታን የሚያጫውቱ አካላት በገቡት ውል መሰረት መስራታቸውን መቆጣጠሩን እና ገቢ መሰብሰቡን በተመለከተ፡-**

11. አገልግሎቱ ፈቃድ በማውጣት የዕድል ሎተሪ ጨዋታን የሚያጫውቱ አካላት በገቡት ውል መሰረት ስራቸውን እየሰሩ ስለመሆናቸው በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ ክትትልና ቁጥጥር የሚደረግበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ እና በፈቃድ ከሚካሄዱ የዕድል ሎተሪዎች አዲስ ፈቃድ ከሚወስዱ፣ ከፈቃድ ዕድሳት እና ከኮሚሽን አገልግሎቱ መሰብሰብ ያለበትን ገቢ በወጣው ታሪፍ መሰረት ሊሰበስብ ይገባል፡፡

12. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡-

- ከአገልግሎቱ ፍቃድ በማውጣት የዕድል ሎተሪ ጨዋታን የሚያጫውቱ አካላት በገቡት ውል መሰረት ስራቸውን እየሰሩ ስለመሆናቸው በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ ክትትልና ቁጥጥር የሚደረግበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፤
- አገልግሎቱ ህገ ወጦችን በተገቢው መንገድ መቆጣጠር ባለመቻሉ ከፍቃድ ማውጫ፣ ከፍቃድ ዕድሳት እና ከኮሚሽን እያገኘ ካለው ገቢ በተጨማሪ ሊያገኝ የሚችለውን ገቢ እንዳያገኝ ያደረገው መሆኑን፤
- እንዲሁም ከአገልግሎቱ ፍቃድ በመውሰድ የዕድል ሎተሪ ጨዋታን የሚያጫውቱ አካላት ገቢ በትክክል ለመቆጣጠር የሚያስችሉ አጋዥ ቴክኖሎጂዎች በማልማት ወይም በመግዛት፣ በመጠቀም፣ በማስተዳደር ከዕድል ጨዋታዎች ተገቢውን ገቢ ለመሰብሰብ በ2014 እና 2015 ዓ.ም የበጀት የዕቅድ መርሀ ግብር ላይ በዕቅድ የተያዘ ቢሆንም በአገልግሎቱ ይህን ለማድረግ የሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎች ተግባራዊ ያልተደረጉ መሆኑን፤

13. **የዕድል ሎተሪ ጨዋታዎች በተመለከተ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች ለህብረተሰቡ ስለመሰጠታቸው በተመለከተ፡-**

14. አገልግሎቱ በፈቃድ የሚሰሩ የዕድል ሎተሪ ጨዋታዎች እና ህገ ወጥ የዕድል ጨዋታዎችን በተመለከተ በተለያዩ መገናኛ ዘዴዎች (በሬዲዩ፣ በቴሌቪዥን፣ በጋዜጣ በመሳሰሉት) በአመታዊ ዕቅድ በመያዝ ለማህበረሰቡ ግንዛቤ የማስፋት ስራ ሊሰራ ይገባል፡፡

15. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡

- ህብረተሰቡ ለስፖርት ውርርድ ጨዋታዎች አደገኝነት ያለው ግንዛቤ አናሳ መሆኑ፤
- አገልግሎቱ በፍቃድ የሚሰሩ የዕድል ሎተሪ ጨዋታዎች እና ህገ ወጥ የዕድል ጨዋታዎችን በተመለከተ በተለያዩ መገናኛ ዘዴዎች (በሬዲዩ፣ በቴሌቪዥን፣ በጋዜጣ በመሳሰሉት) በአመታዊ ዕቅድ በመያዝ ለማህበረሰቡ የግንዛቤ የማስፋፋት ስራ ያልተሰራ መሆኑ

የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፤ የተጠቀሱትን የኦዲት ግኝቶች ለማሻሻል የሚረዱ የማሻሻያ ሀሳቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- በአዋጅ ቁጥር 160/2001 አንቀጽ 6(4) በፍቃድ የዕድል ሎተሪ ጨዋታን ለሚያጫውቱ አካላት ፍቃድ የመስጠት እና የመቆጣጠር ስልጣንና ተግባር ለአገልግሎቱ ተሰጥቶ የነበረ ሲሆን በአዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀጽ 27 ቀ፣ በ፣ ተ መሰረት ለገቢዎች ሚኒስቴር የተሰጠው በመሆኑ አገልግሎቱ ከገቢዎች ሚኒስቴር ጋር በመሆን በአዋጁ የተሰጣቸውን አሁናዊ ኃላፊነት ለማስተግበር የየተቋማቸውን አደረጃጀትና ስልጣንና ተግባር የሚደነግግ ህግ ሊወጣና የተሰጣቸውን ስልጣንና ተግባር መወጣት ይኖርባቸዋል፡፡
- አገልግሎቱ በፍቃድ የሚሰሩ የዕድል ሎተሪ ጨዋታዎች የሚመሩበት መመሪያዎችን ወቅታዊ ሁኔታዎችን ተከትለው ማሻሻል ይጠበቅባቸዋል፡፡
- አገልግሎቱ በራሱም ሆነ በሌሎች አካላት በተጠኑ ጥናቶች መሰረት በፍቃድ የሚሰሩ የእድል ጨዋታዎች በህብረተሰቡ፣ በአስተዳደሩ እንዲሁም በአገሪቱ ላይ የሚያደርሱት ጉዳቶችን ለመከላከል የሚያስችል አሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

- አገልግሎቱ ፍቃድ የሰጣቸውን እንዲሁም ያለ ፍቃድ የሚሰሩትን አጫዋቾች ህጋዊ ሆነው፣ ስታንዳርዱን ጠብቀውና በውሉ መሰረት ስለመስራታቸው ለመከታተል እና ለመቆጣጠር የሚያስችል በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ የቁጥጥር እና ክትትል ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል፡፡
- ከአገልግሎቱ ፍቃድ በመውሰድ የዕድል ሎተሪ ጨዋታን የሚያጫውቱ አካላት ገቢን በትክክል ለመቆጣጠር የሚያስችሉ አጋዥ ቴክኖሎጂዎችን በማልማት ወይም በመግዛት፣ በመጠቀም፣ በማስተዳደር ከዕድል ጨዋታዎች ተገቢውን ገቢ መሰብሰብ ይጠበቅበታል፡፡
- አገልግሎቱ በፍቃድ ስለሚሰሩ የዕድል ሎተሪ ጨዋታዎች እና ህገ ወጥ የዕድል ጨዋታዎችን እንዲሁም የሚያስከትሉትን ተፅዕኖ በተለያዩ መገናኛ ዘዴዎች (በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥን፣ በጋዜጣ በመሳሰሉት) ለማስገንዘብ በአመታዊ ዕቅድ በመያዝ ለህብረተሰቡ የግንዛቤ የማስፋፋት ስራ ሊሰራ ይገባል፡፡

የሚሉ ናቸው፡፡

የፌዴራል የሥነ ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሙስና መከላከል አፈፃፀም ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና እና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት

16. **የሥነ ምግባር ግንባታ እና የሙስና መከላከያ የህግ ማዕቀፎችን መዘጋጀቱንና አፈፃፀሙን መገምገሙን በተመለከተ**

17. ኮሚሽኑ የሥነ ምግባር ግንባታ እና የሙስና መከላከያ የህግ ማዕቀፎችን (ፖሊሲ፣ ስትራቴጂ፣ መመሪያ…) ሊያዘጋጅና በሚመለከታቸው አካላት መከበራቸውን ሊከታተል፣ ሊያረጋግጥ እና ስለ አፈፃፀማቸው የምክር አገልግሎት ሊሰጥ ይገባል፡፡

18. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡-
    - አገራዊ የፀረ-ሙስና ፖሊሲ ለኢ.ፌዲሪ ፕላንና ልማት ሚኒስቴር በቀን 3/04/2016 ዓ.ም አስተያየት እንዲሰጥበት የተላከ ቢሆንም ያልተጠናቀቀ መሆኑ፤
    - አገራዊ የሆነ የመንግስት ባለስልጣናት የሥነ ምግባር ደንብ ህዳር 06/2016 ለኢ..ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት በረቂቅ ላይ አስተያየት እንዲሰጥበት የተላከ ቢሆንም ያልተጠናቀቀ መሆኑ፤

- የፌዴራል ሥነ ምግባርና ፀረሙስና ኮሚሽን በ2014 በጀት ዓመት ለሥራ ኃላፊዎች እና ለመንግስት ሠራተኞች የሥነ-ምግባር እና ሀቀኝነት ግንባታ ስራ የሚመራበት የህግ ማዕቀፍ (National Ethics and Integrity Frame work) ለማዘጋጀት አቅዶ ያላዘጋጀ መሆኑ፤
- እንዲሁም ኮሚሽኑ የሙስና መከላከያ የህግ ማዕቀፎችን (ፖሊሲ፣ ስትራቴጂ፣ መመሪያ...) አፈፃፀም በተመለከተ በናሙና በታዩት የሐረሪ እና የሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፤ ድሬዳዋ እና አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽኖች እንዲሁም ፍትህ ሚኒስቴር፣ ትምህርት ሚኒስቴር፣ ድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ፣ ድሬዳዋ ገቢዎች ቢሮ እና ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የሥነ ምግባር ፀረ ሙስና መከታተያ ክፍሎች እና ጠቅላይ አቃቤ ህግ የምክር አገልግሎት ያልሰጠ መሆኑ፤

19. በመንግስት የልማት ድርጅቶች እና በህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ የሙስና እና ብልሹ አሠራር ለመከላከል የሚያስችል ጥናት ተጠንቶ መተግበሩን በተመለከተ

20. ኮሚሽኑ በመንግስት የልማት ድርጅቶች እና በህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ የሙስና እና ብልሹ አሠራርን ለመከላከል የአሰራር ሥርዓት እና የተጋላጭነት ጥናት በማጥናት የተሰጡ ማሻሻያ ሀሳቦች መተግበራቸውን መከታተሉንና በማይፈፅሙት ላይ ተገቢ የሆነ እርምጃ እንዲወሰድ ለሚመለከተው አካል ሊያቀርብ ይገባል፡፡

21. ይሁን እንጂ በኦዲት ወቅት ኮሚሽኑ በተቋማት የሙስናና ብልሹ አሰራር ለመቀነስ እንዲቻል የተጋላጭነት እና የአሰራር ስርዓት ጥናት ያጠና ቢሆንም የተገኙ አሰራር ክፍተቶች እንዲስተካከሉ የተጠናከረ ድጋፍና ክትትል ሥራዎች በመስራትና በማይፈፅሙት ላይ ተገቢ የሆነ እርምጃ እንዲወሰድ በህግ የመመርመርና የመክሰስ ስልጣን ላለዉ አካል ያላቀረበ መሆኑ፤

22. በተለያዩ ደረጃ ያሉ የመንግስት የስራ ኃላፊዎችና ሰራተኞች ሀብታቸውን ማስመዝገባቸውን በተመለከተ

23. ኮሚሽኑ በተለያዩ ደረጃ ያሉ የመንግስት የስራ ኃላፊዎችና ሰራተኞች ሀብታቸውን ማስመዝገባቸውንና በየሁለት አመቱ ማሳደሳቸውን ማረጋገጥ፣ የሀብት ምዝገባ መረጃ

በዘመናዊ መንገድ መያዝ እና ሀብት ለማስመዝገብ ፍቃደኛ ባልሆኑ አካላት ላይ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

24. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡

➢ የሀብት ማሳወቅና ምዝገባ ህጉ በሚፈቅደው ስርዓት ወጥ በሆነ መልኩ ያልተመዘገበ መሆኑ በዚህም፡

- በኮሚሽኑ አይቲ ክፍል በተያዘው ዳታ ቤዝ (በመረጃ ቋት) ስካን ተደርገው እና ወደ ፒዲኤፍ ተለውጠው የተገኙ የ2013 በጀት አመት የሀብት ምዝገባ መረጃዎች ሲሆን የ2014 በጀት ዓመት የሀብት ምዝገባ መረጃዎች የሌሉ መሆኑ፤ የ2015 እና 2016 በጀት አመት ከከፍተኛ አመራር እና ተመራጮች ውጪ ያሉ ሃብት አስመዝጋቢዎች ሀብት እንዲያስመዘግቡ ያልተደረገ መሆኑ፤
- 2015 በጀት ዓመት 269 የፌዴራል መንግስት ተቋማት ከፍተኛ አመራሮች እና ተመራጮች ሀብታቸውን ያላስመዘገቡ ቢሆንም አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወሰድባቸው ያልተደረገ መሆኑ፤

25. የሀብት ምዝገባ ትክክለኛነትን ለማረጋገጥ የሚያስችል ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ

26. ኮሚሽኑ የሀብት ምዝገባ ትክክለኝነትን ለማረጋገጥ የሚያስችል ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

27. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡-

➢ ኮሚሽኑ የተመዘገበ ሀብት መረጃ ትክክለኛነት ከማረጋገጥና የጥቅም ግጭት ከመከላከል አንፃር በስፋት ተግባራዊ አለመደረጉ፤ ለማሳያም፡-

➢ ኮሚሽኑ ከ2013-2015 በጀት ዓመት በቅደም ተከተል 100፤100 እና 96 የሃብት ምዝገባ መረጃ ትክክለኛነት ማረጋገጥ ተግባራት ማከናወን አቅዶ በሶስቱም በጀት አመት 100% ያከናወነ መሆኑ በእቅድ አፈፃፀም ላይ የተገለፀ ቢሆንም ትክክለኛት ስለማጣራቱ የሚያሳዩ ሂደቶች ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፤

28. **በመረጃ ሰጪዎች የቀረበውን የሙስና መረጃና ማስረጃ በማደራጀት ለፍትህ አካል መላኩንና ውጤቱን መከታተሉን በተመለከተ**

29. ኮሚሽኑ የሙስና መረጃዎችን በመተንተን የህግ ቅርፅ ስለማስያዙ እና ለፍትህ አካላት በመላክ ውጤቱን መከታተሉን ይገባል፡፡

30. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡-

- ➢ ኮሚሽኑ በመረጃ ሰጪዎች የቀረበውን የሙስና መረጃ በመተንተን የህግ ቅርፅ በማስያዝ ለፍትህ አካል በመላክ ውጤቱን ያልተከታተለ እንዲሁም የሙስናና ብልሹ አሠራር ችግሮች መረጃና ማስረጃ በማደራጀት ያልያዘ መሆኑ፤
- የቀረበ ጥቆማ ብዛት ምን ያህል እንደሆነ፣ ከዛ ውስጥ መዝገባቸው ተመርምሮ የተጠናቀቁት ምን ያህል እንደሆኑ፣ ምን ያህል መዝገብ በሂደት ላይ እንዳለ እና ጥቆማው ያልተመረመረ ስንት እንደሆነ በየበጀት ዓመቱ፣ በየተቋማቱ እና በየክልሎቹ በተሟላ ሁኔታ መረጃዎችን ኮሚሽኑ የማይዝ መሆኑ፣

31. **የሙስናና ብልሹ አሠራር ችግሮችን ለመቅረፍ እና የሕዝብና መንግሥት ሀብት ከብክነት ለማዳን ከባለድርሻ አካላት ጋር በትብብርና በቅንጅት መሰራቱን በተመለከተ**

32. ኮሚሽኑ የሙስናና ብልሹ አሠራር ችግሮችን ለመቅረፍ እና የሕዝብና መንግሥት ሀብት ከብክነት ለማዳን ከባለድርሻ አካላት ጋር በትብብርና በቅንጅት መስራቱንና በሥነ-ምግባር ግንባታ፣ በሙስና ወንጀል ምርመራ እና ክስ የመመስረት ስልጣን ከተሰጣቸው እና ከሌሎች አግባብነት ካላቸው አካላት የስራ አፈጻጸም ሪፖርት መቀበል አለበት፡፡

33. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ኮሚሽኑ የሙስናና ብልሹ አሠራር ችግሮችን ለመቅረፍ እና የሕዝብና መንግሥት ሀብት ከብክነት ለማዳን ከባለድርሻ አካላት ጋር በተጠናከረ ትብብርና ቅንጅት ያልሰራ መሆኑ እንዲሁም ከሚመለከታቸው አካላት የተሟላ የስራ አፈጻጸም ሪፖርት ያልተቀበለ መሆኑ፤

34. **ሙስናን የመከላከል አቅም ለመገንባት እንዲቻል ለሁሉም የህብረተስብ ክፍሎች እና ለባለድርሻ አካላት የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ መሰራቱንና ውጤቱ መገምገሙን በተመለከተ**

35. ኮሚሽኑ ሙስናን የመከላከል አቅም ለመገንባት እንዲቻል ለሁሉም የህብረተስብ ክፍሎች እና ለባለድርሻ አካላት ግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ መስራቱንና የግንዛቤ ማስጨበጫው ያስገኘውን ውጤት በየጊዜው መገምገም አለበት፡፡

36. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ኮሚሽኑ ሙስናን የመከላከል አቅም ለመገንባት እንዲቻል ለሁሉም የህብረተስብ ክፍሎች እና ለባለድርሻ አካላት ተደራሽ የሆነ ግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ያልሰራ መሆኑ እንዲሁም የግንዛቤ ማስጨበጫው ያስገኘውን ውጤት ያልገመገመ መሆኑ፣

ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፣ የተጠቀሱትን የኦዲት ግኝቶች ለማሻሻል የሚረዱ የማሻሻያ ሀሳቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- ኮሚሽኑ በረቂቅ ደረጃ ያዘጋጀው አገራዊ የፀረ-ሙስና ፖሊሲና የመንግስት ባለሥልጣናት የሚመሩበት የሥነ ምግባር ደንብ በሚመለከታቸው አካላት አፀድቆ ተግባራዊ ሊያደርግ እንዲሁም የሙስና መከላከያ የህግ ማዕቀፎችን (ፖሊሲ፣ ስትራቴጂ፣ መመሪያ…) አፈፃፀም በተመለከተ ለሚመለከታቸው አካላት የምክር አገልግሎት መስጠት ይኖርበታል፡፡
- ኮሚሽኑ በተቋማት የሙስና እና ብልሹ አሰራር ለመቀነስ እንዲቻል ባጠናው የተጋላጭነት እና የአሰራር ስርዓት ጥናት የተገኙ አሰራር ክፍተቶች እንዲስተካከሉ የተጠናከረ ድጋፍና ክትትል ሥራዎች በመስራትና በማይፈፅሙት ላይ ተገቢ የሆነ እርምጃ እንዲወሰድ በህግ የመመርመርና የመክሰስ ስልጣን ላለዉ አካል ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡
- ኮሚሽኑ በተለያዩ ደረጃ ያሉ የመንግስት የስራ ኃላፊዎችና ሰራተኞች ሀብታቸውን ማስመዝገባቸውንና ማሳደሳቸውን በማረጋገጥ፣ የሀብት ምዝገባ መረጃ በዘመናዊ መንገድ በመያዝ እና ሀብት ለማስመዝገብ ፍቃደኛ ባልሆኑ አካላት ላይ እርምጃ በመወሰድ እንዲሁም የሀብት ምዝገባ ትክክለኛነትን ለማረጋገጥ የሚያስችል ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡
- ኮሚሽኑ በመረጃ ሰጪዎች የቀረበውን የሙስና መረጃ በመተንተን የህግ ቅርፅ

በማስያዝ ለፍትህ አካል በመላክ ውጤቱን በመከታተል እንዲሁም የሙስናና ብልሹ አሠራር ችግሮች መረጃና ማስረጃ ማደራጀት አለበት፡፡

- ኮሚሽኑ የሙስናና ብልሹ አሠራር ችግሮችን ለመቅረፍ እና የሕዝብና መንግሥት ሀብት ከብክነት ለማዳን ከባለድርሻ አካላት ጋር በተጠናከረ ትብብርና ቅንጅት መስራትና ከሚመለከታቸው አካላት የስራ አፈጻጸም ሪፖርት መቀበል አለበት፡፡
- ኮሚሽኑ ሙስናን የመከላከል አቅም ለመገንባት እንዲቻል ለሁሉም የህብረተስብ ክፍሎች እና ለባለድርሻ አካላት ግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ በመስራት የግንዛቤ ማስጨበጫው ያስገኘውን ውጤት በየጊዜው በመገምገም ሙስናን በመከላከል እና በመግታት ረገድ ማህበረሰቡ የጎላ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ማድረግ ይኖርበታል፡፡

የሚሉ ናቸው፡፡

<u>በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የፕሮጀክት ውል እና የሰው ኃብት አስተዳደር አፈጻጸም ውጤታማነትን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት</u>

37. ፕሮጀክቶች ከመቀረጻቸው በፊት የቴክኖሎጂ ፍላጎት እና ክፍተት መሰረት ያደረገ ጥናት (Need assessment) ስለመጠናቱ ፤

38. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለሚያከናውናቸዉ የተለያዩ ፕሮጀክቶች ችግር ፈቺ እና ውጤታማ እንዲሆኑ ለማድረግ ፕሮጀክቶች ከመቀረጻቸዉ በፊት የሀገሪቱን እና የማህበረሰቡን የቴክኖሎጂ ፍላጎት እና ክፍተት መሰረት ያደረገ የደሰሳ ጥናት (Need assessment) በማዘጋጀት እና ግምገማ በማድረግ ተግባራዊ የሚያደርግበትን ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ በተጨማሪም የፕሮጀክት ተጠቃሚዎችን የሚመርጥበት መስፈርት አዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊያድርግ ይገባል፡፡

39. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለሚያከናውናቸዉ የተለያዩ ፕሮጀክቶች ችግር ፈቺ እና ውጤታማ እንዲሆኑ ለማድረግ ፕሮጀክቶች ከመቀረጻቸዉ በፊት የሀገሪቱን እና የማህበረሰቡን የቴክኖሎጂ ፍላጎት እና ክፍተት መሰረት ያደረገ ጥናት (Need assessment) በማዘጋጀት ግምገማ ያልተደረገባቸው ፕሮጀክቶች መኖራቸው፤

40. ፕሮጀክቶች ላይ የቅድመ- አዋጭነት እና የአዋጭነት ጥናት ስለመደረጉ፤

41. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በመንግስት በጀት እንዲሁም በድጋፍና ብድር የሚያከናውናቸው ፕሮጀክቶች ስራ ከመጀመሩ በፊት የቅድመ-አዋጭነት እና የአዋጭነት ጥናት (pre-feasibility and feasibility study) እንዲሁም የአዋጭነት ግምገማ በማድረግ ለሚመለከተው አካል (ለገንዘብ ሚኒስቴር እና ለፕላንና ልማት ሚኒስቴር) አቅርቦ ሊያጸድቅ ይገባል፡፡

42. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡-

- በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚከናወኑ በናሙና ተመርጠው የታዩ 4 የካፒታል በጀት ፕሮጀክቶች ማለትም (የሳይንስና ቴክኖሎጂ ማዕከል ግንባታ ፣ የቡራዩ ኢኖቬሽን ታለንት ልማት ኢንስቲትዩት፣ ነባሩን ዳታ ማዕከል ማሻሻል እና ለብሔራዊ ዳታ ማዕከል የመጠባበቂያ ዳታ ማዕከል ፕሮጀክቶች ወደ ትግበራ ከመግባታቸው በፊት የቅድመ አዋጭነት እና አዋጭነት ጥናት ያልተደረገባቸው መሆኑ፤
- የሞዴል የሳይንስና ቴክኖሎጂ ቤተ-መጽሀፍት ማቋቋም (ሳይንስ ካፌ) ፕሮጀክት የቅድመ አዋጭነት ጥናት ያጠና ቢሆንም የአዋጭነት ጥናት በማጥናት ለገንዘብ ሚኒስቴር እና ለፕላንና ልማት ሚኒስቴር አቅርቦ ያላፀደቀ መሆኑ፤
- በናሙና ተመርጠው ከታዩ በልማት አጋሮች ድጋፍ እና ብድር የሚከናወኑ 2 ፕሮጀክቶች ማለትም የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን እና የዲጂታል ፋውንዴሽን ፕሮጀክቶች ወደ ትግበራ ከመግባታቸው በፊት የቅደመ-አዋጭነት እና የአዋጭነት ጥናት ያልተደረገ መሆኑ፤

43. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፕሮጀክቶችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን በግዥ መመሪያ መሰረት ስለመፈፀሙ፡

44. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፕሮጀክቶችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን እንደየፕሮጀክቱ አይነት በመንግስት የግዥ መመሪያ መሰረት ሊያከናዉን ይገባል፡ ፡

45. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለፕሮጀክቶች የሚያስፈልጉ ግዥዎች በግዥ መመሪያ መሰረት ግዥ ያልተፈጸመ መሆኑ እንዲሁም በዲጂታል

ትራንስፎርሜሽን ፕሮጀክት የመኪና ኪራይ አገልግሎት ከተገባው ውል ውጭ ብር 3,925,055.8 ያለ አግባብ ክፍያ ተፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፤

46. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ፕሮጀክቶች በተገባው ውል፣ በተያዘላቸው ዕቅድ እና በጀት ስለመከናወናቸው፤

47. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚያከናዉናቸው ፕሮጀክቶች እና የሚከታተላቸው ፕሮጀክቶች በተገባው ውል እና ዕቅድ መሰረት መከናወናቸውን በዓመታዊ ዕቅድ ውስጥ በማስገባት የሚያረጋግጥበት ስርዓት ዘርግቶ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ እንዲሁም የፕሮጀክት አፈጻጸም ለገንዘብ ሚኒስቴር እና ለፕላንና ልማት ሚኒስቴር በየሩብ ዓመቱ ሪፖርት ሊያቀርብ ይገባል፡፡

48. ይሁን እንጂ በኦዲት ወቅት እንደታየው፡-

- ➢ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚያከናውናቸው ፕሮጀክቶች በተገባው ውል እና ዕቅድ መሰረት እንዲጠናቀቁ ያልተደረገ በመሆኑ እና ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለተጨማሪ ወጪ የተዳረገ መሆኑ፣ በዚህም፡
  - ✓ ሞዴል የሳይንስና ቴክኖሎጂ ቤተ-መጽሀፍት (ሳይንስ ካፌ) በተያዘለት ጊዜ እና በጀት ባለመጠናቀቁ ሚ/ር መ/ቤቱ ለተጨማሪ ወጪ 43,044,953.22 የተዳረገ መሆኑ፤
  - ✓ ነባሩን ዳታ ማዕከል ማሻሻል ፕሮጀክት በተያዘለት ጊዜ እና በጀት ባለመጠናቀቁ ለተጨማሪ ወጪ ብር 277,071,644.36 የተዳረገ መሆኑ፤
- • እንዲሁም የፕሮጀክት ክትትል እና ቁጥጥር ስርዓት ዘርግቶ የፕሮጀክት አፈጻጸም ክትትል ስራን በዕቅድ በመያዝ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፤

49. ፕሮጀክቶች ለታለመላቸዉ አላማ እየዋሉ ስለመሆኑ እንዲሁም ያስገኙትን ውጤት ስለመገምገሙ

50. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ፕሮጀክቶች ከተጠናቀቁ በኋላ ለታለመላቸዉ አላማ እየዋሉ መሆኑን እንዲሁም ያስገኙትን ጥቅም/ውጤት የሚከታተልበትና የሚገመግምበትን ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

51. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡-

- ➢ በናሙና ከተመረጡ ፕሮጀክቶች ውስጥ 2ቱ ማለትም የቡራዩ ኢኖቬሽንና ታለንት ልማት ኢንስቲትዩት እና የሞዴል የሳይንስና ቴክኖሎጂ ቤተ-

መጽሀፍት ማቋቋም (ሳይንስ ካፌ) ለታለመላቸው አላማ እንዲውሉ ያልተደረገ መሆኑ፤ በዚህም፡-

- የቡራዩ ኢኖቬሽንና ታለንት ልማት ኢንስቲትዩት ፕሮጀክት_በአዋጅ ቁጥር 1263/2014 ዓ.ም እራሱን የቻለ የህግ ሰውነት ያለው የፌዴራል መንግስት አስፈጻሚ አካል ሆኖ በአዋጁ የተቋቋመ ሲሆን አደራጃጀቱ በሚመለከት ረቂቅ ደንብ ተዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ም/ቤት እንዲላክ እና ውሳኔ እንዲሰጥበት ያልተደረገ መሆኑን፤
- የሞዴል የሳይንስና ቴክኖሎጂ ማዕከል (የሳይንስ ካፌ) ፕሮጀክት ወጣቶች በሚቋቋሙ ማዕከላት የሳይንስ፣ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ እውቀት እንዲያዳብሩ እንዲሁም የተለያዩ ይዘት ያላቸው የዲጂታል ቤተ-መጽሀፍ አገልግሎት ለመስጠት የተቋቋመ ፕሮጀክት ሲሆን ነገር ግን ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ያቋቋማቸው 5 የሳይንስ ካፌ ማዕከላት ማለትም (በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 4 የስብዕና መገንቢያ ማዕከል፣ የቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 8 የወጣቶች ስብዕና መገንቢያ ማዕከል ፣ በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 6 የወጣቶች ስብዕና መገንቢያ ማዕከል፤ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 6 ቁጥር 2 የስብዕና መገንቢያ ወጣቶች ማዕከል እና በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 4 ቁጥር 2 የወጣቶች ማዕከል) ሁሉም ማዕከላት ከታለመላቸው አላማ ውጭ ማለትም የካፍቴሪያ አገልግልት፣ የፑል መጫወቻ፣ ፕሌይ ስቴሽን እና ለስፖርት ማዘውተሪያ እንዲውሉ የተደረገ መሆኑ፤

52. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለፕሮጀክቶች ጊዚያዊ /ኮንትራት ሰራተኞችን ቅጥር ሲፈጽም የቅጥር ማወዳደሪያ መስፈርት እና ተፈላጊ ችሎታ አዘጋጅቶ ተግባራዊ ስለማድረጉ

53. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለፕሮጀክቶች ጊዚያዊ /ኮንትራት ሰራተኞችን ቅጥር ሲፈጽም የቅጥር ማወዳደሪያ መስፈርት እና ተፈላጊ ችሎታ አዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

54. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በሚኒስቴር መ/ቤቱ በኦፐን ሶሳይቲ ፋውንዴሽን ድጋፍ ሲተገበር የነበረው የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ፕሮጀክት ላይ በጠቅላይ ሚ/ር

ጽ/ቤት በቀን 10 መጋቢት 2012 ዓ.ም በተዘጋጀው የፕሮጀክት አፈጻጸም ማንዋል ቁጥር 7.4 ላይ የኮንትራት ሰራተኞች ቅጥር በውድድር መፈጸም እንዳለበት ቢገለጸም ሰራተኞች የሚወዳደሩበት የቅጥር ማስታወቂያ ፣የትምህርት እና የስራ ልምድ ማስረጃ እና የመሳሰሉት ተዘጋጅቶ ቅጥር እንዲፈጸም ያልተደረገ መሆኑ፤ ለቃለ መጠይቅ የሚቀርቡ ጥያቄዎች ማስረጃ የቀረበ ቢሆንም ተወዳዳሪዎች በዛ መሰረት ተወዳድረው ስለመቀጠራቸው ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፤

ሚኒስቴር መ/ቤቱ በጊዚያዊነት የሚቀጠሩ ሰራተኞች በሰዉ ሀብት አስተዳደር የስራ ክፍል በኩል ቅጥር ስለመፈጸሙ እና ዓመታዊ ምዘና ስለመደረጉ፡-

ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሚያከናዉናቸዉ ፕሮጀክቶች ላይ የሚቀጠሩ ጊዚያዊ ሰራተኞች የትምህርት፣ የሥራ ልምድ፣ ሌሎች ከቅጥር እስከ ስንብት ያሉ ተያያዥ ሰነዶችን እና አፈጻጸም ዓመታዊ ምዘናዎችን የያዘ ማህደር/መዝገብ አደራጅቶ ሊይዝ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡-

በሚኒስቴር መ/ቤቱ በብድር እና ድጋፍ የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ማለትም (የደጂታል ፋውንዴሽን እና የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ፕሮጀክት) የሚቀጠሩ ጊዜያዊ ሰራተኞች በብቃትና ሰው ኃብት አስተዳደር የስራ ክፍል በኩል ቅጥር እንዲፈጸም ያልተደረገ መሆኑ፤ በተጨማሪም በዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ፕሮጀክት ላይ የቅጥር ውል ሳይኖራቸው እና ውላቸው ለተቋረጠ ስራተኞች የስራ ግብር እና ጡረታ ተቀናንሶ ያለአግባብ አጠቃላይ ብር 2,986,733.31 ደመወዝ የተከፈለ መሆኑ፤ በተጨማሪም በዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ፕሮጀክት አፈጻጸም ማንዋል መጋቢት 2012 ዓ.ም ላይ የሰራተኞች ውል ሲሻሻል የደመወዛቸዉን ከ15% በላይ ጭማሪ መደረግ እንደሌለበት ቢገልጽም 4 ሰራተኞች ውል ሲሻሻል የደመወዝ ጭማሪያቸው ከ15% በላይ ማለትም (ከ25-44%) የተጨመረላቸው መሆኑ በዚህም ብር 645,547 ጭማሪ ክፍያ የተፈፀመ ሲሆን በጠቅላላ ብር 3,632,280.31 ያለ አግባብ ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ፤

55. **በፕሮጀክቶች ላይ የተቀጠሩ ጊዜያዊ ሰራተኞች የተረከቡትን ንብረት ስለመመለሳቸው፤**

56. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፕሮጀክቶች ላይ የተቀጠሩ ጊዚያዊ ሰራተኞች የቅጥር ውላቸዉ ሲጠናቀቅ የስራ ርክክብ ማድርጋቸዉን እና የተረከቡትን ንብረት መመለሳቸዉን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

57. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በኦፕን ሶሳይቲ ፋውንዴሽን ድጋፍ ሲተገበር የነበረው በዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ፕሮጀክት አተገባበር ማንዋል 2012 ዓ.ም ቁጥር 6 ላይ ፕሮጀክቱ ሲጠናቀቀቅ ንብረቶቹ ለሚመለከተው የመንግስት አካል መተላለፍ/ማስረከብ እንዳለበት ቢገልጽም ነገር ግን በዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ፕሮጀክት ላይ የተቀጠሩ ጊዜያዊ ስራተኞች የቅጥር ውላቸው ሲቋረጥ የተረከቡትን ንብረት ያልመለሱ መሆኑ፤ በመሆኑም አጠቃላይ ብር 8,609,114.31 የሚያወጡ የተለያዩ ንብረቶች ወጪ ተደርገው ያልተመለሱ መሆኑ፤ እንዲሁም በፕሮጀክቱ የተሰሩ ስራዎች ርክብብ ያልተደረገ መሆኑ፤

የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፤ የተጠቀሱትን የኦዲት ግኝቶች ለማሻሻል የሚረዱ የማሻሻያ ሀሳቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፕሮጀክት ቀርጾ ወደ ትግበራ ከመግባቱ በፊት የሀገሪቱን እና ማህበረሰቡን የቴክኖሎጂ ችግሮች እና ፍላጎት ላይ ደሳሳ ጥናት (Need assessment) በማድረግና ግምገማ በማድረግ ፕሮጀክቶች ችግር ፈቺ እና ውጤታማ እንዲሆኑ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በመንግስትም ሆነ በአለም አቀፍ ድጋፍና ብድር የሚያከናውናቸው ፕሮጀክቶች ፕሮፖዛል ተዘጋጅቶ ወደ ትግበራ ከመግባታቸው በፊት የቅድመ አዋጭነት እና የአዋጭነት ጥናት እና ግምገማ በማድረግ ለገንዘብ ሚኒስቴር እና ለፕላንና ልማት ሚኒስቴር አቅርቦ እንዲጸድቅ በማድረግ ፕሮጀክቶችን በተመደበላቸው በጀት እና በተያዘላቸው ጊዜ እንዲጠናቀቁ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአንድነት መገዛት የሚችሉ የፕሮጀክት ግብዓቶችን ሳይነጣጥል በግልጽ ጨረታ ግዥ ሊፈጽም እና ለመኪና ኪራይ አገልግሎት ከተገባው ውል ውጭ የተከፈሉ ብር 3,925,055.8 ክፍያዎችን ተመላሽ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፕሮጀክቶች በተገባው ውል፣ በተያዘላቸው ዕቅድ እና በጀት እንዲጠናቀቁ ለማድረግ የሚያስችል የፕሮጀክቶች ክትትልና ቁጥጥር ስርዓት ዘርግቶ ግምገማ ማድረግ እና ግብረ መልስ መስጠት ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም ባልተጀመሩ እና በተቋረጠ ፕሮጀክት ከመንግስት የሚለቀቀውን በጀት ለታለመለት ዓለማ ለማዋል ፕሮጀክቶቹ የገጠማቸውን ችግር በጥናት በመለየት ወደ ትግበራ እንዲገቡ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፕሮጀክቶች ከተጠናቀቁ በኋላ ለታለመላቸው አላማ እየዋሉ ስለመሆኑ እና ያስገኙትን ውጤት/ጥቅም ለመገምገም የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሚያከናውናቸው ፕሮጀክቶች ላይ ጊዜያዊ/ኮንትራት ሰራተኞችን ቅጥር ሲፈጽም በቅጥር ማወዳደሪያ መስፈርት መሰረት ማወዳደር፣ ተፈላጊ ችሎታና የትምህርት ዝግጅት መረጃዎችን አዘጋጅቶ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ለሰው ኃብት አስተዳደር ሊያቀርብና ቅጥር በመፈጸም ግልጽ የሆነ አሰራር መከተል ይጠበቅበታል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአለም አቀፍ ድርጅቶች ድጋፍ በሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ላይ የሚቀጠሩ ጊዜያዊ ሰራተኞች በሰው ኃብት አስተዳደር በኩል ቅጥር እንዲፈጸም በማድረግ የሰራተኞችን የትምህርት፣ የሥራ ልምድ፣ ሌሎች ከቅጥር እስከ ስንብት ያሉ ተያያዥ ሰነዶችን እና ከቅጥር እስከ ስንብት ያሉ መረጃዎችን በማህደር/መዝገብ አደራጅቶ በመያዝ የስራ ውላቸው ተቋርጦ እና ውል ሳይኖራቸው ክፍያ የተፈጸመ ብር 2,986,733.31 እንዲሁም ውላቸው ሲሻሻል ከመመሪያ ውጪ 15 በመቶ በላይ የተጨመረላቸው ሰራተኞች ብር 645,547 በአጠቃላይ ብር 3,632,280.31 ተመላሽ ሊደረግ እና ይህን በፈጸሙ አካላት ላይ ተገቢው እርምጃ መወሰድ ይኖርበታል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፕሮጀክቶች ላይ የተቀጠሩ ጊዜያዊ ሰራተኞች ውላቸው ሲቋረጥ/ሲጠናቀቅ የተረከቡትን ንብረት እንዲሁም የተሰሩ ስራዎችን ለሚመለከተው አካል ተመላሽ እንዲያደርጉ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

የሚሉ ናቸው፡፡

በሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ሴቶችንና ህፃናትን በተመለከተ በአገሪቱ የተፈረሙ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች አፈፃፀምን ለመገምገም የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት

58. **የጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች የህግ ማዕቀፍ እንዲዘጋጅ ስለመደረጉ፣**

59. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሴቶች እና ህፃናት ላይ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን በሚፈፀሙ አካላት ላይ ህጋዊ እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር እንዲዘጋጅ በማድረግ ተፈፃሚነቱን ሊከታተልና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡

60. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት የወንጀለኛ መቅጫ ህግን መሰረት አድርጎ ጎጂ ባህላዊ ድርጊቶች በሚፈፅሙ አካላት ላይ በሚፈለገው ልክ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፤

61. **በሴቶች ላይ የሚፈፀሙ ፆታዊ ጥቃቶችና በህፃናት ላይ የሚደርሱ ችግሮች ስለመጠናታቸው፣**

62. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሴቶች ላይ የሚፈፀሙ ፆታዊ ጥቃቶች የሚያስከትሉትን ተፅእኖ በተመለከተ የሚካሄዱ ጥናቶችን ሊደግፍና ሊያበረታታ እንዲሁም የጥናቱን ውጤት ለህዝብ ተደራሽ ሊያደረግ እና በህፃናት ላይ የሚደርሱ ችግሮችን መንስኤዎቻቸውን፣ የሚያስከትሉትን ተፅእኖ እና መፍትሄዎቻቸውን በግልፅ ማሳየት የሚያስችል የጥናትና ምርምር ስራዎች በየ5 አመቱ ሊያካሂድ ይገባል፡፡

63. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በሚኒስቴር መ/ቤቱ በሴቶች ላይ የሚደረሰውን ፆታዊ ጥቃትን በተመለከተ በሰነልቦናና በማህበራዊ ዘርፍ ላይ የሚያሳድረውን ተፅእኖ ጥናት በማካሄድ ለህብረተሰቡ ተደራሽ እንዲሆን ያልተደረገ መሆኑ፤ የህፃናት ላይ የሚደርሱ ችግሮች በመለየት መንስኤዎቻቸውን፣ የሚያስከትሉትን ተፅእኖ እና መፍትሄዎቻቸውን በግልፅ ለማሳየት የሚያስችል የጥናትና ምርምር ስራዎች ባለፈው 5 አመት ያልተካሄደ መሆኑ፤

64. **በሴቶች እና ህጻናት መብት ዙሪያ በቅንጅት ስለመስራቱ፣**

65. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሴቶችና በህጻናት መብትና ጥበቃ ዙሪያ ከሚመለከታቸው መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ አካላት ጋር በትብብር/በቅንጅት ሊሰራ እና አፈጻጸሙንም በየጊዜው ሊገመግም ይገባል፡፡

66. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ሚኒስቴር መ/ቤቱ በህጻናትና በሴቶች መብትና ጥበቃ ዙሪያ ከሚመለከታቸው መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ አካላት ጋር የተጠናከረ የትብብር/ቅንጅት አሰራር ስርዓት የሌለው መሆኑ፤

67. **በቴክኖሎጂ የተደገፈ የመረጃ ስርዓትን በተመለከተ፡**

68. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአገር አቀፍ ደረጃ የሴቶች እና የህፃናት መብትና ጥበቃ መረጃዎችን በዘመናዊ መንገድ ለማሰባሰብ፣ ለማደራጀትና ለማሰራጨት የሚያስችሉ የመረጃ አያያዝ፣ ልውውጥ ስርዓቶችንና ቴክኖሎጂዎችን በማዘጋጀት ጥቅም ላይ እንዲውሉ ሊያደረግ ይገባል፡፡

69. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ብሄራዊ የሴቶች መረጃ አያያዝ ስርዓት(National gender information system) ሲስተሙ በ2014 ወደ ስራ የገባ ቢሆንም በክልል የዘርፉ መ/ቤቶች በኩል ወጥነት ባለው መልኩ መረጃዎችን ወደ ሲስተሙ ያልገባ መሆኑ፤
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የህጻናትን የመረጃ አያያዝ በተመለከተ የህጻናት ጥበቃ ጉዳዮች መረጃ አያያዝ ስርዓት (CPMIS+) ስራው ለማስጀመር የተለያዩ ሂደቶችን ቢጓዙም ሲስተሙ ተጠናቆ ወደ ስራ ያልገባ መሆኑ

70. **ወላጆቻቸውን ላጡና ለከፍተኛ ችግር ተጋላጭ የሆኑ ህጻናትን በተመለከተ፡**

71. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ወላጆቻቸውን ላጡና ለከፍተኛ ችግር ተጋላጭ ለሆኑ ህጻናት ሊደረጉ ስለሚገባቸው የድጋፍና ክብካቤ ዘዴዎች ዙሪያ የህብረተሰቡን ግንዛቤና አመለካከት የመለወጥ ስራዎችን ለመስራት የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ በአመታዊ እቅድ እየያዘ አፈፃፀሙን ስለመከታተላቸው እንዲሁም የመሰረታዊ ፍላጎት (ምግብ፣ ልብስ እና መጠለያ) ማግኘት ለማይችሉ ህፃናት የማቴሪያል ድጋፍ እንዲሁም ቋሚ የእርዳታ ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት ተደራሽ ሊያደርግ ይገባል፡፡

72. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡-

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ወላጆቻቸውን ላጡና ለከፍተኛ ችግር ተጋላጭ ለሆኑ ህጻናት ሊደረጉ ስለሚገባቸው የድጋፍና ክብካቤ ዘዴዎች ዙሪያ የህብረተሰቡን ግንዛቤና አመለካከት የመለወጥ ስራዎችን ለመስራት

የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ በአመታዊ እቅድ እንዲያዝ ያላደረገ መሆኑ፤

- ➢ ወላጆቻቸውን ላጡና ለከፍተኛ ችግር ተጋላጭ ለሆኑ ህጻናት የመሰረታዊ ፍላጎት (ምግብ፣ ልብስ እና መጠለያ) ማግኘት ለማይችሉ ህፃናት የማቴሪያል ድጋፍ እንዲሁም ቋሚ የእርዳታ ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት ተደራሽ እንዲሆን ያላደረገ መሆኑ፤

73. **ለትምህርት የደረሱ ሕፃናትን በተመለከተ፤**

74. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለትምህርት የደረሱ ሕፃናት ስብዕናቸውን፣ ተሰጥዖዋቸውን፣ የአዕምሮ እና የአካል ችሎታቸውን በተሟላ መልኩ ለማዳበር የሚረዳ ትምህርት እየተማሩ ስለመሆኑ የሚረጋገጥበት እና ሕፃናት ከማንኛውም የሕፃናቱን ትምህርት ከሚያደናቅፍ፣ ለህፃኑ ጤና፣ አካላዊ፣ እና ማህበራዊ እድገታቸው ጎጂ ከሆነ ስራ የተጠበቁ ስለመሆናቸው የሚያረጋግጥበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

75. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለትምህርት የደረሱ ሕፃናት ስብዕናቸውን፣ ተሰጥዖዋቸውን፣ የአዕምሮ እና የአካል ችሎታቸውን በተሟላ መልኩ ለማዳበር የሚረዳ ትምህርት እየተማሩ ስለመሆኑ የሚረጋገጥበት እንዲሁም ሕፃናት ከማንኛውም ትምህርታቸውን ከሚያደናቅፍ፣ ለጤናቸው፣ አካላዊ፣ እና ማህበራዊ እድገታቸው ጎጂ ከሆነ ስራ የተጠበቁ ስለመሆናቸው የሚረጋገጥበት የአሰራር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፤

የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፤ የተጠቀሱትን የኦዲት ግኝቶች ለማሻሻል የሚረዱ የማሻሻያ ሀሳቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሴቶች እና ህፃናት ላይ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን በሚፈፀሙ አካላት ላይ ህጋዊ እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ ተግባራዊ እንዲደረግ መደረጉን መከታተል ይጠበቅበታል፡፡
- ✓ በሚኒስቴር መ/ቤቱ በሴቶች ላይ የሚደረሰውን ፆታዊ ጥቃትን በተመለከተ በሰነልቦናና በማህበራዊ ዘርፍ ላይ የሚያሳድረውን ተፅእኖ በማካተት ሊያጠናና ለህብረተሰቡ ተደራሽ እንዲሆን ማድረግ ይጠበቅበታል፤ የህፃናት ላይ የሚደርሱ ችግሮች በመለየት መንስኤዎቻቸውን፣ የሚያስከትሉትን ተፅእኖ እና

መፍትሄዎቻቸውን በግልፅ ለማሳየት የሚያስችል የጥናትና ምርምር ስራዎች በየአምስት አመቱ ማጥናት ይኖርበታል፡፡

- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በህጻናትና በሴቶች መብትና ጥበቃ ዙሪያ ከሚመለከታቸው መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ አካላት ጋር በተጠናከረ ትብብር/ቅንጅት መስራት ይኖርበታል፡፡
- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የስርዓተ-ጾታ ኢንፎርሜሽን ሥርዓት (National gender information system) መረጃዎችን በዘመናዊ መንገድ ለማሰባሰብ፣ ለማደራጀትና ለማሰራጨት ያሉበትን ችግሮች መፍትሄ በመስጠት ወደ ስራ መግባት ይጠበቅበታል፡፡
- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የህጻናት መብት መረጃ አያያዝ ስርዓት መረጃዎችን በዘመናዊ መንገድ ለማሰባሰብ፣ ለማደራጀትና ለማሰራጨት የሚያስችሉ የመረጃ አያያዝ፣ ልውውጥ ሥርዓቶችንና ሂደቶቹ በማጠናቀቅ ወደ ተግባር እንዲገቡ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡
- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ወላጆቻቸውን ላጡና ለከፍተኛ ችግር ተጋላጭ ለሆኑ ህጻናት ሊደረጉ ስለሚገባቸው የድጋፍና ክብካቤ ዘዴዎች ዙሪያ የህብረተሰቡን ግንዛቤና አመለካከት የመለወጥ ስራዎችን ለመስራት የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ በአመታዊ እቅድ እየያዘ አፈጻጸሙን መከታተል እንዲሁም ወላጆቻቸውን ላጡና ለከፍተኛ ችግር ተጋላጭ ለሆኑ ህጻናት የመሰረታዊ ፍላጎት (ምግብ፣ ልብስ እና መጠለያ) ማግኘት ለማይችሉ ህፃናት የማቴሪያል ድጋፍ እንዲሁም ቋሚ የእርዳታ ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት ተደራሽ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡
- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለትምህርት የደረሱ ሕፃናት ስብዕናቸውን፣ ተሰጥዖዋቸውን፣ የአዕምሮ እና የአካል ችሎታቸውን በተሟላ መልኩ ለማዳበር የሚረዳ ትምህርት እየተማሩ ስለመሆኑ እንዲሁም ሕፃናት ከማንኛውም የሕፃናትን ትምህርት ከሚያደናቅፍ፣ ለህፃናት ጤና፣ አካላዊ፣ እና ማህበራዊ እድገታቸው ጎጂ ከሆነ ስራ የተጠበቁ ስለመሆናቸው የሚረጋገጥበት የአሰራር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊነቱን መከታተል ይኖርበታል፡፡

የሚሉ ናቸው፡፡

በኢትዮጵያ ልማት ባንክ የማምረቻ (Manufacturing) ዘርፍ የብድር አሰጣጥና አመላለስ ስርዓት ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት

76. **የብድር ፖሊሲውን ተከትሎ መመሪያው መሻሻሉን በተመለከተ**

77. የባንኩ የብድር ፖሊሲውን ሲያሻሽል የብድር መመሪያውንም ሊያሻሽል/ሊከለስ ይገባል፡፡

78. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ባንኩ የብድር ፖሊሲውን በ2014 ዓ.ም ቢያሻሽልም ፖሊሲውን ተከትሎ ሰኔ 2006 ዓ.ም የተዘጋጀውን መመሪያ ያላሻሻለ መሆኑ፤

79. **በብድር አፅዳቂ ኮሚቴ አባላት መካከል የጥቅም ግጭት እንዳይኖር አስቀድሞ ማሳወቅን በተመለከተ**

80. ብድር አፅዳቂ ቡድን (Loan approval teams) ሊቀመንበሩን ጨምሮ ሁሉም አባላት ብድርን በሚመለከት ማንኛውንም የጥቅም ግጭት እንዳይኖር አስቀድሞ ማሳወቅ እና በቃለ-ጉባኤ ውስጥ ማካተት እንዲሁም የጥቅም ግጭት የሚፈጥሩ ሁኔታዎች ካሉ ከሂደቱ ራሳቸውን እንዲያገሉ ሊደረግ ይገባል፡፡

81. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ባንኩ በብድር አፅዳቂ ኮሚቴ አባላት መካከል የጥቅም ግጭት እንዳይኖር አስቀድሞ በማሳወቅ እና በቃለ-ጉባኤ እንዲያዝ ያላደረገ መሆኑ፤

82. **በባንኩ በመያዣነት የተያዙ ንብረቶች በየዓመቱ የተገመገሙ መሆናቸውን በተመለከተ**

83. በባንኩ በመያዣነት የተያዙ ንብረቶች ተበዳሪዎች በየዓመቱ የንብረቶችን ዋጋ እንዲያስገመግሙ ሊያስደርግ እና የፕሮጀክቱ ቋሚ ንብረቶች ዋጋ ቢያንስ ከጠቅላላ የብድር ቀሪ ሂሳቦች ጋር ያልተከፈለ ወለድን ጨምሮ እኩል መሆኑን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

84. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ባንኩ የማምረቻ ዘርፍ ፕሮጀክቶችን ቋሚ ንብረት ዋጋ በየዓመቱ በማስገምገም ከጠቅላላ የብድር ቀሪ ሂሳባቸው ያልተከፈለ ወለድን ጨምሮ እኩል መሆን አለመሆኑን የማያረጋግጥባቸው ፕሮጀክቶች እንዲሁም ባንኩ ከገመገማቸው ፕሮጀክቶች የንብረት መያዣን እና ሌሎች መያዣዎችንም ጨምሮ ከ100 ፐርሰንት በታች የሆኑ መኖራቸው፤

85. **ፕሮጀክቶች የ25 እና 50 በመቶ መዋጮ እንዲሸፈኑ መደረጋቸውን በተመለከተ**

86. ባንኩ ቅድሚያ ለሚሰጣቸው አዲስ የፕሮጀክት አካባቢዎች ብድር የሚያመለክቱ የአገር ውስጥ እና የውጭ ፕሮጀክቶች እንደቅደም ተከተላቸው ከአጠቃላይ የፕሮጀክት ወጪ 25 እና 50 በመቶ መዋጮ እንዲሸፍኑ ሊያደርግ እና የብድር ስምምነቱ ከተፈረመበት ቀን አንስቶ በአንድ ጊዜ ወይም በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ በጥሬ ገንዘብ መክፈላቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

87. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በባንኩ ብድር የወሰዱ ፕሮጀክቶች የድርሻ መዋጮ እንዲሸፍኑ የማይደረጉ እና የብድር ስምምነቱ ከተፈረመበት ቀን አንስቶ በአንድ ጊዜ ወይም በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ በጥሬ ገንዘብ መክፈላቸውን የማይረጋገጡ ፕሮጀክቶች መኖራቸው፤

88. **በብድር ዕዳ ምክንያት የተወረሱ የፕሮጀክት ንብረቶች ለሶስተኛ ወገን መተላለፋቸውን በተመለከተ**

89. ባንኩ በብድር ዕዳ ምክንያት የወረሳቸውን የፕሮጀክት ንብረቶች ተገቢ አያያዝ በማድረግ በወቅቱ ለሶስተኛ ወገን በማስተላለፍ የባንኩን የሃብት ጥራት (Asset qulity) ሊያሻሽል ይገባል፡፡

90. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ባንኩ በዲስትሪክቶች በብድር ዕዳ ምክንያት የተወረሱ ንብረቶችን መረጃ በመያዝ ለሶስተኛ ወገን ያላስተላለፋቸው መኖራቸው፤

የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፤

የተጠቀሱትን የኦዲት ግኝቶች ለማሻሻል የሚረዱ የማሻሻያ ሀሳቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- ባንኩ በ2014 ዓ.ም የተሻሻለውን የብድር ፖሊሲ ተከትሎ በ2006 ዓ.ም የወጣውን የብድር መመሪያ ማሻሻል ይጠበቅበታል፡፡
- ባንኩ በብድር አፀዳቂ ኮሚቴ አባላት መካከል የጥቅም ግጭት እንዳይኖር በቅድሚያ አባላቶቹ እራሳቸውን ማግለላቸውን በማረጋገጥ የብድር ሂደቱን ማከናወን ይኖርበታል፡፡

- ባንኩ የማምረቻ ዘርፍ ፕሮጀክቶችን ቋሚ ንብረት ዋጋ በየዓመቱ በማስገምገም ከጠቅላላ የብድር ቀሪ ሂሳባቸው ያልተከፈለ ወለድን ጨምሮ እኩል መሆን አለመሆኑን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡
- በባንኩ ብድር የወሰዱ ፕሮጀክቶች የድርሻ መዋጮ እንዲሸፍኑ በማድረግ የብድር ስምምነቱ ከተፈረመበት ቀን አንስቶ በአንድ ጊዜ ወይም በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ በጥሬ ገንዘብ መክፈላቸውን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡
- ባንኩ በዲስትሪክቶች በብድር ዕዳ ምክንያት የተወረሱ ንብረቶችን መረጃ ይዞ ለሶስተኛ ወገን በማስተላለፍ ድርጅቶቹ ለሀገር ኢኮኖሚና ለማህበራዊ ልማት አስተዋፅኦ እንዲያደርጉ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

የሚሉ ናቸው፡፡

በመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን የቁጥጥር ሥርዓት አፈፃፀም (የልዩ ፈቃድ አሰጣጥ፤ የሚቀርቡ ቅሬታዎች የሚስተናገዱበት ሥርዓት፤ የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ አፈፀፃም) ኢኮኖሚያዊ፤ ቀልጣፋና ውጤታማነትን በተመለከተ የተከናወነ ክዋኔ ኦዲት

91. **የመንግስት ግዥን በኤሌክትሮኒክ የመረጃ ልውውጥ ዘዴ ለመፈጸም የሚያስችል አሰራር ስርዓት መዘጋጀቱን በተመለከተ**

92. ባለሥልጣኑ ሀገሪቱ ለምትገኝበት የዕድገት ደረጃ ተመጣጣኝ የሆነ ግዥን በኤሌክትሮኒክ የመረጃ ልውውጥ ዘዴ ለመፈጸም የሚያስችል አሰራር ስርዓት በማቅረብ ወደ ተግባር ሊገባ እና ለመንግስት የኤሌክትሮኒክ ግዥ (e-GP) ዓላማ የሚያገለግል መደበኛ የአሰራር ሂደት (Standard operating procedure, SOP) ሰነድ ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡

93. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡

    - ባለስልጣኑ ለመንግስት የኤሌክትሮኒክ ግዥ (e-GP) ዓላማ የሚያገለግል መደበኛ የአሰራር ሂደት (Standard operating procedure, SOP) ሰነድ በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩ የሀዋሳ ዩኒቨርስቲ፣ ድሬዳዋ ዩኒቨርስቲ፣ አዳማ ዩኒቨርስቲ፣ ኦዳቡልቱ ዩኒቨርስቲ፣ ሃራማያ ዩኒቨርስቲ፣ ዲላ ዩኒቨርስቲ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ (6 ኪሎ)፤ አዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ፣

ግብርና ሚኒስቴር፣ ትምህርት ሚኒስቴር፣ ገቢዎች ሚኒስቴር እና ኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር ያልደረሳቸው እንዲሁም የመንግስት የኤሌክትሮኒክ ግዥ በክልል መንግስት መ/ቤቶች እንዲጀመር ያላደረገ መሆኑ፤

- ባለሥልጣኑ የዘረጋው ግዥን በኤሌክትሮኒክ የመረጃ ልውውጥ ዘዴ ለመፈጸም የሚያስችል አሰራር ስርዓት ክፍተቶች ያሉበት መሆኑ፡

- በመንግስት የኤሌክትሮኒክስ ግዥ ስርዓት የውል አስተዳደር እና አቤቱታ መተግበርያዎች ተግባራዊ ያልተደረጉ መሆኑ፤ ውል አስተዳደር (Contract Administration) ስርአት መተግበሪያ ስራ ዉስጥ ያልተገባ በመሆኑ የመንግስት መ/ቤቶች ከመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ ውጪ ከአቅራቢዎች ጋር በሰነድ የሚዋዋሉ መሆኑ፤
- በመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ የኔት ወርክ መጨናነቅ ብዙ ጊዜ መውሰድ እንዲሁም በቀላሉ ሂደቱን ለመረዳት እገዛ ኬዝ ማኔጅመንት ሞጁል ተግባራዊ አለመደረጉ፤
- አቅራቢዎች ጨረታው የሚፈለገውን መረጃ እና ማስረጃ 100% አጠናቅቀው በመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ ስርዓት ለመላክ (submit) ለማድረግ አልፎ አልፎ እንደማይሰራ ቀደም ብለው ያሳወቁ ድርጅቶችም መፍትሄ ሳይሰጣቸው ጨረታው የሚያልፋቸው መሆኑ ከአቅራቢዎች ካደረግነው ቃለ መጠይቅ ለማወቅ መቻሉ፤

94. **ለመንግስት የኤሌክትሮኒክ ግዥ ዓላማ የሚያገለግል በመ/ቤቶች የሚፈፀሙ ግዥዎች ዝርዝር ስለመዘጋጀቱና የትግበራ መረጃዎች ለተጠቃሚዎች ይፋ ስለመደረጉ**

95. ባለስልጣኑ ለመንግስት የኤሌክትሮኒክ ግዥ (e-GP) ዓላማ የሚያገለግል በመ/ቤቶች የሚፈፀሙ ግዥዎች ዝርዝር (Item definition) ሊያዘጋጅ እና ለትግበራ የሚረዱ አግባብነት ያላቸው መረጃዎችን ለአቅራቢዎች፤ ለመንግስት መ/ቤት፤ ለተቆጣጣሪ አካላት ፤ለፋይናንስ ተቋማት እና ለሌሎች ተጠቃሚዎች ለሕዝብ ይፋ ሊያደርግ ይገባል፡፡

96. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ባለስልጣኑ ከአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ ጋር ውል ገብቶ የግዥዎች ዝርዝር (Item definition) የያዘ ሰነድ የተጠና ቢሆኑም

ባለስልጣኑ የግዥ ዝርዝሮቹን (Item definition) በመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ (e-GP) ስርዓት ያልተካተተ መሆኑ፤

97. **የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ ስርዓት የኦዲት ሥርዓቱን ሊያግዝ በሚችል መልኩ መልማቱን በተመለከተ**

98. ባለስልጣኑ የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ ስርዓት በተመለከተ የኦዲት ሥርዓቱን ሊያግዝ በሚችል መልኩ አብሮ ሊያለማ ይገባል፡፡

99. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡

- ➢ የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ ሥርዓት ለውጭ ኦዲተሮች መተግበሪያ ማንዋል የተሰራ ቢሆንም
- ለውጭ ኦዲተሮች ስልጠና የተሰጠ ቢሆንም ስራ ውስጥ በሚያስገባ መልኩ በቂ ስልጠና ያላገኙ መሆኑ፤
- ➢ መተግበሪያው ለመጠቀም እንዲቻል የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኦዲተሮች መለያ ስምና ሚስጥር ቁጥር የተሰጠ ቢሆንም በፖርታሉ ላይ ያሉ ክፍተቶች፡-
- ጨረታው በማን ባለሙያ የተረጋገጠ (approve) መሆኑ በስርዓቱ ውስጥ የማያመላክት መሆኑ
- በቴክኒካል ግምገማ ወቅት ኮምፕላይ እና ነን ኮምፕላይ ከማለት ባሻገር መስፈርቱ በምን እንደወደቀ ለሶስተኛ ወገን በሚያስረዳ መልኩ የማይገልፅ መሆኑ፤
- ውል የሚዋዋሉት በማንዋል በመሆኑ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ያለው የጨረታ ሂደቶች ለኦዲት የሚያስፈልጉ መረጃዎች በመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ ስርዓት ውስጥ አለመካተት፤

100. **የሚመለከታቸው አካላት የእርስ በእርስ ግንኙነት በመንግስት የኤሌክትሮኒክ ግዥ መፈፀሙን በተመለከተ**

101. ከመንግስት ግዥና ንብረት ሽያጭ ጋር በተያያዘ ባለሥልጣኑ፣ በመ/ቤቶች፣ በዕጩ ተወዳዳሪዎች፣ ተጫራቾች እና አቅራቢዎች፣ በፋይናንስ ተቋማት መካከል እንዲሁም

እርስ በእርስ የሚደረግ ማንኛውም ግንኙነት በኤሌክትሮኒክ ሥርዓት የተደገፈ ሊሆን ይገባል፡፡

102. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ባለስልጣኑ የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ ስርዓት ከፋይናንሻል ተቋማት ጋር ያልተሳሰረ በመሆኑ የግዥ ትዕዛዝ በመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ ስርዓት ክፍያ ለመፈፀም አለመቻሉ፤ የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ ከገቢዎች ሚኒስቴር መለያ ቁጥር /tin number/ እና ከንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ንግድ ፈቃድ /tax identification number የተሳሰረ /integrated/ የሆነ ቢሆንም አቅራቢዎች የግብር ግዴታቸውን ስለመወጣታቸው (tax clearance)፤ የአቅራቢዎች የኦዲት ሪፖርት (audit report)፣ የብቃት ማረጋገጫ እና የመሳሰሉት ጉዳዮችን በተመለከተ ያልተሳሰረ መሆኑ፤

103. ባለስልጣኑ ከተፈቀዱ የግዥ ዘዴዎች ውጪ ግዥ ለመፈፀም በመንግሥት መ/ቤቶች ጥያቄ ሲቀርብለት ጥያቄውን መርምሮ ውሣኔ ስለመስጠቱ

104. ባለስልጣኑ የሚቀርቡለት የልዩ ፈቃድ ጥያቄ መ/ቤቶች ከተፈቀዱ የግዥ ዘዴዎች እና የወሰዱትን አማራጭ ከወጪ፣ ከጥራት፣ ከጊዜ እና ሌሎች አስፈላጊ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ የሚያስገኘውን ጠቀሜታ ያካተተ መግለጫ አግባብነት ካላቸው ደጋፊ ሰነዶች ጋር ማቅረባቸውን በመመርመር ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

105. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ባለስልጣኑ ለባለበጀት መ/ቤቶች የልዩ ፈቃድ ግዢ ሲፈቅድ ከጊዜ፣ ከወጪ እና ከጥራት አንፃር ጠቀሜታ ያካተተ መግለጫ አግባብነት ካላቸው ደጋፊ ሰነዶች ጋር ማቅረባቸውን ሳያረጋግጥ ልዩ ፈቃድ እየሰጠ መሆኑ፤

የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፤ የተጠቀሱትን የኦዲት ግኝቶች ለማሻሻል የሚረዱ የማሻሻያ ሀሳቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- ባለሥልጣኑ ሀገሪቱ ለምትገኝበት የዕድገት ደረጃ ተመጣጣኝ የሆነ ግዥን በኤሌክትሮኒክ የመረጃ ልውውጥ ዘዴ ለመፈጸም የሚያስችል የተሟላ የአሰራር ስርዓት በማቅረብ ሙሉ በሙሉ ወደ ተግባር መግባት ይኖርበታል፡፡ እንዲሁም ለመንግስት የኤሌክትሮኒክ ግዥ (e-GP) ዓላማ የሚያገለግል መደበኛ የአሰራር ሂደት (Standard operating procedure, SOP) ሰነድ ማዘጋጀት እንዲሁም

የመንግስት የኤሌክትሮኒክ ግዥ በክልል መንግስት መ/ቤቶች እንዲጀመር ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

- ባለስልጣኑ በአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ ያሰራውን ለመንግስት የኤሌክትሮኒክ ግዥ (e-GP) ዓላማ የሚያገለግል በመ/ቤቶች የሚፈፀሙ ግዥዎች ዝርዝር (Item definition) ከኢጂፒ ስርዓቱ በማስተሳሰር ለኤሌክትሮኒክ ስርዓቱ ትግበራ የሚረዱ አግባብነት ያላቸው መረጃዎችን ለአቅራቢዎች፣ ለመንግስት መ/ቤት፣ ለተቆጣጣሪ አካላት ፣ለፋይናንስ ተቋማት እና ለሌሎች ተጠቃሚዎች ለሕዝብ ይፋ ማድረግ ይኖርበታል፡፡
- ባለስልጣኑ የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ ስርዓት በተመለከተ የኦዲት ሥርዓቱን ለማገዝ የተዘጋጀው መተግበሪያ የተሟሉ መረጃዎች እንዲጫኑላቸው በማድረግ የተሟላ ግምገማ ለማድረግ እንዲቻል ማድረግ ይገባዋል፡፡ ለኦዲተሮች የተዘጋጀው የስልጠና መተግበሪያ አስፈላጊውን ማሳያ እንዲያሟላ በማድረግ በስራ ላይ ተግባራዊ ለማድረግ በሚቻል መልኩ ለኦዲተሮች ስልጠና መስጠት ይጠበቅበታል፡፡
- ከመንግስት ግዥና ንብረት ሽያጭ ጋር በተያያዘ ባለሥልጣኑ፣ በመ/ቤቶች፣ በዕጩ ተወዳዳሪዎች፣ ተጫራቾች እና አቅራቢዎች፣ በፋይናንስ ተቋማት መካከል እንዲሁም እርስ በእርስ የሚደረግ ማንኛውም ግንኙነት በኤሌክትሮኒክ ሥርዓት የተደገፈ እንዲሆን ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ እንዲሁም በመንግስት ግዥ የሚሳተፉ ተጫራቾች ማናቸውንም ከፋይናንስ ተቋማት የሚቀርቡ ክፍያዎች እና ዋስትናዎች በኤሌክትሮኒክ ስርዓቱ በመጠቀም እንዲፈፀም ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡
- ባለስልጣኑ የሚቀርቡለት የልዩ ፈቃድ ጥያቄ መ/ቤቶች የወሰዱትን አማራጭ ከወጪ፣ ከጥራት፣ ከጊዜ እና ሌሎች አስፈላጊ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ የሚያስገኘውን ጠቀሜታ ያካተተ መግለጫ አግባብነት ካላቸው ደጋፊ ሰነዶች ጋር ማቅረባቸውን በመመርመር ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡

1. <u>ኢኮኖሚ አገልግሎት የ2014 /15 የክዋኔ ኦዲት</u>

በኢትዮጵያ ቅርስ ባለስልጣን የተንቀሳቃሽ ቅርሶች ምዝገባ፣ ጥበቃና እንክብካቤ የሥራ አፈፃፀም ኢኮኖሚያዊ፤ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን አስመልክቶ የተካሄደ የክዋኔ ኦዲት

ባለስልጣኑ ተንቀሳቃሽ ቅርሶችን ለመለየት ግልፅ መስፈርት አዘጋጅቶ ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፡-

1. የኢትዮጵያ ቅርስ ባለስልጣን ተንቀሳቃሽ ቅርሶችን ለመለየት ግልፅ መስፈርት አዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

2. ነገር ግን ባለስልጣኑ በየዘርፉና እንደ የባህሪያቸው **ምን ሲያሟሉ** በተንቀሳቃሽ ቅርስነት ለመለየትና ለመመዝገብ የሚያስችል ዝርዝርና ግልፅ መስፈርቶችን የያዘ የጸደቀ ህግ/ መመሪያ የሌለ መሆኑ፣

የቅርስ ጥበቃን የሚመለከት ፖሊሲ እና አዋጅ ደንብና መመሪያዎችን በተመለከተ፡-

3. የኢትዮጵያ ቅርስ ባለስልጣን በአዋጅ 209/1992 የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ለመወጣት የሚያስችል ፖሊሲ፣ ደንብና መመሪያዎች በማዘጋጀትና በሚመለከተው አካል በማጸደቅ ሥራ ላይ ሊያውል ይገባል፡፡

4. ኢትዮጵያ እንደ ሀገር የራሷ የሆነ የቅርስ ጥበቃና ልማት ፖሊሲ የሌላት መሆኑን፤ በአዋጅ 209/1992 አንቀጽ 31፣ 32 እና 46 መሰረት ለባለስልጣኑ አዋጅ ማስፈፀሚያ የሚሆን ደንብ መውጣት እንዳለበት ቢደነግግም የአዋጅ ማስፈፀሚያ ደንብ ላለፉት 23 (ሀያ ሦስት) ዓመታት ሳይወጣ መቆየቱን፤

ባለስልጣኑ በሀገሪቱ የሚገኙ የተንቀሳቃሽ ቅርሶችን በመለየት አግባብ ካለው አካል ጋር በመተባበር ምዝገባ ማከናወኑን በተመለከተ፡-

5. የኢትዮጵያ ቅርስ ባለስልጣን በሀገሪቱ የሚገኙ የተንቀሳቃሽ ቅርሶችን በመለየት አግባብ ካለው አካል ጋር በመተባበር ምዝገባ ሊያከናውን ይገባል፡፡

6. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት

- ❖ ባለስልጣኑ ከሚመለከታቸው የክልልና ሌሎች ቅርስ ከሚያስተዳድሩ አካላት ጋር በመተባበር ተንቀሳቃሽ ቅርሶችን በመለየት ቅርሶች ምዝገባ ስራ በሀገር አቀፍ የቅርስ መመዝገቢያ ማንዋል መሰረት በአግባቡ እየተከናወኑ አለመሆኑ፣
- ❖ እንዲሁም በቅርስ ምዝገባ ዙሪያ በሀገር አቀፍ ደረጃ ወጥ የሆነ የቅርስ ምዝገባ፣ መረጃ ልውውጥ እና ዶክመንቴሽን ሥርዓት የሌለ መሆኑን፣
- ❖ ምዝገባ የተደረገላቸውን የተንቀሳቃሽ ቅርሶች መረጃ ሙሉ በሙሉ ወደ ኤሌክትሮኒክስ መረጃነት በመለወጥ የኤሌክቶሮኒክ ኮፒ እንዲኖርና ለዳታቤዝ መረጃነት ዝግጁ እንዲሆኑ አለመደረጉን፤

ለአደጋ የተጋለጡ ወይም ሊጋለጡና ሊጠፉ ይችላሉ ተብለው የሚገመቱ ተንቀሳቃሽ ቅርሶች መስፈርት ወጥቶላቸው በቅድሚያ ምዝገባ የሚከናወንላቸው መሆኑን በተመለከተ፡-

7. የኢትዮጵያ ቅርስ ባለስልጣን በተለያዩ ክስተቶች ምክንያት ለአደጋ የተጋለጡ ወይም ሊጋለጡና ሊጠፉ ይችላሉ ተብለው የሚገመቱ ተንቀሳቃሽ ቅርሶች መስፈርት ወጥቶላቸው በቅድሚያ ምዝገባ ሊያካሂድላቸው ይገባል፡፡

8. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት

- ❖ ተንቀሳቃሽ ቅርሶች በቀላሉ ከቦታ ቦታ የሚንቀሳቀሱና ለተለያዩ ሰው ሰራሽና ተፈጥሯዊ አደጋዎች ማለትም በአስተዳደር ስርዓት (management system) ለውጦች፣ በጦርነት ጊዜ በቀላሉ ሊሸጡ፣ ሊዘዋወሩ ወይም ሊጣሉ (discarded) የሚችሉ በመሆኑ ተጋላጭ የሆኑ ወይም ይሆናሉ ተብለው ለሚገመቱ ቅርሶችን መስፈርት በማውጣት ቅድሚያ ምዝገባ የተከናወነላቸው የተንቀሳቃሽ ቅርሶች ዝርዝር አለመኖሩን፤ እንዲሁም

❖ ለአደጋ ተጋላጭ ይሆናሉ ተብሎ የሚታሰቡ ቅርሶችን ለመለየት የሚያስችል መስፈርት/መመዘኛ ሰነድ በማዘጋጀት ተግባራዊ አለማድረጉን፤

ባለስልጣኑ ቅርሶችን በተመለከተ ሀገሪቱ የተቀበለቻቸውን አለምአቀፍ ስምምነቶችን ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፡-

9. የኢትዮጵያ ቅርስ ባለስልጣን ቅርሶችን በተመለከተ ሀገሪቱ የተቀበለቻቸውን አለምአቀፍ ስምምነቶችን ለአብነት (በጦርነት ጊዜ ቅርሶችን ለመጠበቅ፣ ቅርስን በህገ-ወጥ መንገድ ከሀገር ማስወጣት፣ ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባትና ባለቤትነት ማዞርን ለመከላከል ወዘተ) ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ እንዲሁም አፈፃፀማቸውን ሊከታተል ይገባል፡፡

10. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ-መጠይቆች

- ኢትዮጵያ በጦርነት ጊዜ ቅርሶችን ለመጠበቅ እ.ኤ.አ. ሜይ 14 ቀን 1954 በሄግ የተደረገውን ስምምነት እና ፕሮቶኮሉን (The Convention for the protection of cultural property in the event of Armed Conflict and its first protocol) ለመቀበል የወጣ አዋጅ ቁጥር 373/ 1996 እና ቅርስን በህገ-ወጥ መንገድ ከሀገር ማስወጣት፣ ወደ ሀገር ማስገባትንና ባለቤትነት ማዞርን ለመከላከል የተደረገ አለምአቀፍ ስምምነት (Convention on the Means of Prohibiting and Preventing the Illicit Import, Export and Transfer of Ownership of Cultural Property) እ.ኤ.አ ኖቬምበር 14 ቀን 1970 የፈረመችና በህዝብ ተወካዮች ምክርቤት አዋጅ ቁጥር 374/1996 ተብሎ የፀደቀ መሆኑ፤

- በአዋጅ ቁጥር 373/1996 እና አዋጅ ቁጥር 374/1996 አንቀፅ 3 መሰረት የቅርስ ባለስልጣን ስምምነቱን በስራ ላይ ማዋልና አፈፃፀሙን መከታተል እንዳለበት የሚደነግጉ ቢሆንም በስምምነቱ ላይ ያሉትን ተግባራትና ነጥቦች በአመታዊም ሆነ ስትራቴጂክ እቅዶች ውስጥ በማካተት ተግባራዊ እያደረገ ስለመሆኑ እንዲሁም በስምምነቶቹ አፈፃፀም ዙሪያ ውይይትና

ግምገማ የሚደረግ ስለመሆኑ የሚያመላክት ማስረጃ ተጠይቆ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ አለመቅረቡ፤

- እንዲሁም ስምምነቶቹ የፌዴራልና ክልል ባለድርሻ አካላት በቂ ግንዘቤና እውቅና ኖሯቸው እንዲተገብሯቸው ለማስቻል በፌዴራል የስራ ቋንቋ እና በተዋረድ በክልሎች የስራ ቋንቋ ተተርጉመው ያልተሰናዱ መሆናቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡

ባለስልጣኑ በስጦታ ወደ ውጭ ሀገር የሚሄዱ ዕቃዎች ቅርስ መሆንና አለመሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት በመዘረጋት ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፡-

11. የኢትዮጵያ ቅርስ ባለስልጣን በስጦታ ወደ ውጭ ሀገር የሚሄዱ ዕቃዎች ቅርስ መሆንና አለመሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

12. ይሁን እንጂ

    - የባለስልጣኑ ይዞታ ሥር ያሉ የተለያዩ ተንቀሳቃሽ ቅርሶች በባለሙያ ቢሮዎች ጭምር የሚቀመጡ በመሆኑ፤
    - የቅርስ ስብስብ ክፍሎች አስተማማኝ በርና የጥበቃ ካሜራ የሌላቸው መሆኑ፣
    - በባለስልጣኑ ለጎብኝዎችም ሆነ ሰራተኞች በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ አስተማማኝ የፍተሻ ስርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ፤

ባለስልጣኑ ቅርሶችን በተመለከተ ሀገሪቱ የተቀበለቻቸውን አለምአቀፍ ስምምነቶችን ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፡-

13. የኢትዮጵያ ቅርስ ባለስልጣን ቅርሶችን በተመለከተ ሀገሪቱ የተቀበለቻቸውን አለምአቀፍ ስምምነቶችን ለአብነት (በጦርነት ጊዜ ቅርሶችን ለመጠበቅ፣ ቅርስን በህገ-ወጥ መንገድ ከሀገር ማስወጣት፣ ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባትና ባለቤትነት ማዞርን ለመከላከል ወዘተ) ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል

የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ እንዲሁም አፈፃፀማቸውን ሊከታተል ይገባል፡፡

14. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በአዋጅ ቁጥር 373/1996 እና አዋጅ ቁጥር 374/1996 አንቀፅ 3 መሰረት ሀገሪቱ የተቀበለቻቸውን አለምአቀፍ ስምምነቶችን የቅርስ ባለስልጣን ስምምነቱን በስራ ላይ ማዋልና አፈፃፀሙን መከታተል እንዳለበት የሚደነግጉ ቢሆንም በስምምነቱ ላይ ያሉትን ተግባራትና ነጥቦች በአመታዊም ሆነ ስትራቴጂክ እቅዶች ውስጥ በማካተት ተግባራዊ እያደረገ እንዲሁም በስምምነቶቹ አፈፃፀም ዙሪያ ውይይትና ግምገማ የሚደረግ ስለመሆኑ የሚያመላክት ማስረጃ ተጠይቆ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ አለመቅረቡ፤ ባለስልጣኑ ወጥ የሆነ የተንቀሳቃሽ ቅርስ ቆጠራ (Inventory) የሚያከናወንበት አሰራር አለመኖሩ፤

- **ባለስልጣኑ ሙዚየሞችን ማቋቋሙን፣ ደረጃ ማውጣቱንና የብቃት ማረጋገጫ መስጠቱን እንዲሁም ክትትልና ቁጥጥር ማከናወኑን በተመለከተ፡-**

15. የኢትዮጵያ ቅርስ ባለስልጣን ሙዚየሞችን ሊያቋቁም፣ በሀገሪቱ ውስጥ ለሚቋቋሙ ሙዚየሞች ደረጃ ሊያወጣና የብቃት ማረጋገጫ ሊሰጥ እንዲሁም ውጤታማ የክትትልና ቁጥጥር ስራ ሊያከናውን ይገባል፡፡

16. ይሁን እንጂ

- ባለስልጣኑ የሙዚየሞች የሙያና የብቃት ማረጋገጫ ማንዋል በታህሳስ 2005 ያዘጋጀ ቢሆንም የሙዚየም ስታንዳርዶችንና መመዘኛ መስፈርቶችን በማዘጋጀት በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ለሚገኙ ሙዚየሞች ፈቃድ መስጠት የጀመረው ከ10 ዓመት በኋላ ባለስልጣኑ ስድስት (6) ለሚሆኑ ሙዚየሞች በ2015 ዓ.ም ሰርተፍኬት የሰጡ መሆኑን ነገር ግን በመመሪያው መሰረት የሙዚየሞችን ደረጃ በመለየት ደረጃ አንድ፣ ደረጃ ሁለት፣ ደረጃ ሦስት ሙዚየሞች ተብለው የተለዩ አለመሆኑን

❖ የባለስልጣኑ የቅርስ ስብስብ ክፍሎች ደህንነት መከታተያ መሳሪያዎች/ካሜራዎች (security camera) ያልተገጠመላቸው መሆኑን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሙዚየም ህንፃ የአካል ጉዳተኞችን ታሳቢ ተደርጎ የተገነባ ባለመሆኑ አካል ጉዳተኞች ወደ ሙዚየሙ መግባት የሚችሉበት አሳንሰር (ሊፍት) እንዲሁም ለአካል ጉዳተኛ ተሸከርካሪ ወንበሮች (wheelchair) ለማንቀሳቀስ የሚያስችል መንገድ (ramp way for support wheelchair disabled people) የሌለው መሆኑ፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሙዚየም የቅርሶችን ደህንነት ለማስጠበቅ የሚያስችል ተቋሙ ወደ ውስጥ ለሚገቡና ለሚወጡ ጎብኝዎችና ሠራተኞች ዘመናዊ የፍተሻ ስክሪን ማሽን (X-Ray Security Machine) የሌለው በመሆኑ ማንኛውም ጎብኝ፣ ተመራማሪም ሆነ ሰራተኛ የጀርባ ሻንጣዎችንም ሆነ ሌሎች የእቃ መያዣዎችን በጥብቅ ለመፈተሽ የሚያስችል የተጠናከረ የጥበቃ ስርዓት አለመኖሩን፤ በምድረ-ግቢው ውስጥ የጥበቃ ካሜራዎች (security camera) አለመኖሩን፤

ባለስልጣኑ ለቅርስ እንክብካቤና ጥገና ስራዎች ፈቃድ መስጠቱንና መቆጣጠሩን በተመለከተ፡-

17. የኢትዮጵያ ቅርስ ባለስልጣን ለቅርስ እንክብካቤና ጥገና ስራዎች የሙያና የብቃት ፈቃድ ሊሰጥና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡

18. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ማናቸውንም የቅርስ እንክብካቤና ጥገና ለማከናወን በቅድሚያ ከባለስልጣኑ ፈቃድ ማግኘት እንደሚገባ የተቀመጠ ቢሆንም ባለስልጣኑ እስካሁን የመመዘኛ መስፈርት በማውጣት ለተንቀሳቃሽ ቅርስ እንክብካቤና ጥገና ለሚያከናውኑ ተቋማት ፈቃድ መስጠት እንዳልጀመረ፣

ባለስልጣኑ በባለስልጣኑ፣ በክልሎችና ከሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ጋር ቀልጣፋና ውጤታማ የመረጃ ልውውጥ ለማድረግ የሚያስችል በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈና ደረጃውን የጠበቀ ብሔራዊ የቅርስ መረጃ አስተዳደር ስርዓት (database system) መዘርጋቱን በተመለከተ፡-

19. የኢትዮጵያ ቅርስ ባለስልጣን በባለስልጣኑ፣ በክልሎችና ከሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ጋር ቀልጣፋና ውጤታማ የመረጃ ልውውጥ ለማድረግ የሚያስችል በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈና ደረጃውን የጠበቀ ብሔራዊ የቅርስ መረጃ አስተዳደር ስርዓት (database system) ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደያርግ ይገባል፡፡

20. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ባለስልጣኑ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈና የተማከለ የቅርስ መረጃና አስተዳደር ስርዓት የሌለው መሆኑን እንዲሁም በዘመናዊ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ በመታገዝ አገር አቀፍ የባህላዊ ቅርስ ኢንቨንተሪ አስተዳደር ስርዓት (ዳታ-ቤዝ) ያልተዘረጋ መሆኑ ከባለድርሻ አካላት ጋር ዘመናዊ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት አለመዘርጋቱ ታውቋል፡፡

ባለስልጣኑ ከክልሎች፣ ከተማ አስተዳደሮች፣ ከቅርስ ባለቤቶች እንዲሁም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት የሚሰራበትን የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፡-

21. የኢትዮጵያ ቅርስ ባለስልጣን ከክልሎች፣ ከተማ አስተዳደሮች፣ ከቅርስ ባለቤቶች እንዲሁም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት የሚሰራበትን ውጤታማ የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

22. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት የቅርስ ምዝገባና ቁጥጥር ለማከናወን ከክልልና ከተማ አስተዳደር ጋር ቅንጅታዊ አሰራር ችግሮችና የመረጃ ልውውጥ ክፍተት ያለ መሆኑ እንዲሁም ከክልል፣ ከከተማ አስተዳደሮችና ከሌሎች የቅርስ ባለይዞታዎች ጋር ያለው የስራ ግንኙነትና ድርሻ ተለይቶ በአግባቡና

በግልጽ ያልተቀመጠ መሆኑን እና በዕቅድ የተያዘ የጋራ ምክክር መድረክ አለመኖሩ፤

በመሆኑም

- ☞ ባለስልጣኑ አንድ ተንቀሳቃሽ ቅርስን በቅርስነት ለመመደብ የሚያስችል በአዋጅ ቁጥር 209/1992 አንቀጽ 8 ላይ በተለዩበት ምድብ መሰረት እንደባህሪያቸው ግልጽ የሆነ መሟላት ያለባቸውን ዝቅተኛ የመመዘኛ መስፈርት በማዘጋጀትና በሚመለከተው አካል በማጸደቅ ሥራ ላይ ሊያውል እና ሌሎች ቅርስን የሚያስተዳድር መንግስታዊ ሆኑ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት እንዲጠቀሙበት ለማድረግ የግንዛቤ ሥራ በመስራት ወደ ተግባር እንዲገቡ በዚሁ መስፈርት መሰረት ተግባር እንዲገቡ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ☞ ባለስልጣኑ የቅርስ ጥበቃና ልማት ፖሊሲ ሊያዘጋጅ፣ የማቋቋሚያ አዋጅ ማስፈፀሚያ መውጣት አለበት ተብሎ የተደነገገው ደንብ እንዲወጣ ረቂቅ ደንብ በማዘጋጀት ለሚመለከተው አካል በማቅረብ አፈጻጸሙን ሊከታተል፣ እንዲሁም መውጣት እያለባቸው ያልወጡ የተለያዩ መመሪያዎችና የአሰራር ማንዋሎችን መመሪያዎች በማውጣት፤ እንዲሁም በሥራ ላያ ያሉ መመሪያዎችን በመፈተሽ ወቅታዊ በማድረግና በሚመለከተው አካል በማጸደቅ ወደ ሥራ ሊገባ ለሚመለከታቸው አካላትም እንዲደርሳቸው በማድረግ ተፈጻሚ እንዲሆኑ ሊያደርግና አፈጻጸማቸውንም ሊከታተል ይገባል፡፡

- ☞ ባለስልጣኑ ኢትዮጵያ እንደ ሀገር ያሏትን ታሪካዊ፣ ባህላዊና ሀይማኖታዊ ተንቀሳቃሽ ቅርሶችን ሳይንሳዊና ደረጃውን በጠበቀ የምዝገባ መስፈርት/ቅፅ መሰረት በመለየት (identifications) እና የተንቀሳቃሽ ቅርሶች የምዝገባ ሶፍትዌር "Registration of Cultural Heritage Software" በማልማት አና ዳታ ቤዙን በማደራጀት በጽሁፍ ያሉ ምዝገባዎችን መረጃዎቹ ወደ ኤሌክትሮኒክስ ቅጂ እንዲቀየሩ በማድረግ በተሟላና ወጥ በሆነ መልኩ ሀገር አቀፍ ምዝገባ በማከናወን

ሀገሪቱ ያሏትን ተንቀሳቃሽ ቅርሶች **ሙሉ በሙሉ** ሊመዘግብና በሌሎች ቅርስን በሚያስተዳደሩ አካላት ያሉትም በተመሳሳይ ሁኔታ እንዲመዘግቡ ሊያደርግና የእነርሱንም መረጃ በዳታ ቤዙ የሚያዝበትን ሥርዓት መፍጠር መዘርጋት አለበት፡፡

☞ ባለስልጣኑ ለተለያዩ አደጋዎችና ጉዳቶች ተጋላጭ በሆኑ ተንቀሳቃሽ ቅርሶች ዙሪያ አመላካች መስፈርቶችን መሰረት ያደረገ የአደጋ ተጋላጭነት የግምገማ ማዕቀፍ (Indicator and Criteria based Vulnerability Assessment Framework) በማዘጋጀትና በማዕቀፉ መሰረት ጥናት በማከናወን ተጋላጭ የሆኑ ተንቀሳቃሽ ቅርሶችን ደረጃ በማውጣት፣ በመለየት እና እነርሱን ቅድሚያ ሰጥቶ ሊመዘግብና ከመመዝገባቸው በፊት ለጥፋት እንዳይዳረጉ ሊያደርግ ይገባል፡፡

☞ ባለስልጣኑ በቅርሶች ጥበቃ ዙሪያ ኢትዮጵያ ተቀብላ ያፀደቀቻቸውን አለምአቀፍ ስምምነቶች በአመታዊ እና ስትራቴጅክ እቅዶች አካቶ ተግባራዊ ሊያደርግ እንዲሁም በሌሎች በሚመለከታቸው አካላት መተግበራቸውን አፈፃፀማቸውን ሊከታተልና በህጉ መሰረት ለሚመለከታቸው አካላት ሪፖርት ሊያደርግ ይገባል፡፡

☞ ባለስልጣኑ ሳይንሳዊ የሆኑ የሙዚየም ስታንዳርዶችንና መመዘኛ መስፈርቶችን የያዘ ማንዋል በማዘጋጀት ከብሔራዊ ሙዚየም ጀምሮ በተለያዩ ሙዚየሞች ላይ የምዘና ተግባራት በማከናወን ደረጃና የብቃት ማረጋገጫ በመስጠት ደረጃቸውን የጠበቁ ሙዚየሞች እንዲኖሩ ቱሪስቶችን የመሳብ አቅም ያላቸው ሆነው እንዲደራጁ ሊያደርግ ይገባል፡፡

☞ ባለስልጣኑ የቅርስ ባለይዞታዎችና ባለቤቶች ቅርሶችን በአግባቡ ጥበቃ፣ እንክብካቤና ጥገና እያደረጉ ስለመሆኑ ለመከታተል የሚያስችል ወጥ የሆነ የክትትል ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ሊያደርግ እንዲሁም በባለስልጣኑ የቅርስ ስብስብ ክፍሎች ያሉ

ቅርሶችን ደህንነታቸውን የሚያስጠብቁ አሰራሮችን በመከተል ቅርሶችን በአግባቡ ሊይዝና ሊያስተዳደር ይገባል፡፡

- ☞ ባለስልጣኑ የተንቀሳቃሽ ቅርስ እንክብካቤና ጥገና ስራዎችን ለሚያከናውኑ አካላት ፈቃድ ለመስጠት የሚያስችል መመሪያ በማዘጋጀት ፈቃድ ሊሰጥ፣ የተንቀሳቃሽ ቅርስ የጥገና ላይ የተሰማሩ ተቋማት እንዲፈጠሩ የበኩሉን ድርሻ ሊወጣ እንዲሁም በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የሚገኙ ውድና የማይተኩ ሀገራዊ የቅርስ ሀብቶች ፈቃድ ባላቸው ባለሙያዎችና ተቋማት ብቻ እንክብካቤና ጥገና እንዲያገኙ ሊያደርግ እንዲሁም መደረጋቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

- ☞ ባለስልጣኑ የተንቀሳቃሽ ቅርስ ምዝገባ ሶፍትዌር በማልማትና የመረጃ ቋት (database system) በማደራጀት የተንቀሳቃሽ ቅርሶችን የምርምር ትርጓሜዎች፣ የምርምር ዘገባዎች፣ ፎቶግራፎች፣ ስላይዶች፣ የድምጽና የቪዲዮ ቀረጻዎች፣ የእድሳት አጭር ሪፖርቶችን የመሳሰሉ መረጃዎችን በቴክኖሎጂ በታገዘ ስርዓት በማደራጀት የቅርሶችን ምዝገባ፣ ምደባ (classification)፣ እንክብካቤና ጥበቃ (conservation) እና ውርስ (inheriting) የመሳሰሉ መረጃዎችን እንዲሁም በክልሎችና በሙዚየሞች የተንቀሳቃሽ ቅርስ ምዝገባ ሶፍትዌር በመጫን ሀገራዊና የተዋሃደ የቅርስ ምዝገባ እና የመረጃ ልውውጥ ስርዓት (a unified state registration and information database system) እንዲኖር ሊያደርግ ይገባል፡፡ ሌሎች ቅርስን በሚያስተዳድሩ አካላት የበለጸጉ የተለያዩ ሶፍትዌሮች እና የመረጃ ቋቶች (ዳታ ቤዝ) ጋር እርስ በእርስ ከባለሥልጣኑ ዳታ ቤዝ ጋር እንዲተሳሰሩ የማድረግ ሥራ ሊሰራና ተጠቃሚዎች ሁሉንም መረጃ በአንድ ቦታ ማግኘት እንዲችሉ የራሱ የሆነ ፖርታል ሊያበልጽግ ይገባል፡፡

- ☞ ባለስልጣኑ ወጥና በአሰራር ስርዓት የተደገፈ ቅንጅታዊ አሰራር ስርዓት በመዘርጋት ከሚመለከታቸው ቅርስን በመያዝ ከሚያስተዳድሩ ተቋማት፣ በየደረጃው ካሉ የአስተዳደር እርከኖች፣ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ የእምነት ተቋማት፣ የፖሊስና የደህንነት ተቋማት፣ የአቬሽን

ተቋማትና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ጋር በተንቀሳቃሽ ቅርሶች ዙሪያ ውጤታማና ተጨባጭ ተግባራትን ሊያከናውን ይገባል፡፡

የሚሉትን የማሻሻያ ሃሳቦች ሰጥተናል፡፡

የፌዴራልና የክልል መንግሥታት የጋራ ገቢዎች አስተዳደርና ክፍፍል አፈፃፀምን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት

ግብርና ሽያጭ ታክስ በጋራ መጣሉንና መሰብሰቡን በተመለከተ፣

23. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከክልል መንግሥታት ጋር በድርጅቶች የንግድ ትርፍ ላይ እና በባለ አክሲዮኖች የትርፍ ድርሻ ላይ ግብርና የሽያጭ ታክስ በጋራ ሊጥልና ሊሰበስብ ይገባል፡፡

24. የፌዴራል መንግሥት እና የክልል መንግሥታት በድርጅቶች የንግድ ትርፍ ላይ እና ባለአክሲዮኖች የትርፍ ድርሻ ላይ ግብርና የሽያጭ ታክስ በጋራ መጣልና መሰብሰብ እንዳለባቸው በህገ መንግስቱ አንቀጽ 98 ተ.ቁ 2 የተገለጸ ቢሆንም በተገለጸው መሰረት ከክልሎች ጋር በመቀናጀት በጋራ ገቢ ሥር የሚወድቁት ገቢዎች ታክስ በጋራ ስለመጣሉ ማስረጃ የገንዘብ ሚኒስቴር ተጠይቆ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ አልቀረበም፡፡ የጋራ ገቢው በገቢዎች ሚኒስቴር ብቻ ነው የሚሰበሰበው

ክልሎች በአቅራቢያቸው ባሉ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የጋራ ገቢዎችን በሚመለከተ ተገቢውን መረጃ ማግኘታቸውን በተመለከተ፤

25. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በክልል የሚገኙ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች መሰብሰብ ያለባቸውን የጋራ ገቢዎች ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ ትክክለኛውን መረጃ እንዲያገኙ ሊያደርግ ይገባል፡፡

26. በኦዲቱ ወቅት በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ራሱን ችሎ ከተመሰረተ በኋላ በቀድሞው የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ክልል ስም ተይዞ የነበረው 17 የግብር ከፋዩ አድራሻ አለመቀየር ቅሬታ ቀርቦ የነበረ እና አሁን በ16 ድርጅቶች ላይ

ማስተካከያ ተደርጎ ገቢው ስለመተላለፉ እና አንድ ድርጅት ግን ማስተካከያ ስለመደረጉ ማስረጃ ማቅረብ አለመቻሉን፣

27. እንዲሁም የሥራ አድራሻቸው ሙሉ በሙሉ በኦሮሚያ ክልል ውስጥ የሚገኙ 20 ድርጅቶች የግብር ከፋይ መለያ ቁጥራቸውን ከአዲስ አበባ በማውጣታቸው ክልሉ ከነዚህ ድርጅቶች ማግኘት የነበረበትን የንግድ ትርፍ ድርሻ እያገኘ አለመሆኑ ቅሬታ የቀረበ እና 15 ድርጅቶች የማስተካከያ መልስ ያገኙ መሆኑን ማስረጃ በማቅረብ የገለፁ ሲሆን ቀሪዎቹ 5 ድርጅቶች በሂደት ላይ ያሉ መሆናቸው ታውቋል፡፡

ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የጋራ ገቢዎችን አስተዳደር በተመለከተ በጋራ በማቀድ መሰራቱን በተመለከተ፤

28. የገቢዎች ሚኒስቴር የጋራ ገቢዎች አስተዳደርና ክፍፍል በተመለከተ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ እስትራቴጂክ ዕቅድ ሊያቅድና ዕቅዱን መሰረት በማድረግ አመታዊ ዕቅድ በማቀድ ሊሰራና አፈጻጸሙን ሊገመግም ይገባል፡፡

29. በኦዲቱ ወቅት ሚኒስቴር መ/ቤቱ የጋራ ገቢዎች አስተዳደርና ክፍፍልን በተመለከተ ከክልል ገቢዎች ቢሮና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ የማያቀድና አፈጻጸሙንም የማይገመግም መሆኑ ታውቋል፡፡

ከአንድ ክልል በላይ የሚንቀሳቀሱ ግብር ከፋዮች ግብር አከፋፈል መረጃና ድርጅቶች ለሠራተኞቻቸው በሚያወጡት ወጪ መሠረት ክፍፍል መደረጉን በተመለከተ፤

30. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ዋናው መ/ቤቶች አንድ ቦታ ላይ ሆኖ በተለያዩ ክልል ባሉ ቅርንጫፎቻቸው፣ የማምረቻና አገልግሎት መስጫ ያላቸው ድርጅቶች ዋና መ/ቤታቸው ካለበት ክልል/ከተማ ውጭ ያሉ ክልሎች በክልላቸው ውስጥ የመነጨውን ገቢ የሚያውቁበትንና ድርጅቶች ግብር መክፈል አለመክፈላቸውን፣ ከከፈሉም የተከፈለውን ግብር በጋራ የሚከታተሉበትና የሚረጋግጡበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ የክልሎች

ድርሻ ድርጅቶቹ ለሠራተኞቻቸው የሚያወጡትን ወጪ መሠረት በማድረግ በክልሎች መካከል ክፍፍል ሊደርግ ይገባል፡፡

31. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት የንግድ ትርፍ ገቢ ግብርና የባለ አክሲዮኖች የትርፍ ገቢ ግብር ድርጅቶች ከአንድ በላይ በተለያዩ ክልሎች ውስጥ ሥራ ሲሰሩ የክፍፍል ቀመሩ መሠረት የሚያደርገው ድርጅቶቹ ለሠራተኞች ያወጡትን ወጪ መሠረት በማድረግ በመሆኑ እያንዳንዱ ድርጅት በየክልሉ ለሠራተኞቹ ያወጣውን ወጪ፤ የሠራተኛ ብዛት ግብር ለሚከፍልበት ቅርንጫፍ እንዲያሳውቅ በፌዴሬሽን ምክር ቤት የጋራ ገቢ ቀመር ተግባራዊ እንዲሆን በተወሰነው ላይ ቢጠቀስም ድርጅቶቹ የሠራተኞቻቸውን ዝርዝር እና ወጪ አሟልተው ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የማያቀርቡ መሆኑ፣

የጋራ ገቢዎች አስተዳደርና ትልልፍ ዙሪያ ቅሬታዎችን ለመፍታት የሚያስችል ሥርዓት መኖሩን በተመለከተ፤

32. የጋራ ገቢዎች አስተዳደርና ትልልፍ ዙሪያ ከክልል መንግሥታት እና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት የሚነሱ ቅሬታዎችን ለመፍታት የሚያስችል የቅሬታ አፈታት ሥርዓት ሊኖር ይገባል፡፡

33. ይሁን እንጂ በኦዲት ወቅት ሚኒስቴር መ/ቤቱ በጋራ ገቢዎች አሰባሰብ፤ አስተዳደርና ክፍፍልን አስመልክቶ ለሚነሱ ቅሬታዎች አልፎ አልፎ በመድረክ ላይ ከሚደረግ ውይይት በዘለለ ቅሬታዎች የሚስተናገዱበት እና የሚፈቱበትን የቅሬታ አፈታት ሥርዓት ያልዘረጋ መሆኑ፣

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ምን ያህል የጋራ ገቢ እንደተሰበሰበ በወቅቱ ማሳወቁን በተመለከተ፣

34. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከእያንዳንዱ ድርጅትና ክልል ምን ያህል የጋራ ገቢ፡ እንደተሰበሰበ፡ በተወሰነው ቀመር መሠረትም ለፌዴራልና ለክልሎች ምን ያህል እንዳስተላለፈ በወቅቱ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት እና ለሚመለከታቸው አካላት ሊያሳወቅ ይገባል፡፡

35. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 1250/2013 አንቀጽ 25 መሠረት ሚኒስቴር መ/ቤቱ በቀመሩ መሠረት የጋራ ገቢዎች የፌዴሬሽን ምክር ቤቱ በወሰነው የማከፋፈያ ቀመር መሠረት ከ2013-2015 ድረስ ብር 105,811,207,908.90 ክፍፍል መከናወኑን እና ወቅቱን የጠበቀ ዓመታዊ ሪፖርት (በአጠቃላይ የተሰበሰበውን የሀብት መጠን በገቢ ዓይነት፣ እንዲሁም ከእያንዳንዱ የገቢ ዓይነት ላይ የፌዴራል መንግሥቱንና የእያንዳንዱን ክልል ድርሻ የሚያሳይ) ለፌዴሬሽን ምክር ቤት የሚያቀርብ መሆኑ ታውቋል፡፡

በመሆኑም

- የፌዴራልና የክልል መንግሥታት በድርጅቶች የንግድ ትርፍ ላይ እና በባለ አክሲዮኖች የትርፍ ድርሻ ላይ የጋራ ገቢ ታክስ ተመን በጋራ እንዲጣል ሊደረግና በሚመለከተው አካል በመሰብሰብ በቀመሩ መሰረት ክፍፍሉ ሊቀጥል እንዲሁም የመሰብሰብና የማከፋፈል ስልጣን የተሰጠው የፌደራሉ መንግስት ኃላፊነቱ የተጠናከረ እና ተጠያቂነትን የማያስነሳ እንዲሆን በሁለቱ ምክር ቤቶች በተናጠልና በጋራ የጸደቀው የህገመንግስት ማሻሻያ ረቂቅ የሕግ አወጣጥ ሥርዓቱን ተከትሎ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚኒስትሮች ምክር ቤት እና ከፌዴሬሽን ም/ቤት ጋር በመመካከር በነጋሪት ጋዜጣ እንዲወጣ ሊማድረግ ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የጋራ ገቢዎች አሰባሰብ፤ አስተዳደርና ክፍፍል ውጤታማ እና ግልጸኝነትን በተላበሰ መልኩ ተሰብስቦ ክልሎች ያለ ቅሬታ ድርሻቸውን ማግኘት እንዲችሉ እንዲሁም ክልሎች በአሰባሰብና ትልልፍ ወቅት ያጋጠማቸውን ችግር አፋጣኝ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ በጋራ ሊያቅድ እና አፈፃፀሙን በጋራ ሊገመግም ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በጋራ ገቢዎች አሰባሰብ፤ አስተዳደርና ክፍፍል ዙሪያ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ

ለመሥራት የዘረጋው ቅንጅታዊ አሠራር ጠንካራ እና ወጥነት ያለው ሊሆን ይገባል፡፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የጋራ ገቢዎች አስተዳደርን አስመልክቶ ከባለድርሻ አካላት ጋር አፈፃፀሙን በጋራ የሚገመግምበት ጊዜ በማስቀመጥ በጋራ ሊያቅድ ሊገመግምና በአፈጻጸም ለሚስተዋሉ ችግሮች የመፍትሄ አቅጣጫዎች በማስቀመጥ እርምጃ ሊወስድና አፈጻጸሙን በማጠናከር ሊሰራ ይገባል፡፡ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፌዴራልና የክልል መንግሥታት የገቢ አስተዳደር ተቋማት ከፌዴሬሽን በተላለፈው የጋራ ገቢዎች አስተዳደርና ክፍፍል ውሳኔ መሰረት የጋራ ገቢዎች አስተዳደር፣ አሰባሰብና ትልልፍ ግልጽነት የተላበሰ ቀልጣፋና ተጠያቂነትን ያረጋገጠ እንዲሆን እና ስርዓቱን በየጊዜው ማሻሻል የሚቻልበት ቋሚና ተከታታይነት ያለው የመወያያ መድረክ በመፍጠር ሊሠራ ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከእያንዳንዱ ድርጅትና ክልል ምን ያህል የጋራ ገቢ እንደተሰበሰበ፡ በተወሰነው ቀመር መሠረት ለፌዴራልና ለክልሎች ምን ያህል እንዳስተላለፈ እና በአሰባሰቡና ክፍፍሉ ወቅት የጋጠሙ ችግሮች የማስተካከያ እርምጃ ሊወሰድባቸው የሚገቡ የአሠራር ክፍተቶችን በመግለጽ ለሚመለከታቸው አካላት ተከታታይነት ያለው ሪፖርት የሚያቀርብበት አሠራር ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል፡፡

የሚሉትን የማሻሻያ ሃሳቦች ሰጥተናል፡፡

በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን የኢንቨስትመንት ፍቃድ አሰጣጥ፣ ድህረ ኢንቨስትመንት ክትትል እና የኢንቨስትመንት ማበረታቻ መብት አጠቃቀምን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት

ባለሀብቶች የመሬት እና የኤሌክትሪክ አገልግሎት ለማግኘት እንዲችሉ ድጋፍ ለማድረግ የሚያስችል ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፤

36. ኮሚሽኑ ባለሀብቶች ለኢንቨስትመንት ፕሮጀክታቸው የሚያስፈልግ መሬት እና የኤሌክትሪክ ኃይል አገልግሎቶች ለማግኘት እንዲችሉ ድጋፍ ለማድረግ የሚያስችል ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

37. ኮሚሽኑ ባለሀብቶች ለኢንቨስትመንት ፕሮጀክታቸው የሚያቀርቡትን የመሬት ጥያቄ ተከትሎ ለሚመለከተው የክልል አስተዳደር የድጋፍ ጥያቄ የሚያቀርብ ሲሆን፤ከክልል መስተዳደሮች ጋር በመሆን ለኢንቨስትመንት የሚሆን መሬት በመለየት የሚያዘጋጁበት አሰራር አለመኖሩ እና ኢንቨስተሮች መሬት ለማግኘት እየተቸገሩ እና የተረከቡትንም መሬት ለሌላ የልማትሥራ ተብሎ እንደሚወሰድባቸው፤ በተጨማሪም የኤሌክትሪክ አገልግሎት ለማግኘት የሚፈለግቸውን ክፍያ ከከፈሉ በኋላ የማይገባላቸው መሆኑን፣

የውጭ ሀገር ዜጋ የሚቀጠርበትን ስርአት በተመለከተ፤

38. ኮሚሽኑ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የውጭ ሀገር ዜጋ የሚቀጠርበት የስራ መደብ አስፈላጊነትና የሙያ ተገቢነት፣የፈቃድ እድሳት፣ ተፈላጊ ችሎታ ያለው ተተኪ የሰው ኃይል መኖርና አለመኖሩን የሚያረጋግጥበት ስርአት እና ለተተኪ ኢትዮጵያውያን ሰራተኞች የስልጠና መርሀ ግብርን የሚመለከት መመሪያ በማዘጋጀት ተፈጻሚ ሊያደርግ ይገባል፡፡

39. ኮሚሽኑ በኢንቨስትመንቶች ውስጥ ለሚሰሩ የውጭ አገር ሰራተኞች የስራ ፈቃድ የሚሰጥበት ከውጭ አገር ሰራተኞች ወደ ኢትዮጵያውያን የሚሸጋገር

እውቀት እና ክህሎት አፈጻጸምን ለመምራት በወጣው መመሪያ ቁጥር 772/2013 መሰረት የማይረጋገጥ መሆኑ፣

ኮሚሽኑ የውጭ ባለሀብቶች ወደ አገር ውስጥ ለፕሮጀክት ያስገቡትን እና የንግድ ካፒታል በማረጋገጥ መመዝገቡን በተመለከተ፤

40. ኮሚሽኑ የውጭ ባለሀብቶች ወደ አገር ውስጥ ለፕሮጀክት ያስገቡትን እና ለንግድ ፈቃድ ሲያወጡ ያቀረቡትን ካፒታል በማረጋገጥ ሊመዘግብ ይገባል፡፡

41. በኦዲት ወቅት በናሙና ከታዩት 153 የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ፋይሎች ውስጥ ለመረዳት እንደተቻለው በትግበራ እና በቅድመ ትግበራ ላይ ያሉ ፕሮጀክቶች በህጉ መሰረት ለውጭ ባለሀብቶች ሁለት መቶ ሺ የአሜሪካ ዶላር እና ከዛ በላይ፣ ከትውልደ ኢትዮጵያውያን ጋር በጋራ ሲሆን አንድ መቶ ሃምሳ ሺ የአሜሪካ ዶላር እና ከዛ በላይ ስለማስያዛቸው በኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶቹ ፋይል ላይ ማስረጃዉ አለመገኘቱ ፕሮጀክቶች ከትግበራ ወደ ስራ እንዲገቡ የንግድ ፈቃድ ሲሰጥም ካፒታላቸው ያልተመዘገበ ባለሀብቶች መኖራቸው፣ የንግድ ፈቃድ ከመውጣቱ በፊት ኮሚሽኑ ውሳኔ ለመስጠት በሚያደርገው የክትትል ሪፖርት ላይ ወደ አገር ውስጥ ያስገቡትን ካፒታል የባንክ ማስረጃ የሚያይዝ መሆኑ

የኢንቨስትመንት ፈቃድ የመስጠት፣ የማደስ እና የመሰረዝ ስራዎችን በተመለከተ

42. ኮሚሽኑ ለውጭ ባለሀብቶች ክፍት በሆኑ የኢንቨስትመንት መስኮች ለሚሰማሩ ባለ ኃብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ የመስጠት፣ የማደስ እና የመሰረዝ ስራዎችን በስራ ላይ ባሉ ህጎች መስረት በማከናወን ለሚመለከታቸው አካላት ሊያሳውቅ ይገባል፡፡

43. ኮሚሽኑ ከ1992 ዓ.ም ጀምሮ ለ18,559 ፕሮጀክቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ የሰጠ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 4490 ፕሮጀክቶች (24.1%) ወደ ስራ

መግባታቸውን፣ 9061 ፕሮጀክቶች (48.8%) የኢንቨስትመንት ፈቃድ የተሰረዘ መሆኑ፤

የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ያሉበትን ደረጃ እና አፈጻጸም የሚከታተልበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፤

44. ኮሚሽኑ የኢንቨስትመንት ፈቃድ የሰጣቸውን ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ደረጃ እና አፈጻጸም የሚከታተልበት ስርአት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

45. ኮሚሽኑ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ያሉበትን ደረጃ የሚከታተልበት ሥርዓትና አደረጃጀት ዘርግቷል፡፡ ነገር ግን በኦዲቱ ወቅት ኮሚሽኑ ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት (ለጉምሩክ ኮሚሽን እና ለሚመለከታቸው ለክልል ሴክተር መስሪያ ቤቶች) የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን ያሉበትን ደረጃ እና የተሰረዙ ፕሮጀክቶችን የሚያሳውቅበት ስርአት ዘርግቶ ተግባራዊ አለማድረጉ፤

46. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት 153 የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ፋይል እንደተመለከትነው ኮሚሽኑ ፕሮጀክቶችን ለመከታተል በአመት፣በስድስት ወር ወይም በሩብ አመት እቅድ በመያዝ የድጋፍ እና ክትትል ስራ በማከናወን ለድርጅቱ የተሰጠ ግብረ መልስ አለመገኘቱ፤

ወቅታዊ የመረጃ ፍሰት እንዲኖር የሚያስችል የመረጃ መለዋወጫ ስርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፤

47. ኮሚሽኑ በባለሀብቶች እና በሌሎች መንግስታዊ አካላት መካከል ወቅታዊ የመረጃ ፍሰት እንዲኖር የሚያስችል የመረጃ መለዋወጫ ስርአት ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡

48. ይሁን እንጂ በኦዲት ወቅት ማስረጃ ከተሰበሰበባቸው የአዲስ አበባ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን፣ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ከኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽኑ ኢንቨስትመንት ፈቃድ

ወስደው በከተማ አስተዳደሩ ወይም በክልሉ ኢንቨስት የሚደረጉ ፕሮጀክቶችን በተመለከተ የመረጃ ልውውጥ ስርዓት አለመኖሩ፤

በመሆኑም

- ኮሚሽኑ ባለሀብቶች ለኢንቨስትመንት ፕሮጀክታቸው የሚያስፈልግ መሬት እና የኤሌክትሪክ ኃይል አገልግሎቶች ለማግኘት እንዲችሉ ድጋፍ ለማድረግ የሚያስችል ስርአት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡ በተጨማሪም አስፈላጊውን የኤሌክትሪክ አቅርቦት እንዲሟላላቸው ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ጋር በመነጋር ጥያቄያቸው በአጭር ቀናት ውስጥ ምላሽ የሚያገኝበትን አሠራር ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ኮሚሽኑ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የውጭ ባለሀብቶች የውጭ ሀገር ዜጋ ሚቀጠርበት የስራ መድብ አስፈላጊነትና የሙያ ተገቢነት፣ መደቡ በኢትዮጵያውያን ሊተካ አለመቻሉ፣ የክህሎት ሽግግር ዕቅድ ስለመኖሩ በማረጋገጥ፤የሥራ ፈቃድ የሚሰጥበት፤ ፈቃዱ የሚታደስበትና የሚያረጋግጥበት ስርአት ሊዘረጋና ሊተገብር ይገባል፡፡
- ኮሚሽኑ የውጭ ባለሀብቶች ወደ አገር ውስጥ ለፕሮጄክት ትግበራ በአዋጁ መሰረት ያስገቡትን ካፒታል መጠን የኢንቨስትመንት ፈቃድ ከመስጠቱ በፊት ሊያረጋግጥ እንዲሁም የንግድ ፈቃድ ሲያወጡም የድርጅቶቹን ካፒታል በማረጋገጥ መመዝገብ፣ የንግድ ፈቃድ ሲሰወስዱ ካፒታላቸውን ያላስመዘገቡ ባለሀብቶችን በዕቅድ ላይ የተመሰረተ ክትትል በማድረግ በአዋጁ መሰረት ሊመዘግብ እና ይህንንም ለሚመለከታቸው አካላት ማሳወቅ አለበት፡፡
- ኮሚሽኑ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለሰጣቸው የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች በአቀረቡት የአዋጭነት ጥናትና ዕቅድ መሰረት የቅድመ ትግበራ እና ትግበራ ደረጃን አከናውነው ወደ ሥራ እንዲገቡ በዕቅድ ላይ የተመሰረተ ድጋፍና ክትትል በማከናወን ወደ ማምረት ሥራ እንዲሸጋገሩ ሊያርግ ይገባል፡፡ የሚያከናውነው የኢንቨስትመንት

ፈቃድ እድሳትም በትክክል የኢንቨስትመንቱ ያለበትን ደረጃ በክትትልና ድጋፍ ወቅት የተገኙ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት ሊሆን እና ወደ ትግበራና ወደ ማምረት ሥራ በዕቅዳቸው መሰረት የማይገቡና የሚጓተቱ የኢንቨስትመንት ፈቃዶችን በህጉ መሰረት ሊሰርዝ ይገባል፡፡ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ሲያስመልስ ሆነ ሲሰረዝ በስራ ላይ ባሉ ህጎች መስረት ለሚመለከታቸው አካላት ማሳወቅ አለበት፡፡

- ኮሚሽኑ የባለሀብቶቹን መረጃ የመረጃ ቋት በማደራጀት ሊመዘግብና ወቅታዊ ሊያደርግ፣ በባለሀብቶች እና በሌሎች መንግስታዊ አካላት መካከል ወቅታዊ የመረጃ ፍሰት እንዲኖር የሚያስችል ዘመናዊ የሆነ የመረጃ መለዋወጫ ስርአት ዘርግቶ ተግራዊ ሊያደርግ፣ ከሚመለከታቸው አካላት የመረጃ ቋት ጋር እርስ በእርሱ እንዲናበብ (interfaced) ሊያደርግ ይገባል፡

የሚሉትን የማሻሻያ ሃሳቦች ሰጥተናል፡፡

በወሎ ተርሸሪ ኬር የህክምናና የማስተማሪያ ሆስፒታል ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት እና በወሎ ዩኒቨርሲቲ ለወሎ ተርሸሪ ኬር የህክምናና የማስተማሪያ ሆስፒታል ግንባታ ፕሮጀክት ከህብረተሰቡ የተሰበሰበው ገንዘብ ለታለመለት ዓላማ መዋሉን ማረጋገጥ በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት

ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ለወሎ ተርሸሪ ኬር የህክምናና የማስተማሪያ ሆስፒታል ግንባታ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ያሰራጫቸውን የገቢ ማሰባሰቢያዎች ሽያጭ ተከናውኖ ገንዘቡ ባንክ ገቢ መሆኑን በተመለከተ፡-

49. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ለወሎ ተርሸሪ ኬር የህክምናና የማስተማሪያ ሆስፒታል ግንባታ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ያሰራጫቸውን የገቢ ማሰባሰቢያ ደረሰኞች፣ የቶምቦላ ሎተሪ ትኬቶች እና የብር ኩፖኖች ሽያጭ ተከናውኖ ገንዘቡ ባንክ ገቢ መሆኑን ሊከታተል እና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡

50. ለወሎ ተሪሸሪ ኬር የህክምናና የማስተማሪያ ሆስፒታል ፕሮጀክት ግንባታ የሚውል ወደ ተለያዩ ክልሎች፣ በውጭ ሀገራት በሚገኙ የኢትዮጵያ ኤምባሲዎችና ቆንሲላ ጽ/ቤቶች በኩል ይሸጣል ተብሎ ተሰራጭቶ ከነበረው የብር ኩፖን ቲኬት ብር 9,388,635.19 የሚያወጣ የብር ኩፖን የጠፋ መሆኑ እና የስራ አመራር ቦርዱ በሀገር ውስጥ ባንክ ያልገባ ብር 7,705,445.00፣ ያልተመለሰ ቶምቦላ ብር 20,640.00 እና በውጭ ሀገራት ብር 9,388,635.19 ለኢትዮጵያ ኤምባሲዎችና ቆንስላ ጽ/ቤቶች ተሰራጭቶ የጠፋ በሚል በአጠቃላይ ብር 17,114,720.19 የእዳ ስረዛ ያደረገ መሆኑ፣ **ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የግንባታ ፕሮጀክቱን ለማስፈፀም የሚያከናውናቸው ተግባራት የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን አዋጅና መመሪያን መሰረት ያደረጉ እና የሃብት ብክነት በሚፈፅሙ ተጠያቂነትን ማስፈኑን በተመለከተ፡-**

51. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የወሎ ተርሸሪ ኬር የህክምናና የማስተማሪያ ሆስፒታል ግንባታ ፕሮጀክት ለማስፈፀም ከህብረተሰቡ በተሰበሰበው ገንዘብ የሚያከናውናቸው ተግባራት የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን አዋጅና መመሪያን መሰረት ያደረጉ አሰራሮችን ሊተገብር እና የሃብት ብክነት በሚፈፅሙ አካላት ላይ ተጠያቂነትን የሚያሰፍንበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

52. በኦዲቱ ወቅት፡- የቀድሞው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ ለበጎ አድራጎት ኮሚቴው በ07/06/2009 ዓ.ም በፃፈው ደብዳቤ የበጎ አድራጎት ኮሚቴው ፈቃድ ከ01/06/2009 ዓ.ም እስከ 30/05/2010 ዓ.ም ድረስ ለመጨረሻ ጊዜ ለአንድ ዓመት እንዲያሳድስ ቢያሳውቀውም ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በአዲሱ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን አዋጅ 1113 /2011 ሳይመዘገብና ፈቃድ ሳያገኝ ኦዲቱ እስከተከናወነበት ቀን ድረስ ያለ ምንም ምዝገባ እና ፈቃድ እየሰራ መሆኑ፣

የፕሮጀክት ማስተባበሪያ ጽ/ቤቱ ለወሎ ተርሸሪ ኬር የህክምናና የማስተማሪያ ሆስፒታል ግንባታ ፕሮጀክት ከህብረተሰቡ የተሰበሰበውን ገንዘብ ለወሎ ዩኒቨርሲቲ ማስረከቡን በተመለከተ፡-

53. የፕሮጀክት ማስተባበሪያ ጽ/ቤቱ ለወሎ ተርሸሪ ኬር የህክምናና የማስተማሪያ ሆስፒታል ግንባታ ፕሮጀክት ከህብረተሰቡ የተሰበሰበውን ገንዘብ እና ንብረት አጠቃላይ ኦዲት በማስደረግ ለወሎ ዩኒቨርሲቲ ሊያስረክብ ይገባል፡፡
54. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ከህብረተሰቡ የተሰበሰበውን ገንዘብና ንብረት አጠቃላይ ኦዲት በማስደረግ ሰነዶችን ጨምሮ ለወሎ ዩኒቨርሲቲ ማስረከብ እንዳለበት እና ዩኒቨርሲቲው እራሱን የቻለ የባንክ አካውንት መክፈት እንዳለበት የውሳኔ አቅጣጫ ቢሰጥም ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ኦዲቱ እስከተከናወበነት ቀን ድረስ ከህብረተሰቡ የተሰበሰበውን ገንዘብ እና ንብረት ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ከጀመረበት እስካሁን ድረስ ያለውን አጠቃላይ ኦዲት በማስደረግ ለዩኒቨርስቲው አለማስረከቡ፣

የፕሮጀክቱ የሥራ አመራር ቦርድ ለወሎ ተርሸሪ ኬር የህክምናና የማስተማሪያ ሆስፒታል ግንባታ ፕሮጀክት ከህብረተሰቡ በተሰበሰበው ገንዘብ የህዝቡን አስተዎፅኦ ሊዘክር የሚችል በህዝብ ስም ራሱን የቻለ ህንፃ መገንባቱን በተመለከተ፡-

55. የፕሮጀክቱ የሥራ አመራር ቦርድ ከወሎ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር ለወሎ ተርሸሪ ኬር የህክምናና የማስተማሪያ ሆስፒታል ግንባታ ፕሮጀክት ከህብረተሰቡ በተሰበሰበው ገንዘብ የህዝቡን አስተዎፅኦ ሊዘክር የሚችል በህዝብ ስም ራሱን የቻለ ህንፃ ሊገነባ ይገባል፡፡
56. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ /የፕሮጀክቱ የስራ አመራር ቦርዱ/ ከዩኒቨርሲቲው ጋር ነሐሴ 24 በ2008 ዓ.ም ባደረጉት የፕሮጀክቱ የርክክብ ስምምነት ላይ የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ /የፕሮጀክቱ የስራ አመራር ቦርድ/ ግዴታዎችና ሃላፊነቶች ውስጥ ለፕሮጀክቱ ራሱን የቻለ አንድ ብሎክ /ህንፃ/ ለመገንባት የሚውል ሀብት በማፈላለግ በአገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ተንቀሳቅሶ የፋይናንስ፣ የግንባታ ቁሳቁሶች፣ የህክምና መሳሪያዎችና ሌሎች ሀብቶችን

በማሰባሰብ እና ከህብረተሰቡ በተሰበሰበው ገንዘብ የአንድ ብሎክ /ህንፃ/ ግንባታ ወጪ ሙሉ በሙሉ ሸፍኖ በመስራት ለዩኒቨርሲቲው እንደሚያስረክብ በግልፅ ቢቀመጥም ኦዲቱ እስከተከናወነበት ቀን ድረስ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ /የፕሮጀክቱ የስራ አመራር ቦርዱ/ ምንም ዓይነት ህንፃ መገንባት አለመቻሉ፣

ዩኒቨርሲቲው ከማስተባበሪያ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ጋር በመነጋገርና በመመካከር የወሎ ተርሸሪ ኬር የህክምናና የማስተማሪያ ሆስፒታል ግንባታ ፕሮጀክት የጋራ አማካሪ ቦርድ ማቋቋሙን በተመለከተ፡-

57. ዩኒቨርሲቲው ከማስተባበሪያ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ጋር በመነጋገርና በመመካከር የወሎ ተርሸሪ ኬር የህክምናና የማስተማሪያ ሆስፒታል ግንባታ ፕሮጀክት በበላይነት ሊከታተል እና ሊያስፈፅም እንዲሁም ከህብረተሰቡ የተሰበሰበው ገንዘብ ለታለመለት አላማ መዋሉንና ህዝባዊነቱን ሊያረጋግጥ የሚያስችል የፕሮጀክቱ የጋራ አማካሪ ቦርድ ሊያቋቁም ይገባል፡፡
58. የወሎ ተርሸሪ ኬር የህክምናና የማስተማሪያ ሆስፒታል ግንባታ ፕሮጀክትን ህዝባዊነት ለማረጋገጥ፣ አለም አቀፋዊ ስታንዳርዱን የጠበቀ መሆኑን ለመከታተል፣ በየጊዜው የተፈፀሙና ያልተፈፀሙ ተግባራትን በመከታተል ለማስተካከል እና ፕሮጀክቱን ለታለመለት አላማ መዋሉን ማረጋገጥ የሚያስችል ከወሎ ተርሸሪ ኬርና የማስተማሪያ ሆስፒታል ግንባታ ፕሮጀክት የስራ አመራር ቦርድ አባላት፣ ከወሎ ዩኒቨርሲቲ ሥራ አመራር ቦርድ፣ ከህብረተሰቡና ከአካባቢው መስተዳደር የተውጣጣ ከ9-11 አባላት ያሉት የጋራ አማካሪ ቦርድ መቋቋም እንዳለበት ውሳኔ ላይ ቢደረስም ኦዲቱ እስከተከናወነበት ቀን ድረስ የዩኒቨርሲቲው እና የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የጋራ አማካሪ ቦርዱ ያላቋቋሙ መሆኑ፣

ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ከፌደራልና ከክልሉ ከፍተኛ የሥራ አመራሮች፣ ከስራ አመራር ቦርድ አባሎች እንዲሁም ከዩኒቨርሲቲው ጋር ባደረጋቸው ስምምነቶችና የጋራ ውሳኔዎች መሰረት የስራ ጊዜውን አጠናቆ መዘጋቱን በተመለከተ፡-

59. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ከፌደራልና ከክልሉ ከፍተኛ የሥራ አመራሮች፣ ከስራ አመራር ቦርድ አባሎች እንዲሁም ከዩኒቨርሲቲው ጋር ባደረጋቸው ስምምነቶችና የጋራ ውሳኔዎች መሰረት የስራ ጊዜውን አጠናቆ ሊዘጋ ይገባል፡፡

60. የወሎ ተሪሸሪ ኬር የህክምናና የማስተማሪያ ሆስፒታል ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ከህዝብ የተሰበሰበውን ገንዘብና ቁሳቁስ ኦዲት በማስደረግ ሰነዶችን ጨምሮ ለወሎ ዩኒቨርሲቲ እንዲያስረክብ እና ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የስራ ጊዜውን አጠናቆ እንዲዘጋ በ29/09/2010 ዓ.ም ቢወሰንም ኦዲቱ እስከተከናወነበት ቀን ድረስ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በውሳኔው መሰረት የስራ ጊዜውን አጠናቆ አለመዘጋቱ፣

በመሆኑም

- የወሎ ተሪሸሪ ኬር የህክምናና የማስተማሪያ ሆስፒታልን ፕሮጄክት ጽ/ቤት ንብረቱን ኦዲት በማድግ የተሰበሰበውን ገንዘብና ንብረት ኦዲት በማስደረግ ለወሎ ዩኒቨርሲቲ በማስረከብ ሥራውን አጠናቆ እስከሚዘጋ ድረስ የሥራ አመራር ቦርዱ በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ መሰረት በየጊዜው እየተሰበሰበ ቀሪ ሥራዎችን በበላይነት ሊመራ እና የተሰበሰበው ገንዘብና ሀብት ኦዲት እንዲደረግና ለወሎ ዩኒቨርሲቲ እንዲረከብ ለማድረግ ስትራቴጂካዊ አመራሩን በመወጣት ከህዝብ የተጣለበትን ኃላፊነት ሊወጣ ይገባል፡፡
- የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ለወሎ ተርሸሪ ኬር የህክምናና የማስተማሪያ ሆስፒታል ግንባታ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ለማዋል ለተለያዩ አካላት የተሰራጩ የገቢ ማስገኛ ኩፖኖች፣ ቶምቦላዎችና የተሰበሰቡ ገንዘቦችና ቁሳቁሶች የሚሰበስብበት፣ የሚተዳድርበት እና ተጠያቂነትን የሚያሰፍን ሥርዓት ዘርግቶ በፕሮጄክት ጽ/ቤቱ

ተግባራዊ ሊያስደርግና ክትትል በማድረግ ገንዘቦችን ወይንም ቶምቦላና ኩፖኖች የተለያዩ ቁሳቁሶቹን ባልመለሱ አካላት ላይ አስተዳደራዊና ህጋዊ እርምጃ በወቅቱ እንዲወሰድ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ለወሎ ተርሸሪ ኬር የህክምናና የማስተማሪያ ሆስፒታል ግንባታ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ያሰራጫቸውን የገቢ ማሰባሰቢያ ደረሰኞች፣ የቶምቦላ ሎተሪ ትኬቶች እና የብር ኩፖኖች ሽያጭ ወቅቱን ጠብቆ በመሰብሰብ ገንዘቡን ባንክ ገቢ በማድረግ ገቢውን ማሳደግ እና ተጠያቂነትን በማስፈንና የሃብት ብክነትን መቆጣጠር እንዲችል በማድረግ እና ለሥራ አመራር ቦርዱ በማቅረብ እርምጃ እንዲወስድ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ አጠቃላይ የሂሳብና የንብረት ኦዲት አድርጎ ከወሎ ዩኒቨርሲቲ ጋር ርክክብ እስኪፈጽም ድረስ ለወሎ ተርሸሪ ኬር የህክምናና የማስተማሪያ ሆስፒታል ግንባታ ፕሮጀክት ለማስፈፀም ከህብረተሰቡ በተሰበሰበው ገንዘብ የሚያከናውናቸው ተግባራት የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን የሚመለከቱ አዋጅና መመሪያዎችን መሰረት ያደረጉ አሰራሮችን ሊተገብር እንደ አስፈላጊነቱም ኦዲቱ ረጅም ጊዜ የሚወስድ መሆኑ ከታመነበት ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በአዲሱ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን አዋጅ ቁጥር 1113 /2011 መሰረት በድጋሚ ሊመዘገብ ይገባል፡፡
- የወሎ ዩኒቨርሲቲ ከወሎ ተርሸሪ ኬር የህክምናና የማስተማሪያ ሆስፒታል ግንባታ ፕሮጀክት የሥራ አመራር ቦርድ እና ጽ/ቤት ጋር በመቀናጀት ከህብረተሰቡ የተሰበሰበውን ገንዘብ ከፕሮጀክት ማስተባበሪያ ጽ/ቤቱ በመረከብ በ29/09/2010 ዓ.ም ከፍተኛ የፌደራልና የክልሉ እንዲሁም የስራ አመራር ቦርዱ ዩኒቨርሲቲውን ጨምሮ ፕሮጀክቱን በተመለከተ ባካሄዱት ስብሰባ በተደረሰው የጋራ ውሳኔ መሰረት ከህብረተሰቡ በተሰበሰበው ገንዘብ የህዝቡን አስተዋፅኦ ሲዘከር እንዲኖር ለማድረግ በህዝብ ስም አንድ ራሱን የቻለ ህንፃ ዩኒቨርስቲው ኃላፊነቱን ወስዶ ሊገነባ እና በማስታወሻነት መሰየም ይጠበቅበታል፡፡

- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ለወሎ ተርሸሪ ኬር የህክምናና የማስተማሪያ ሆስፒታል ግንባታ ፕሮጀክት ከህብረተሰቡ የተሰበሰበውን ገንዘብ እና ንብረት በተቻለ ፍጥነት አጠቃላይ ኦዲት በማስደረግ የተሰበሰበውን ሀብትና ንብረት ለዩኒቨርሲቲው ሊያስረክብ እና የኦዲት ሪፖርት ውጤቱን ለአማራ ብሔራዊ ክልልዊ መንግስት፣ ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን እና ሌሎች ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ሊያሳውቅ ይገባል፡፡ የሥራ አመራር ቦርዱም ይህን በበላይነት መምራት ይጠበቅበታል፡፡ ይህንን ሥራ ለማከናውንም በተደረሰው ስምምነት መሰረት የሥራ አመራር ቦርዱ ከወሎ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመቀናጀት የጋራ አማካሪ ቦርድ ሊያቋቁሙ ይገባል፡፡ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ አጠቃላይ ኦዲት አስደርጎ ርክክብ በማከናወን የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሥራ ጊዜ እንዲጠናቀቅ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- የፕሮጀክቱ የሥራ አመራር ቦርድ እና ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የወሎ ተርሸሪ ኬር የህክምናና የማስተማሪያ ሆስፒታል ግንባታ ፕሮጀክት በተመለከተ እስከ አሁን ስላከናወናቸው ሥራዎች፣ ስለሚቀሩ ሥራዎች እና በከፍተኛ አመራሮች ስለተወሰኑ ውሳኔዎች እንዲሁም ከህብረተሰቡ የተሰበሰበው ሀብትና ንብረትን በተመለከተ ያለውን መረጃ ከወሎ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር ለአካባቢው ማህበረሰብ እና ሀብት በማዋጣት ለተሳተፉና ለሌሎች የፌዴራልና የክልል ባለድርሻ አካላት መረጃ በየወቅቱ ሊያደርስ ይገባል፡፡ ከሚመለከታቸው አካላት ጋርም እየተገናኙ የሚመክርበትና መረጃ የሚለዋወጥበት አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ እንዲሁም የወሎ ዩኒቨርሲቲም ፕሮጀክቱን ከተረከበ ጀምሮ ስላከናወናቸው ተግባራት በተመሳሳይ ለህብረተሰቡና ለሚመለከታቸው አካላት በየጊዜው መረጃ ሊሰጥ ይገባል፡፡

የሚሉትን የማሻሻያ ሃሳቦች ሰጥተናል፡፡

የመንግስት ግዥ አገልግሎት የተሽከርካሪ እና መለዋወጫዎች ግዥ አፈጻጸም ውጤታማነትን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት

የአገልግሎቱን ስትራቴጂዎችና የአሰራር መመሪያዎች ማዘጋጀቱንና በቦርድ ማጸደቁን በተመለከተ

61. ስትራቴጂዎችና የአሰራር መመሪያዎች በማዘጋጀት በበላይነት ለሚያስተዳድረው ቦርድ በማቅረብ ሊያጸድቅና ሥራ ላይ ሊያውል ይገባል፡፡
62. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከ2013 በጀት ዓመት ጀምሮ የአገልግሎት መስሪያ ቤቱ የውስጥ አሰራር መመሪያ እንዲሻሻል በተደጋጋሚ ለቦርዱ የቀረበ ቢሆንም እስካሁን ድረስ ያልጸደቀ መሆኑ፣ በአገልግሎቱ በፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቶች በጋራ የሚፈለጉ ዕቃዎችን (የተሽከረካሪ ጎማን ጨምሮ) የግዥ ፍላጎት ሳያቀርቡ ግዥ የሚፈጽሙ መስሪያ ቤቶች በመኖራቸው በእነርሱ ላይ በአስተዳደራዊ እርምጃ ተጠያቂ የሚሆኑበት የአሰራር ስርዓት አለመኖሩ፡፡

ቦርዱ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ የተሰበሰበ መሆኑን በተመለከተ

63. አገልግሎቱን በበላይነት የሚያስተዳድረው ቦርድ በደንብ ቁጥር 184/2002 መሰረት ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ሊሰበሰብና የአገልግሎቱን አፈጻጸም ሊገመግምና ውሳኔ ሊሰጥ ይገባል::
64. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት አገልግሎቱን በበላይነት የሚያስተዳድረው ቦርድ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ወይም በአመት 12 ጊዜ መሰብሰብ ሲገባው በ2012 በጀት ዓመት 4 ጊዜ፣ በ2013 በጀት አመት 8 ጊዜ በ2014 ሦስት ጊዜ እና በ2015 በጀት አመት ሦስት ጊዜ ብቻ የተሰበሰቡ መሆኑ፣

አገልግሎት መ/ቤቱ የሚያከናውናቸውን ግዥዎች በበጀት መደገፉን የሚያረጋግጥ መሆኑን በተመለከተ፡-

65. አገልግሎቱ የግዥ አገልግሎት ጠያቂ መ/ቤቶች ግዥ በሚጠይቁበት ጊዜ በበጀት መደገፉን ሊያረጋግጥ ይገባል፣
66. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅትአገልግሎቱ አገልግሎት በሚሰጣቸው ባለ በጀት መ/ቤቶች በማዕቀፍ ለሚገዙ የተሽከርካሪዎች መለዋወጫዎች (የተሽከርካሪ

ኅማን ጨምሮ) እና በገንዘብ ሚኒስቴር የሚታዘዙ የተሽከርካሪ ግዥ ጥያቄዎች በበጀት መደገፋቸውን እና አለመደገፋቸውን የማያረጋግጥ (ዕውቅና የሌለው) መሆኑ፣

አገልግሎቱ የሚከናወኑ ግዥዎችን በግዥ ፍላጎት፣ በናሙናና በስፔሲፊኬሽኑ መሰረት መረከቡን በተመለከተ

67. አገልግሎቱ የተሽከርካሪ እና መለዋወጫዎች ግዥ ሲፈጽም ግዥ ጠያቂዎች በጠየቁት መሰረትና በጨረታ ሰነዱ ላይ በተገለጸው የሥራ ዝርዝር /Specification/ እና ናሙና መሰረት መሆናቸውን በማረጋገጥ ሊረከብ ይገባል፡፡

68. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት አገልግሎቱ አገልግሎት በሚሰጣቸው መ/ቤቶች የሚፈልጓቸውን የተሽከርካሪ ኅማዎች በማዕቀፍ ግዥ ውስጥ የማይካተቱ መኖራቸው፣

አገልግሎቱ አጠናቀው በማያስረክቡ አቅራቢዎች ላይ ላዘገዩበት ጊዜ ባቀረበው የውል መጠን በየቀኑ 0.1% የጉዳት ካሳ (liquidity damage) ማስከፈሉን በተመለከተ

69. አገልግሎቱ በውሉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ተሽከርካሪ፣ ኅማዎችን እና መለዋወጫዎችን አጠናቀው በማያስረክቡ አቅራቢዎች ላይ ላዘገዩበት ጊዜ ባቀረበው የውል መጠን በየቀኑ 0.1% የጉዳት ካሳ (liquidity damage) ሊያስከፍል እና አስተዳደራዊ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

70. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት አገልግሎቱ በውሉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ተሽከርካሪ፣ ኅማዎችን እና መለዋወጫዎችን አጠናቀው በማያስረክቡ አቅራቢዎች ላይ ላዘገዩበት ጊዜ ባቀረበው የውል መጠን በየቀኑ 0.1% የጉዳት ካሳ (liquidity damage) የማይቀጣ መሆኑን፣

አገልግሎቱ የተሽከርካሪዎችን ግዥ ሲፈጽም መለዋወጫዎቹ እና የጥገና አገልግሎት ተደራሽነትን ከግምት ውስጥ ማስገባቱን በተመለከተ

71. አገልግሎቱ የተሽከርካሪዎችን ግዥ ሲፈጽም መለዋወጫዎቹ በሚፈለገው የአቅርቦት መጠን እና የጥገና አገልግሎት ተደራሽነትን ከግምት ውስጥ ያስገባ ሊሆን ይገባል፡፡
72. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በኤሌክትሪክ የሚሰሩ ተሽከርካሪ ግዥን በተመለከተ የባትሪ መሙያ ጣቢያዎች (Charging centers)፣ ከጥገና አገልግሎት፣ መለዋወጫና ኢንሹራንስ ጋር በተያያዘ ቅድመ ዝግጅት ያልተደረገ መሆኑ፣

አገልግሎቱ በኢፌዴሪ የግዥና ንብረት ባለስልጣን እና ከኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ አገልግሎት በተገኘው የገበያ ዋጋ ጋር ማነፃፀሩን በተመለከተ

73. አገልግሎቱ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ የግዥና ንብረት ባለስልጣን (በቀድሞው ኤጀንሲ) እና ከኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ አገልግሎት (የቀድሞው የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ) በተገኘው የገበያ መረጃና አቅራቢዎች ከጠየቁት ዋጋ ጋር ሊያነጻጽር ይገባል፡፡
74. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት አገልግሎቱ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ የግዥና ንብረት ባለስልጣን እና ከኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ አገልግሎት የገበያ መረጃ በየጊዜው በመሰብሰብ በማደራጀትና አቅራቢዎች ከሰጡት ዋጋ ጋር በማነጻጸር ለግዥ ሂደቱ በግብዓትነት የማይጠቀም መሆኑ፣

የሚሉት ናቸው፡፡ በመሆኑም፡-

- አገልግሎቱ የሚጠቀምባቸውን የአሰራር መመሪያዎች አሁን እየተሻሻለ በሚገኘው የግዥ አዋጅ መሰረት እንዲጣጣሙ በማድረግ መከለስ በቦርዱ ማጸደቅ ይጠበቅበታል፡፡ በተጨማሪም በሥራ ላይ ባለው የግዥ መመሪያ ያልተሸፈኑ የጉዳት ካሣ ክፍያ አከፋፈል፣ ዕቃዎችን በማዕቀፍ ለመግዛት አስፈላጊ የሆነው አነስተኛ ብዛት

የመሳሰሉት እንዲካተቱ ለሚንስቴር መ/ቤቱ በማሳወቅና ግብዓት በመስጠት እንዲካተቱ ሊያደርግ ይገባል፡፡

➢ አገልግሎቱን በበላይነት የሚያስተዳድረው ቦርድ በህግ በተቀመጠው መሰረት በየወሩ በመሰብሰብ የአገልግሎቱን አፈጻጸም መገምገምና የሚቀርቡለትን የተለያዩ መመሪያዎች መርምሮ ሊያጸድቅ ይገባል፡፡

➢ አገልግሎቱ ለሚፈጽማቸው የተሽከርካሪ ግዥዎች የግዥ ሂደቱ ከመጀመሩ በፊት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ቅንጅት በመፍጠር ለግዥዎቹ በቂ በጀት መያዙን ማረጋገጥ፤ በማዕቀፍ ለሚገዙ ግዥዎች ደግሞ ግዥውን ከጠየቀው መስሪያ ቤት ጋር በመቀናጀት በበጀት መደገፋቸውን በማረጋገጥ የግዥ ሂደቱ በሚፈለግበት ጊዜና መጠን እና በተያዘው በጀት በመፈጸም የቀረበው ዋጋ ደግሞ ከተያዘው በጀት በላይ ከሆነ ግዥን ከጠየቀው አካል ጋር በመመካከር በመወሰን የተቋቋመበትን አላማ ሊያሳካ ይገባል፡፡

➢ አገልግሎቱ የተሽከርካሪ እና መለዋወጫዎች ግዥ ሲፈጽም ሁሉም የመንግስት ተቋማት የጠየቁትን ግዥ መሰረት ያደረገ ዝርዝር ስፔስፊኬሽን ባለሙያ በማዘጋጀት ጨረታ ሊያወጣና ውድድሩን አሸንፈው እንዲያቀርቡ ከተመረጡት ጋር ውል የገባባቸውን ንብረቶች በጨረታ ሰነዱ ላይ በተገለጸው የሥራ ዝርዝር /Specification/ እና ናሙና መሰረት መሆናቸውን የሚያረጋግጥበት ስርዓት ዘርግቶ ለተግባራዊነቱም ክትትል የሚያደርግበት፣ እንዲሁም በማዕቀፍ የሚገዙ መለዋወጫዎችንና ጎማዎች አቅራቢ ድርጅቶች ከተጠቃሚ መ/ቤቶች የግዥ ማዘዣ (perchese order) ሲደርሳቸው በሥራ ዝርዝር /Specification/ እና ናሙና መሰረት በ14 ቀን ውስጥ ማቅረባቸውን የሚረጋግጥበት የክትትል እና ቁጥጥር ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

➢ አገልግሎቱ ውድድሩን አሸንፈው አሸናፊ የተደረጉና ውል የገቡ አቅራቢዎች በውሉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ተሽከርካሪ እና መለዋወጫዎችን —በማያስረክቡ አቅራቢዎች ላይ ላዘገዩበት ጊዜ ባቀረበው የውል መጠን በየቀኑ 0.1% የጉዳት ካሳ (liquidity

damage) የሚቀጡበትን አግባብ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ከገንዘብ ሚኒስቴር እና የመንግስት ግዥና ንብረት ባለሥልጣን ጋር በመመካከር ውል በገባው በአገልግሎቱና ክፍያ በሚፈጽሙ ባለበጀት መ/ቤቶች የተፈጠረውን የትግበራ የህግ ክፍተት ሊስተካከል እና የሚቀጡበትን ሁኔታ ሊያመቻች ይገባል፡፡

- አገልግሎቱ የተሽከርካሪዎችን ግዥ ሲፈጽም ዋጋቸው እና አገልግሎታቸው ተመጣጣኝ እንዲሆን ከሃገሪቱ ነባራዊ እና የአየር ሁኔታ የተጣጣሙ እንዲሆኑ፤ የመለዋወጫ አቅርቦት በሃገር ውስጥ መኖሩንና የጥገና አገልግሎትን ተደራሽነት ግምት እንዲሁም የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች ሲሆኑ ደግሞ ባትሪያቸውን የሚሞሉበት ጣቢያዎች (Charging centers) የሚመሉበትን ሁኔታ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ሊያመቻች እና የበኩሉን ድርሻውን ሊወጣ ይገባል፡፡
- አገልግሎቱ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ የግዥና ንብረት ባለስልጣን እና ከኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ አገልግሎት የተገኘው የገበያ መረጃ በየጊዜው በመሰብሰብ በማደራጀትና አቅራቢዎች ከሰጡት ዋጋ ጋር በማነጻጸር ለግዥ ሂደቱ በግብዓትነት ሊጠቀም ይገባል፡፡

የሚሉትን የማሻሻያ ሃሳቦች ሰጥተናል፡፡

በኢትዮ-ኢንጂነሪንግ ግሩፕ የአቃቂ ቤዚክ ሜታልስ ኢንዱስትሪ የስራ አፈፃፀም ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት

የነቀምት ስቲል ፕሮሰሲንግ ፋብሪካ ፕሮጀክትን በተመለከተ፡-

75. ኢንዱስትሪው የነቀምት ስቲል ፕሮሰሲንግ ፋብሪካ ፕሮጀክትን በታቀደለት በጀት፣ ጊዜ፣ ጥራትና ስፔስፍኬሽን መሰረት ሊያጠናቀቅ ይገባል፡፡
76. ይሁን እንጂ የኦዲት ወቅት
    - ☞ ኢንዱስትሪው የነቀምት ስቲል ፕሮሰሲንግ ፋብሪካ ፕሮጀክት በሁለት ዙር በገንዘብ መጠን ዮሮ 43,500,000 (አርባ ሶስት ሚሊዮን አምስት

መቶ ሺህ ዩሮ) ውል በመፈራረም ስራው በ2006/2007 (2014 G.C) የተጀመረና ዮሮ 43,266,843.16 (አርባ ሶስት ሚሊዮን ሁለት መቶ ስልሳ ስድስት ሺህ ስምንት መቶ አርባ ሶስት ከ16/100 ዩሮ) ወጪ የተደረገበት ቢሆንም አለመጠናቀቁ፤

☞ የነቀምት ስቲል ፕሮሰሲንግ ፋብሪካ ፕሮጀክቱን ለመገንባት ከጣሊያን ሀገር በቀረጥ ነፃ የተገዙ ማሽነሪዎችና ተያያዥ ዕቃዎች ከውጪ ሀገር ሲመጡ ወጪያቸው ያልተከፈለባቸው፡- የባሕር ትራንስፖርት ዶላር 321,196 (ሶስት መቶ ሃያ አንድ ሺህ አንድ መቶ ዘጠና ስድስት ዶላር)፣ የየብስ ትራንስፖርት፣ የኮንቴይነር ዲሜሬጅ እና የጂቡቲ ትራንዚት በአጠቃላይ ብር 35,282,236.22 (ሰላሳ አምስት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሰማንያ ሁለት ሺህ ሁለት መቶ ሰላሳ ስድስት ብር ከ22/100) በላይ የሚሆን ገንዘብ አገልግሎት ለሰጠው አካል ባለመከፈሉ ዕቃዎች በቢሾፍቱ ቦንድድ መጋዘን እና ጂቡቲ ወደብ ላይ መያዛቸው፣

የ10 ቶን ማቅለጫ (ኢንዳክሽን) እና 15 ቶን እንዳይረጋ ማቆያ (ሆልዲንግ) ፈርነሶች ፕሮጀክትን በተመለከተ፡-

77. የ10 ቶን ማቅለጫ (ኢንዳክሽን) እና 15 ቶን እንዳይረጋ ማቆያ (ሆልዲንግ) ፈርነሶች ፕሮጀክትን በታቀደለት በጀት፣ ጊዜ፣ ጥራትና ስፔስፍኬሽን መሰረት ሊያጠናቀቅ ይገባል፡፡
78. ይሁን እንጂ የ10 ቶን እና 15 ቶን ፈርነሶች ለመሣሪዎች (ኢኩፕመንት) አቅርቦት፣ የተከላ (ለኢሬክሽን)፣ ለሱፐርቪዥን እና ለኮሚሽኒንግ ስራ የውሉን ጠቅላላ ዋጋ USD1,185,467.00 (አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሰማንያ አምስት ሺህ አራት መቶ ስልሳ ሰባት የአሜሪካን ዶላር) ሙሉ በሙሉ ክፍያ ፈጽሞ ስራው ሳይጠናቀቅ ከ10 ዓመት በላይ የቆየ መሆኑ፤

የመቀሌ ማግኔት አልባ (Nonferrous) ብረታ ብረት ማምረቻ ፕሮጀክትን በተመለከተ፡-

79. ኢንዱስትሪው የመቀሌ ማግኔት አልባ (Nonferrous) ብረታ ብረት (አልሙኒየም፣ መዳብ፣ ዚንክ፣ ወዘተ.) ማምረቻ ፕሮጀክትን በታቀደለት በጀት፣ ጊዜ፣ ጥራትና ስፔስፍኬሽን መሰረት ሊያጠናቀቅ ይገባል፡፡

80. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ለመቀሌ ማግኔት አልባ (Nonferrous) ብረታ ብረት ማምረቻ ፕሮጀክት ብር 232,943,132 (ሁለት መቶ ሰላሳ ሁለት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ አርባ ሶስት ሺህ አንድ መቶ ሰላሳ ሁለት ብር) ወጪ ያደረገ ቢሆንም የፕሮጀክቱ ውል፣ ለፕሮጀክቱ የተያዘው ጠቅላላ በጀት፣ ፕሮጀክቱ መጠናቀቅ የነበረበት፣ አሁን ያለበት አፈጻጸም ደረጃ ተጠይቆ ማስረጃ አለመቅረቡ፣

ኢንዱስትሪው የተከፋይ ሂሳቦችን በወቅቱ ለባለመብቶች የሚከፈልበት የአሰራር ስርዓትን በተመለከተ፡-

81. ኢንዱስትሪው የተከፋይ ሂሳቦችን በወቅቱ ለባለመብቶች የሚከፈልበት የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

82. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ኢንዱስትሪው የሂሳብ መዝገቡን ያላስታረቀ፣ ኢንዱስትሪው እ.ኤ.አ ከ2008 ጀምሮ እስከ ሰኔ 30/2015 ዓ.ም ድረስ ብር 123,131,617.55 (መቶ ሃያ ሶስት ሚሊዮን መቶ ሰላሳ አንድ ሺህ ስድስት መቶ አስራ ሰባት ብር ከ55/100 ተሰብሳቢ ሂሳቦችን ያልሰበሰበና ብር 104,207,941.52 ተከፋይ ሂሳብ ያለበት መሆኑ፣ ኢንዱስትሪው በኢትዮ-ኢንጂነሪንግ ግሩፕ በቀድሞው ኮርፖሬሽን ሥር ካሉ ኢንዱስትሪዎች ጋር ብር 539,412,881 ተሰብሳቢ ሂሳብ እና ለዘጠኝ ኢንዱስትሪዎች የሚከፈል ብር 2,557,220,682 ተከፋይ ሂሳብ ያለበት መሆኑ፣

ኢንዱስትሪው ከደንበኞች ጋር የገባውን ውል መፈጸሙን እና የደንበኞች ቅሬታ አፈታትን በተመለከተ፡-

83. ኢንዱስትሪው ከደንበኞች ጋር የገባውን ውል ሊፈፀም እና የደንበኞች ቅሬታ አፈታት ስርዓትን በመዘርጋት ሊተገበር ይገባል፡፡

84. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ኢንዱስትሪው ለምርት እና አገልግሎት የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን በጥናት በመለየት የምርት ዕቅድ ባለማዘጋጀቱ ከደንበኞች ጋር የገባው ውል በሚፈለጉበት ግዜና መጠን የማያደርስ መሆኑ፣ የደንበኞች ቅሬታ አፈታት ስርዓት ያልዘረጋ መሆኑ፣

ኢንዱስትሪው የአካባቢ ደህንነት ጥናት በማጥናት ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፡-

85. ኢንዱስትሪው የአከባቢ ደህንነት አስተዳደር ጥናት በማጥናት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

86. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ኢንዱስትሪው የአካባቢ ደህንነት አስተዳደር ሥርዓት (Environmental Management System) ጥናት በማጥናት ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፣ ኢንዱስትሪው የጥራት ማረጋገጫ ሥርዓት ያልዘረጋ መሆኑ፣

ኢንዱስትሪው የንብረት አያያዝ ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፡-

87. ኢንዱስትሪው የንብረት አያያዝ ስርዓት ሊዘረጋና ለተግባራዊነቱ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡

88. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በኢንዱስትሪው ንብረቶች ተበታትነው በየቦታው ያሉ፣ በዳታ፣ በዋጋና በቁጥር ያልተመዘገቡ፣ ከ2013-2015 ዓ.ም ብቻ ከብር 51,796,261.53 (ሃምሳ አንድ ሚሊዮን ሰባት መቶ ዘጠና ስድስት ሽህ ሁለት መቶ ስልሳ አንድ ብር ከ53/100) በላይ የሚያወጣ ንብረቶች ከኢንዱስትሪው የጠፉ እና ኢንዱስትሪው ከ2007 ዓ.ም ጀምሮ ለመንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ብር 30,507,481.16 (ሰላሳ ሚሊዮን አምስት መቶ ሰባት ሺህ አራት መቶ ሰማንያ አንድ ብር ከ16/100) በላይ የሚሆኑ ንብረቶች በውሰት የሰጣቸውና ያልተመለሱ መሆኑ፣

ኢንዱስትሪው አገልግሎት የማይሰጡ ግብዓቶች፣ ምርቶች፣ መለዋወጫዎችና ተሸከርካሪዎችን የአወጋገድ ሥርዓት በመዘርጋት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ማስወገዱን በተመለከት፡-

89. ኢንዱስትሪው አገልግሎት የማይሰጡ ግብዓቶች፣ ምርቶች፣ መለዋወጫዎችና ተሸከርካሪዎችን የአወጋገድ ሥርዓት በመዘርጋት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ሊያስወግድ ይገባል፡፡

90. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በኢንዱስትሪው በየወርክ ሾፖች ጥቅም የማይሰጡ ማሽነሪዎችና ኢኩፕመንቶች፣ በላብራቶሪ ክፍሎች የላብራቶሪ መሳሪያዎች፣ ኢንዱስትሪው ከተመሰረተ ጀምሮ የተመረቱ ነገር ግን ደንበኞች ያልተወሰዱ ምርቶች፣ ለጥሬ ዕቃነት የሚያገለግሉ ግብዓቶች እና መለዋወጫ ዕቃዎች በየቦታ ያሉ ቢሆንም ጥቅም ያላቸውና የሌላቸው ተለይተው እንዲቀመጡና እንዲወገዱ ያልተደረጉ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

በመሆኑም

- ኢንዱስትሪው የሚያከናውናቸውን የነቀምት ብረት ማቅለጫ ፋብሪካ፣ የመቀሌ ማግኔት አልባ (Nonferrous) ብረታ ብረት ማምረቻ፣ የ10 ቶን እንዳክሽንና 15 ቶን ሆልዲንግ ፈርነስ ፕሮጀክቶችን የሚመለከቱ መረጃዎችን በማሰባሰብ አሁን ያሉበትን ሁኔታ በጥናት በማስደገፍ ሊያረጋግጥ፣ ተዘጋጅተው የነበሩትን ስፔሲኬሽን አንደገና በመከለስ፣ ሊያስወጡት የሚችለውን ሀብት እና አዋጭነታቸውን ሊገመግም፣ በአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ እያስጠና ያለውን ጥናት በመጨመር እና በኢትዮ- ኢንጂነሪንግ ግሩፕ ውሳኔ ሊያሰጥበት ይገባል፡፡ የግምገማውን ውጤት እና የግሩፑን ውሳኔ መሰረት በማድረግ በሚያቅደው ዓመታዊ ዕቅድ ውስጥ በማካተት ለፕሮጀክቶቹ ድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ዳግም ውል በመፈፀም በታቀደላቸው በጀት፣ ጊዜ፣ ጥራትና ስፔስፍኬሽን መሰረት ሊያጠናቀቅ ይባል፡፡

➢ ኢንዱስትሪው ለፕሮጀክቶቹ ተገዝተው የነበሩ ንብረቶችንም ሥራ ላይ ሊያውልና ተጠያቂ ሊሆኑ የሚገባቸው አካላት ከሉ ተጠያቂ እንዲሆኑ ሊያደርግ ይገባል፡፡

➢ የነቀምት ስቲል ፕሮሰሲንግ ፋብሪካ ፕሮጀክቱን ለመገንባት ከጣሊያን ሀገር በቀረጥ ነፃ የተገዙ ማሽነሪዎችና ተያያዥ ዕቃዎች በቢሾፍቱ ቦንድድ መጋዘን እና ጂቡቲ ወደብ ላይ የተቀመጡት ንረቶች በአፋጣኝ ጉዳያቸው እለባት እንዲያገኙ በማድረግ ወደ ሥራ እንዲገቡ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

➢ ኢንዱስትሪው የተለያዩ የሂሳብ ሰነዶችን የማስታረቅ ሥራ በመሥራት በዞረ ሂሳብ እና በመነሻ ሂሳብ ያሉ ልዩነቶች ሊያስታርቅና ትክክለኛ የሂሳብ መግለጫ ማዘጋጀት ይጠበቅበታል፡፡ ከተለያዩ ደንበኞች መሰብሰብ ያለበትን ተሰብሳቢ ሂሳብ የሚሰበሰብበትን መንገድ በማመቻቸት ገንዘቡን ሊሰበስብ እና ያለበትንም ተከፋይ ሂሳብ በማጣራት ሊከፍል ይገባል፡፡ በተጨማሪም ኢንዱስትሪው በኮርፖሬሽኑ ሥር ከነበሩ ሌሎች ኢንዱስትሪዎች የሚፈለግ ተሰብሳቢ ሂሳብ እና ለሌሎቹ ኢንዱስትሪዎች የሚከፈል ተከፋይ ሂሳብ በማጣራት ግዴታውን ሊወጣ ይገባል፡፡

➢ ኢንዱስትሪው ለምርት እና አገልግሎት የሚያስፈልጉ ሀብቶችን የቴክኖሎጅ ደረጃ እና ተያያዥ ጉዳዮችን በጥናት በመለየትና ዕቅድ በማዘጋጀት ከደንበኞች ጋር የገባውን ውል ሊፈፅም ይገባል፡፡ ሥራውንም ለማሻሻልና ሊያቀላጥፍ የሚችል ከሌላ ተመሳሳይ ምርት ከሚያመርቱ ድርጅቶች ጋር የልምድ ልውውጥ በማድረግ አሰራራቸውን በመመልከትና በመቀመር ወደ ኢንዱስትሪው በማምጣት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ በዚህ ሂደት ለሚከሰቱ ችግሮች የደንበኞች ቅሬታ አፈታት ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

➢ ኢንዱስትሪው ዘመናዊ የሆነ የንብረት አያያዝ ስርዓትን ቀልጣፋና ወጭ ቆጣቢ በማድረግ ተበታትነው በየቦታው ያሉ ንብረቶችን መረጃ ሊያደራጅ፣ በሥርዓቱ ሊያከማች፣ የጠፉ ንብረቶችን በሚመለከት

ተጠያቂነትን ሊያሰፈን፣ እንዲሁም በተለያየ ለመንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት በውሰት የተሰጡ ንብረቶችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ተከታትለው ሊያስመልስ ይገባል፡፡

☞ ኢንዱስትሪው በየወርክ ሾፖች ጥቅም የማይሰጡ ማሽነሪዎች፣ ኢኩፕመንቶች፣ የላብራቶሪ መሳሪያዎች፣ ኢንዱስትሪው ከተመሰረተ ጀምሮ ተመርተው ደንበኞች ያልተወሰዱ ምርቶች፣ ግዜያቸው ያለፈባቸው ኬሚካሎች፣ ለጥሬ ዕቃነት የማያገለግሉ ግብዓቶች እና መለዋወጫ ዕቃዎችን በመለየት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን እንዲወገድ ሊያደርግ ይገባል፡፡

የሚሉትን የማሻሻያ ሃሳቦች ሰጥተናል፡፡

በኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት የምግብ ሳይንስና ስነ-ምግብ ምርምር ፈንድ አጠቃቀምን በተመለከተ የክዋኔ ኦዲት

የምርምር ሥነ ምግባር / research Ethical guidelines / እና የምርምር ፈንድ አስተዳደርና አጠቃቀም መመሪያ ስለመዘጋጀቱ እና በሚመለከተው አካል መጸደቁን በተመለከተ፣-

ኢንስቲትዩቱ **የምርምር ሥነ ምግባር / research Ethical guidelines / እና የምርምር ፈንድ አስተዳደርና አጠቃቀም መመሪያ** በማዘጋጀትና **በሚመለከተው አካል በማጸደቅ** ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ኢንስቲትዩቱ የሚያገኘውን የምርምር ፈንድ የሚያስተዳድረው የኢንስቲትዩቱ ማኔጅመንት ባወጣው የጥቅማ ጥቅም እና የግራንት ፕሮጀክቶች የጋራ ወጪዎች (overhead) መመሪያ በሚመለከተው አካል ያልጸደቁ መሆናቸው፣

ኢንስቲትዩቱ ለምርምር የሚመደበውን ገንዘብ / ሀብት / ለምርምር ተግባር ብቻ ማዋሉን በተመለከተ፡-

ኢንስቲትዩቱ ለምርምር የሚመደበውን ገንዘብ /ሀብት/ ለምርምር ተግባር ብቻ ማዋሉን ለመከታተልና ለመቆጣጠር የሚያስችል የአሰራር ስርዓት የዘረጋ እና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በኢንስቲትዩቱ ማኔጅመንት በወጣ ነገር ግን በሚመለከተው አካል ባልጸደቀ መጋቢት 2011 ዓ.ም በወጣ የoverhead መመሪያ መሠረት ከእያንዳንዱ ለምርምር ስራ ከሚመደበው ፈንድ ላይ 15% አስተዳደራዊ ወጪ (overhead cost) ተብሎ እየተቀረጠ በኢንስቲትዩቱ የበላይ ኃላፊ ፈቃድ ለተለያዩ ግዥዎች እና መሰረተ ልማት ወጪዎች እንደሚውል፣ በዚህም መሰረት በኢንስቲትዩቱ ማኔጅመንት ታህሳስ /2010 ዓ.ም በወጣ ነገር ግን በሚመለከተው አካል ያልጸደቀ መመሪያን መሠረት በማድረግ ለምርምር ሥራ ከመጡ ፕሮጀክቶች /ፈንዶች/ ላይ ከ 2011ዓ/ም-2015ዓ/ም ለጋራ ወጪ /overhead cost/ ወጪ ለማድረግ ከተቀረጠው ብር 59,591,189. ውሰጥ ብር 33,014,425. ለኢንስቲትዩቱ ለተለያዩ ግዥዎች እና መሰረተ ልማት ወጪ የተደረገ መሆኑን፡

እንዲሁም መጋቢት 2011ዓ/ም ኢንስቲትዩቱ በሚመለከተው አካል የጸደቀ የጥቅማ ጥቅም ተመን ሳይኖር ባወጣው የጥቅማ ጥቅም መመሪያ መሠረት ለምርምር ሥራ ከመጡ ፕሮጀክቶች /ፈንዶች/ ላይ ለኢንስቲትዩቱ ሰራተኞች እና ኃላፊዎች የማበረታቻ ክፍያ ከ2012ዓ/ም-2015ዓ/ም ብር 27,169,453.91/ ሃያ ሰባት ሚሊዮን አንድ መቶ ስልሳ ዘጠኝ ሺ አራት መቶ ሃምሳ ሶስት ከዘጠና አንድ ሣንቲም/ የተከፈለ መሆኑ፣

የምግብ ምርምር ሥራዎች በታቀደላቸው ጊዜ የተከናወኑ መሆኑን በተመለከተ፡

በኢንስቲትዩቱ የሚከናወኑ የምግብ ምርምር ሥራዎች በታቀደላቸው ጊዜ መሰረት ሊከናወኑ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ኢንስቲትዩቱ ለምርምር የሚመደበውን ገንዘብ /ሀብት/ ለምርምር ተግባር ብቻ ማዋሉን ለመከታተልና ለመቆጣጠር የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ያልዘረጋ እና ኢንስቲትዩት የሚያከናውናቸው ምርምሮችን በተያዘላቸው ጊዜ የማይጠናቀቁ ፕሮጀክቶች መኖራቸው፣

ኢንስቲትዩቱ ለስነ-ምግብ እና ምግብ ነክ ምርምሮች እንዲውሉ የተገዙ ግብአቶች አወጋገድን በተመለከተ፡

ኢንስቲትዩቱ ለስነ-ምግብ እና ምግብ ነክ ምርምሮች እንዲውሉ የተገዙ ግብአቶች ማለትም ኬሚካሎች እና የላባራቶሪ ሪኤጀንቶች ስራ ላይ ስለመዋላቸው ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ እንዲሁም የማያስፈልጉና ጊዜ ያለፈባቸው መሆኑ የታመነባቸው ግብዓቶች በመንግስት የንብረት አወጋገድ መመሪያ መሰረት በወቅቱ እንዲወገዱ ሊያደርግና እስኪወገዱ ድረስም ለብቻቸው ሊያከማቻቸው ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ በኢንስቲትዩቱ ከ1967 ዓ.ም ጀምሮ በገንዘብ ሲተመን ብር 70,799,745.16 /ሰባ ሚሊዮን ሰባት መቶ ዘጠና ዘጠኝ ሺ ሰባት መቶ አርባ አምስት ከ16 ሳንቲም የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈባቸው እና ያልተወገዱ ለምግብ ምርምር እና ለሌሎች የኢንስቲትዩቱ ሥራዎች የተገዙ ኬሚካሎች እና የላቦራቶሪ ሪኤጀንቶች ኦዲቱ እስከተከናወነበት ጊዜ ለ45 ዓመታት ተከማችተው ሳይወገዱ በመጋዘን ውስጥ የሚገኙ መሆኑ፣

በመሆኑም

- ኢንስቲትዩቱ የራሱን ነባራዊ ሁኔታ ግምት ውስጥ ያስገባ የምርምር ትግበራ መመሪያ /research guideline/፣ የምርምር ፈንድ አስተዳደርና አጠቃቀም መመሪያ፣ እንዲሁም ለተመራማሪዎችና ለምርምሩ ድጋፍ ለሚሰጡ ሠራተኞች ስለሚከፈል የተለያዩ የጥቅማ ጥቅም መመሪያ የሚመለከታቸውን የውስጥና የውጭ ባለድርሻ አካላት በማሳተፍና ግብዓት በመሰብሰብ መመሪያዎቹን ሥልጣን በተሰጠው አካል ለማጸደቅ የተጀመረውን ሂደት ክትትል በማድረግ ሊያጸድቅና እና መመሪያዎቹን በአዋጅ ቁጥር 1183/2012 መሰረት በፍትህ ሚኒስቴር በማስመዝገብ ወደ ሥራ ሊገባ ይገባል፡

- ኢንስቲትዩቱ ለምርምር የሚመደበውን ገንዘብ /ሀብት/ ለምርምር ተግባር ብቻ ማዋሉን ለመከታተልና ለመቆጣጠር የሚያስችል ውጤታማ የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ እና ተግባራዊ ሊያደረግ፤ የኢንስቲትዩቱ ተመራማሪዎች በራሳቸው ጥረት የሚያመጡትን ፈንድ ከኢንስቲትዩቱ ጋር በማቀናጀት ሥራ ላይ የሚውልበት ህጋዊ እና ግልጸኝነት ያለው የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ እና ተግባራዊ በማድረግ በኢንስቲትዩቱ የሚከናወኑ የምግብ ምርምር ሥራዎች በታቀደላቸው ጊዜ ተከናውነው በወቅቱ ምርምሮች የተከናወነበት ዓላማ እንዲያሳኩ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ለኢንስቲትዩቱ አገልግሎት የሚገዙ ግብአቶች ለምሳሌ ኬሚካሎች እና የላባራቶሪ ሪኤጀንቶች ስራ ላይ ስለመዋላቸው ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ እና የመጠቀሚያ ግዜያቸው ሳያልፍ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ሊያደረግ፣ እንዲሁም የአገልግሎት ጊዜ ያለፈባቸው መሆኑ የታመነባቸው ግብዓቶች ለብቻቸው በጥንቃቄ እንዲከማቹ በማድረግ በመንግስት የንብረት አወጋገድ መመሪያ መሰረት በወቅቱ እንዲወገዱ ሊያደርግ ይገባል፡

በአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪ ምርምርና ልማት ማዕከል፡ የቆዳና የቆዳ ውጤቶች አምራች ኢንዱስትሪ ክትትልና ድጋፍ ውጤታማነት በተመለከተ የተከናወነ ክዋኔ ኦዲት

ማዕከሉ የስልጠና ፍላጎት ሰነድ ማዘጋጀቱን እና የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን መስጠቱን በተመለከተ

ማዕከሉ በሚያዘጋጃቸው ስልጠና ላይ ለሚሳተፉ አምራች ኢንዱስትሪ ባለሙያዎች የስልጠና መምረጫ መስፈርት በማዘጋጀት እና የአቅም ክፍተት በመለየትና የስልጠና ፍላጎት ሰነድ በማዘጋጀት የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን ሊሰጥ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ማዕከሉ የስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት የሚያካሂድ ቢሆንም ከጥናቱ በተገኘው የስልጠና ፍላጎት መሰረት በተከታታይነት በዕቅድ ላይ የተመሰረተ ስልጠና የማይሰጥ፣ የሰጠውንም ስልጠና በመገምገም ግብረ መልስ አለመስጠቱ፤

ማዕከሉ በቁርኝት ፕሮግራም የሁለተኛ ድግሪ እና የሶስተኛ ድግሪ (በፒኤች ዲ) የትምህርት መርሃ ግብር በአጠቃላይ 79 ሰራተኛ ትምህርታቸውን አጠናቀው የጨረሱ 30 (38%) ሰራተኞች የውል ግዴታቸውን ሳይወጡ ማዕከሉን የለቀቁ መሆኑ፤

ለቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት የቴክኒክ ድጋፍ ማድረጉን በተመለከተ

ማዕከሉ በጫማ ማምረት ዘርፍ የትምህርትና ስልጠና ለሚሰጡ የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማትን መስፈርት አዘጋጅቶ በመምረጥ የቴክኒክ ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ማዕከሉ Twinning Agrement II Extention (በቁርኝት ፕሮግራም) እ.ኤ.አ ከ2020 ጀምሮ በጫማና በቆዳ ውጤቶች ማምረት ዘርፍ የትምህርትና ስልጠና ለሚሰጡ የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማትን ቀድሞ የነበረውን የትምህርት አሰጣጥ ሂደት በማሻሻል እና ለስርዓተ ትምህርቱ የሚመጥን (curriculum preparation) የትምህርት ስርዓት በማዘጋጀት የቴክኒክ ድጋፍና የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን ለመስጠት ከተቋማት ጋር እቅድ ቢይዝም ተቋማቱ በምን መስፈርት እንደተመረጡ እና ስልጠና ስለመስጠቱ መረጃ አለመቅረቡ፤

ማዕከሉ ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቅሰም ለአምራች ኢንዱስትሪዎች ማስተዋወቁን በተመለከተ

ማዕከሉ የዘርፉን ኢንዱስትሪ ልማት ሊያፋጥኑና ተወዳዳሪ ሊያደርጉ የሚችሉ ቴክኖሎጂዎችን በመምረጥ እና አለም አቀፍ ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቅሰምና በመቀመር በዘርፉ ለተሰማሩ አምራች ኢንዱስትሪዎች ሊያስተዋውቅ ይገባል፡፡
ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ማዕከሉ ለቆዳና ቆዳ ውጤቶች አምራች ኢንዱስትሪዎች የዘርፉን ኢንዱስትሪ ልማት ሊያፋጥኑና ተወዳዳሪ ሊያደርጉ የሚችሉ ቴክኖሎጂዎችን ምርምር ከተደረገና ሙከራ ከተደረገባቸው በኋላ ተሞክሮዎችን በመቀመር በዘርፉ ለተሰማሩ አምራች ኢንዱስትሪዎች እንዲያውቁት ያላደረገ መሆኑ፤

ማዕከሉ በፋሽንና ዲዛይን ላይ ድጋፍ ማድረጉን በተመለከተ፣

ማዕከሉ ለአነስተኛና መካከለኛ ጫማና ለቆዳ ውጤቶች አምራች ኢንዱስትሪዎች በፋሽንና ዲዛይን ስራዎች ላይ ድጋፍ ማድረጉን በተመለከተ፣
ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ማዕከሉ የተለዩ ደንበኞች ላይ ትኩረት የሚያድርጉ (niche market) የጫማ እና ለቆዳ ውጤቶች አምራች ኢንዱስትሪዎች በፋሽንና ዲዛይን ስራዎች ላይ ድጋፍ ያላደረገላቸው መሆኑ፤

በማዕከሉ በአምራቾች የጥራት ደረጃዎች እንዲተገበሩ እና የጥራት ፍተሻ መሰረተ ልማት መሟላቱን በተመለከተ

ማዕከሉ የቆዳና ቆዳ ውጤቶች የጥራት ደረጃዎች እንዲተገበሩ መሥራቱን እና ኢንዱስትሪዎች የምርት ጥራትና የልዕቀት ደረጃቸውን ማረጋገጫ የጥራት ፍተሻ መሰረተ ልማት እንዲያሟሉ (እንዲያቋቁሙ) የቴክኒክና የስልጠና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡
እንጂ በኦዲቱ ወቅት ማዕከሉ ቆዳ ፋብሪካዎች አለም-አቀፍ የቆዳ ውጤቶች ምርትና ንግድ ሥራዎች ቡድን (leather working Group-LWG) ኦዲት ስታንዳርዶች እንዲያሟሉ በቂ የስልጠና እና ድጋፍ ያላደረገ መሆኑ፤

ማዕከሉ የሞጆ ቆዳ ክላስተር ማቋቋሙን እና ለኢንዱትሪዎቹ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ መዘጋጀቱን በተመለከተ

ማዕከሉ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የሞጆ ቆዳ ክላስተር ሊያቋቁም እና ኢንዱትሪዎቹ ደረጃውን የጠበቀ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ እንዲኖራቸው ከሚመለከታቸው ጋር በጋራ ሊሰራ ይገባል፡፡

ይሁን ኢንጂ በኦዲቱ ወቅት ማዕከሉ በ2012 በጀት ዓመት በሞጆ ከተማ የሞጆ ቆዳ ክላስተር እንደ ሞዴል ለመገንባት እቅድ ቢይዝም እስካሁን ያልተቋቋመ መሆኑ፤ በመሆኑም

- ማዕከሉ በቆዳ እና በቆዳ ውጤቶች አምራች ኢንዱስትሪዎች የሚታየውን የእውቀትና የክህሎት ክፍተት ለመሙላት በየዓመቱ የስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት በማካሄድ በዕቅድ ላይ የተመሰረተ የአቅም ግንባታ ስልጠና ሊሰጥ፣ የሰጠውም ስልጠናን ሊገመግም እና ግብረ መልስ ሊሰጥ ይገባል፡፡ በተጨማሪም የተቋሙን አቅም ለመገንባት ለሠራተኞቹ የተለያየ የትምህርትና ሥልጠና ዕድል ሲሰጥ የዕድሉ ተጠቃሚዎች ከመስሪያ ቤቱ ጋር የገቡትን ውል መፈጸሙን ሊረጋግጥና በማያከብሩትም ላይ በውሉ መሰረት እርምጃ መውሰድ አለበት፡፡
- ማዕከሉ በቁርኝት ፕሮግራም (Twinning Agrement II Extention) በተገኘው ዕውቀትና ድጋፍ በጫማና በቆዳ ውጤቶች ማምረት ዘርፍ የትምህርትና ስልጠና ለሚሰጡ የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት የትምህርት አሰጣጥ ሂደት በማሻሻል እና ለስርዓተ ትምህርቱ የሚመጥን (curriculum preparation) የትምህርት ስርዓት ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በማዘጋጀት መስፈርት በማውጣትና የትምህርት ተቋማትን በመምረጥ በአዲሱ ካሪኩለም ላይ የቴክኒክ ድጋፍና የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን ሊሰጥ ይገባል፡፡
- ማዕከሉ የቆዳና ቆዳ ውጤቶች አምራች ኢንዱስትሪዎች በአለም ገበያ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የዘርፉን የኢንዱስትሪ ልማት ሊያፋጥኑና ተወዳዳሪ ሊያደርጉ የሚችሉ እና ከፍተኛ ወጪ የወጣባቸውን በተቋም ሆነ በሌላ አካል የተከናወኑ ምርምሮችን እንዲሁም አለም አቀፍ ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቅሰም እና የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችን በመምረጥ በናሙና ኢንዱትሪዎችን በመመረጥ

ተግባራዊነታቸውን በመፈተሽና አዋጭነታቸውን በመገምገም በሁሉም የቆዳ ኢንዱስትሪዎች የሚተገበሩበትን ሁኔታዎች ሊያመቻች ይገባል፡፡

- የቆዳና የቆዳ ውጤቶችን በአለምአቀፍ እና በአገር አቀፍ ደረጃ ያሉ የፋሽን ዲዛይን ተለዋዋጭነት ከግምት ያስገባ የሚሰጡ ስልጠናዎችና ድጋፎች ተከታታይና ቀጣይነት ባለው እና በእውቀት በተደገፈ መልኩ ሊሰራ እና ተወዳዳሪ የሚሆኑበትን መንገድ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ሊተገብር ይገባል፡፡
- ማዕከሉ ቆዳ ፋብሪካዎች በአለም አቀፍ ገበያ ተቀባይነትና ተወዳዳሪነት እንዲኖራቸው አለም-አቀፍ የቆዳ ውጤቶች ምርትና ንግድ ሥራዎች ቡድን (Leather Wng Group) ኦዲት ስታንዳርዶች በመተግበር ተወዳዳሪ እንዲሆኑ፣ በአቅም አጠቃቀም፣ በምርት ጥራት እና የስራ ቦታ ደህንነት ላይ መሻሻል እንዲያሳዩ ኢንዱስትሪዎቹ የካይዘን ፍልስፍና ላይ ግንዛቤ እንዲኖራቸውና እንዲያሟሉ ለቆዳ ፋብሪካዎች የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በቂ ግንዛቤ እና ድጋፍ በማድረግ ተግባራዊነቱን መከታተል ይጠበቅበታል፡፡
- በዕቅድ ተይዞ ወደ ተግባር ያልተገባው የሞጆ የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ማምረቻ ክላስተርን የሚመለከታቸውን የፌዴራልና የክልል አካላትን በማሰተባባር ተቋቁሞ ወደ ሥራ እንዲገባ ሊያደርግ ይገባል፡፡

የሚሉትን የማሻሻያ ሃሳቦች ሰጥተናል፡፡

2. መሠረተ ልማት የክዋኔ ኦዲት የ2015/2016 የተከናወኑ የክዋኔ ኦዲቶች ላይ የተገኙ ዋና ዋና ግኝቶች እና የቀረቡ የማሻሻያ ሃሳቦች ማጠቃለያ ዘገባ

በኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት

የፓስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ውጤታማነትን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት ላይ የተዘጋጀ ዘገባ

ተቋሙ ለፓስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ የሚያገለግሉ የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፤

ተቋሙ ለፓስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ የሚያገለግሉ የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት እና መመሪያና ስታንዳርድ አዘጋጅቶ በማጸደቅ ተግባራዊ ሊያደርግና አፈፃፀሙን ሊከታተል ይገባል።

ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ሰነዶች፣ ከተቋሙ የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ እና በተደረገ የአካል ምልከታ፡-

- ተቋሙ ለፓስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ የሚያገለግሉ የጸደቀ እና ወቅታዊ የሆነ መመሪያና ስታንዳርድ የሌለው መሆኑ፤
- የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት በአዋጅ ቁጥር 1263/2014 እና በደንብ ቁጥር 449/2011 በተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት የተቋሙን አሰራር ስርዓትና የድርጊት መርሀ-ግብር እንደሚያዘጋጅና አፈጻጸሙን እንደሚከታል የተገለጸ ቢሆንም መመሪያዎችን የማዘጋጀት እንጂ የማጽደቅ ኃላፊነት ያልተሰጠው ሆኖ ሳለ ተቋሙ ሰኔ 2015 ዓ.ም የተሻሻለ የአስቸኳይ ፓስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ መመሪያ አዘጋጅቶ በዋና ዳይሬክተር አጸድቆ (በሚመለከተው አካል ያልጸደቀ) ስራ ላይ ያዋለ መሆኑ፤ ለፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ በመላክ እንዲመዘገብ ያላደረገ መሆኑ፤
- እንዲሁም መመሪያው በግልጽ ያላስቀመጣቸው ጉዳዮች ያሉ መሆኑ ለማሳያ፡-
    - በሶስት ሀኪሞች የተፈረመ ታማሚው ግለሰብ ውጭ አገር ሄዶ እንዲታከም የታዘዘ ከህክምና ቦርድ ከመንግስትም ይሁን ከግል ሆስፒታል የተጻፈ ማስረጃ እንዲሁም ከታማሚው ጋር አብሮ የሚጓዝ አንድ ቤተሰብ አስታማሚ፤ የሚል ሲሆን ምንም እንኳን የአስታማሚው ስም በደብዳቤው ላይ ይጠቀስ የሚል በመመሪያው ባልተገለፀበት ሁኔታ ታማሚዎች ይዘው የሚመጡትን

አስታማሚ ስሙ በደብዳቤ ላይ አልተጠቀሰም በማለት አገልግሎቱን የማይሰጡ መሆኑ፤

- የውጭ የትምህርት እድል የተሰጣቸውና የትምህርት እድሉን ካመቻቸላቸው የትምህርት ተቋም የተጻፈ ደብዳቤና ሌሎች ከዚህ ጋር የተያያዙ **ደጋፊ ማስረጃዎች** የሚል ሲሆን ደጋፊ ማስረጃዎቹ ምን ምን እንደሆኑ በግልጽ ያልተቀመጠ መሆኑ፤
- ውጭ ሀገር እቃ በማስመጣት እና በመላክ ንግድ ላይ የተሰማሩ ተቋማት ወይም በውጭ ሀገር ከሚገኙ ድርጅቶች ጋር የስራ ግንኙነት ያላቸው ከፍተኛ ግብር ከፋዮች፣ የባንክ ኤል ሲ ባለቤትና ስራ አስኪያጅ አስቸኳይ ፓስፖርት ማውጣት እንደሚችሉ የተገለጸ ቢሆንም ምን አይነት ማስረጃዎች አሟልተው መምጣት እንዳለባቸው በግልጽ ያልተቀመጠ መሆኑ፤

- በቀን 6/5/2015 የአገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻያ ዳይሬክቶሬት ባቀረበው የቅሬታ አቤቱታ ሰሚ ሁለተኛ ሩብ ዓመት ሪፖርት ላይ የሪፈራል ሆስፒታል ወረቀቶች ከጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ብቻ ካልሆነ አንቀበልም የሚሉ ባለሙያዎች መኖራቸው የተገለጸ መሆኑ፤
- የዜጎች ቻርተር አዘጋጅቶ ወደ ተግባር ለማስገባት በ2013 ዓ.ም ያቀደ ቢሆንም እስከ አሁን ድረስ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑን፤
- የፓስፖርት አገልግሎትን በተመለከተ እያንዳንዱ ተግባር የአፈጻጸም ስታንዳርድ ወጥቶለት በምን ያህል ጊዜ፣ ጥራትና መጠን መከናወን እንዳለበት ተለይቶ የማይታወቅ መሆኑን፤ለመረዳት ተችሏል።

ተቋሙ አጠራጣሪ የሆኑ ተገልጋዮች ሲያጋጥሙ ዜግነታቸው የሚጣራበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፤

ተቋሙ ከድንበርና ከጎረቤት ሃገራት መሆናቸው አጠራጣሪ የሆኑ ተገልጋዮች ሲያጋጥሙ ዜግነታቸው የሚጣራበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ሰነዶች፣ ከተቋሙ የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ እና በተደረገ የአካል ምልከታ፡-

- ተቋሙ ከድንበርና ከጎረቤት ሃገራት መሆናቸው አጠራጣሪ የሆኑ ተገልጋዮች ሲያጋጥሙ ዜግነታቸው የሚጣራበት መመሪያ የሌለው መሆኑ፤

- ዜግነት የማጣራት ስራው በልምድ የሚከናወን፣ ውሳኔው ዜግነትን በሚያጣራው ግለሰብ መልካም ፈቃድ ላይ የተመሰረተና ወጥ የሆነ አሰራር የማይከተል መሆኑ፤
- አንዳንድ ዜግነት የሚያጣሩ ሰራተኞች ባለጉዳዩን የሚቆጡ፣ የሚያመናጭቁ፣ የሰውን ክብር የሚነኩ፣ አግባብ ያለው ምላሽ የማይሰጡና አናስተናግድም እስከማለት የሚደርሱ መሆኑ፤
- በዋና መ/ቤት በሶማሌ ዜግነት የተጠረጠሩ ተገልጋዮችን የማጣራት ስራ የሚከናወነው ባልተሟላ የሰው ኃይል (በአንድ ባለሙያ ብቻ) መሆኑና ባለሙያው በተለያየ ምክንያት በስራ ገበታው ባይገኝ ስራው የሚቆም መሆኑ፤ ለማወቅ ተችሏል።

ተቋሙ የፓስፖርት አገልግሎት ፈላጊዎች በተቀመጠላቸው መመሪያ፣ ስታንዳርድ እና የጊዜ ሰሌዳ መሰረት አገልግሎቱን ማግኘታቸውን የሚከታተል መሆኑን በተመለከተ፤

1. ተቋሙ የአዲስ መደበኛ ፓስፖርት፣ ለአስቸኳይ ፓስፖርት እና የፓስፖርት እድሳት አገልግሎት ፈላጊዎች በተቀመጠላቸው መመሪያ፣ ስታንዳርድ እና የጊዜ ሰሌዳ መሰረት አገልግሎቱን ማግኘታቸውን የሚከታተልበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
2. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ሰነዶች፣ ከተቋሙ የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ እና በተደረገ የአካል ምልከታ፡-
   - የአዲስ መደበኛ ፓስፖርት እና የፓስፖርት እድሳት አገልግሎት ፈላጊዎች አገልግሎቱን በምን ያህል ጊዜ እንደሚያገኙ የተቀመጠ መመሪያ እና የጊዜ ሰሌዳ የሌለ መሆኑ፤
   - ተቋሙ የተሻሻለ የአስቸኳይ ፓስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ መመሪያ ሰኔ 2015 ዓ.ም ያዘጋጀ ቢሆንም ተገልጋዮች አገልግሎቱን በስንት ጊዜ እንደሚያገኙ የተቀመጠ የጊዜ ሰሌዳ አለመኖሩ፤
   - የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በኢሚግሬሽን፣ የዜግነትና የወሳኝ ኩነት ኤጀንሲ የመደበኛ ፓስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ጥር 2012 ዓ.ም በተከናወነ የክዋኔ የክትትል ኦዲት ሪፖርት መደበኛ ፓስፖርት ለሚጠይቅ ባለጉዳይ በዋናዉ መምሪያ በ3 ቀናት እና በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በ7 ቀናት ዉስጥ የጉዞ ሰነድ ተዘጋጅቶ እንደሚሰጥ የተገለጸ ቢሆንም አሁን ተቋሙ የአዲስ መደበኛ ፓስፖርት እና

የፓስፖርት እድሳት አገልግሎት ፈላጊዎች አገልግሎቱን በምን ያህል ጊዜ እንደሚያገኙ የተቀመጠ መመሪያ እና የጊዜ ሰሌዳ የሌለው መሆኑ፤

- በኦዲቱ ወቅት የኦዲት ቡድኑ በ5/4/2016 ዓ.ም ከሰኔ 1/2015 ዓ.ም እስከ ህዳር 30/2016 ዓ.ም አስቸኳይ ፓስፖርት የተሰጣቸው ተገልጋዮች ዝርዝር ጠይቆ በዛ መሰረት በናሙና ተመርጠው ከተጠየቁ 60 የተገልጋይ ፋይሎች ውስጥ የቀረበው 46 ፋይል ብቻ መሆኑ፤
- ከታዩት 46 አስቸኳይ ፓስፖርት ከጠየቁ ፋይሎች ውስጥ 10ሩ አስቸኳይ ፓስፖርት መመሪያ ተራ ቁጥር 6 ላይ ከተገለፀው ቅድመ ሁኔታዎች ውጭ (ምንም ማስረጃ ላላመጡ፣ ቪዛ ላላቸው፣ ከግል መ/ቤት ለመጡ ሰራተኞች፣ የአውሮፕላን ቲኬት ላላቸው ወዘተ) በኃላፊዎች ፊርማ (እየተመራ) ፓስፖርት የተሰጣቸው መሆኑ፤
- የተቋሙ የኦንላይን መመዝገቢያ ድረ ገጽ ላይ ያሉ መረጃዎች ያልተሻሻሉና አብዛኛው ህብረተሰብ ሊረዳው በሚችል ቋንቋ ያልተዘጋጀ መሆኑ፤ ለማሳያ፡-
    - ድረ ገጹ በአንድ ቋንቋ (በእንግሊዝኛ) ብቻ መሆኑ፤ አብዛኛው ተገልጋይ ሊረዳው በሚችል (በሀገር ውስጥ) ቋንቋ ያልተዘጋጀ መሆኑ፤
    - ከአምስት ዓመት በታች ላሉ ህጻናት ፎቶ ማምጣት እንዳለባቸው የሚገልጽ መረጃ የሌለ ቢሆንም ልጆቻቸውን ይዘው የሚመጡ ቤተሰቦች ግን ፎቶ የሚጠየቁ መሆኑ፤
    - በድረ ገጹ ላይ የአስቸኳይ ፓስፖርት ለማውጣት መሟላት ስላለበት ቅድመ ሁኔታ ሰኔ 2015 ዓ.ም በወጣው የተሻሻለ የአስቸኳይ ፓስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ መመሪያ መሰረት ያልተሻሻለ መሆኑ፤
- የኦንላይን የፓስፖርት አገልግሎት አሰጣጡ የአሰራር ስርዓት ሂደት (Standard operating procedure/SOP) የሌለ መሆኑ፤ ማን ምን እንደሚሰራ አለመታወቁና አንድ ባለሙያ በቀን ምን ያህል መመዝገብ እንዳለበት የተቀመጠ ስታንዳርድ አለመኖሩ፤
- አንድ ተገልጋይ አዲስ ፓስፖርት ለማውጣት ሲስተሙ እስከ ስድስት ወር የሚቀጥረው መሆኑ፤
- ተቋሙ ፓስፖርት በቀነ ቀጠሮ የማይሰጥ፤ በቀጠሮ ያልደረሰላቸው ተገልጋዮች ማንን መጠየቅ እንዳለባቸው የሚገለጽበት አሰራር አለመኖሩ እና አገልግሎቱን በወቅቱ ማግኘታቸውን የማይከታተል መሆኑን፤ ለማወቅ ተችሏል።

ተቋሙ የፓስፖርት ምዝገባ ቀን ቀጠሮ ያሳለፉ ግለሰቦች የሚስተናገዱበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፤

3. ተቋሙ የፓስፖርት ምዝገባ ቀን ቀጠሮ ያሳለፉ ግለሰቦች የሚስተናገዱበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል።
4. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ሰነዶች፣ ከተቋሙ የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ እና በተደረገ የአካል ምልከታ፡-
   - በኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት ለሚሰጡ አገልግሎቶች የአገልግሎት ክፍያ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 516/2022 የወጣ ቢሆንም የቅጣት ክፍያ ያልተካተተ መሆኑ፤
   - የኢትዮጵያ ፌደራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 3 ላይ በህግ ካልተፈቀደ በስተቀር ማናቸውንም የመንግስት ገንዘብ መሰብሰብ እንደማይቻልና የመንግስት ገንዘብ እንዲቀበል ወይም እንዲሰበስብ ሥልጣን የተሰጠው ሰው ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ መሰረት የተቀበለውን ወይም የተሰበሰበውን የመንግስት ገንዘብ ወደተጠቃለለው ፈንድ ገቢ እንደሚያደርግ፣ ገንዘብ የተቀበለበትን እና ገቢ ያደረገበትን ደረሰኝ መዝግቦ እንደሚይዝ ቢገልጽም፤
     - ተቋሙ ገንዘብ ለመሰብሰብ መመሪያ የማውጣት ስልጣን ሳይኖረው በ21/12/2015 ዓ.ም የፓስፖርት ምዝገባ ቀን ቀጠሮ ያሳለፉ ግለሰቦችን በቅጣት ለማስተናገድ (የቅጣት ክፍያ ተመን) መመሪያ አዘጋጅቶ በዋና ዳይሬክተር ያጸደቀ መሆኑ፤
     - በመመሪያው የተተመነው ቅጣት ገንዘብ (ከ1-60 ቀናት ያሳለፉ በብር አንድ ሺህ / ብር 1000 እና ከ61-90 ቀናት ያሳለፉ ብር አንድ ሺህ አምስት መቶ/1500 ብር) የሚያስከፍል ሲሆን ገንዘቡ ለተቋሙ በገንዘብ ሚኒስቴር በተፈቀደ አካውንት ውስጥ የማይገባ መሆኑ፤
     - የመንግስት የባንክ ሂሳብ የመክፈትና የመዝጋት የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ስልጣን ሆኖ ሳለ ተቋሙ የሂሳብ ቁጥር 1000569485782 በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በግለሰቦች ስም ከፍቶ ገቢ የሚሰበስብ መሆኑ ዝርዝሩ እንደሚከተለው ተገልጿል፡-

- ✓ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በደብዳቤ ቁጥር አአቅ/እአ/4575/23 በቀን 18/04/2016 ዓ.ም ለኢሚግሬሽንና ዜግነትና ወሳኝ ኩነት ኤጀንሲ በላከው ደብዳቤ የሂሳብ ቁጥር 1000569485782 በቅድመአለም እና በቅድስት እና ጌትነት ስም እ.ኤ.አ በ01/09/23 አካውንት የተከፈተ ሲሆን እ.ኤ.አ በ15/09/23 ያለው የገንዘብ መጠን ብር 491,500.00 (አራት መቶ ዘጠና አንድ ሺህ አምስት መቶ ብር) መሆኑን፤ እ.ኤ.አ በ01/09/23 በግለሰቦች ስም የተከፈተው አካውንት እ.ኤ.አ በ16/09/23 ወደ ኢሚግሬሽን ሰራተኞች መረዳጃ እድር የተቀየረ መሆኑ፤
- ✓ በአጠቃላይ አካውንቱ ከተከፈተበት እ.ኤ.አ ከ01/09/2023 እስከ 29/01/2024 ድረስ በአምስት ወራት ውስጥ ብር 17,940,165.91 (አስራ ሰባት ሚሊየን ዘጠኝ መቶ አርባ ሺህ አንድ መቶ ስልሳ አምስት ብር ከ91/100) ወደ አካውንቱ ገቢ የተደረገ ሲሆን፤ ከዚህ ውስጥ የስራ ኃላፊዎቹ በቃል እንደገለጹት ለትርፍ ሰዓት ክፍያ እና ለበዓል ለሰራተኛው ስጦታ ብር 9,324,355.76 (ዘጠኝ ሚሊየን ሶስት መቶ ሀያ አራት ሺህ ሶስት መቶ ሀምሳ አምስት ብር ከ76/100) ከመንግስት ስራ የተሰበሰበን ገንዘብ ላይ ያለገንዘብ ሚኒስቴር ፈቃድ ወጪ የተደረገ መሆኑ እና እ.ኤ.አ በ29/01/2024 ብር 8,615,810.15 (ስምንት ሚሊየን ስድስት መቶ አስራ አምስት ሺህ ስምንት መቶ አስር ብር ከ15/100) ቀሪ በአካውንቱ ላይ የሚገኝ መሆኑን፤ ለማወቅ ተችሏል።

ተቋሙ የፓስፖርት ስርጭትን ለማካሄድ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፤

5. ተቋሙ ከመልዕክት አስተላላፊ ተቋማት ጋር የፓስፖርት ስርጭትን ለማካሄድ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል።
6. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ሰነዶችና ከተቋሙ የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ፤
   - ተቋሙ ከኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት ጋር በሀገር ውስጥ እና በውጭ ሀገራት የፓስፖርት ስርጭትን ለማካሄድ መጋቢት 03/ 2013 ዓ.ም የተገባ ውል ቢኖርም በደብዳቤ ቁጥር ኢሚ6/492/15461 በቀን 20/12/2015 የኢሚግሬሽን ዜግነት አገልግሎት ለፖስታ አገልግሎት ድርጅት በላከው ደብዳቤ አገልግሎቱን አቋርጧል፡፡ ከመስከረም 2016 ዓ.ም እስከ ህዳር 30/2016 ዓ.ም ድረስ ተቋሙ

እራሱ ፓስፖርት የማደል ስራውን ሲያከናውን የቆየ ቢሆንም ከታህሳስ 2016 ዓ.ም ጀምሮ በኢሚግሬሽን ሽማቾችና ህብረት ስራ ማህበር ውል በመዋዋል የፓስፖርት እደላ ስራውን በተቋሙ ግቢ ውስጥ እንዲያድሉ ያደረገ መሆኑ፤

- የኢትዮጵያ ፌደራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 2 ላይ ማናቸውም የመንግስት ገንዘብ የሚሰበሰበው ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሚያሳትመው ወይም እንዲታተም በሚፈቅደው ደረሰኝ ብቻ እንደሆነ የተገለጸ ቢሆንም ተቋሙ ፓስፖርት ለመውሰድ ከሚመጡ ተገልጋዮች ከመስከረም 2016 ዓ.ም ጀምሮ ብር 50 (ሀምሳ ብር) ያለደረሰኝ ሲቀበልና ሲሰበስብ የቆየ ሲሆን ከታህሳስ 2016 ዓ.ም ጀምሮ ብር 100 (አንድ መቶ ብር) የሚቀበል ሲሆን፤ በገንዘብ ሚኒስቴር እውቅና ባለው የሂሳብ ቁጥር ሳይሆን በግለሰቦች ስም በተከፈተ በሂሳብ ቁጥር 1000569485782 ገቢ እንደሚደረግ የተገለጸ መሆኑን፤
- ተቋሙ ከ20/01/2016 ዓ.ም እስከ 18/05/2016 ዓ.ም በዋናው መ/ቤት እና በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በቁጥር 85,696 (ሰማንያ አምስት ሺህ ስድስት መቶ ዘጠና ስድስት) ፓስፖርት ከእያንዳንዱ ተገልጋይ ሀምሳ ብር ያለደረሰኝ በመቀበል ያደለ ሲሆን ለዚህም በድምሩ በብር 4,284,800 (አራት ሚሊየን ሁለት መቶ ሰማንያ አራት ሺህ ስምንት መቶ ብር) የሰበሰበ ሲሆን፤ በገንዘብ ሚኒስቴር በተፈቀደለት በሂሳብ ቁጥር ገቢ ያላደረገ እና ከላይ በተጠቀሰው የግለሰብ አካውንትም ገቢ ስለመደረጉ ማስረጃው ያልቀረበ መሆኑ፤
- ተቋሙ ከታህሳስ 2016 ዓ.ም ጀምሮ የፓስፖርት እደላውን በመ/ቤቱ ሰራተኞች በተቋቋመ ሽማቾች ማህበር እንዲያድልለት በተቋሙ ግቢ ውስጥ የማደያ ቦታ በማዘጋጀት ስራውን አሳልፎ የሰጠ እና ለዚህም ለአገልግሎት ብር 100 (አንድ መቶ ብር) ማህበሩ የሚቀበልና የሚሰበስብ መሆኑ፤
- ተቋሙ የፓስፖርት እደላ ሥራው በተቋሙ ሰራተኞች ማሰራት የሚችል በመሆኑ ለሌላ አካል አሳልፎ መስጠቱ ተገቢነት የሌለው መሆኑ፤ ይሁን እና የፓስፖርት እደላ ሥራውን ለሌላ አካል አሳልፎ መስጠት ቢኖርበት እንኳን የመንግስትን የግዥ ህግ መሰረት አድርጎ ያልሰጠ መሆኑ፤
- ተቋሙ ቪዲቸር (Viditure) ከተባለ የግል ድርጅት ጋር እ.ኤ.አ ከመስከረም 6/2021 እስከ መስከረም 30/2024 የሚቆይ በ28/12/2013 ዓ.ም በገባው የውል ስምምነት

መሰረት ከሀገር ውጭ ያሉ ነዋሪዎች ለፓስፖርት አገልግሎት አንላይን ሲያመለክቱ ሰነዱን አጣርቶ ወደ ኢሚግሬሽን የሚያስተላልፍ እና ፓስፖርቱ ተዘጋጅቶ ሲያልቅ ከኢሚግሬሽን ተቀብሎ ወደ ደንበኛው ተቋሙ ካወጣው የአገልግሎት ክፍያ በተጨማሪ አንድ መቶ ዶላር (100$) በማስከፈል የሚያስተላልፍ ሲሆን ይህንን ስራ ለመስራት የተመረጠበትን መስፈርት፣ የግዥ ሂደት እና ፓስፖርትን ለማሰራጨት ፈቃድ (License) ያለው መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፤

- ቪዲቸር ይህንን የፓስፖርት ስራ ለመስራት በሀገሪቱ የንግድ ህግ መሰረት ንግድ ፈቃድ ያላወጣ እና በታክስ ህጉ መሰረት ግብር የማይከፍል መሆኑ፤
- የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት በአዋጅ ቁጥር 1263/2014 እና በደንብ ቁጥር 449/2011 በተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት ላይ የፓስፖርት አገልግሎትን በውክልና እንደሚሰጥ የተገለጸ ነገር ባይኖርም አገልግሎቱን ቪዲቸር ለተባለው የግል ድርጅት የሰጠ መሆኑ፤
- ተቋሙ በደንብ ቁጥር 449/2011 በተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት መሰረት ለኢትዮጵያውያንና ለውጭ አገር ዜጎች የኢሚግሬሽን አገልግሎት መስጠትና ደህንነቱን የጠበቀ ቁጥጥር ያደርጋል ቢልም ደህንነቱ በተጠበቀ መልኩ መያዝ ያለበት የግለሰቦች መረጃን ያለምንም የህግ አግባብ (የመንግስትን የግዥ መመሪያን ሳይከተል) ቪዲቸር ለተባለ ለግል ድርጅት አሳልፎ የሰጠ መሆኑ፤
- የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት በአዋጅ ቁጥር 1263/2014 እና በደንብ ቁጥር 449/2011 ላይ ተቋሙ መደበኛ ስራውን ለሶስተኛ ወገን በማስተላለፍ ማሰራት ስለመቻሉ ያልተገለፀ/ያልተቀመጠ/ በመሆኑ የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት፣ ቪዲቸርም ሆነ የተቋሙ የሸማቾች ማህበር ፓስፖርትን ማሰራጨት/ማደል ስራዎችን መስጠቱ የህግ መሰረት የሌለው መሆኑን፤ ለማወቅ ተችሏል፡፡

ተቋሙ የሰራተኞች የስነ ምግባር መመሪያና የብልሹ አሰራሮችን ለመከላከል የሚያስችል አሰራር በመዘርጋት ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፤

7. በተቋሙ የሰራተኞች የስነ ምግባር መመሪያ ተዘጋጅቶ ተጠያቂነት ያለበት አሰራር በመዘርጋት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
8. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ሰነዶች፣ ከተቋሙ የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ እና በተደረገ የአካል ምልከታ፡-

- የሰራተኞች የስነ ምግባር መመሪያ የተዘጋጀ ሲሆን ጸድቆ ለሁሉም ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በመላክ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑንና
- የተቋሙ ሰራተኞች ተገልጋዩን በአክብሮትና በትህትና የማያስተናግዱ መሆኑ፤ ለማሳያ፡-
- የስነምግባር ችግር ያለባቸው የተቋሙ ሰራተኞች መኖራቸው ከበር ጥበቃ ጀምሮ አስተባባሪዎችና አገልግሎት የሚሰጡ ኦፊሰሮች ተገልጋዩን የማመናጨቅ፣ አልባሌ ቃላት የመጠቀም አልፎም የመነተት፣ የመገፍተርና የመማታት ሁኔታዎች መኖራቸውን በኦዲቱ ወቅት በተደረገ ምልከታ የታወቀ መሆኑ፤
- እንዲሁም በ2015 በጀት ዓመት ተቋማዊ የመልካም አስተዳደር እቅድ ላይ ከተገልጋይ ጋር በቀጥታ የሚገናኙ ሰራተኞች ከተገልጋዩ ጋር በሚኖራቸው መስተጋብር በትህትና ከመቅረብ ይልቅ የማመናጨቅና የመሳደብ ባህሪ እንደሚያሳዩ የተገለጸ መሆኑ፤
- ተገልጋዮች ሊያሟሉት የሚገባቸውን ማስረጃዎች እንዲያሟሉ በትህትና የማይገልጹላቸው መሆኑ፤
- በቀን 6/5/2014 የአገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻያ ዳይሬክቶሬት ባቀረበው የቅሬታ አቤቱታ ሰሚ ሁለተኛ ሩብ ዓመት ሪፖርት ላይ አንዳንድ ቡድን መሪዎችና ባለሙያዎች የተገልጋይን ማስረጃ በጥንቃቄ ሳያጤኑ ማስረጃ ነጥቀው ከግቢ የሚያባርሩ፣ በዋናው ማስረጃቸው ላይ አላስፈላጊ ጽሁፍ መጻፍና መሰረዝ፤ ዶክሜንቱን እንዳይጠቀም የሚያደርጉና እንደዚህ አይነት ከመርህ ውጭ የሆኑ ስራዎች በየቀኑ እንደየሚታዩ የተገለጸ መሆኑ፤
- ተቋሙ በፓስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ የሚታዩ የብልሹ አሰራር ችግሮችን ለመከላከል የሚያስችል አሰራር ያልዘረጋና የተጠያቂነት አሰራሩ ያልተጠናከረ (ብልሹ አሰራር ሲፈጽሙ የተገኙ የተቋሙ ሰራተኞችን ተከታትሎ እርምጃ መውሰድና ማስወሰድ ላይ ክፍተት ያለ) መሆኑ፤
    - የመልካም አስተዳደር እቅድ ከ2013-2015 ዓ.ም የተዘጋጀ ቢሆንም አፈጻጸሙን በተመለከተ ሪፖርት ተዘጋጅቶ የማይገመገም መሆኑ፤
    - በቀን 6/5/2014 የአገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻያ ዳይሬክቶሬት ባቀረበው የቅሬታ አቤቱታ ሰሚ ሁለተኛ ሩብ ዓመት ሪፖርት ላይ ትክክለኛ ማስረጃ

ለሌለውና ህጋዊ ላልሆነ ተገልጋይ ፓስፖርት የሚሰጥበት ሁኔታ እንዳለ የተገለጸ መሆኑ፤

- ከ2014 ዓ.ም በፊት በዋና መ/ቤትና በቅርንጫፎች በዲስፕሊን ጉድለት ምክንያት የተከሰሱ የተቋሙ ሰራተኞች ክሱ ያለበት ሁኔታ ሳይታወቅና ውሳኔ ሳይሰጣቸው ጉዳያቸው ተንጠልጥሎ ያለ አስራ ሁለት (12) ሰራተኞች መኖራቸው፤
- ከህዳር 2013 ዓ.ም እስከ ሰኔ 2013 ዓ.ም በህገወጥ መንገድ ፓስፖርት እንዲታተም ያደረጉ ሀያ ሶስት (23) ሰራተኞች በዲሲፕሊን የተከሰሱ ሲሆን አስራ ሁለቱ (12) በሙስና ተከሰው ጉዳያቸው በጠ/ዐ/ህግ አማካኝነት በህግ ሂደት ውሳኔ የተሰጣቸው ቢሆንም አስራ አንዱ (11) ግን ክሳቸው ምን ላይ እንደደረሰ የማይታወቅ መሆኑን፤ ለማወቅ ተችሏል፡፡

በተቋሙ የፓስፖርት ግብዓቶች የግዥ ዕቅድ ስለመኖሩና ግዥው በውሉ መሰረት መከናወኑን በተመለከተ፤

9. ተቋሙ የፓስፖርት ግብዓቶች የግዥ ዕቅድ ሊኖረውና ግዥውም በዕቅዱ እና በተገባው ውል መሰረት ተግባራዊ ስለመደረጉ የሚከታተልበት ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡
10. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ሰነዶች እና ከተቋሙ የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ፡-
    - ተቋሙ የፓስፖርት ግብዓቶች የግዥ ዕቅድ በወጥነት የማያቅድ እና ግዥውም በዕቅዱ መሰረት ተግባራዊ ስለመደረጉ የማይከታተል መሆኑ፤ ለማሳያ፡-
    - በ19/12/2015 ዓ.ም ተቋሙ ከ2013-2015 ዓ.ም የግዥ እቅድና በዕቅዱ መሰረት ግዥው መከናወኑን የሚያሳይ ማስረጃ እንዲያቀርብ ቢጠየቅም የቀረበው መረጃ የ2013 እና በ2014 ዓ.ም የግዥ እቅድ ብቻ መሆኑና የ2015 ዓ.ም እቅድ ተጠይቆ ያልቀረበ መሆኑ፤
    - ከ2013-2015 ዓ.ም የግዥ እቅድ አፈፃፀም ያልቀረበ መሆኑ፤ ግዥው በእቅድ መሰረት ስለመከናወኑ የማይከታተልና የግዥ ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት በማዘጋጀት የማይገመገም መሆኑ፤
    - በደብዳቤ ቁጥር ኢ.ሚ.6/492/8949 በቀን 21/12/2012 ዓ.ም የ2013 ዓ.ም የግዥ ዕቅድን ለማሳወቅ ለመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በተላከ ደብዳቤ መደበኛ ፓስፖርት 32 እና 64 ገጽ ብዛት 1,000,000 (አንድ ሚሊየን) እና

ሆሎግራፊክ ፓስፖርት ላሚኔሽን ብዛት 1,154,000.00 (አንድ ሚሊየን አንድ መቶ ሀምሳ አራት ሺ.ህ) በጨረታ ለመግዛት የታቀደ ቢሆንም ግዥው በእቅዱ መሰረት ስለመከናወኑ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፣

- በደብዳቤ ቁጥር ኢ.ሚ.6/492/32384 በቀን 27/12/2013 ዓ.ም የ2014 ዓ.ም የግዥ ዕቅድን ለማሳወቅ ለመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በመሸኛ ደብዳቤ የተላከ ቢሆንም የፓስፖርት ደብተርና ላሚኔት ለመግዛት ያልታቀደ መሆኑ፣
- ተቋሙ ከሁለት ድርጅቶች (እስራኤል ሀገር ካለ ሱፐርኮም /SUPERCOM ከተባለ ድርጅት ላሚኔት ለማስመጣት እና ፈረንሳይ ካለ አይዴሚያ/ IDEMIA ከተባለ ድርጅት ፓስፖርት ለማስመጣት) ጋር የውል ስምምነት እንዳለው የገለጹ ቢሆንም ዋናው የውል ስምምነት ሰነድ ለኦዲት ቡድኑ ያልቀረበ መሆኑን፣ ለማወቅ ተችሏል፡ ፡

ከላይ ለተገኙት ክፍተቶች ለማሻሻል አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ተብሎ የታመነባቸው የማሻሻያ ሃሣቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- ተቋሙ ለፓስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ የሚያገለግሉ የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት እና መመሪያና ስታንዳርድ አዘጋጅቶ በማጸደቅ ተግባራዊ ሊያደርግና ተጠያቂነትን በማስፈን ለተገልጋዩ ቀልጣፋ አገልግሎት ሊሰጥ ይገባል።
- ተቋሙ የአሰራር ስርዓት ማሻሻያ በማዘጋጀት የፓስፖርት አገልግሎትን ለማሳለጥ የሚያስችል የዜጎች ቻርተር ሰነድ አዘጋጅቶ በማጽደቅ ተግባራዊ በማድረግ ተጠያቂነትን በግልጽ በማመላከት ተገልጋዮች የሚያገኙትን የአገልግሎት አይነት ፣ የሚወስደውን ጊዜና ወጪ በማሳወቅ ለተገልጋዩ ቀልጣፋ እና ውጤታማ አገልግሎት በመስጠት አፈጻጸሙን ሊከታተል ይገባል።
- ተቋሙ ከድንበርና ከጎረቤት ሃገራት መሆናቸው አጠራጣሪ የሆኑ ተገልጋዮች ሲያጋጥሙ ዜግነታቸው የሚጣራበት ወጥ የሆነ የአሰራር መመሪያ አዘጋጅቶ በማጸደቅ በመመሪያው መሰረት ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠት ይኖርበታል።
- ተቋሙ የአዲስ መደበኛ ፓስፖርት፣ የፓስፖርት እድሳት፣ የጠፋ ፓስፖርት እና የፓስፖርት እርማት አገልግሎት ፈላጊዎች አገልግሎቱን በምን ያህል ጊዜ እንደሚያገኙ የሚገልጽ የአገልግሎት ስታንዳርድ ሊያዘጋጅና አገልግሎቱን በወቅቱ የሚሰጥበትና ተገልጋዩን እኩል ተጠቃሚ የሚያደርግበት እንዲሁም ፓስፖርት

ለመውሰድ የሚወስደውን የቀጠሮ ጊዜ የሚያሳጥርበት ቀልጣፋና ውጤታማ አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል።

- ተቋሙ የአስቸኳይ ፓስፖርት መመሪያውን አሻሽሎ ግልጽና ሁሉንም ተገልጋይ እኩል ተጠቃሚ ሊያደርግ በሚያስችል መልኩ ማዘጋጀት ይኖርበታል።
- የተቋሙ የኦንላይን መመዝገቢያ ድረ ገጽ ላይ ያሉ መረጃዎች ተገልጋዩ (ፓስፖርት አገልግሎት ለማግኘት ማሟለት ያለበት ቅድመ ሁኔታ) በተቋሙ መጥቶ በሚጠየቀው መረጃ ልክ ሊሻሻልና አብዛኛው ህብረተሰብ ሊረዳው በሚችል ቋንቋ ሊዘጋጅ ይገባል።
- ተቋሙ ፓስፖርት ለመውሰድ ከሚመጡ ተገልጋዮች የሚሰበስበውን ገንዘብ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሚያሳትመው ወይም እንዲታተም በሚፈቅደው ደረሰኝ ሊያደርግ እንዲሁም ለተቋሙ በገንዘብ ሚኒስቴር በተፈቀደ አካውንት ውስጥ ሊያስገባ ይገባል።
- ተቋሙ ከመልክት አስተላላፊ ተቋማት ጋር የፓስፖርት ስርጭትን ለማካሄድ የሚያስችል ህጋዊ መሰረት ያለው ቀልጣፋ የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል።
- ተቋሙ የሰራተኞች የስነ ምግባር መመሪያ አዘጋጅቶ በሚመለከተው አካል በማጸደቅ መመሪያው ተግባራዊ ስለመደረጉና ሰራተኞች ከተገልጋዩ ጋር ባላቸው የስራ ግንኙነት ተገልጋዩን በአክብሮትና በትህትና የሚያስተናግዱ ስለመሆኑ ውጤታማ የክትትልና የቁጥጥር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል፡፡
- ተቋሙ የፓስፖርት ግብዓቶች የግዥ ዕቅድ በየአመቱ በማዘጋጀት ግዥውን በዕቅዱ መሰረት ሊያከናውንና ተግባራዊነቱን ለመገምገም የአፈጻጸም ሪፖርት አዘጋጅቶ ቀልጣፋ እና ውጤታማ ክትትል ሊያርግ ይገባል፡፡
- ተቋሙ ለፓስፖርት ግብቶች ግዥ የውል ስምምነት በግዥ መመሪያ መሰረት አደራጅቶ ሊያስቀምጥና ግዥው በውሉ መሰረት ስለመከናወኑ ውጤታማ ክትትል ማድረግ ይኖርበታል።

በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ

የውጭ ምንዛሪ አፈቃቀድና አጠቃቀምን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት ዘገባ

የተከናወኑ የውጭ ምንዛሪ ግብይቶች ከአሰራር መመሪያው ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን በተመለከተ፤

1. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በአስመጪዎችና በላኪዎች የተከናወኑ የውጭ ምንዛሪ ግብይቶች ከአሰራር መመሪያው ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡
2. ይሁን እንጂ በኦዲት ወቅት በናሙና ከታዩት ባንኮች ከተከለሱ መረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ-መጠይቆች ለመረዳት እንደተቻለው፡-

   ☞ የውጭ ምንዛሪ ድልድልና የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ግልፀኝነት መመሪያ በFXD/77/2021 በአንቀፅ 8 ንዑስ አንቀጽ 8.2 መሰረት አንድ ባንክ በብሔራዊ ባንክ የተዘጋጀውን ማዕከላዊ የድረ-ገጽ ምዝገባ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሥርዓትን በመጠቀም በመጀመሪያ የውጭ ምንዛሪ ጥያቄዎችን መመዝገብና ማጽደቅ እንዳለበት የተገለፀ ቢሆንም በናሙና በታዩት ባንኮች መካከል በዳሽን ባንክ በተለያየ ወቅት ለ138 የባንኩ ደንበኞች አጠቃላይ የውጭ ምንዛሪ መጠን USD 14,021,399.43 እና Euro 544,192.47 የማዕከላዊ የዌብ ቤዝድ አይቲ ሪጄስትሬሽን ሲስተም (EFCAS) ውስጥ የተመዘገበው የውጭ ምንዛሪ ምደባ ከተደረገ እና ድልድል ከፀደቀ በኋላ መሆኑ በዳሽን ባንክ የወስጥ ኦዲት የተረጋገጠ መሆኑ፤

   ☞ በFXD/67/2020 አንቀፅ 7 ንዑስ በአንቀፅ 7.7 መሰረት የውጭ ምንዛሪ ማስመጣት ማመልከቻ 15 ቀን ካለፈው ጥቅም ላይ እንዲውል የሚከለክል ቢሆንም የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና ህብረት ባንክ ለ29 ደንበኞች ጠቅላላ መጠኑ 5,659,633.63 USD እና EUR 815,438.12 የሚሆኑ ባንክ ፐርሚት የመጠቀሚያው ጊዜ ካለፈ በኋላ የኢትዩጵያ ልማት ባንክና የህብረት ባንክ ደንበኞቻቸው እንዲጠቀሙ የፈቀዱ መሆኑን፤

   ☞ በFXD/67/2020 አንቀፅ 7 ንኡስ በአንቀፅ 7.2 በማኑፋክቸሪንግ ሴክተር ከሚደረግ የማስመጣት ማመልከቻ (አፕልኬሽን) በስተቀር ባንክ ሙሉ በሙሉ ከግገር ማዘዣ ዋጋ ብር ሳይሰበስብ በጥሬ ገንዘብ የግገር ትዕዛዝ ማፅደቅ CAD

መመሪያው የሚከለክል ቢሆንም የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ለ13 ደንበኞች 233,660.82 USD እና 31,966.8 EUR ሙሉ በሙሉ ግዢ ማዘዣ ዋጋ ብር ሳይሰበስብ በበጥሬ ገንዘብ የግዢ ትዕዛዝ (CAD) ያፀደቀ መሆኑ፣

☞ በዘመን ባንክ፣ ቡና ባንክ እና ብርሃን ካንክ ላይ በFXD/69/2021 የውጭ ምንዛሪ መመሪያ ላይ በተደረገ ኢንስፔክሽን በሶስቱ ባንኮች በምርመራ ወቅት በተገኘ 94 የህግ ጥሰት በአጠቃላይ የ710,000.00 USD እና የ370,000.00 ብር በመመሪያው መሰረት የሚያስቀጣቸው ቢሆንም፣ ብሔራዊ ባንክ ከመመሪያ ውጪ 45,000.00 USD እና 60,000.00 ብር ብቻ እንዲቀጡ ያደረገ መሆኑ በኦዲት ወቅት ከተከለሱ መረጃዎችና በናሙና ከታዩ ባንኮች ከቀረበላቸው ቃለ መጠይቆች ለማወቅ ተችሏል፡፡

በብሔራዊ ባንክ የሚከናወኑ ጥናቶችን በተመለከተ

3. ብሔራዊ ባንክ የክፍያ ሚዛን፣ የገንዘብ አቅርቦት፣ የዋጋ ትንበያዎችን እና የመሳሰሉትን ለኢኮኖሚ ጠቃሚ የሆኑ ጥናቶችን ሊያካሂድ እና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
4. ይሁን እንጂ በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች እንደታየው፡-

☞ ባንኩ ሀገራችን ያገኘችውን የውጪ ምንዛሪ በቁጠባ ለመጠቀም የሚያስችሉ ጥናቶች በኦዲቱ ወቅት ተጠይቀው ያልቀረቡ መሆኑ፤

☞ ብሔራዊ ባንክ የውጪ ምንዛሪ አጠቃቀምን ለማሻሻል በተመረጡ የውጪ ምንዛሪ አጠቃቀም ላይ የጎላ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገቡ እቃዎች ላይ የዋጋ ትንበያ ጥናቶችን እያደረገ አለመሆኑ፣ እንዲሁም የገበያ ትንበያ መረጃዎችን በየወቅቱ በመሰብሰብ የውጭ ምንዛሬ ከመፈቀዱ በፊት የዋጋ ማረጋገጫ/ማጣቀሻ እንዲሆን ያልተደረገ መሆኑ፤

☞ ብሔራዊ ባንክ የሚፈቀዱ የውጭ ምንዛሬ በትክክል ለተባለው ግዥ የተጠየቀ መሆኑን የሚያረጋግጥበት ሥርዓት እና በአቅራቢውንና በገዥው መካከል ያሉ ሰንሰለቶችን የሚቆርጥ (የሚያሳጥር) ሥርዓት ያልዘረጋ መሆኑ፤ ለምሳሌ ግዥዎች ሲከናወኑ በተቻለ መጠን ከአምራቾች በቀጥታ ግዥ እንዲፈፀም የሚያስችል እና የመሳሰሉትን በጥናት ያልተለየ

ከመሆኑም ባሻገር በዚህ ረገድ ክትትል እና ቁጥጥር የማይደረግ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች ለመረዳት ተችሏል፡፡

ወደሀገር የሚገቡ እቃዎች ዋጋን በተመለከተ፤

5. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ወደ ሀገር ውስጥ በሚገቡ እቃዎች ከደረሰኝ በታች (Under Invoice) እና ከደረሰኝ በላይ (Over Invoice) እንዳይሆኑ እና በትክክለኛ የገበያ ዋጋ ወደ ሀገር እንዲገቡ ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ በማድረግ የውጭ ምንዛሪ አጠቃቀምን ሊያሻሽልና እና በባንኮች የሚከፈቱ ኤል ሲ ውል ግዴታቸው መሰረት ኃላፊነታቸውን በወቅቱ ስለመወጣታቸው ክትትል ሊያደርግ ይገባል ፡፡
6. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች፡-
   - ☞ ብሔራዊ ባንክ ሀገሪቱ የምታገኘውን የውጭ ምንዛሪ በተዘረጋው የአሰራር ሥርዓት በቁጠባ ሊጠቀም የሚገባው ሲሆን እቃዎችን ከውጪ ለሚያስገቡ አስመጪዎች የሚፈቀደው የውጪ ምንዛሪ ትክክለኛ የገበያ ዋጋን መሰረት ያደረገ መሆኑን የሚያረጋግጥበት ሥርዓት ያልዘረጋ መሆኑ፤ ይሁን እና የሚገቡ እቃዎች ከዋጋ በታች እንዳይፈቀድና እንዳይገቡ በ22/01/2018 ጥናቱ ተጠናቆ ወደ ስራ የገባ ቢሆንም የሲዲ ዋጋ እና የሸቀጦች ዋጋ መግለጫ ክለሳ ያልተደረገበት መሆኑ፤
   - ☞ በሀገራችን ያሉ ባንኮች የኤል ሲ የውል ግዴታቸውን በተቀመጠው ጊዜ እየተወጡ ባለመሆኑ የውጭ ሀገራት ባንኮች በኢትዮጵያ የሚከፈቱ ኤልሲዎችን መቀበል ማቆማቸው እና ከሌላ ሀገር ባንክ የተረጋገጠ ኤል ሲ (Confermed LC) እንዲያመጡ የሚያስገድዱ መሆኑ፤ በዚህ መሰረት ባንኮች አስመጪዎች በተረጋገጠ ኤል ሲ ተጨማሪ ክፍያ እንዲከፍሉ በማድረግ ወደ አገር የሚገቡ እቃዎችን ላይ የሚጫን በመሆኑ እና የዋጋ ጭማሪው በህብረተሰቡ ላይ የሚጫን መሆኑ፤ ብሔራዊ ባንክም ይህን በተመለከተ ባንኮች ኃላፊነቱን የሚወስዱበት የቁጥጥር ስርዓት ያልዘረጋ መሆኑ፤
   - ☞ ብሔራዊ ባንክ ባንኮች በፐርፎርማ (በዋጋ ማቅረቢያው) ላይ የቀረበው ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ካልሆነ እና ባንኩ የዋጋውን ትክክለኛነት የሚያረጋግጥበት የአሰራር ስርዓት ሳይኖረው እንዲሁ አስመጪው ያቀረበው ዋጋ ትክክለኛ ባይሆን በባንኩ ለሚጣልበት ቅጣት እና ሃላፊነት እንደሚወስድ (undertake) እንዲፈርሙ

በማድረግ እቃዎችን እንዲያስገቡ ፈቃድ እየሰጡ መሆኑን፤ በተጨማሪም በአስመጪው ሃላፊነት ተፈርመው ከመጡም በኃላ ባንኩ በትክክለኛው ዋጋ ስለመግባታቸው አረጋግጦ ኃላፊነት እንዲወስዱ አድርጎ የማያውቅ መሆኑ ከተከለሱ ማስረጃዎችና ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች ለመረዳት ተችሏል፡፡

☞ ብሔራዊ ባንክ ከትክክለኛው የገበያ ዋጋ በላይ (Over Invoice) ለሚያቀርቡ አስመጪዎች ቁጥጥር ለማድረግ እንዲቻል የሚያስከትለውን ተፅኖውን በጥናት እንዲለይ እና እንዲገመገም በማድረግ መመሪያ ያላወጣ መሆኑ እና ከትክክለኛው የገበያ ዋጋ በላይ (Over Invoice) ምክንያት ሀገራችን ያገኘችው የውጪ ምንዛሬ በቁጠባ ለመጠቀም የሚያስችል እና አላግባብ ከአገር እንዳይወጣ የሚያስችል ጥናት ያልተካሄደ መሆኑ፤በተጨማሪም ለተመሳሳይ እቃዎች/ተሸከርካሪዎች ለማስገባት በሚቀርበው የዋጋ ማቅረቢያ መሰረት በተለያየ ዋጋ የሚሰጥ እና እንዲገባ የሚፈቀድ መሆኑ፤ ይህን በተመለከተ የተዘረጋ የቁጥጥር ሥርዓት አለመኖሩን፤

በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ሰነዶች እና ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች ለማወቅ ተችሏል፡፡

በብሔራዊ ባንክ የሚያዝ የውጭ ምንዛሪ ክምችትን በተመለከተ;

7. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ለሦስት ወራት ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን ለመሸፈን የሚያስችል የውጭ ምንዛሪ ክምችት ሊይዝ ይገባል፡፡
8. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለመረዳት እንደተቻለው የውጭ ምንዛሪ ቁጥጥር እና መጠባበቂያ አስተዳደር የአሰራር ማንዋል ላይ ብሔራዊ ባንክ ለሶስት ወራት ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ምርቶችን መሸፈን የሚያስችል የውጭ ምንዛሪ ክምችት መያዝ እንዳለበት ቢገልፅም ነገር ግን ባንኩ በየአመቱ ሊይዝ ያቀደው የውጭ ምንዛሪ መጠባበቂያ ክምችት (ሪዘርቭ) እቅድ እና አፈፃፀሙ በየዓመቱ ከእቅድ በታች የአሰራር ማንዋሉ ላይ ከተቀመጠው ስታንዳርድ በታች የሆነ የመጣ መሆኑ፤

አስመጪዎችና ላኪዎች ላይ ክትትል መደረጉን በተመለከተ፤

9. ብሔራዊ ባንክ አስመጪዎችና ላኪዎች ባንኩ ባወጣው የጊዜ ገደብ ዕቃ ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባታቸውን ክትትል ሊያደርግና በየወሩ ግዴታቸውን ባልተወጡ አስመጪና ላኪዎች ላይ የባንክ አገልግሎት እንዳያገኙ መረጃ ሊያሰራጭ እና ግዴታቸውን ለተወጡ ክሊራንስ በወቅቱ ሊሰጥ ይገባል፡፡

❖ በመመሪያ FXD/07/1998 መሰረት አስመጪዎች የወሰዱትን የባንክ ፈቃድ 4 ወር ጊዜ ውስጥ ማወራረድ እንደሚገባቸው ቢያዝም ነገር ግን በናሙና ከታዩት የመንግስት ተቋማት በአስመጪዎች (importer) የባንክ ፍቃድ ወስደው በወቅቱ የወሰዱትን የባንክ ፍቃድ ሳያወራርዱ ለረጅም ጊዜ የቆዩ የመንግስት ተቋማት መኖራቸው፤ ለማሳያ ያህል

❖ በባንኩ FEMOS ሲስተም መሰረት ከ10/12/2010 እስከ 07/04/2023 እ.ኤ.አ ባለው ጊዜ በናሙና ከታዩት 10 የመንግስት ተቋማት በ 486 የማስመጣት የባንክ ፍቃድ ጠቅላላ ድምሩ 392,361,035.24 USD (ሶስት መቶ ዘጠና ሁለት ሚሊዮን ሶስት መቶ ስልሳ አንድ ሺ ሰላሳ አምስት ከ24/100 ዶላር) ፤ 7,083,007.46 EURO (ስምንት ሚሊዮን አምስት መቶ ስልሳ አንድ ሺ አራት ከ62/100 ዩሮ)፤ 1,274,544,276 (አንድ ሚሊዮን ሁለት መቶ ሰባ አራት ሺ አምስት መቶ አርባ አራት ሺ ሁለት መቶ ሰባ ስድስት የጃፓን የን) እና 676,672.73 GBP (ስድስት መቶ ሰባ ስድስት ሺ ስድስት መቶ ሰባ ሁለት ከ73/100 የእንግሊዝ ፓውንድ) ወደ አገር ውስጥ ገንዘብ ሲቀየር 11,718,337,374.43 ብር (አስራ አንድ ቢሊየን ሰባት መቶ አስራ ስምንት ሚሊዮን ሶስት መቶ ሰላሳ ሰባት ሺ ሶስት መቶ ሰባ አራት ከ43/100 ብር) የገንዘብ መጠን (በመመሪያው መሰረት ሳይወራረድ 1 እስከ 14 አመት የቆየ መሆኑ፤

❖ በተጨማሪ በናሙና ከታዩት 4 ላኪዎች በ84 የመላክ የባንክ ፍቃድ ወስደው ጠቅላላ ድምሩ 24,029,752.11 USD (ሃያ አራት ሚሊዮን ሃያ ዘጠኝ ሺ ሰባት መቶ አምሳ ሁለት ከ11/100 ዶላር) የውጭ ምንዛሪው ወደ ሀገር መግባቱ ሳይረጋገጥ ከ 1 እስከ 7 አመት የቆየ መሆኑ፤

☞ አስመጪዎችና ላኪዎች የወሰዱትን የኢንፖርትና የኤክስርት ፍቃድ ሳያወራርዱ በተደጋጋሚ ተጨማሪ የባንክ ፍቃዶች የሚሰጥበት አሰራር ያለ መሆኑ፣

☞ የውጭ ምንዛሪ ክትትል የስራ ክፍል በባንክ መመሪያ መሰረት ግዴታቸውን ያልተወጡ ላኪዎች (Deliquent) ለክትትል እና ለውሳኔ አሰጣጥ በሚያመች መልኩ በዘርፍ ከፋፍሎ ክትትል የሚያደርግበት አሰራር የሌለ መሆኑ፤

☞ በባንክ መመሪያ መሰረት ግዴታቸውን ያልተወጡ አስመጪዎች እና ላኪዎች(Deliquent) በወቅት እንዲመልሱ ድጋፍ ሊያደርጉ ለሚችሉ ተቋማት እንደ ንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚንስቴር ላሉ ተቋማት (Deliquent) መረጃዎችን የማሰራጨት ላይ ውስንነት ያለ መሆኑ፤

☞ አስመጪዎችና ላኪዎች ዴሊኬንት እያለባቸው ተጨማሪ የባንክ ፍቃድ የሚሰጥበትን መስፈርት በግልፅ ተዘርዝሮ ያልተቀመጠ መሆኑ፣ የወሰዱትን የባንክ ፍቃድ ሳያወራርዱ ተጨማሪ የሚሰጡ የባንክ ፍቃድ ገደብ ለረዥም ጊዜ ሳይወራረዱ የቆዩ የባንክ ፈቃዶች በአስተዳደራዊም ሆነ በህግ ውሳኔ የሚያገኙበት አሰራር ያልተቀመጠ መሆኑ፣ መመሪያው ላይ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ በተለያዩ ችግሮች ማወራረድ ላልቻሉ አስመጪዎችና ላኪዎች የማወራረጃ ጊዜ ማራዘሚያን በሚመለከት የተቀመጠ መስፈርትና የአስተዳደራዊ ውሳኔ አሰራር ስርዓትን በሚመለከት በግልፅ ተዘርዝሮ FXD/07/1998 መመሪያው ውስጥ የተቀመጡ ባለመሆናቸው ተደጋጋሚ የመመሪያ ጥሰት እንዲኖር ያደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

ብሔራዊ ባንክ የተቀላጠፈ የመረጃ ልውውጥ አሰራር መዘርጋትን በተመለከተ፤

10. ብሔራዊ ባንክ የውጭ ምንዛሪ ቁጥጥር ስርዓት (FEMOS) መተግበሪያ ከኢትዮጵያ ኤሌክትሮኒክስ ነጠላ መስኮት ሲስተም በመጠቀም ለተቀላጠፈ እና ውጤታማ ተግባራት አስፈላጊ የሆኑትን ተመላሽና ተዛማጅ መረጃዎችን አደራጅቶ ሊይዝ ይገባል፡፡

11. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና በናሙና ከታዩት ባንኮች ለመረዳት እንደተቻለው፡-

☞ የኢትዮጵያ ኤሌክትሮኒክ ነጠላ መስኮት ሲስተም ከብሔራዊ ባንክ የውጭ ምንዛሪ ቁጥጥር ስርዓት (FEMOS) ጋር እንዲተሳሰር (ኢንተግሬት) ያልተደረገ በመሆኑ ባንኮች እየበዙ በሄዱ ቁጥር ከባንኮች የሚመጡ

መረጃዎችን ወደ FEMOS በማንዋል ስለሚገቡ የባንኩ ሰራተኞች ላይ የስራ ጫና የሚፈጥር እና የመረጃ ጥራት ላይ ተፅእኖ እያሳደረ መሆኑ፤

- ☞ የነጠላ መስኮት ሲስተም በአፕሊኬሽኑ ዋጋን ለመመዝገብ የማይችል በመሆኑ የሀገር ውስጥ ምንዛሪን በዶላር/ዩሮ በእጅ (በማንዋል) ስሌቱን የሚያሰሉ መሆናቸው፤
- ☞ የቅድሚያ ክፍያ ሲመዘገብ እና የማጣቀሻ ቁጥር ሲገባ ስርዓቱ የደንበኛውን ቀሪ ሂሳብ የማያሳይ መሆኑ፣ ስርዓቱ የአውታረ መረብ የሚጨናነቅ በመሆኑ ምክንያት ከአንድ መስኮት ወደ FEMOS አፕሊኬሽን መረጃን ለመውሰድ የአውታረ መረብ መቆራረጥ እና የባክሎክ (የመጠባበቂያ) ሰነዶች እንዲኖር የሚያደርግ መሆኑ፤
- ☞ FEMOS አሰራር ወደ ወረቀት ስራ የሚመራ መሆኑ ለምሳሌ፡- ባለሞያዎቹ መረጃውን ወደ FEMOS መተግበሪያ ለማስገባት የማስመጣት እና የመላክ ፍቃድ ከሲስተም ላይ እንደሚያወርዱ በዚህ ምክንያት የአንድ አቅራቢ የማስመጣት ፍቃድ 182 የንጥል ቁጥሮች ከሲስተም ላይ በማውረድ (ዳውንሎድ) ተደርገው (ፕሪንት ተደርገው) ወደ FEMOS መተግበሪያ እንዲገቡ የሚደረግ መሆኑ፤
- ☞ በባንኩ የውስጥ ኦዲት በFEMOS መተግበሪያ ላይ በተደረገ ኦዲት በተገኙ ጉድለቶች የውጭ ምንዛሪ ቁጥጥር እና የመጠባበቂያ አስተዳደር ዳይሬክተር እስከ ሰኔ 30/2021 ድረስ መርሀ ግብር በማዘጋጀት በስርዓቱ ላይ ያለውን ችግር እንደሚፈታ ቢስማማም ነገር ግን ይህ ኦዲት እስከተጠናቀቀበት ወቅት ድረስ ባንኩ ስርዓቱን እንዲዘምን በማድረግ ከንግድ ባንኮችና ከጉምሩክ ጋር እንዲተሳሰር (ኢንተግሬት) እንዲሆን ያልተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

ከላይ ለተገኙት ክፍተቶች ለማሻሻል አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ተብሎ የታመነባቸው የማሻሻያ ሃሣቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- ❖ ብሔራዊ ባንክ የውጭ ምንዛሪን በሚመለከት የሚያወጣቸው የተለያ መመሪያዎች የሕግ ማእቀፎችን በንግድ ባንኮች በአግባቡ ተግባራዊ

እየተደረጉ ስለመሆናቸው እና የሚከናወኑ ግብይቶች ከአሰራር መመሪያ ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን ሊያረጋግጥና ጠንካራ የክትትል እና ድጋፍ ስራዎች እንዲሰራ በማድረግ በኢንስፔክሽን ወቅት በሚገኙ የህግ ጥሰቶች ላይ የአሰራር መመሪያው በሚያዘው መሰረት የህግ ጥሰት ለፈፀሙት ባንኮች በወጣው መመሪያ መሰረት ቅጣት እንዲጣልባቸው ሊያደርግ ይገባል፡፡

❖ ብሔራዊ ባንክ የውጪ ምንዛሪ አጠቃቀምን ለማሻሻል በተመረጡ የውጪ ምንዛሪ አጠቃቀም ላይ የጎላ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገቡ እቃዎች ላይ የዋጋ ትንበያ ጥናቶችን ሊያደርግ ይገባል፡፡ እንዲሁም የገበያ ትንበያ መረጃዎችን በየወቅቱ በመሰብሰብ የውጭ ምንዛሬ ከመፈቀዱ በፊት የዋጋ ማረጋገጫ/ማጣቀሻ መረጃ የሚሰበስብበትን ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

❖ ብሔራዊ ባንክ የሚፈቀዱ የውጭ ምንዛሬ በትክክል ለተባለው ግዥ የተጠየቀ መሆኑን የሚያረጋግጥበት ሥርዓት እና በአቅራቢውንና በገዥው መካከል ያሉ ሰንሰለቶችን የሚቆርጥ (የሚያሳጥር) ሥርዓት፣ ለምሳሌ ግዥዎች ሲከናወኑ በተቻለ መጠን ከአምራቾች በቀጥታ ግዥ እንዲፈፀም የሚያስችል እና የመሳሰሉትን ጥናትን መሰረት ያደረገ ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

❖ የአቅራቢዎችን ብድር፣ የውጭ ብድር (external loan and supplier credit) የመመዝገቢያ ሂደት፣ የብድር ዋናውን ወለድ ስሌት፣ ክፍያ ስራዎችን ተገቢውን የሶፍትዌር አፕሊኬሽን/ዳታቤዝ በማልማት የስራ ክፍሉ ስራዎች በዘመናዊ ቴክኖሎጂ እንዲደገፉ ሊያደርግና የኢንስፔክሽን የስራ ክፍልም የውጭ ብድር እና የአቅራቢዎች ብድር (external loan and supplier credit) ዳይሬክቲቭ ላይ የኢንስፔክሽን ስራዎችን እንዲሰራ ሊያደርግ ይገባል፡፡

❖ ብሔራዊ ባንክ የውጭ ምንዛሪ ቁጥጥር እና የመጠባበቂያ አስተዳደር የአሰራር ማንዋል ላይ በተቀመጠው መሰረት ለሦስት ወራት ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን ለመሸፈን የሚያስችል የውጭ ምንዛሪ ክምችት ሊይዝ ይገባል፡፡

❖ ብሔራዊ ባንክ FXD/07/1998 በሚያዘው መሰረት ላኪዎች ወደ ውጭ የሚላኩ ማመልከቻዎች ከወጡበት ቀን ጀምሮ ባሉት 90 ቀናት ውስጥ ወደ ውጭ የላኩትን ገቢ በውጭ ምንዛሪ ወደ ሀገር መመለሳቸውን እና አስመጪዎች ከውጭ የሚገቡ ዕቃዎች ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ ከተፈቀደላቸው ቀን ጀምሮ በ120 ቀናት ውስጥ ማስረጃ ማቅረባቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

- ብሔራዊ ባንክ አስመጪዎችና ላኪዎች የወሰዱትን የኢንፖርትና የኤክስፖርት ባንክ ፍቃድ ሳያወራርዱ ተጨማሪ የባንክ ፍቃዶች የሚሰጥበት መስፈርት በግልፅ ተዘርዝሮ ሊቀመጥና፣ የወሰዱትን የባንክ ፍቃድ ሳያወራርዱ ተጨማሪ የሚሰጡ ባንክ ፍቃዶች ገደብ፣ ለረዥም ጊዜ ሳይወራረዱ የቆዩ የባንክ ፍቃዶች በአስተዳደራዊም ሆነ በህግ ውሳኔ የሚያገኙበት አሰራር እና መመሪያው ላይ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ በተለያዩ ችግሮች ማወራረድ ላልቻሉ አስመጪዎችና ላኪዎች በአስተዳደራዊ ውሳኔ ሊታዩ የሚችሉ ጉዳዮች በግልፅ ተዘርዝረው በመመሪያው ውስጥ እንዲካተት ሊደረግና መመሪያውን ሊያሰራ በሚችል መልኩ እንዲሻሻል በማድረግ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- የውጭ ምንዛሪ ክትትል የስራ ክፍል በባንክ መመሪያ መሰረት ግዴታቸውን ያልተወጡ ላኪዎች (Deliquent) ለክትትል እና ለውሳኔ አሰጣጥ በሚያመች መልኩ በዘርፍ ከፋፍሎ ክትትል የሚያደርግበት አሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ እና በባንኩ ለምቶ ስራ ላይ ያለው FEMOS አፕልኬሽን የአበባ ኤክስፖርት ግዴታቸውን ያልተወጡ ላኪዎች (Deliquent) ለማስተዳደር በሚመች መልኩ እንዲለማ እና እንዲዘምን በማነድረግ የስራ ክፍሉ ሰራተኞች በአበባ ዘርፍ ግዴታቸውን ያልተወጡ ላኪዎች (ዴሊኼዌንት) መረጃ በFEMOS አፕልኬሽን ክትትል እንዲደረግበት ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ንግድ ባንኮች ለብሔራዊ ባንክ FXD/78/2022 አንቀፅ-4 ንኢስ አንቀፅ-4.2 በሚያዘው መሰረት የወርሃዊ የውጭ ምንዛሪ አቅርቦት ሪፖርት መመሪያው ላይ በተቀመጠው ቀን እንዲያቀርቡ ሊደረግና ባንኮች ወርሃዊ ሪፖርቶችን ዘግይተው የሚያቀርቡበት አሰራር እና የውጭ ምንዛሪ አቅርቦት ወርሃዊ ሪፖርት ላይ ከተወራረዱ (settelmant) ከተደረጉ የቆዩ የማስመጣት ፍቃዶች (Import permit) አካተው ሪፖርት የማያደርጉ አሰራር እንዲስተካከል ሊደረግ ይገባል፡፡
- የኢትዮጵያ ኤሌክትሮኒክ ነጠላ መስኮት ሲስተም ከብሔራዊ ባንክ FEMOS ስርዓት ጋር እንዲተሳሰር (ኢንተግሬት) እንዲደረግ በማድረግ የነጠላ መስኮት ሲስተም በአፕሊኬሽኑ ውስጥ ዋጋን እንዲካተት፣ የቅድሚያ ክፍያ ሲመዘገብ እና የማጣቀሻ ቁጥር ሲገባ ስርዓቱ የደንበኛውን ቀሪ ሂሳብ እንዲያሳይ ሊደረግና ከአንድ መስኮት ወደ FEMOS አፕሊኬሽን መረጃን ለመውሰድ የአውታር መረብ መቆራረጥ ለማስወገድ ደረጃውን የማሻሻል (upgrading) ስራዎችን

እንዲሰራ በማድረግ የባክሎክ (የመጠባበቂያ) ሰነዶች እንዳይኖር ሊደረግና፣ ባለሞያዎቹ መረጃውን ወደ FEMOS መተግበሪያ ለማስገባት የማስመጣት እና የመላክ ፍቃድ ከሲስተም ላይ በቀጥታ ለማግኘት በሚያስችል መልኩ ስርዓቱን እንዲዘምን በማድረግ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

❖ በመመሪያው FXD/53/2018 አንቀፅ-3 የተዘረዘሩትን እቃዎች ሲዲ ፕራይስ ከወቅቱ የአለም አቀፍ የዋጋ ለውጥ ጋር አብሮ እንዲሄድ ተደርጎ እንዲከለስ፣ ወቅታዊ የገበያ ዋጋ ዝርዝር እንዲይዝ በማድረግ የዋጋ ሲዲውን ባንኮች እንዲጠቀሙበት ሊያደርግ፣ አስመጪዎች የሚያቀርቧቸው በፐርፎርማ (በዋጋ ማቅረቢያ) ላይ የቀረበው ትክክለኛ የገበያ ዋጋ መሆናቸውን ንግድ ባንኮች እያረጋገጡ አስመጪው እቃዎችን ወደ ሀገር ውስጥ እንዲያስገቡ እና ከደረሰኝ በታች (የአንደር ኢንቮይስ) ችግር እንዲቀረፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

❖ ብሔራዊ ባንክ ከትክክለኛው የገበያ ዋጋ በላይ (Over Invoice) ለሚያቀርቡ አስመጪዎች ቁጥጥር ለማድረግ እንዲቻል እና ከትክክለኛው የገበያ ዋጋ በላይ (Over Invoice) ምክንያት ከአገር ሊሸሹ የሚችል የውጭ ምንዛሪ መጠን እንዲታወቅ እንዲሁም የሚያስከትለውን ተፅፅኖውን በጥናት እንዲለይ እና እንዲገመገም በማድረግ መመሪያ እንዲወጣ ሊያደርግና ይገባል፡፡

☞ በሀገራችን ያሉ ባንኮች የኤል ሲ የውል ግዴታቸውን በተቀመጠው ጊዜ እየተወጡ መሆኑን ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡ በውል ግዴታቸው መሰረት ሃላፊነታቸውን ባለመወጣታቸው ምክንያት ከሌላ ሀገር ባንክ የተረጋገጠ ኤል ሲ (Conformed LC) እንዲያመጡ የሚገደዱትን ባንኮች በመለየት ተጠያቂ የሚሆኑበትን ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ በዚሁ መሰረት ተጨማሪ የሚከፈለው ክፍያ በህብረተሰቡ ላይ የሚያደርሰውን ጫና እንዲቀንስ የሚያስችል ሥራ ሊሰራ ይገባል፡፡

☞ ብሔራዊ ባንክ ባንኮች በፐርፎርማ (በዋጋ ማቅረቢያው) ላይ የቀረበው ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ካልሆነ አስመጪው ያቀረበው ዋጋ ትክክለኛ ባይሆን በባንኩ ለሚጣልበት ቅጣት እና ሃላፊነት እንደሚወስድ (undertake) እንዲፈርሙ በማድረግ እቃዎችን እንዲያስገቡ ፈቃድ እየሰጡ ሲሆን፤ በአስመጪው ሃላፊነት ተፈርመው እቃዎቹ ወደሃገር ከገቡም በኃላ ባንኩ በትክክለኛው ዋጋ

ስለመግባታቸው የሚያረጋግጥበት ስርዓት በመዘርጋት ተግባር ላይ ሊያውል እና ኃላፊነት እንዲወስዱ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ብሔራዊ ባንክ ከጉምሩክ ኮሚሽን እና ከንግድ ባንኮች ጋር አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ማለትም ጉምሩክ መግለጫ፣ ያለባቸውን እዳ በወቅቱ ያላወራረዱ (ዴሊኬንት) አስመጪና ላኪዎች መረጃ፣ ከባኮች የሚመጡ የተለያዩ ሪፖርቶችንና መረጃዎችን ለመቀበልና ለመላክ የሚያስችል የተቀላጠፈ እና ውጤታማ የመረጃ ልውውጥ አሰራር ለመተግበር የሚያስችል ዌብ ቤዝድ አይቲ ሲስተም (ኢንተግሬት አውቶሜትድ ሲስተም) ስርዓት በባንኩ እንዲዘረጋ እና ተግባራዊ እንዲደረግ ሊያደርግ ይገባል፡፡

በኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለሥልጣን

የፌደራል መንግስት የተቋረጡ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች ክትትልና ቁጥጥር ፣ የሥራ ተቋራጮች ብቃት ምዘናና ክትትል እና የሰራተኞች የሙያ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ አፈፃፀምን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት ዘገባ

የተቋረጡ የመንግስት ፕሮጀክቶች ክትትልና ቁጥጥርን በተመለከተ

1. ባለሥልጣን መ/ቤቱ በፌደራል መንግስት በጀት የሚገነቡ ውለታቸው በተቋረጡ ፕሮጀክቶች የታዩ የአፈፃፀም ግድፈቶችን ተከትሎ በመንግስት ሀብት ላይ እየፈጠረ ያለውን ብክነት እና የፕሮጀክቶች ባለቤቶችም ተግባርና ኃላፊነታቸውን እየተወጡ መሆኑን ክትትል በማድረግ ችግሮች እንዲፈቱ ሊያደርግ ይገባል፡፡
2. በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ መጠይቶች ለመረዳት እንደተቻለው፡- በፌዴራል በጀት የሚሰሩ ፕሮጀክቶችን የያዙ ሥራ ተቋራጮች የያዙትን ፕሮጀክት ሳያጠናቅቁ ወይም አፈፃፀማቸው ሳይታይ በሌላ ጨረታ ላይ እንዳይወዳደሩ የሚከለክል የአሰራር ሥርዓት ተዘርግቶ ቁጥጥርና ክትትል ባለመደረጉ ከአንድ በላይ ፕሮጀክቶችን ይዘው ያቋረጡ ሥራ ተቋራጮች መኖራቸው፤ የውል ዋጋቸው በድምሩ ብር10,764,373,751.02 (**አስር ቢሊዮን ሰባት መቶ ስልሳ አራት ሚሊዮን ሶስት መቶ ሰባ ሶስት ሺ ሰባት መቶ አምሳ አንድ ከ02/100 ብር**) የሆኑ 12 **ፕሮጀክቶች በሁለት ሥራ ተቋራጮች የተያዙ** መሆናቸው፤
3. በሀገሪቱ ያሉ የተቋረጡ ፕሮጀክቶችን አጠቃላይ መረጃ በመያዝ የተቋረጡ ፕሮጀክቶች በፍጥነት ተመልሰው ወደ ሥራ እንዲገቡ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ባለመሰራቱ በናሙና ከታዩ 41 የተቋረጡ ፕሮጀክቶች ውስጥ 13 ፕሮጀክቶች ተመልሰው ወደ ግንባታ የገቡ ቢሆንም 28ቱ ግን ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ወደ ግንባታ እንዲገቡ ያልተደረገ መሆኑ፤
4. ፕሮጀክቶች በሚቋረጡበት ጊዜ የፕሮጀክት ባለቤቶች ተግባርና ኃላፊነታቸውን ባለመወጣታቸው እና በባለሥልጣኑም በኩል የተቋረጡ ፕሮጀክቶች ላይ ትኩረት ተሰጥቶ ክትትል ባለመደረጉ በናሙና ከታዩ 41 የተቋረጡ ፕሮጀክቶች ውስጥ የ12 ፕሮጀክቶች ሳይት ላይ የነበሩ ንብረቶች ተመዝግበው ያልተያዙ ሲሆን የ27 ፕሮጀክቶች ደግሞ በሰነድ ደረጃ ተመዝግበው የተያዙ ቢሆንም ንብረቶቹ በተገቢው ሁኔታ ተጠብቀው ያልተያዙ መሆናቸው፤

5. የፕሮጀክቶች መቋረጥ በመንግስት ሀብት ላይ እየፈጠረ ያለውን ከፍተኛ የገንዘብ ብክነት መኖሩ፣ በናሙና ከታዩ 41 የተቋረጡ ፕሮጀክቶች ውስጥ ተመልሰው ወደ ግንባታ የገቡ 13 ፕሮጀክቶችን መሰረት በማድረግ ፕሮጀክቶቹ በመጀመሪያ ውለታቸው ተገንብተው ባለመጠናቀቃቸው በመንግስት ላይ ያስከተሉትን ተጨማሪ ወጪ በድምሩ ብር 16,681,131,031.64 (**አስራ ስድስት ቢሊዮን ስድስት መቶ ሰማኒያ አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሰላሳ አንድ ሺ ሰላሳ አንድ ከ64/100 ብር**) **መሆኑ፣**

ውለታቸው የተቋረጡ ፕሮጀክቶች ከብልሽት መጠበቃቸውን በተመለከተ

6. ባለሥልጣን መ/ቤቱ በፌደራል መንግስት በጀት የሚገነቡ ውለታቸው ተቋርጦ ረጅም ጊዜ ያስቆጠሩ ፕሮጀክቶች ለዘላቂ የጥራት ችግር ከመጋለጣቸው በፊት ክትትል በማድረግ ወደ ውለታ የሚገቡበትን ሁኔታ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ሊሰራ ይገባል፡፡

7. በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ መጠይቶች ለመረዳት እንደተቻለው ባለሥልጣን መ/ቤቱ በተወሰኑ የተቋረጡ ፕሮጀክቶች ላይ የቁጥጥርና ክትትል ስራዎችን ያከናወነ ቢሆንም ውለታቸው ተቋርጦ ረጅም ጊዜ ያስቆጠሩ ፕሮጀክቶች ለዘላቂ የጥራት ችግር ከመጋለጣቸው በፊት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል ሥራ አለመሰራቱ፣ ለአብነት ያህል በሀረማያ ዩኒቨርሲቲ የፋና ህይወት ጠቅላላ ሆስፒታል፣ በሃዋሳ ዩኒቨርሲቲ የዳዬ ካምፓስ ሁለት የተማሪዎች ማደሪያ፣ አንድ መጋዘን፣ ሁለት የሠራተኛ መኖሪያ እና የአንድ ካፍቴሪያ ፕሮጀክቶች የማጠናቀቅያ ሥራ (Finishing) ሲቀራቸው ተቋርጠው ከ2ዓመት በላይ በመቆየታቸው በጣሪያ መገንጠል እና የጣሪያ ፍሳሽ ማስወጋጃ (joint Expansion) ባለመገጠሙ ምክንያት ለብልሽት የተጋለጡ መሆኑ፣ ታውቋል፡፡

ውለታቸው የተቋረጡ ፕሮጀክቶች የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና አፈፃፀም በተመለከተ

8. ባለሥልጣን መ/ቤቱ በፌደራል መንግስት በጀት የሚገነቡ ውለታቸው የተቋረጡ ፕሮጀክቶች የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና (Performance Guarantees) በውለታቸው መሰረት ገቢ መደረጉን ሊቆጣጣር ይገባል፡፡

9. በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ መጠይቶች ለመረዳት እንደተቻለው በናሙና ተመርጠው ማስረጃቸው ከተከለሱ 41 የተቋረጡ ፕሮጀክቶች ውስጥ የ3 ፕሮጀክቶች በፍርድ ቤት ሂደት ላይ ያሉ ብር 471,182,026.54 (አራት መቶ

ሰባ አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሰማንያ ሁለት ሺ ሃያ ስድስት ከ54/100 ብር) እና በክስ ሂደት ላይ ስለመሆናቸው ማስረጃ ያልቀረበላቸው የ35 ፕሮጀክቶች ብር1,976,020,351.87 (አንድ ቢሊዮን ዘጠኝ መቶ ሰባ ስድስት ሚሊዮን ሃያ ሺ ሶስት መቶ ሃምሳ አንድ ከ87/100 ብር) በአጠቃላይ የ38 ፕሮጀክቶች በድምሩ ብር 2,447,202,378.41 (ሁለት ቢሊዮን አራት መቶ አርባ ሰባት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሁለት ሺ ሶስት መቶ ሰባ ስምንት ከ41/100 ብር) የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና (Performance Guarantees) ከሥራ ተቋራጮች ጋር የተገባውን ውል መሰረት ተግባራዊ ባለማድረጋቸው ያልተወረሰ /ገቢ/ ያልተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

ለተቋረጡ ፕሮጀክቶች የተከፈሉ የቅድመ ክፍያዎች ተመላሽ እንዲደረጉ ቁጥጥር መደረጉን በተመለከተ

10.ባለሥልጣን መ/ቤቱ በፌደራል መንግስት በጀት የሚገነቡ ውለታቸው ለተቋረጡ ፕሮጀክቶች የተከፈሉ የቅድመ ክፍያዎች ተመላሽ ስለመደረጋቸው ቁጥጥርና ክትትል በማድረግ እርምጃ እንዲወሰድ ሊያደርግ ይገባል፡፡

11.በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ መጠይቶች ለመረዳት እንደተቻለው በናሙና ከታዩ 41 የተቋረጡ ፕሮጀክቶች ውስጥ ለ25 ፕሮጀክቶች ከተከፈለው የቅድመ ክፍያ (Advance Payments) ብር 3,220,090,230.46 (ሦስት ቢሊዮን ሁለት መቶ ሃያ ሚሊዮን ዘጠና ሺ ሁለት መቶ ሰላሳ ከ46/100 ብር) ውስጥ በፍርድ ቤት ሂደት ላይ ያሉ የ6 ፕሮጀክቶች ብር 672,540,236.97 (ስድስት መቶ ሰባ ሁለት ሚሊዮን አምስት መቶ አርባ ሺ ሁለት መቶ ሰላሳ ስድስት ከ97/100 ብር) እና በክስ ሂደት ላይ ስለመሆናቸው ማስረጃ ያልቀረበላቸው የ19 ፕሮጀክቶች ብር 1,795,255,090.20 (አንድ ቢሊዮን ሰባት መቶ ዘጠና አምስት ሚሊዮን ሁለት መቶ አምሳ አምስት ሺ ዘጠና ከ20/100 ብር) በድምሩ ብር 2,467,795,327.17 (ሁለት ቢሊዮን አራት መቶ ስልሳ ሰባት ሚሊዮን ሰባት መቶ ዘጠና አምስት ሺ ሶስት መቶ ሃያ ሰባት ከ17/100 ብር) ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑን እንደሚከተለው ማሳየት ይቻላል፡፡

የኮንስትራክሽን ሥራዎች በአካባቢ፣ በሠራተኞች እና በህብረተሰቡ ጤንነትና ደህንነት አጠባበቅ በተመለከተ

12. ባለሥልጣን መ/ቤቱ የኮንስትራክሽን ሥራዎች በአካባቢ፣ በባህላዊ ቅርሶች፣ በሠራተኞች እና በህብረተሰቡ ጤንነትና ደህንነት ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ ለመከላከል የሚያስችሉ አሰራሮችን ሊዘረጋና አፈፃፀማቸውንም ሊቆጣጠር ይገባል፡፡

13. ባለሥልጣን መ/ቤቱ የኮንስትራክሽን ሥራዎች በአካባቢ፣ በባህላዊ ቅርሶች፣ በሠራተኞች እና በህብረተሰቡ ጤንነትና ደህንነት ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ ለመከላከል የሚያስችሉ አሰራሮችን ዘርግቶ ክትትልና ቁጥጥር እያደረገ መሆኑን፤ ለማሳያ

- ✓ የሰራተኞች የስራ ልብስ፣ የጭንቅላት መከላከያ ቆብ፣ የሥራ ጫማ ስቶር ውስጥ ከማስቀመጥ ውጭ ጥቅም ላይ እያዋሉ አለመሆናቸው፤ የተቆፈሩ ጉድጓዶች ውስጥ ሰራተኛው ወይም ማህበረሰቡ እንዳይገባ መከለያ አጥሮች የማይደረጉ መሆናቸው፤ በግንባታ ወቅት ለሥራ የሚያስፈልጉ ቁሶች ሊወድቁ በሚችሉባቸው ቦታዎች የመቅለቢያ መድረኮች ያልተዘጋጁ መሆናቸው፤ከአምስት በላይ ፎቅ ያላቸው የህንፃ ፕሮጀክቶች የሚጠቀሙበት መወጣጫ ብረት መሆን ሲገባው እንጨት እየተጠቀሙ መሆኑ፤በሥራ ቦታዎች ለሠራተኞች እንቅስቃሴ አስፈላጊ ከሆኑ ቦታዎች ውጭ ያሉ ክፍተቶች ተሸፍነው ለሠራተኛው አደጋ መቀንስ በሚችል መልኩ ያልተዘጋጁ መሆኑ፤ የህንፃዎች ውጫዊ ክፍል የማይሸፈን መሆኑ፤የመጀመሪያ እርዳታ ሊሰጥ የሚችል ጊዜያዊ ክሊኒክ /ባለሙያ የሌለ መሆኑ፤ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በኮንስትራክሽን ስራዎች ላይ የሚፈጠሩ የአደጋ አጋጣሚዎችን መረጃ አያያዝንና ክትትል በተመለከተ

14. ባለሥልጣን መ/ቤቱ የግል ድርጅቶች የኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ውሎች ላይ የአካባቢን፣የሠራተኞችን እና የህብረተሰቡን ጤንነትና ደህንነት በተመለከተ ስለመካተቱ ሊያረጋግጥ እና በኮንስትራክሽን ስራዎችና ግንባታዎች የአደጋ አጋጣሚዎ ሲፈጠሩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ሊፈትሽ ቁጥጥርና ክትትልና ሪፓርት በማድረግ የህግ ተጠያቂነት እንዲኖር ሊያደርግ ይገባል፡፡

15. በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ መጠይቶች ለመረዳት እንደተቻለው፡-

- ❖ ባለሥልጣን መ/ቤቱ በፌዴራል መንግስት በጀት የሚሰሩ ፕሮጀክቶችን ከሚሰሩ ሥራ ተቋራጮች ውጭ የግል ድርጅቶች በሚያሰሯቸው ፕሮጀክት ውሎች ላይ የአካባቢን፣ የሠራተኞችን እና የህብረተሰቡን ጤንነትና ደህንነት የሚመለከቱ ጉዳዮችን አካተው ተግባራዊ እያደረጉ ስለመሆኑ ቁጥጥርና ክትትል በማድረግ የእርምት እርምጃ እየወሰደ አለመሆኑ፣
- ❖ ባለሥልጣን መስሪያ ቤቱ እንደ ሀገር በኮንስትራክሽን ስራዎችና ግንባታዎች ላይ እየደረሱ ያሉ የአደጋ አጋጣሚዎችን ክትትል በማድረግ ግላጭ በሆነ መልኩ በየትኛው ፕሮጀክት ምን አይነት አደጋ እንደደረሰ የሚያሳይ የተደራጀ መረጃ ባለመያዙ ናሙናዎችን መርጦ ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፣

በ2014 ዕቅድ አፈፃፀም 1804 እና በ2015 የ9 ወር ዕቅድ አፈፃፀም ላይ 142 በአጠቃላይ 1946 የአደጋዎች መረጃ እንደተሰበሰበ የተቀመጠ ቢሆንም መረጃው በቁጥር ብቻ የተቀመጠ እንጂ በየትኛው ፕሮጀክት ምን አይነት አደጋ ደረሰ የሚለውን ከትክክለኛ የመረጃው ምንጭ ያልተገኘ መሆኑ እና በደረሱ አደጋዎች ላይ በህግ መሰረት ተጠያቂነት እንዲኖር ስለመደረጉ የተሰራ የክትትልና ቁጥጥር ሪፖርት ያልቀረበ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

በኮንስትራክሽን ስራዎች ላይ የሚፈጠሩ የአደጋ አጋጣሚዎችን መረጃ አያያዝንና ክትትል በተመለከተ

16. ባለሥልጣን መ/ቤቱ የግል ድርጅቶች የኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ውሎች ላይ የአካባቢን፣የሠራተኞችን እና የህብረተሰቡን ጤንነትና ደህንነት በተመለከተ ስለመካተቱ ሊያረጋግጥ እና በኮንስትራክሽን ስራዎችና ግንባታዎች የአደጋ አጋጣሚዎ ሲፈጠሩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ሊፈትሽ ቁጥጥርና ክትትልና ሪፖርት በማድረግ የህግ ተጠያቂነት እንዲኖር ሊያደርግ ይገባል፡፡
17. በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ መጠይቶች ለመረዳት እንደተቻለው፡-
    - ❖ ባለሥልጣን መ/ቤቱ በፌዴራል መንግስት በጀት የሚሰሩ ፕሮጀክቶችን ከሚሰሩ ሥራ ተቋራጮች ውጪ የግል ድርጅቶች በሚያሰሯቸው ፕሮጀክት ውሎች ላይ የአካባቢን፣ የሠራተኞችን እና የህብረተሰቡን ጤንነትና ደህንነት የሚመለከቱ ጉዳዮችን አካተው ተግባራዊ እያደረጉ ስለመሆኑ ቁጥጥርና ክትትል በማድረግ የእርምት እርምጃ እየወሰደ አለመሆኑ፣

- ባለሥልጣን መስሪያ ቤቱ እንደ ሀገር በኮንስትራክሽን ስራዎችና ግንባታዎች ላይ እየደረሱ ያሉ የአደጋ አጋጣሚዎችን ክትትል በማድረግ ገላጭ በሆነ መልኩ በየትኛው ፕሮጀክት ምን አይነት አደጋ እንደደረሰ የሚያሳይ የተደራጀ መረጃ ባለመያዙ ናሙናዎችን መርጦ ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፤
- በ2014 ዕቅድ አፈፃፀም 1804 እና በ2015 የ9 ወር ዕቅድ አፈፃፀም ላይ 142 በአጠቃላይ 1946 የአደጋዎች መረጃ እንደተሰበሰበ የተቀመጠ ቢሆንም መረጃው በቁጥር ብቻ የተቀመጠ እንጂ በየትኛው ፕሮጀክት ምን አይነት አደጋ ደረሰ የሚለውን ከትክክለኛ የመረጃው ምንጭ ያልተገኘ መሆኑ እና በደረሱ አደጋዎች ላይ በህግ መሰረት ተጠያቂነት እንዲኖር ስለመደረጉ የተሰራ የክትትልና ቁጥጥር ሪፖርት ያልቀረበ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን ለማስተዳደር የወጡ ህጎችና ደንቦችን መተግበራቸውን በተመለከተ

18. በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ዘርፍ የሚሰማሩ የሥራ ተቋራጮችን ፈቃድ አሰጣጥ እና የፕሮጀክቶችን ቁጥጥርና ክትትል የሚመለከቱ አዋጆች፣ ደንቦች መመሪያዎችና ማንዋሎች ተዘጋጅተው በሚመለከተው አካል ጸድቀው ተግባራዊ ሊደረጉ ይገባል፡፡
19. በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ መጠይቶች ለመረዳት እንደተቻለው፡-
    - በደንብ ቁጥር 439/2011 እና 524/2015 በተሰጠው የመቆጣጠር ሥልጣን መሰረት ክትትልና ቁጥጥር አድርጎ ግብረ መልስ የተሰጣቸው የፕሮጀክት ባለቤቶች በተሰጠው ግብረ መልስ መሰረት ማስተካከያ ሳያደርጉ ሲቀሩ እንደየጥፋታቸው ደረጃ ተጠያቂ ማድረግ የሚያስችል የፕሮጀክት ቁጥጥርና አፈፃፀም መመሪያ ያላዘጋጀ መሆኑ፤
    - ለሥራ ተቋራጮች ብቃት ማረጋገጫ ከተሰጠ በኋላ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ለየትኛው ጥፋት ምን አይነት እርምጃ መወሰድ እንዳለበት በግልፅ የሚያስቀምጥ የክትትልና ቁጥጥር መመሪያ ያላዘጋጀ መሆኑ፤
    - በፌዴራል እና በክልል ያሉ የመንግስትም ሆነ የግል ፕሮጀክቶች የትኞቹ ፕሮጀክቶች በፌዴራል ደረጃ የትኞቹ ደግሞ በክልል ደረጃ መመዝገብ እንዳለባቸው በግልፅ የሚያስቀምጥ የፕሮጀክት ምዝገባ መመሪያ ያልተዘጋጀ

በመሆኑ ክልሎች/ከተማ አስተዳደሮች ፕሮጀክቶችን መዝግበው እንዳይዙ እንቅፋት የፈጠረ መሆኑ፤

- የኮንስትራክሽን ቁጥጥር አዋጅ በረቂቅ ደረጃ የተዘጋጀ ቢሆንም በሚመለከተው አካል አፀድቆ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፤
- በመመሪያ ቁጥር 648/2013 ለብቃት ማረጋገጫ አሰጣጡ እንደተግዳሮት ይነሱ የነበሩ ነጥቦችን ለማሻሻል ረቂቅ የመመሪያ ማሻሻያ ያዘጋጀ ቢሆንም በሚመለከተው አካል አፀድቆ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፤

ለሥራ ተቋራጮች የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አሰጣጥን በተመለከተ

20. ባለስልጣን መ/ቤቱ ለሁሉም አይነት ሥራ ተቋራጮች (ጠቅላላ፣ የህንፃ፣ የመንገድ እና ልዩ ሥራ ተቋራጭ) የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ሲሰጥ በየደረጃው የተቀመጠውን መስፈርት (ማሽነሪ፣ አመታዊ ተርንኦቨርና የሰው ኃይል…) ያሟሉ መሆኑ የሚያረጋግጥበት የአሠራር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
21. በኦዲቱ ወቅት በናሙና የተመረጡ በቀድሞው መመሪያ ቁጥር 19/2006 መሰረት የብቃት ማረጋገጫ የወሰዱ 40 እና በአሁኑ መመሪያ ቁጥር 648/13 መሰረት የብቃት ማረጋገጫ የወሰዱ 40 በአጠቃላይ 80 የሥራ ተቋራጮች የግል ማህደር ሲከለስ የሚከተሉት ታይተዋል ፡፡
    - በየደረጃው የተቀመጠውን የሰው ሀይል፣ የተሽከርካሪና ማሽነሪ መጠን ሳያሟላ የደረጃ-3 የብቃት ማረጋገጫ የተሰጠው አንድ ሥራ ተቋራጭ መኖሩ፤
    - የማሽነሪ ቴክኒካል ምርመራ ማስረጃ ሳያቀርቡ እና ሳያድሱ ከአንድ ደረጃ ወደ ሌላ ደረጃ እንዲያድጉ የተደረጉ 2 ሥራ ተቋራጮች መኖራቸው፤
    - በናሙና የታዩ ሁሉም ሥራ ተቋራጮች የብቃት ማረጋገጫ ለመውሰድ በሰው ኃይል መስፈርትነት የሚያቀርቧቸው ባለሙያዎች እና በልዩ ሁኔታ የስራ ተቋራጭነት የብቃት ማረጋገጫ የተሰጣቸው ባለሙያዎች የሚያቅርቡት የስራ ልምድ ግብር የተከፈለበት ስለመሆኑ ማስረጃ መጠየቅ ያለበት ቢሆንም በመመሪያው በመስፈርትነት ያልተቀመጠ መሆኑ፤
    - በመመሪያ 648/13 መሰረት የብቃት ማረጋገጫ ከተሰጣቸው በናሙና ከታዩ 40 ሥራ ተቋራጮች ውስጥ አንድ ሥራ ተቋራጭ ለሰው ኃይል መስፈርትነት ያቀረበው ባለሙያ የትምህርት ማስረጃው እና የሙያ ምዝገባ ሰርተፊኬቱ

በተለያየ ሰው ሆኖ እንደ አንድ ሰው ማስረጃ የቀረበና ተቀባይነትን ያገኘ መሆኑ ፤

- ❖ በማህበር ተደራጅተው የደረጃ አምስት ሥራ ተቋራጭነት ሲወስዱ የማህበሩ አባል ያልሆነን ሰው መታወቂያ አስይዘው የብቃት ማረጋገጫውን የወሰዱ መሆኑ፤
- ❖ በተለያዩ ደረጃዎች በልዩ ሁኔታ በብቃት አሰጣጥ መመሪያው አንቀፅ 27 መሰረት ከተሰጣቸው ባለሙያዎች ውስጥ አንድ ባለሙያ የተሰጠውን ደረጃ-5 ሊያሰጥ የሚያስችል በራሱ ወይም በተቆጣጣሪነት የሰራውን ሥራ የሚያሳይ ማስረጃ ያላቀረበ መሆኑ፤
- ❖ በየደረጃው የተቀመጠውን የተሽከርካሪና ማሽነሪ መጠን በመስፈርቱ መሰረት ሳያሟላ በብዛት ያለውን ብቻ በማቅረብ፣ ማሽንን በተሽከርካሪ በማተካካት ከሚያዚያ 2013 ዓ.ም በኋላ የብቃት ማረጋገጫ የተሰጠው ሥራ ተቋራጭ መኖሩ፤
- ❖ ከሚያዚያ 2013 ዓ.ም በኋላ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የደረጃ ማሻሻያ ያደረጉ ተርን ኦቨር ማቅረብ የነበረባቸው 4 ሥራ ተቋራጮች የድርጅቱን ተርን ኦቨር የሚያሳይ በውጭ ኦዲተር የተረጋገጠ ማስረጃ እንዲያቀርቡ ያልተደረገ መሆኑ፤
- ❖ በናሙና ለታዩ 10 ልዩ ስራ ተቋራጮች የተሰጠው የብቃት ማረጋገጫ ዘርፍ እና መመሪያ ላይ የተቀመጠው ዘርፍ ባለመመሳሰሉ የተሰጡትን የብቃት ማረጋገጫዎች በተቀመጠው መስፈርት መሰርት ለመገምገም ያልተቻለ መሆኑ፤ ለማወቅ ተችሏል፡፡

ለውጭ አገር ሥራተቋራጮች የሚደረገውን ቁጥጥርና ክትትል በተመለከተ

22. ባለሥልጣን መ/ቤቱ በሁሉም አይነት ሥራ ተቋራጭነት (ጠቅላላ፣ የህንፃ፣ የመንገድ እና ልዩ ሥራ ተቋራጭ) ለሚሳተፉ የውጭ አገር ሥራ ተቋራጮች በመመሪያው በተቀመጠው መስፈርት መሰረት የብቃት ማረጋገጫ በመስጠት ቁጥጥርና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡
23. በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች ለመረዳት እንደተቻለው፡-
    - ❖ በጠቅላላ፣ በህንፃ፣ በመንገድ እና በልዩ ሥራ ተቋራጭነት ዘርፍ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ወስደው እየተንቀሳቀሱ የሚገኙ 261 የውጭ አገር

ሥራ ተቋራጮች እንዳሉ ከኢንቨስትመንት ኮሚሽን የተገኘ መረጃ የሚያሳይ ቢሆንም ከ14 ሥራ ተቋራጮች ውጪ በሀገሪቱ የሚንቀሳቀሱ ሁሉንም የውጭ አገር ሥራ ተቋራጮች በምዝገባ መመሪያው በተቀመጠው መስፈርት መሰረት የብቃት ማረጋገጫ በመስጠት ቁጥጥርና ክትትል እየተደረገ አለመሆኑ፤

- ❖ በመመሪያ ቁጥር 648/13 መሰረት በደረጃ አንድ ሥራ ተቋራጭነት (በጠቅላላ፣ በህንፃ፣ በመንገድ እና በልዩ) የብቃት ማረጋገጫ የተሰጣቸው 10 የውጭ አገር ሥራ ተቋራጮች የግል ማህደር ተወስዶ ከታዩ ሥራ ተቋራጮች ውስጥ ለደረጃ አንድ የተቀመጠውን የሰው ሀይል፣ የተሽከርካሪና ማሽነሪ መጠን በተቀመጠው መስፈርት መሰረት ሳያሟሉ እና በማሽን ቦታ ተሽከርካሪ በማተካካት የብቃት ማረጋገጫ የተሰጣቸው 3 ሥራ ተቋራጮች መኖራቸው፤
- ❖ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ለመውሰድ በሰው ኃይል መስፈርትነት የሚቀርቡ ባለሙያዎች የሚያቅርቡት የስራ ልምድ ግብር የተከፈለበት ስለመሆኑ ማስረጃ የማይጠየቅ መሆኑ፤በመስፈርቱ የተቀመጠውን ተርን ኦቨር ሳያሟሉ እና የተለያዩ ፕሮጀክቶችን ያጠናቀቁ መሆንን የሚያሳይ ማስረጃ፣ የመኖሪያ ፈቃድ የሚያሳይ ማስረጃ ያላቀረቡ ሥራ ተቋራጮች መኖራቸው፤ የሚሉ ናቸው፡፡

ከላይ ለተገኙት ክፍተቶች ለማሻሻል አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ተብሎ የታመነባቸው የማሻሻያ ሃሣቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- ❖ ባለሥልጣን መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በመንግሰት በጀት የሚገነቡ ፕሮጀክቶችን አጠቃላይ መረጃ በመያዝ በፕሮጀክቶች መቋረጥ እየደረሰ ያለውን ከፍተኛ የገንዘብና የንብረት ብክነት እና የአገልግሎት አቅርቦት ችግር ከመሰረቱ ሊፈታ የሚያስችል አሰራር ሥርዓት ዘርግቶ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ኃላፊነታቸውን የማይወጡ የፕሮጀክት ባለቤቶች እና ሥራ ተቋራጮች ላይ የእርምት እርምጃ የሚወስድበት አሰራር ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል፡፡
- ❖ ባለስልጣን መ/ቤቱ ለፕሮጀክቶች መልካም አፈፃፀም ሲባል የመንግስትን ፕሮጀክት የሚሰሩ ተቋራጮች አስቀድመው በወሰዱት ፕሮጀክት ላይ ያሳዩት አፈፃፀም በቀጣይ የሚወዳደሩበት ፕሮጀክት ለማሸነፍ እንደመስፈርት እንዲገባ በማድረግ ተቋራጮችን የያዙትን ፕሮጀክት ጊዜውንና ጥራቱን ጠብቀው በኃላፊነት መስራት ለቀጣይ ሥራዎች ዋስትና መሆኑን እንዲገነዘቡ የሚያስችል

የአሰራር ስርዓት ሊዘርጋ የሚያስችለውን የህግ ማዕቀፍ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆኑ ማዘጋጀት ይገባል፡፡

❖ ባለሥልጣን መ/ቤቱ ውለታቸው ተቋርጦ ረጅም ጊዜ ያስቆጠሩ ፕሮጀክቶች ለዘላቂ የጥራት ችግር እየተጋለጡ በመሆኑ ከፕሮጀክት ባለቤቶች እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ውይይቶችን በማድረግ በአጭር ጊዜ ውስጥ የመፍትሔ አቅጣጫዎችን ሊያስቀምጥ ይገባል፡፡

❖ ባለሥልጣን መ/ቤቱ በገቡት ውል መሰረት ግዴታቸውን ሳይወጡ ፕሮጀክቶችን አቋርጠው ከሄዱ ሥራ ተቋራጮች ለመንግስት ገቢ መደረግ የነበረበት የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና (PerformanceGuarantees)ገቢ እንዲደረግ ከፕሮጀክት ባለቤቶች እና ከሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ጠንካራ የክትትል ሥራ መስራት ይኖርበታል፡፡

❖ ባለሥልጣን መ/ቤቱ ጠንካራ ክትትል በማድረግ ለተቋረጡ ፕሮጀክቶች የተከፈለው የቅድመ ክፍያ ተመላሽ ሆኖ ለሌሎች የልማት ሥራዎች እንዲውል ማድረግ ይኖርበታል፡፡

❖ ባለሥልጣን መ/ቤቱ ገንዘብ አውጥቶ ያስጠናቸውን ጥናቶች ወደ መመሪያና ማንዋሎች በመቀየር በተጠናላቸው አላማ መሰረት እንዲተገበሩ ሊያደርግ ይገባል፡ ፡

❖ ባለሥልጣን መ/ቤቱ በደንብ ቁጥር 439/2011 እና 524/2015 በተሰጠው ኃላፊነት መሰረት በአካባቢ ፣በባህላዊ ቅርሶች፣በሠራተኞች እና በህብረተሰቡ ጤንነትና ደህንነት ላይ እየደረሰ ያለውን ከፍተኛ ጉዳት ለመከላከል የሚያስችል ጠንካራ የቁጥጥርና ክትትል ሥርዓት ዘርግቶ ኃላፊነቱን መወጣት ይኖርበታል፡፡

❖ ባለሥልጣን መ/ቤቱ የግል ድርጅቶች በሚያሰሯቸው የፕሮጀክት ውሎች ላይ የአካባቢን፣ የሠራተኞችን እና የህብረተሰቡን ጤንነትና ደህንነት የሚመለከቱ ጉዳዮች ተካተው ተግባራዊ እየተደረጉ መሆኑን ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ የእርምት እርምጃ የሚወስድበት አሰራር ሊዘረጋ ይገባል፡፡

❖ ባለሥልጣን መስሪያ ቤቱ እንደ ሀገር በኮንስትራክሽን ስራዎችና ግንባታዎች ላይ እየደረሱ ያሉ የአደጋ አጋጣሚዎችን ክትትል በማድረግ ገለጭ በሆነ መልኩ በየትኛው ፕሮጀክት ምን አይነት አደጋ እንደደረሰ የሚያሳይ የተደራጀ መረጃ

በመያዝ ተጎጅዎች ወቅቱን የጠበቀ መፍትሔ እዲያገኙ እና የህግ ተጠያቂነት እንዲኖር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ሊሰራ ይገባል፡፡

❖ ባለሥልጣን መ/ቤቱ በደንብ ቁጥር 439/2011እና524/2015 በተሰጠው የመቆጣጠር ኃላፊነት መሰረት የፕሮጀክት ባለቤቶችን እንደየጥፋታቸው ደረጃ ተጠያቂ ማድረግ የሚያስችል የፕሮጀክት ቁጥጥርና አፈፃፀም መመሪያ፣ለሥራ ተቋራጮች ብቃት ማረጋገጫ ከተሰጠ በኋላ ክትትልና ቁጥጥር የሚደረግበት መመሪያ፣የባለሥልጣኑን እና የክልሎችን ሚና በግልፅ ለይቶ የሚያስቀምጥ የፕሮጀክት ምዝገባ መመሪያ አዘጋጅቶ በማፅደቅ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

❖ ባለሥልጣን መ/ቤቱ በጠቅላላ፣ በህንፃ፣ በመንገድ ሥራ እና በልዩ ሥራ ተቋራጭነት የብቃት ማረጋገጫ ሲሰጥና ደረጃ ሲያድጉ በየደረጃው በአነስተኛ መስፈርትነት የተቀመጠውን የማሽነሪና የተሽከርካሪ፣የሰው ኃይል፣አመታዊ ተርንኦቨር….ወዘተ ያሚሉ መሆኑ፣ ከሌሎች የመንግስትና የግል ተቋማት የሚቀርቡ የሰነድ ማስጃዎች ትክክለኛ መሆናቸውን ለማረጋገጥ እና የታዩ ክፍተቶችን ለማረም የሚረዳ የአሠራር ሥርዓት ተዘርግቶ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

❖ ባለሥልጣን መ/ቤቱ በጠቅላላ፣በህንፃ፣በመንገድ እና በልዩ ሥራ ተቋራጭነት ዘርፍ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ወስደው እየተንቀሳቀሱ ለሚገኙ ሁሉም የውጭ አገር ሥራ ተቋራጮች በመመሪያው በተቀመጠው መስፈርት መሰረት የብቃት ማረጋገጫ በመስጠት እና በሌሎች የሀገሪቱ ህጎች ላይ ለውጭ አገር ድርጅቶች የተቀመጡ ቅድመ ሆኔታዎችን(የሀገር ውስጥ ባለሙያዎችን እያሳተፉ መሆኑን፣ በዘርፉ የቴክኖሎጅ ወይም ዕውቀት ሽግግር መደረጉን…ወዘተ) በተመለከተ ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት በመስራት ጠንካራ ቁጥጥርና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

❖ ባለሥልጣን መ/ቤቱ በሁሉም ዓይነት የስራ ተቋራጭነት የብቃት ማረጋገጫ ለመውሰድ እና ደረጃቸውን ለማሳደግ የሚመጡ ሥራ ተቋራጮች በሰነድ የሚያቀርቧቸው መሳሪያዎች፣ ተሽከርካሪዎችና የሰው ኃይል በአካል መኖራቸውን የሚያረጋግጥበት፣ከተሠጣቸው ደረጃ ውጭ የሚሰሩ የሥራ ተቋራጮች እንዳይኖሩ፣ እንዲሁም የብቃት ማረጋገጫቸውን ለሌላ አካል አሳልፈው የሚሰጡ የስራ ተቋራጮችን በቅድሚያ ለመከላከል የሚያስችል፣ ወደ ህገ ወጥ ሥራ ገብተው

ሲገኙም እርምጃ የሚወሰድበት የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

- ❖ ባለሥልጣን መ/ቤቱ እድሳት ለማድረግ የሚመጡ ሥራ ተቋራጮች በሰነድ የሚያቀርቧቸው ማሽነሪዎችና ተሽከርካሪዎች እንዲሁም የሰው ኃይል በአካል መኖራቸው በክትትልና ቁጥጥር ሪፖርት ከተረጋገጠ በኋላ እድሳት ሊያድርግ ይገባል፡፡
- ❖ በፌደራል እና በክልሎች፣በከተማ አስተዳደሮች ያለው በየደረጃው የሚከናወነው የስራ ተቋራጮች የብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥ፣የቁጥጥር እና የምዝገባ ሥራ ተመጋጋቢና ተደጋጋፊ በሆነ መልኩ ለመምራት የሚያስችል ተመሳሳይ ስታንዳርድ በማዘጋጀት እና ክልሎች ወጥ በሆነ መልኩ እንዲጠቀሙበት ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ❖ በባለስልጣን መ/ቤቱ በአሁኑ ወቅት እየተሰጠ ያለውን የብቃት አሰጣጥና ምዝገባ አገልግሎት የቃኘ ስታንዳርድ በማዘጋጀት ዘርፉ እንዲጠቀምበት ሊያደርግ ይገባል፡፡

በኢትዮጵያ ማሪታይም ባለሥልጣን
የሞጆ ሎጅስቲክስ ማዕከል ፕሮጀክት አፈፃፀምን
በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት ላይ የተዘጋጀ ዘገባ

የሞጆ አረንጓዴ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክት በጥናት ላይ የተመሰረተ የዲዛይንና የግንባታ ውል አስተዳደር በተመለከተ

1. የሞጆ አረንጓዴ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክት በጥናት ላይ የተመሰረተ የዲዛይንና የግንባታ ውል አስተዳደር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል።
2. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ መጠይቶች እንደተገኘው ባለስልጣን መ/ቤቱ የሞጆ አረንጓዴ ሎጂስቲክስ ማዕከል ፕሮጀክት ግንባታ ላይ በተደረገ የአማካሪዎች ጨረታ ሴሌሆርን-ኤችፒሲ ጄ.ቪ. / Sellehorn-HPC JV/ አሸናፊ ሲሆን፤ የፍላጎት ትንተና፤ ማስተር ፕላን፤ ዝርዝር ዲዛይን እና የጨረታ ሰነድ አዘጋጅቶ በስድስት ወራት አጠናቆ ለማስረከብ ውል የፈረመ ቢሆንም በውሉ መሰረት ያላከናወነ መሆኑ ለማሳያ ያህል፡-

☞ (በሴሌሆርን-ኤችፒሲ ጄ.ቪ) Sellehorn-HPC JV የተሰራ የሎጂስቲክስ መሰረተ ልማት የምህንድስና ዝርዝር ዲዛይን፣ የግንባታ ቁጥጥር እና የውል አስተዳደር አገልግሎቶችን ያላሟላ፤ እንዲሁም ፕሮጀክቱ መጀመሪያ ዓመት ላይ በውሉ መሠረት የተሟላ ዲዛይን ሰርቶ ማስረከብ ያልቻለ መሆኑ፣

☞ ሴሌሆርን-ኤችፒሲ ጄ.ቪ /Sellehorn-HPC JV/ ውሉን አቋርጦ ከወጣ በኋላ ዲዛይኑን እንዲሰሩ በመ/ቤቱ በኩል የተወከሉ ባለሙያዎች የሰሩት ዲዛይን ኮንትራክተሩ ሥራውን ለመስራት ወደ ሳይት በገባበት ወቅት ሊያሰራው ያልቻለ መሆኑ፣ ለማሳያ ያህል የመንገድ የሌቭሊንግ ችግር፣ የድሬኔጅ ችግር፣ የፋየርፋይቲንግ እና የእስትራክቸር ችግር እንዲሁም የአካባቢው አፈር የመሰነጣጠቅ እና ወደ ውስጥ የመንሸራተት ባህሪ የነበረበት መሆኑ መገለፁ፣

☞ ሴሌሆርን-ኤችፒሲ ጄ.ቪ /Sellehorn-HPC JV/ በሞጆ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክት ከንድፍ ጋር የተያያዙ ችግሮች መኖራቸው ለማሳያ ኦርጂናል የተሳለው ዲዛይን እና ማስተር ፕላኑ የተሟላና ግልጽ አለመሆኑን ነሐሴ 2014 ዓ.ም በቀረበው የሂደት ሪፖርት (progress report) የተመላከተ መሆኑ፣

☞ የፕሮጀክቱ የመጀመሪያው አርክቴክቸር ዲዛይን የግንባታ ሳይቱን አጠቃላይ ገጽታ፣ የሎጀስቲክስ ግንባታ ቦታ እና በዙርያው ያሉ ነገሮችን በፍጥነት ለመረዳት የሚያስችለው የድሮዊንግ ርዕስ (drawing Title) የጎደለው መሆኑ፤

☞ በሎጂስቲክስ መሰረተ ልማት አፈፃፀም የዲዛይንና የግንባታ ፕሮጀክቶች ኮንትራት አስተዳደር ችግር መኖሩ በማሪታይም እና ሎጂስቲክስ ዘርፍ የአምስት ዓመት ስትራቴጅክ ዕቅድ ላይ የተመላከተ መሆኑ፣

☞ አብዛኞቹ የግንባታ ውል ሥዕሎች (contract drawings) የተሟሉ እና ግልፅ ያልሆኑ መሆናቸው፤

ባለስልጠን መ/ቤቱ በጨረታ ተወዳዳሪዎች ቅድመ-ብቃት ምዘና ማድረጉን በተመለከተ

3. ባለስልጣን መ/ቤቱ በጨረታ ተወዳዳሪዎች ላይ ቅድመ-ብቃት /Pre-qualification/ ምዘና ማድረግ ይኖርበታል፡፡

   ✍ የፕሮጀክቱ የግምገማ ሰነድ ሲዘጋጅ የጨረታ ቅድመ ብቃት እና ድህረ ብቃት የማወዳደርያ ዘዴዎች እንዳስፈላጊነቱ መጠቀም በሚያስችል መልኩ እቅድ ላይ ሳይካተት የጸደቀ መሆኑ፣

- ባለስልጣን መ/ቤቱ ውስብስብ ለሆኑ ለፕሮጀክት ስራዎች የግዥ ምዘና ሲያከናውን የትኛውን ግዥ በቅድመ ብቃት ምዘና እና በድህረ ብቃት ምዘና ስርአትን መጠቀም እንደሚገባ ተለይቶ ያልተቀመጠ መሆኑ፣
- በሞጆ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክት የTOS/GOS የጨረታ ሂደት በድህረ ብቃት ምዘና /Post Qualification/ መሰረት ጨረታው የተደረገ ቢሆንም ፕሮጀክቱ አሁን ላይ ስራ የጀመረ ቢሆንም መጀመር ከነበረበት ጊዜ በላይ የዘገየ መሆኑ፣ለማወቅ ተችሏል፡፡

ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ተቋራጭ እና አማካሪው በውሉ መሰረት ስራቸውን በወቅቱ መጀመራቸውን በተመለከተ፡፡

4. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ተቋራጭ እና አማካሪ ተቋም በውሉ መሰረት ስራቸውን በተቀመጠው ግዜ መጀመራቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡
    - ባለስልጣን መ/ቤቱ በዚሁ መሰረት በውል ስምምነት ልዩ ሁኔታዎች (Particular Condition) ሥራ መጀመሩን የተከታተለ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ፡- የምህንድስና አማካሪው ኢፐቲሳ ሰርቪሲዮስ ዲ ኢንጂነርያ ለአራት ወራት ያህል ዘግይቶ በመግባቱ የግንባታ ስራው እንዲዘገይና የግንባታ ቁጥጥር ስራውም በእቅዱ መሰረት ካልተከናወኑት ተግባራት ውስጥ እንዲሆን ያደረገው መሆኑን፣

ባለስልጣን መ/ቤቱ የፕሮጀክት አስተዳደር ማኑዋል ማዘጋጀቱንና ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ

5. ባለስልጣን መ/ቤቱ የፕሮጀክት አስተዳደር ማኑዋል/Project Administrative Manual/ በማዘጋጀት እና በሚመለከተው አካል በማፀደቅ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
6. ይሁን እንጅ በኦዲቱ ወቅት፡-
    - በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ቀድሞ ተግባራዊ የሆነው የፕሮጀክት አስተዳደር ማኑዋል/Project Administrative Manual/ ከ6 አመት በላይ የቆየ እና ወቅቱን ያላገናዘበ ሲሆን በእ.ኤ.አ መጋቢት 2021 ተከልሶ የቀረበው የፕሮጀክት አስተዳደር ማኑዋል /Project Administrative Manual/ ያለ ቢሆንም በሚመለከተው አካል ጸድቆ ወደ ሥራ ያልገባ መሆኑ እንዲሁም በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ተሻሽሎ የቀረበውም ቢሆን ለሚመለከተው አካል ቀርቦ ያልጸደቀ መሆኑ፣
    - ስራ ተቋራጩ ሊያቀርብ የሚገባው ማንዋል American Society for Testing Materials (ASTM) Standards, Deutsches Institut for Normung e.V. (DIN) Standards,

British Standard (BS), American Concrete Institute(ACI) Standards, ባለመቅረቡ ቴክኒካል ስራዎችን አዛምዶ ማረጋገጥ ያልቻለ መሆኑ፣

የሞጆ አረንጓዴ ሎጂስቲክስ ማዕከል ግንባታ ፕሮጀክቶች በዕቅድ በተያዘለት የጊዜ ሰሌዳና ጥራት መሰራቱን በተመለከተ

7. የሞጆ አረንጓዴ ሎጂስቲክስ ማዕከል ግንባታ ፕሮጀክት በተገባው የኮንትራት ውል መሰረት በዕቅድ በተያዘለት የጊዜ ሰሌዳና ጥራት ሊጠናቀቅ ይገባል።

- ፕሮጅክቱ እ.ኤ.አ መጋቢት 2017 ተጀምሮ ሐምሌ 2023 ይጠናቀቃል ተብሎ የታቀደ ቢሆንም በይፋ ስራ ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ እስከ 2016 የሁለተኛው ሩብ በጀት ዓመት ድረስ ጠቅላላ የፕሮጀክቱ አፈጻጸም 61.51% ብቻ በመሆኑ ከዕቅድ አንፃር ሲታይ ፕሮጀክቱ የዘገየ መሆኑ፤
- የመሰረተ-ልማት ማሻሻያ ስራው በ2013 በጀት ዓመት መጨረሻ ከደረሰበት 30.92% የክንውን አፈፃፀም በበጀት ዓመቱ 15.82% በማከናወን አጠቃላይ ስራውን 46.74% ለማድረስ ታቅዶ የነበረ ቢሆንም በበጀት አመቱ 2.31% ብቻ የተከናወነ መሆኑ፣
- በሞጆ ደረቅ ወደብ የሚከናወነው የመሰረተ ልማት ማስፋፊያ ስራ በ2014 በጀት ዓመት መጨረሻ ከደረሰበት 33.23% በ2015 በበጀት ዓመት 30.06% በማከናወን በበጀት ዓመቱ መጨረሻ 63.29% ለማድረስ ታቅዶ የነበረ ቢሆንም በበጀት ዓመቱ 17.53% ብቻ ተከናውኖ አጠቃላይ አፈጻጸሙ ዝቅተኛ መሆኑ፣
- በሎጂስቲክስ መሰረተ ልማት አፈፃፀም የምህንድስና ግዥ ክፍተት መኖሩ፣ ለማሳያ፡- በ2013 በጀት ዓመት የሲቪል ግንባታ የግዥ ሂደት ተጠናቆ የግንባታ ስራው 8.3% ያህሉ ይጠናቀቃል ተብሎ ታቅዶ የነበረ ቢሆንም የግዥ ሂደቱ በታሰበው ጊዜ ያልተጠናቀቀ መሆኑ እና የግንባታ ስራውም የዘገየ መሆኑ፣
- በ2014 በጀት ዓመት የሲቪል ግንባታ የጨረታ ሂደት ተጠናቆና ውል ተፈርሞ የግንባታ ስራው በበጀት ዓመቱ 18.21% ይደርሳል ተብሎ ታቅዶ የነበረ ቢሆንም 3% ብቻ የተከናወነ መሆኑ፣
- በ2015 በጀት ዓመት የሲቪል ግንባታ ስራ ከነበረበት 2.5% በበጀት ዓመቱ ውስጥ 33.72% በማከናወን 36.22% ላማድረስ ታቅዶ 23.80% ብቻ የተከናወነ በመሆኑ አፈፃፀሙን ዝቅተኛ መሆኑ፣
- የአይ.ሲ.ቲ. መሰረተ-ልማት ማስፋፋትን በተመለከተ፡- የተለያዩ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅ ስራዎችን በማከናወን በዘርፉ ያለውን ቅንጅታዊ አሰራር ለማሻሻል ስራው በ2014 በጀት ዓመት ከደረሰበት 42.04% በ2015 በጀት ዓመት 23.24% በማከናወን 65.28% ለማድረስ ታቅዶ የነበረ ቢሆንም በበጀት ዓመቱ 2.09% ብቻ ተከናውኖ አጠቃላይ አፈጻጸሙ ዝቅተኛ መሆኑ።

- የTerminal Operating System (TOS)፣ Gate Operating System (GOS) እና የPort Community System (PCS) በ2014 በጀት ዓመት 4.62 ለማከናወን ታቅዶ አመታዊ አፈፃፀሙ ዜሮ መሆኑ፣
- የTOS-GOS ስራው እንዲሰጠው ከተደረገው JV CCECC, with Huadong Electron and CSI እ. አ .አ ጁላይ(ሐምሌ) 5 2023 የውል ስምምነት የተደረገ ቢሆንም ውሉ ተፈርሞ አምስት ወር ያለፈው ሲሆን ስራው ግን በአግባቡና በውሉ መሰረት እየተከናወነ አለመሆኑ እና ተገቢ ክትትል ያልተደረገበት መሆኑ፤
- ከፕሮጀክቱ ሰራተኞች ወደ ተጫራጮች የTOS-GOS ሚስጥራዊ መረጃዎች ሾልከው በመውጣታቸው እስኪጣራ ድረስ በሚል ሰበብ የውል ስምምነት ከሚገባው በላይ መዘግየቱ በ2015 በጀት ዓመት ዕቅድ ሪፖርት ላይ የተመላከተ መሆኑ።
- የፕሮጀክቱን ግዥዎች ለማከናወን የተቀመጡ የግዥ ሂደቶች የሚወስዱት ጊዜ ከታሰበው በላይ የፕሮጀክቱን የትግበራ ጊዜ ማራዘሙ እና የግዥ ሂደቱ ሊወስድ የሚችለው ጊዜ ግንዛቤ ውስጥ አለመግባቱ በፕሮጀክቱ አፈፃፀም ላይ ተፅዕኖ የፈጠረ መሆኑ

የፕሮጀክት ስትሪንግ ኮሚቴን በተመለከተ

8. የፕሮጀክት ስትሪንግ ኮሚቴው ለፕሮጀክቱ አፈፃፀም የሚረዱ የፖሊሲ አቅጣጫዎችን ሊያመላክት፣ ዕቅድ እና በጀትን ገምግሞ ሊያፀድቅ እንዲሁም የፕሮጀክቱን አፈፃፀም በበላይ ሆኖ ሊከታተል እና ሊገመግም ይገባል።
9. ይሁን እንጂ ጉዳዩን አስመልክቶ የኦዲት ቡድኑ ባካሄዳቸው የሰነድ ክለሳዎች መሰረት የሚከተሉት ክፍተቶች ተለይተዋል፡-
   - የፕሮጀክት ስትሪንግ ኮሚቴ እንደ ኮሚቴ የፕሮጀክቱን እንቅስቃሴ በመስክ ላይ በመገኘት የፕሮጀክቱ ተግባራት ያሉበትን ደረጃ ገምግሞ አቅጣጫዎችን የማስቀመጥ እና የውሳኔ ሃሳብ ያልሰጠ መሆኑ፣
   - ስትሪንግ ኮሚቴው ለፕሮጀክቱ ጠቀሜታ ሲባል ከተለያዩ አካላት ጋር የትብብር ግንኙነቶች እንዲኖሩ ያላደረገ መሆኑ እና የፕሮጀክቱ ስራዎች በጊዜው እንዲከናወኑ የፖሊሲ አቅጣጫዎችን ያላስቀመጠ እንዲሁም የፕሮጀክቱን ባለድረሻ አካላት/stakeholders/ በተፈለገው ጊዜ በአንድ ላይ መገኘት አለመቻልና ፕሮጀክቱ ላይ ባጋጠሙ ችግሮችና መፍትዎቻችው ዙሪያ በጋራ መወያየት ያልተቻለ መሆኑ።
   - የፕሮጀክት አስተባባሪ ኮሚቴው (PSC) የፕሮጀክቱን ስራዎች በበላይ ሆኖ ለመገምገም፣ ቁጥጥር እና ክትትል ለማድረግ እንዲሁም የዓመታዊ የሥራ ዕቅዶችን እና በጀትን ለማፅደቅ በመደበኛነት የማይሰበሰብ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል።

የዳኝነት ቦርድ ማቋቋሙን በተመለከተ

10.በባለስልጣን መ/ቤቱ እና ኮንትራክተሩ የጋራ የሆነ ያለመግባባትን የሚፈታ/ የዳኝነት ቦርድ (Dispute Avoidance/Adjudication Board) ሊያቋቁሙ ይገባል፡፡

11.በዚሁ መሰረት የፈፀመ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ፡-

- በባለስልጣን መ/ቤቱ እና ኮንትራክተሩ የጋራ የሆነ ያለመግባባትን የሚፈታ /የዳኝነት ቦርድ ውሉ በተፈረመ በ42 ቀን ውስጥ መቋቋም ቢኖርበትም (Dispute Avoidance/Adjudication Board) ያልተቋቋመ መሆኑ፣
- በአሰሪው ተቋም እና በስራ ተቋራጩ የውል የሂሳብ ዝርዝር (Bill of Quantity) ላይ በአሰሪው ተቋም በኩል ለዳኝነት ቦርድ አባላት ተብሎ 3 ሚሊዮን ብር በጀት የተያዘ ቢሆንም ለታለመለት አላማ እየዋለ አለመሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ የሰነድ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

ከላይ ለተገኙት ክፍተቶች ለማሻሻል አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ተብሎ የታመነባቸው የማሻሻያ ሃሣቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- የኢትዮጵያ ማሪታይም ባለስልጣን የሞጆ ሎጂስቲክስ ማዕከል ፕሮጀክትን ሲተገብር የቅድመ አዋጭነት እና የአዋጭነት ጥናት በማስጠናት፣ የፕሮጀክት ግምገማ ሰነድ እና የፕሮጅክት ትግበራዎች በቅድም ተከተል በማከናወን በጥልቅ በተጠና ዲዛይን ሥራውን መስራት በሀገር ውስጥ ለሚተገበሩ ማናቸውም የግንባታ ፕሮጀክቶች ውጤታማ እንዲሆኑ ሲለሚያስችል፣ የሞጆ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክትም ሆነ ወደ ፊት በብድር እና በመንግስት ፋይናንስ የሚሰሩ ትላልቅ ሀገራዊ ፕሮጀክቶች በጥናት ላይ የተመሰረተ የዲዛይንና የግንባታ ኮንትራት አስተዳደር ስርዓት ሊኖራቸው ይገባል፡፡
- የግንባታ ፕሮጀክቶች ስራን ለመተግበር የተሟላ የዲዛይን ንድፍ መንደፍ ወጪን ለመቀነስ፣ በጊዜ ለመጨረስ፣ አጠቃላይ ጥራትን ለማሻሻል እና የግንባታው ሂደቱን የበለጠ ውጤታማ መሆኑን ለማረጋገጥ እንዲሁም ሥራ ተቋራጭ እና አማካሪ ተቋም ስራቸውን በብቃት እንዲሰሩና የግንባታ ፕሮጀክቱ እንዴት እንደሚሠራ በቀላሉ እንዲረዱ የሚያግዝ በመሆኑ የሞጆ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክትም ሆነ ወደ ፊት በብድር እና በመንግስት ፋይናንስ የሚሰሩ ትላልቅ ሀገራዊ ፕሮጀክቶች ሲቀርፅ የፕሮጀክቱን ገፅታ በተገቢው መንገድ የሚሳይ ግልጽ እና የተሟላ ዲዛይን መነደፍ ይኖርበታል፡፡

❖ ፕሮጀክቱን በተሳካ ሁኔታ ለማጠናቀቅ ቅድመ-ብቃት /Pre-qualification/ ምዘናን በእቅድ ውስጥ በማካተት እንደ አማራጭ በመጠቀም መስራት ከፍተኛ ጥራት ያለው ሥራ ለማቅረብ፣ አስፈላጊ ክህሎት፣ ልምድ እና ግብዓት ያላቸውን ብቁ ተጫራቾች ለመለየት እንዲሁም ኮንትራቱ የፕሮጀክቱን መስፈርቶች ሟሟላት ለሚችል ተጫራች መሰጠቱን ለማረጋገጥ ይረዳል፡፡ በተጨማሪም ኮንትራክተሩ ወደ ሥራ ከመሰማራቱ በፊት ያለውን አደጋ ለመቀነስ እና ትላልቅ እና ውስብስብ ስራዎችን ለማከናወን የሚረዳ ሂደት በመሆኑ ባለስልጣን መ/ቤቱ የሞጆ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክትም ሆነ ወደ ፊት በብድር እና በመንግስት ፋይናንስ የሚሰሩ ትላልቅ ሀገራዊ ፕሮጀክቶችን ሲቀርፅ በጨረታ ተወዳዳሪዎች ላይ ቅድመ-ብቃት /Pre-qualification/ ምዘናን እንደ አንዱ የዕቅዱ አካል አድርጎ በማካተት መስራት ይኖርበታል፡፡

❖ ባለስልጣን መ/ቤቱ የሞጆ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክትም ሆነ ወደ ፊት በብድር እና በመንግስት ፋይናንስ የሚሰሩ ትላልቅ ሀገራዊ ፕሮጀክቶችን ሲቀርፅ ተቋራጭ እና አማካሪ ጨረታውን አሸንፈው ሥራውን ለመጀመር ውል በገቡበት ቀናት ውስጥ ሥራው መጀመሩን ሊከታተል ይገባል፡፡

❖ የፕሮጀክት አስተዳደር መመሪያ /Project Administrative Manual/ የፕሮጀክቶችን ሥራ በየደረጃው ለማከናወን፣ ለመከታተል፣ ለመገምገምና ለመቆጣጠር እንዲሁም የፕሮጀክቶች ትግበራን ለማቀላጠፍ እና ለግንባታ ፕሮጀክቶች የአስተዳደር ሂደቶችን፣ አሰራሮችን እና ኃላፊነቶችን ለመለየት እንዲሁም የፕሮጀክት ሥራዎች በቅድሚያ በተነደፈላቸው ስልት ወይም ዘዴ መሰረት እንዲከናወኑ፣ በተያዘላቸው እቅድ መሠረት እንዲጠናቀቁ እና የተቀረፁበትን ዓላማ እንዲያሳኩ አመቺ ሁኔታን የሚፈጥር በመሆኑ ባለስልጣን መ/ቤቱ የሞጆ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክትም ሆነ ወደ ፊት በብድር እና በመንግስት ፋይናንስ የሚሰሩ ትላልቅ ሀገራዊ ፕሮጀክቶችን ሲቀርፅ የፕሮጀክት አስተዳደር ማኑዋሉን በየግዜው ወቅታዊ በማድረግ እና በሚመለከተው አካል በማፀደቅ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

❖ አንድ የግንባታ ፕሮጀክት ውጤታማ ነው ለመባል በተያዘለት የጊዜ እቅድ እና በተመደበለት በጀት ማለቅ ሲችል በመሆኑ ይህ ትልቅ ሀገራዊ ፕሮጀክት ከአለም ባንክ በተገኘ ብድር የሚሰራ ፕሮጀክት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ፕሮጀክቱ በተያዘለት በጀት ስራዎችን በተገቢው መንገድ ሊከናወኑ ይገባል፡፡ እንዲሁም የፕሮጀክቱ

ስራዎች ሲከናወኑ ውጤታማ፣ ወጪ ቆጣቢ በሆነ መልኩ ሲተገበሩ አመርቂ ውጤት ስለሚያስገኝ ባለስልጠን መ/ቤቱ የሞጆ ሎጂስቲክስ ፕሮጀክትም ሆነ ወደ ፊት በብድር እና በመንግስት ፋይናንስ የሚሰሩ ትላልቅ ሀገራዊ ፕሮጀክቶችን ሲቀርፅ ፕሮጀክቶች በተገባው የኮንትራት ውል መሰረት በታቀደው የጊዜ ሰሌዳ እና ዋጋ (በጀት) እንዲጠናቀቁ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ❖ የፕሮጀክት ስትሪንግ ኮሚቴ እንደ ኮሚቴ የፕሮጀክት ጽ/ቤቱን ስራዎች በበላይነት ለመምራት በመደበኛነት በመሰብሰብ የፕሮጀክቱን ሥራዎች መከታተል፣ በመደገፍ፣ ምክር እና መመሪያ መስጠት፣ ጥራትን መቆጣጠር፣ አቅጣጫዎችን እና የውሳኔ ሃሳብ ማስተላለፍ ሃላፊነቱን መወጣት ይኖርበታል።
- ❖ የሞጆ ሎጅስቲክስ ማዕከል ግንባታ ፕሮጀክትን ለመገንባት ሲታቀድ በሎጅስቲክስ ግንባታው ሂደት በባለስልጣን መ/ቤቱ እና ስራ ተቋራጭ በሚጠበቅባቸው መብት እና ግዴታዎች ላይ ያሳለፉትን ውሳኔ እንዳይጥሱ እንዲሁም ለሚፈጠሩ አለመግባባቶች መፍትሄ የሚያስቀምጥ ከማንኛው ወገንተኝነት ነፃ እና ገለልተኛ አካል የሆነ የግልግል ዳኝነት (Dispute Avoidance/Adjudication Board) ውሉ መሰረት ሊያቋቋሙ ይገባል።

በኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን
የሬዲዮና የቴሌቪዥን የዜናና ወቅታዊ ጉዳዮች አገልግሎት አሰጣጥ አፈፀፃም ውጤታማነት በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት ዘገባ

የስራ አመራር ቦርዱ የራሱ የሆነ የአሰራር መመሪያ ማውጣቱን በተመለከተ

1. የኮርፖሬሽኑ የስራ አመራር ቦርድ የራሱ የሆነ የአሰራር መመሪያ ሊያወጣ ይገባል፡ ፡
2. ይሁን እንጂ የኮርፖሬሽኑ የስራ አመራር ቦርድ ስራዎችን ለመምራት የሚያስችለው የራሱ የሆነ የአሰራር መመሪያ የሌለው እና ያላወጣ መሆኑን ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ለስራ አመራር ቦርዱ ሰብሳቢ ከቀረበ ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

የኮርፖሬሽኑ የስራ አመራር ቦርድ አመራር የስብሰባ ጊዜን በተመለከተ

3. የኮርፖሬሽኑ ስራ አመራር ቦርድ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ሊሰበሰብ ይገባል፡፡

4. ይሁን እንጂ የኮርፖሬሽኑ ስራ አመራር ቦርድ ወቅቱን ጠብቆ ስብሰባውን የማያካሄድ መሆኑን፣ እንዲሁም ቦርዱ በ2013 ዓ.ም አንድ (1) ጊዜ ፤ በ2014 ዓ.ም ሶስት(3) ጊዜ እና በ2015 ዓ.ም ደግሞ ሁለት(2) ጊዜ ብቻ የስራ አመራር ቦርዱ የተሰበሰበ መሆኑን ከቦርዱ የስብሰባ ቃለ ጉባኤ ለማወቅ ተችሏል፡፡
5. በተጨማሪም ቦርዱ እንደየሁኔታው እና በአጀንዳዎች ሁኔታ አሳሳቢነት የሚሰበሰብ መሆኑንና ቢያንስ በ3 ወር ስብሰባውን የሚያደርግ መሆኑን የቦርዱ ሰብሳቢ በቃለ መጠይቅ ወቅት ገልፀዋል፡፡

ኮርፖሬሽኑ የአርካይቭ ፖሊሲና የአፈፃፀም ማንዋል ያለው መሆኑን በተመለከተ

6. ኮርፖሬሽኑ የአርካይቭ ፖሊሲና የአፈፃፀም ማንዋል ሊኖረው ይገባል፡፡
7. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱት መረጃዎች እንደታየው፡-
    - የቴሌቪዥን አርካይቭን እስከ ህዳር 3/3/2016 ዓ.ም ድረስ አስራ አራት ሺህ ሰዓት ብቻ ፋይል ዲጂታላይዝድ የተደረገ መሆኑ፣
    - የቴሌቪዥን አርካይቭ እስከ አሁን ከአርባ ሺህ ሰዓት በላይ ፋይል ዲጂታላይዝድ ያልተደረገ መሆኑ፣
    - በኮርፖሬሽኑ የ2013-2017 ዓ.ም ስትራቴጂካያዊ ዕቅድ ላይ እንደተገለፀው ለአመታት ያከማቻቸውን አለም አቀፍ እና ሃገራዊ ፋይዳ ያላቸው መረጃዎችን ወደ ዲጂታል በመቀየር ለይዘት ስራዎች ግብአት በመፍጠር እንዲሁም ሃብት ለማግኘት ፕሮጀክት ቢቀርፅም ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፣
    - እንዲሁም በኮርፖሬሽኑ የ2013-2017ዓ.ም ስትራቴጂካያዊ ዕቅድ ላይ እንደተገለፀው የዲጂታል አርካይቭ ሲስተም አፕግሬድ በማድረግ ደረጃውን በማሻሻል ተደራሽነቱን በማረጋገጥ እንዲሁም የዲጂታል አርካይቭ ሀብትን ለገቢ ምንጭነት መጠቀም እንዲቻል ቢታቀድም ከተወሰኑ የኒውስ ሩም፤ ኤዲቲንግ ሲስተም ሶፍትዌር ማሻሻያ (upgrade) በስተቀር ሙሉ ለሙሉ በሚፈለገው ደረጃ ያልተከናወነ መሆኑን ከተከለሱ ሰነዶች ለማወቅ ተችሏል፡፡

ኮርፖሬሽኑ የኤዲቶሪያል ፖሊሲውን መከለሱን በተመለከተ

8. ኮርፖሬሽኑ የሚዲያውን ኢንዱስትሪ እና የአገሪቱን የእድገት ሽግግር ከግምት ውስጥ በማስገባት የኤዲቶሪያል ፖሊሲው በየአምስት አመቱ ሊከለስ ይገባል ፡፡
9. ይሁን እንጂ የኢዲቶሪያል ፖሊሲው ከወጣ ከ10 አመት በላይ ቢሆንም በኮርፖሬሽኑ አንድም ጊዜ የሚዲያውን ኢንዱስትሪ እና የአገሪቱን የእድገት ሽግግር ከግምት ውስጥ

በማስገባት የኢዲቶሪያል ፖሊሲው ያልከለሰ መሆኑን ከተከለሱ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

ኮርፖሬሽኑ ኤዲቶሪያል ነፃነት በተጠበቀ ከማንኛውም አካል ነፃና ገለልተኛ መሆኑን በተመለከተ

10. ኮርፖሬሽኑ ኤዲቶሪያል ነፃነት በተጠበቀ እና በሥራውም ሆነ በአስተዳደሩ መንግሥትና የመንግሥት ተቋማትን ጨምሮ ከማንኛውም አካል ነፃና ገለልተኛ ሊሆን ይገባል ፡፡

11. ይሁን እንጂ ከተከለሱ ሰነዶች ለማወቅ እንደተቻለው ኮርፖሬሽኑ ከማንኛውም አካል ነፃና ገለልተኛ ሆኖ እየሰራ አለመሆኑን ከተከለሱ ሰነዶች እና ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ከቀረበ ቃለ መጠይቅ ለመረዳት ተችሏል፡፡ ለማሳያ ያህል፤

- ኮርፖሬሽኑ የመንግስትን የመልካም አስተዳደር ችግር የሚያጋልጥ ዜና ወይም ፕሮግራም ከሰራ ለምን ተብሎ ከመንግስት አካላት ስልክ የሚደወል መሆኑን መጋቢት 27/2015 ዓ.ም ከተካሄደው የስራ አመራር ቦርዱ የስብሰባ ቃለ ጉባኤ ለማወቅ ተችሏል፡፡
- በ2014 ዓ.ም የኮርፖሬሽኑ ፍኖተ ካርታ ላይ እንደተገለፀው የኮርፖሬሽኑ ዜናዎች ዋና ችግር በተቋሙ ውስጣዊና ውጫዊ ጫናዎች፣ ግለሰባዊና ፖለቲካዊ ግፊቶች የተነሳ አዲስ መረጃ ለሕዝብ ማቅረብ አለመቻሉ መገለፁ፤
- የኮርፖሬሽኑ ሥራ አመራር ቦርድ በነሀሴ 19/2015 ካደርገው ስብሰባ ቃለ ጉባኤ ለማወቅ እንደተቻለው የመንግስት አስፈፃሚ አካላት በሚዲያው ላይ በሚያሳዩት ጣልቃ ገብነት በኮርፖሬሽኑ ላይ ተፅዕኖ እያሳደረ መሆኑ መገለፁ፤

ኮርፖሬሽኑ በቋንቋዎች የሚያሰራጫቸው ስርጭቶች ሽፋንን በተመለከተ

12. ኮርፖሬሽኑ በቋንቋዎች ከሚያሰራጫቸው ስርጭቶች እስከ 70% ሽፋናቸው በክልሎች በሚከናወኑ ሀገራዊ ፋይዳ ያላቸው የተሞክሮ ልውውጥ ሊደረግባቸው በሚገቡ ጉዳዮች ላይ ትኩረት አደርጎ ሊሰራ ይገባል::

13. ይሁን እንጂ ኮርፖሬሽኑ በቋንቋዎች ከሚያሰራጫቸው የዜና ይዘቶች 70% በክልል 30% በማዕከል አድርጎ እየሰራ አለመሆኑንና ኮርፖሬሽኑ በቋንቋዎች ከሚያሰራጫቸው ይዘቶች አብዛኛዎቹ ከማዕከል አካባቢ መሆኑ፣ እንዲሁም የቋንቋዎች ዜናና ወቅታዊ ጉዳዮች ዲቪዥን የሰው ሀይል እና የሚፈልገው ስራ በጣም ሰፊ ልዩነት ያለው በመሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከቀረበ በቃለ መጠይቅ የተገኘ መሆኑ፣ በተጨማሪም የቋንቋዎች ዜናና ወቅታዊ ጉዳዮች ዲቪዥን በመዋቅር መሰረት

የሚፈልገው የሰው ሀይል ብዛት 244 ሲሆን እስከ የካቲት 2016 ዓ.ም ያለው የሰው ሀይል 81 ብቻ ሲሆን ከተፈከደው መዋቅር 33% የሚሸፍን መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

ኮርፖሬሽኑ የሰብአዊ መብቶች መከበራቸውን አጉልቶ የሚያሳይ የአሰራር ስርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ

14. ኮርፖሬሽኑ በሚያቀርባቸው ዜናዎችም ሆነ ፕሮግራሞች የሰብአዊ መብቶች መከበራቸውን አጉልቶ የሚያሳይ የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል ፡፡

15. ይሁን እንጂ ኮርፖሬሽኑ በሚያቀርባቸው ዜናዎችም ሆነ ፕሮግራሞች የሰብአዊ መብቶች መከበራቸውን አጉልቶ የሚያሳይ የአሰራር ስርዓት ያልዘረጋ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ሰነዶች እና ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ከቀረበ ቃለ መጠይቅ ለመረዳት ተችሏል፡፡ ለማሳያ፤

- ኮርፖሬሽኑ እንደማንኛውም ተቋም የሰብዓዊ መብቶች የሚስተናግድ ሲሆን ነገር ግን ለሰብዓዊ መብቶች ዘገባ ተብሎ የራሱ የሆነ ፎርማት/ፕሮግራም/ የሌለው መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከቀረበ በቃለ መጠይቅ የተገኘ መሆኑ፣
- አብዛኛውን ጊዜ በሰብዓዊ መብቶች በኩል የሚወጡ መግለጫዎች ግጭት ቀስቃሽ ስለሆኑ በሚል ምክንያት በኮርፖሬሽኑ በኩል የዘገባ ሽፋን የማይሰጥ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከቀረበ በቃለ መጠይቅ የተገኘ መሆኑ፣ እንዲሁም ግጭት ቀስቃሽ ናቸው ለማለት የሚያስችል የተዘጋጀ መመሪያ/መግለጫ/ ማሳያ ስለመኖሩ ማስረጃው አልቀረበም፣
- ኮርፖሬሽኑ ሰብአዊ መብቶች ጉዳዮችን በተመለከተ ከ2013-2015 ዓ.ም ድረስ ከ17 በማይበልጡ ጉዳዮች ላይ ብቻ የዘገባ ሽፋን የሰጠ መሆኑ፤
- የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን የሚያወጣቸውን በርካታ መግለጫዎች እና መሰል ሪፖርቶች ኢቢሲን ጨምሮ ለበርካታ የሚዲያ ተቋማት በኢሜል እንዲሁም በተቋሙ ሚዲያ እና በማህበራዊ ሚዲያ ይፋ የሚደረግ መሆኑ እና ከዚህ ውስጥ በኮርፖሬሽኑ የአካል ጉዳተኞችና የአረጋዊያን ሪፖርቶች ሽፋን ያገኙ ቢሆንም ከ20-30% የሚሆኑት ብቻ ሽፋን ያገኙ መሆኑን ለኮሚሽኑ ከቀረበው ቃለ መጠይቅ የገለፁ መሆኑ፤

➢ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ መግለጫዎች በሚያወጣበት ጊዜ በአካል በኢሜል በፋክስ ለኮርፖሬሽኑ የሚላክ ቢሆንም የዘገባ ሽፋን የማይሰጥ መሆኑ ለጉባኤው ከቀረበው ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል ፡፡

ኮርፖሬሽኑ በሚያስተላልፋቸው የዜና ዘገባዎች የስርጭት ጥራታችውና ተደራሽነት በተመለከተ

16. ኮርፖሬሽኑ በሚያስተላልፋቸው የዜና ዘገባዎች የስርጭት ጥራታቸው በጠበቀ መልኩ ተደራሽነት ሊኖረው ይገባል፡፡

17. ይሁን እንጂ የኮርፖሬሽኑ በሚያስተላልፋቸው የዜና ዘገባዎ የስርጭት ጥራታቸው በጠበቀና ተደራሽነት ባለው መልኩ አለመሆኑን ከተከለሱ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡ ለማሳያ ያህል ፡-

   ➢ የኮርፖሬሽኑ የሬዲዮ ማሰራጫ ኤፍኤም ጣቢያዎች ካሉት 33ቱም ከተማ አካባቢ በመሆኑ ለገጠሩ ነዋሪዎች የሬዲዮ ስርጭት ተደራሽ አለመሆኑ፣

   ➢ ኮርፖሬሽኑ የሬዲዮ ስርጭትን በተመለከተ በ2013 ዓ.ም ባጠናው ጥናት መሰረት አብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች የኢትዮጵያ ሬዲዮ ስርጭት የማይሰማ መሆኑ፤

   ➢ ኮርፖሬሽኑ ሬዲዮ ስርጭት ጥራትን በተመለከተ በ2013ዓ.ም በራሱ ባለሙያዎች የዳሰሳ ጥናት ባስጠናው መሰረት በተለዩ ክፍተቶች (የስርጭት ጥራት)ማነስና ተደራሽነት ላይ ያሉ ችግሮች የማስተካከያ እርምጃ ያልወሰደ መሆኑ፤ እንዲሁም በ2013ዓ.ም ላይ የነበሩ የሬዲዮ ስርጭት ችግሮች እስከ ህዳር 2016 ዓ.ም ሳይፈቱ አሁንም ድረስ ችግሮቹ ያሉ መሆኑ፤

   ➢ በ2015 ዓ.ም የሬዲዮ ማሰራጫ ጣቢያዎችን ለማሻሻል ከቀረበው ፕሮፖዛል ለማወቅ እንደተቻለው ኮርፖሬሽኑ የሬዲዮ ስርጭትን ተደራሽ ለማድረግ ካሉት 43 የሬዲዮ ማሰራጫ ጣቢያዎች በተጨማሪ 50 የኤፍ ኤም የማሰራጫ ጣቢያዎች የሚያስፈልጉት መሆኑ፣

   ➢ በ2015 ዓ.ም የሬዲዮ ማሰራጫ ጣቢያዎችን ለማሻሻል ከቀረበው ፕሮፖዛል ለማወቅ እንደተቻለው ኮርፖሬሽኑ ካሉት 43 የሬዲዮ ማሰራጫ ጣቢያዎች እና የኤፍኤም ትራንስሚተሮች የተወሰኑት የሬዲዮ ማሰራጫ ጣቢያዎች እና የኤፍኤም ትራንስሚተሮች የሚያሰራጩት ካላቸው አቅም በታች መሆናቸው፣

- ኮርፖሬሽኑ 50 የኤፍ ኤም የማሰራጫ ጣቢያዎች ለመገንባት በፕሮፖዛል ደረጃ ብር 689,412,094.47 (ስድስት መቶ ሰማኒያ ዘጠኝ ሚሊዮን አራት መቶ አሰራ ሁለት ሺ ዘጠና አራት ብር ከ47/100 ሳንቲም) የሚያስፈልግ መሆኑ፡፡ እንዲሁም ለማሰራጫ ጣቢያ ግንባታ የተፈለገው በጀት በመንግስት ድጋፍ በኩል ይሁን በኮርፖሬሽኑ ገቢ የተፈቀደ በጀት አለመኖሩ፡፡
- በተደጋጋሚ ከአድማጭ ተመልካች ግብረ መልስ ሪፖርት ለማወቅ እንደተቻለው ኮርፖሬሽኑ የሬዴዮ ስርጭት ጥራት ችግርና ተደራሽነት ላይ በተደጋጋሚ የህዝብ ቅሬታዎች የሚነሱበት ሲሆን ነገር ግን ኮርፖሬሽኑ ችግርን ለመፍታት የሄደበት ሁኔታ የሌለ መሆኑ፡፡
- በኮርፖሬሽኑ ከሚቀርቡ የአድማጭ ተመልካች አስተያየቶች መካከል በብዛት የስርጭት መቋረጥና የስርጭት ጥራት ማነስ የሚገልፅ መሆኑ፤
- በኮርፖሬሽኑ የ2013-2017 ዓ.ም ስትራቴጂካዊ ዕቅድ ላይ እንደተገለፀው የመካከለኛ ሞገድ ሬዴዮ ማሰራጫ ጣቢያዎች ለረዥም አመታት ያገለገሉ፣ ከቴክኖሎጂ እድገት አንጻር ኋላ ቀርና የመለዋወጫ ዕቃ እጥረት ያለባቸው መሆኑ እንዲሁም የስርጭት ጥራት ደረጃቸውም የወረዱ መሆናቸው፡፡
- በኮርፖሬሽኑ የ2013-2017ዓ.ም ስትራቴጂካዊ ዕቅድ ላይ እንደተገለፀው በኤፍ.ኤም. ትራንስሚተሮች ስርጭት ያልተሸፈኑ አካባቢዎች በመኖራቸው እና የስርጭት ችግር ያለ ቢሆንም ይህን ችግር ለመቅረፍ ስርጭቱን በቀላል መቀበያ ሊደመጥ እንዲችል ለማድረግ በስትራቴጂያዊ ዕቅድ ዘመኑ ታቅዶ የነበረ ቢሆንም ያሉትን ከማስቀጠል ውጪ ሌላ የማስተካከያ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ ፡፡
- በሀገሪቱ ባሉት የትራንስሚተር ጣቢያዎች የመብራት መቋረጥን ተከትሎ ስርጭቱን በጀነሬተር ለመሸፈን ቢሞከርም ጀነሬተሮቹ ረዘም ላለ አመታት ያገለገሉ በመሆናቸው በአሁኑ ሰዓት ከፍተኛ የነዳጅ ፍጆታ ስለሚጠቀሙ ጥዋትና ማታ ለአንድ ስዓት ብቻ እንዲሰሩ የሚደረግ መሆኑ፡፡
- በአብዛኛው የሬዲዮ የማሰራጫ መሳሪያ መጠባበቂያ የሌላቸው መሆኑ በተጨማሪም ኮርፖሬሽኑ ምንም አይነት የሬዲዮ ማሰራጫ ጣቢያ መለዋወጫ ከአስር አመት በላይ ያልተገዛ መሆኑ፡፡

ኮርፖሬሽኑ የአድማጭ ተመልካችን ቅሬታዎችን መፍታቱን በተመለከተ

18. ኮርፖሬሽኑ የአድማጭ ተመልካች ቅሬታዎችን የሚፈታበትና ግብረመልስ የሚሰጥበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

19. ይሁን እንጂ ኮርፖሬሽኑ የአድማጭ ተመልካች ግብረመልስ የሚሰጥበት የአሰራር ስርዓት ያልዘረጋ መሆኑ፤ እንዲሁም ኮርፖሬሽኑ ለአድማጭ ተመልካቾች በምን ሁኔታ እና መቼ ግብረ መልስ መስጠት እንዳለበት በግልፅ የተቀመጠ የአሰራር ስርዓት የሌለው መሆኑ፤

20. በኮርፖሬሽኑ ከሚቀርቡ የአድማጭ ተመልካች አስተያየቶች መካከል በብዛት የስርጭት መቋረጥና የስርጭት ጥራት ማነስ መሆኑ፤ይህም በየጊዜው ችግሮቹ እየቀጠሉ በመሆኑ ችግሮቹን ተከታትሎ መፍትሄ ከመስጠትና ችግሮቹ እንዳይከሰቱ ከማድረግ አንፃር ክፍትት ያለበት መሆኑ፤ ለኮርፖሬሽኑ ከአድማጭ ተመልካች የኢትዮጵያ ሬዲዮ የስርጭት መቋረጥናተ ተደራሽነት ላይ ቅሬታዎች የሚቀርቡ ሲሆን ነገር ግን የቀረቡ ቅሬታዎች ስለመፈታታቸው የሚያሳይ ማስረጃ ለኦዲት ቡድኑ ያልቀረበ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

ከላይ ለተገኙት ክፍተቶች ለማሻሻል አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ተብሎ የታመነባቸው የማሻሻያ ሃሣቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- የኮርፖሬሽኑ የስራ አመራር ቦርድ በአዋጁ የተሰጡትን ዝርዝር ተግባራትን ለመወጣትና ስራዎችን ለመስራት የራሱ የሆነ የስራ መመሪያ ሊያወጣ ይገባል፡፡
- የኮርፖሬሽኑ የስራ አመራር ቦርድ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ሊሰበሰብና የስራ አመራር ቦርዱ ኮርፖሬሽኑን ወደ ተሻለ ምዕራፍ ሊያሸጋግሩ የሚችሉ እቅዶችን አቅዶ በመስራት የተቋሙን ጊዜያዊና ዘላቂ ችግሮችን ለመቅረፍ በሚያስችል መልኩ ወቅቱን የጠበቀ ግንኙነት ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ኮርፖሬሽኑ ያሉትን ፋይሎች ደህንነቱ በተጠበቀ መልኩ በማስቀመጥና ለትውልድ ሊያስተላለፍ ይገባል፡፡
- ኮርፖሬሽኑ የኤዲቶሪያል ፖሊሲው ተጨባጭ ሁኔታዎችንና የሚደያ ኢንዱስትሪውን ለውጥና ዕድገት የሚጠይቀውን በማካተት በየአምስት አመቱ በመከለስ የኤዲቶሪያል ፖሊሲው ተከትሎ በሚወጡ መመሪያዎች ላይ በየጊዜው

ክፍተታቸውን እየፈተሹ ደረጃቸውን እንዲጠብቁም ሆነ የአሰራር ውጤታማነት እንዲያስገኙ ሊያድግ ይገባል፡፡

- ኮርፖሬሽኑ የኤዲቶሪያል ነፃነት በተጠበቀ እና በሥራውም ሆነ በአስተዳደሩ መንግሥትና የመንግሥት ተቋማትን ጨምሮ ከማንኛውም አካል ነፃና ገለልተኛ ሆኖ ህዝቡ የሚፈልገውን መረጃ እንዲያገኝና እንዲያውቅ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ኮርፖሬሽኑ በቋንቋዎች ከሚያሰራጫቸው ስርጭቶች እስከ 70% ሽፋናቸው በክልሎች በሚከናወኑ ሀገራዊ ፋይዳ ያላቸው የተሞክሮ ልምድ ልውውጥ ሊደረግባቸው በሚገቡ ጉዳዮች ላይ ትኩረት አደርጎ ትምህርት እንዲወስዱ ሊያደግ ይገባል፡፡
- ኮርፖሬሽኑ በሚያቀርባቸው ዜናዎችም ሆነ ፕሮግራሞች የሰብአዊ መብቶች መከበራቸውን አጉልቶ የሚያሳይ የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡
- ኮርፖሬሽኑ የሚያስተላልፋቸው ዜናዎችና ፕሮግራሞች በህዝቡ እንዲደመጡና ማህበረሰቡ በሀገሪቱ ያለውን ማህበራዊ ፤ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች ግንዛቤ እንዲኖራቸው የሬዲዮና የቴሌቪዥን የስርጭት ጥራታቸው በጠበቀ መልኩ ተደራሽነት ባለው መልኩ ሊሆን ይገባል፡፡
- ሬዲዮ ስርጭት በቀላሉ ከቦታ ቦታ ይዞ በመንቀሳቀስ ወቅታዊ መረጃ ከዳር እስከ ዳር በማዳረስ፣ በማስተማር፣ በማዝናናት እንዲሁም መንግስትንና ህዝብን እንደ ድልድይ ሆኖ በማገናኘት አውንታዊ ሚና የሚጫወት በመሆኑ እንዲሁም በሀገራችን 80% የገጠር ነዋሪ በመሆኑ መረጃዎችንም በብዛት የሚያገኙት በሬዲዮ ስለሆነ ኮርፖሬሽኑ ሬዲዮ ስርጭት ላይ ትኩረት አድርጎ ሊሰራ ይገባል፡፡
- ኮርፖሬሽኑ ከሚሰራቸው የዜና ዘገባዎች ላይ የፕሮጅክት ዜናዎችን ላይ ትኩረት በማድረግ የህዝቡን ችግሮች ነቅሶ በማውጣትና መንግስትና ባለድርሻ አካላት መፍትሂ እንዲፈልግላቸው በማድረግ ላይ ትኩረት አደርጎ ሊሰራ ይገባል፡፡
- ኮርፖሬሽኑ የአድማጭ ተመልካች ቅሬታዎችን ግብረመልስ የሚሰጥበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋና ኮርፖሬሽኑ ለአድማጭ ተመልካቾች በምን ሁኔታ እና መቸ ግብረ መልስ መስጠት እንዳለበት በግልፅ የተቀመጠ የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

በመንግስት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር

የመንግስት የልማት ድርጅቶች የእዳ እና የትርፍ ድርሻ ክፍያ አፈጻጸም በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት ዘገባ

አስተዳደሩ የልማት ድርጅቶች የእዳ አከፋፈልና የትርፍ ድርሻ አፈጻጸምን ወጪ ቆጣቢ፣ ብቃት ባለውና ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመምራት የሚያስችል የአሰራር ስርዓት የዘረጋና ተግባራዊ ማድረጉን መገምገም፤

አስተዳደሩ የልማት ድርጅቶች የዕዳና የትርፍ ድርሻ ክፍያን ስራዎችን ለማስፈፀም የሚረዱ በወጡ የህግ ማዕቀፎች (አዋጅ፣ ፖሊሲ፣ ደንብ፣ መመሪያ)፣ ስትራቴጂ በማጸደቅና ሲፈቀድም በስራ ላይ ወጥ በሆነ መልኩ መተግበሩን ሊከታተልና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡

አስተዳደሩ የእዳ እና የመንግስት የትርፍ ድርሻ ክፍያ ሥራዎችን ለማስፈጸም ቀደም ብለው በወጡት የህግ ማዕቀፎች (አዋጆች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች) በልማት ድርጅቶች በተሟሏ ሁኔታ በስራ ላይ በትክክል እየተገበረ ስለመሆኑ፤እንዲሁም በአፈፃፀም ወቅት ያጋጠሙትን ክፍተቶችን ለይቶ በማውጣት ከወቅቱ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ ለማሻሻል የሚያስችል ውጤታማ የሆነ የክትትልና ቁጥጥር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ በማድረግ የማስተካከያ እርምጃ እንዲደረግባቸው በተሟላ መልኩ የተሰራ አለመሆኑን በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

አስተዳደሩ በልማት ድርጅቶች የተወሰዱ ብድሮችን በተመለከተ፤

አስተዳደሩ በልማት ድርጅቶች የተወሰዱ ብድሮችን ያሉበትን ሁኔታ እና ወደፊት የሚወስዱትን ብድሮች ከመክፈል አቅም ጋር በማነፃፀር ትንተና እንዲሰሩ ሊከታተልና ሊቆጣጠር ይገባል::

በኦዲቱ ወቅት አስተዳደሩ በአምስት ዓመት ስትራቴጂክ እቅዱ (2013 እስከ 2017) እቅዱና በአመታዊ እቅዱና በአፈጻጸሙ መሠረት የልማት ድርጅቶችን የፋይናንስ ጤናማነት የመከታተል፣ የፋይናንስ ትንተና እና ጤናማነቱን በመፈተሸ ማስተካከያ እንዲደረግ አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወሰድ እና የድጋፍ ስራዎችን እንደሚሰራ የተመላከተ ቢሆንም በልማት ድርጅቶች የተወሰዱ ብድሮች ያሉበት ሁኔታ እና ወደፊት

በሚወስዱት ብድሮች ያጋጠሙት ችግሮችን ለይቶ የፋይናንስ ጤናማነት በመፈተሽ የማስተካከያ እርምጃ እንዲደረግባቸው እየሠራ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

አስተዳደሩ የመንግስት የልማት ድርጅቶች በብድር አሰተዳደር ስትራቴጂ እቅድ ማዘጋጀታቸውን እና አፈጻጸሙን መከታተሉን በተመለከተ፤

አስተዳደሩ የመንግስት የልማት ድርጅቶች የብድር አወሳሰድ፣ አሰተዳደር እና አመላለሳቸው በስትራቴጂክ እና በዓመታዊ እቅድ መሰረት መፈጸሙን ለማረጋገጥ የሚያስችል ወጥነት ያለው የክትትልና ቁጥጥር ስርዓት ዘርግቶ የድጋፍና ማስተካከያ ሥራ ሊሥራ ይገባል፡፡

አስተዳደሩ የልማት ድርጅቶችን የብድር አስተዳደር ስርዓትን በአምስት ዓመት ስትራቴጂክ እቅድና በዓመታዊ እቅድ አካተው ትኩረት በመስጠት አፈፃፀሙን ላይ የሚደረገው ክትትል በቂ አለመሆኑ፣ ብድሮችን በወቅቱ እንዲመለሱ በቂ ክትትል አለመደረጉ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

አስተዳደሩ የልማት ድርጅቶች እዳ ወደመንግስት ከመተላለፉ በፊት በጥናት የተደገፈ መሆኑን በተመለከተ፤

አስተዳደሩ የልማት ድርጅቶች እዳ ወደመንግስት ከመተላለፉ በፊት የዕዳው ምንጭ፣ በድርጅቱ ሊከፈል ያልቻለበትን ምክንያት እና በመንግስት ዕዳው ቢሸፈንለት ስለሚያስገኘው ጥቅም ጥናት ሊያደርግ ይገባል፡፡

የመንግሥት የልማት ድርጅቶች እዳ ወደ መንግስት ከመተላለፉ በፊት የተጠናው የጥናት ሰነድ በአስተዳደሩ እና በልማት ድርጅቶቹ ያልተገኘ መሆኑ እንዲሁም ለኦዲት ቡድኑ የጥናት ሰነድ ተብሎ በገንዘብ ሚኒስቴር የቀረበው ሰነድ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች እዳ ወደ መንግስት ከመተላለፉ በፊት የዕዳው ምንጭ፣ ሊከፈል ያልቻለበትን ምክንያትና በመንግስት ዕዳው ቢሸፈን ስለሚያስገኘው ጥቅም በማካተት የተሟላ ጥናት ስለመቅረቡ ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ እና የልማት ድርጅቶች ያለባቸው እዳ በዝርዝር ያላስቀመጠ መሆኑ እንዲሁም እዳው ከተዛወረ በኃላ የመጣው ለውጥ ላይ የመገምገም ክፍተት ያለበት መሆኑ ታውቋል፡፡

የትርፍ ድርሻ ክፍፍል ፖሊሲ ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፤

አስተዳደሩ የትርፍ ድርሻ ፖሊሲ በማዘጋጀት፣ በየበጀት አመቱ ከልማት ድርጅቶች ለመንግስት ስለሚከፈል የትርፍ ድርሻ ክፍያ ለገንዘብ ሚኒስቴር የውሳኔ ሀሳብ በማቅረብ፣ ተግባራዊነቱን በወጥነት ሊከታተልና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡

በአስተዳደሩ የትርፍ ድርሻ ክፍፍል ፖሊሲ በማዘጋጀት ለልማት ድርጅቶች ተደራሽ ያላደረገ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

አስተዳደሩ የልማት ድርጅቶች ያለባቸው ውዝፍ እዳና የትርፍ ድርሻ ክፍያ መርሃ-ግብር መሰረት እንዲከፍሉ ማድረጉን በተመለከተ፤

አስተዳደሩ ውዝፍ እዳና የትርፍ ድርሻ ክፍያ ያለባቸው የልማት ድርጅቶች መርሃ-ግብር በማዘጋጀት አፈጻጸማቸውን ሊገመግም፣ ወቅታዊነት ያለው ግብረ መልስ በመስጠት በዘላቂነት እንዲከፍሉ የክትትልና የቁጥጥር ስርዓት ዘርግቶ ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

በአስተዳደሩ ስር የነበሩ የልማት ድርጅቶች ያለባቸው ውዝፍ እዳ እና የትርፍ ድርሻ አከፋፈል ዙሪያ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግ ከአስተዳደሩ ጋር ውይይት እና ርክክብ ያላደረገ መሆኑ፤

እንዲሁም አስተዳደሩ የልማት ድርጅቶች ያለባቸው ውዝፍ እዳ እና የመንግስት የትርፍ ድርሻ ክፍያ ሥራዎችን በተመለከተ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በዕቅድ የተመራ የክትትልና የድጋፍ ስራዎችን ማከናወን ላይ ክፍተት ያለበት መሆኑ፤ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

የልማት ድርጅቶች ያለባቸውን ስጋቶች እና ችግሮችን በጥናት ለይተው የማስተዳደር ሥራዎችን በእቅድ አካተው እንዲመሩ ማድረጉን በተመለከተ፣

አስተዳደሩ የልማት ድርጅቶች የዕዳ እና የትርፍ ድርሻ አከፋፈል ዙሪያ ያለባቸውንስጋቶችን በጥናት በመለየት የመከላከል፣ የመፍታት እና የማስተዳደር ሥራዎችን በእቅድ እንዲመሩ ለማድረግ የሚያስችል የክትትልና ቁጥጥር ድጋፍ ሥራ ሊሰራ ይገባል፡፡

አስተዳደሩ የትርፍ ድርሻ ክፍያ በማይከፍሉት እና በየበጀት አመቱ ሲከባለል የመጣ ውዝፍ የትርፍ ድርሻ ክፍያ ያለባቸው የልማት ድርጅቶችን አፈጻጸማቸውን ገምግሞ ግብረ መልስ በመስጠት ተግባራዊ እንዲሆን የክትትል እና ቁጥጥር ስራ በመስራት ተፈጻሚ

የማያደረጉትን ለይቶ በማሳወቅ ተጠያቂ እንዲሆኑ እያደረገ አለመሆኑን በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

ከላይ ለተገኙት ክፍተቶች ለማሻሻል አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ተብሎ የታመነባቸው የማሻሻያ ሃሣቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- አስተዳደሩ የእዳ እና የትርፍ ድርሻ አከፋፈል ስራዎችን ለማስፈጸም የወጡ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ጉዳዩ በሚመለከታቸው ፈፃሚ አካላት በትክክል መተግበራቸውን እንዲሁም ቀደም ብለው የወጡና ማሻሻያ ያልተደረገላቸው የህግ ማዕቀፎች አፈጻጸም ክፍተቶችን በመገምገም ማሻሻያ የሚያስፈልጋቸውን በወቅቱ እንዲሻሻሉ በማስደረግ ወደ ልማት ድርጅቶች በማውረድ ተፈጻሚ እንዲሆኑና በህጉ መሠረት የማይሰሩ አካላትን ጉዳዩ ለሚመለከተው የበላይ አካላት በማሳወቅ ያጋጠሙት ችግሮች እንዲቀረፉ የሚያስችል ውጤታማ የክትትል እና የቁጥጥር ሥርዓት ዘርግቶ ሊሰራ ይገባል፡፡

- አስተዳደሩ በማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 445/2011 በአንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 5 የተመላከቱ ዓላማዎችን በአንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 10 የተሰጠው ኃላፊነት በአግባቡ እንዲሳካ በልማት ድርጅቶች የተወሰዱ ብድሮች ያሉበትን ሁኔታ እና ወደፊት የሚወስዱትን ብድሮች የፋይናንስ የመክፈል አቅም ያገናዘበ ትንተናና ፍተሻ በማድረግ የፋይናንስ የጤናማነት ደረጃ ገምግሞ ችግሮቹ እንዲቀረፉ ለሚመለከተው አካል የውሳኔ ሃሳብ እያቀረበ አስፈላጊውን የማስተካኪያ እርምጃ እንዲወሰድ የሚያስችል የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት ዘርግቶ የብድር አስተዳደርና አፈጻጸም ስርዓት እንዲረጋገጥ በተጠያቂነት ሊሰራ ይገባል፡፡

- አስተዳደሩ በመቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 445/2011 አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1 እና በአምስት ዓመቱ ስትራቴጂክ እቅድ በጥቅል በተቀመጠው መሠረት የመንግስት የልማት ድርጅቶች የብድር አወሳሰድ፣ አሰተዳደር እና አመላለሳቸው በብድር አሰተዳደር ስትራቴጂዎች፣ በዓመታዊ እቅድ እና በመርሃ ግብሮች መሰረት የሚፈጽሙ መሆኑን በማረጋገጥ በዝርዝርና በጥልቅት የአፈጻጸሙ መገምገሚያ መለኪያዎችን አዘጋጅቶ የታዩ ክፍተቶች ለይቶ እያሳወቀ እንዲታረም የሚያስችል የክትትል እና ቁጥጥር ስርዓት ዘርግቶ የድጋፍና ተጠያቂነት ባለው ሁኔታ የማስተካከያ ስራ ሊሰራ ይገባል፡፡

- አስተዳደሩ የልማት ድርጅቶች እዳ ወደመንግስት ከመተላለፉ በፊት የዕዳው ምንጭ፣ በድርጅቱ ሊከፈል ያልቻለበትን ምክንያት እና በመንግስት ዕዳው ቢሸፈን ስለሚያስገኘው ጥቅም በጥናት ስለመካተቱ እንዲሁም የጥናቱ አፈጻጸም በተቀመጠው መሰረት መሆኑን ሊገመግም እና ችግሮች ካሉ ለውሳኔ ሊያቀርብ ይገባል፡፡
- አስተዳደሩ በማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 445/2011 በተቀመጠው መሠረት የትርፍ ድርሻ ፖሊሲ ክፍፍል አዘጋጅቶ በስራ ላይ እንዲያውል እንዲሁም የትርፍ ድርሻ ክፍፍል ፖሊሲ በማፀደቅ ወደ ልማት ድርጅቶች በማውረድ በስራ ላይ በማዋል በየበጀት ዓመቱ ከልማት ድርጅቶች ለመንግስት ስለሚከፈል የትርፍ ድርሻ ክፍያ ለገንዘብ ሚኒስቴር የውሳኔ ሀሳብ በማቅረብ፣ ተግባራዊነቱን ለማረጋገጥ የሚያስችል የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት ዘርግቶ አፈጻጸሙን በመገምገም ኃላፊነት የተሰጣቸው አመራሮችና ፈጻሚዎች ግብረ መልስ በመስጠት ግዴታቸውን እንዲወጡና ተጠያቂነት ባለው መልኩ እንዲፈጸሙ ሊሰራ ይገባል፡፡
- አስተዳደሩ በማቋቋሚያ ደንብ በተሰጠውን ኃላፊነት መሠረት የልማት ድርጅቶችን የእዳ እና የትርፍ ድርሻ ክፍያ ሥራዎችን በመርሃ-ግብር፣ በስትራቴጂክ ዕቅድ፣ በዓመታዊ ዕቅድ መያዛቸውን በማረጋገጥና በማጸደቅ አፈጻጸማቸውን ብቃት ባለውና ውጤታማ በሆነ መልኩ በወጥነት ገምግሞ ወቅታዊ ግብረ-መልስ በመስጠት ተግባራዊነቱ የሚያረጋግጥበትን ጠንካራ የክትትል እና የቁጥጥር ሥርዓት ዘርግቶ ማስተካከያ እንዲደረግ ሊሰራ ይገባል፡፡
- አስተዳደሩ የልማት ድርጅቶ የትርፍ ድርሻ ለገንዘብ ሚኒስቴር በወቅቱ ገቢ ስለማድረጋቸው በማረጋገጥ የማይከፍሉትን ለይቶ የማሳወቅና ተጠያቂነት እንዲኖር በማድረግ መንግሥት ከልማት ድርጅቶች መሰብሰብና ማግኘት ያለበት ዓመታዊ የትርፍ ድርሻ ክፍያ በወቅቱ ገቢ እንዲያደርጉ የድጋፍና የክትትል ሥራዎችን ሊሰራ ይገባል፡፡

በንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር

የሲሚንቶ እና መሰረታዊ ሸቀጦች ስርጭት አፈፃፀም በተመለከተ፤

የሲሚንቶ እና መሰረታዊ ሸቀጦች ስርጭትን ለማሳለጥ የህግ ማእቀፎች መዘጋጀቱን በተመለከተ

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሲሚንቶና መሰረታዊ ሸቀጦች ስርጭትን የሚያሳልጡ የህግ ማእቀፎችን (ፖሊሲ፣ ደንብ፣ መመሪያ፣ ወዘተ) ሊያወጣ እና ሊተገብር ይገባል፡፡

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሲሚንቶ እና የመሰረታዊ ሸቀጦች ስርጭት ለማሳለጥና ተግባራዊ ለማድረግ በተለይ በፍራንኮቫሎታ(የራሳቸው የውጪ ምንዛሬ ያላቸው ዲያስፖራዎች) ሸቀጦችን ወደሃገር እንዲያስገቡ ፈቃድ በተሰጣቸው አስመጪዎች የሚመጡ ሸቀጦች የስርጭት፣ የግብይትና የቁጥጥር ስርዓት ያልተዘረጋላቸው መሆኑ እና ምርቶቹ ወደ ሀገር ውስጥ ከገቡ በኋላ የስርጭትና የግብይት ሰንሰለቱ የማይታወቅና ቁጥጥር የማይደረግባቸው መሆኑ፤ እንዲሁም የሲሚንቶ መመሪያዎች በግብይቱ ሂደት ላይ ክፍተትን በሚፈታ መልኩ የሚመለከታቸውን አካላት በማሳተፍ ሀገራዊ ጥናት በማካሄድ ሁሉም አካታች በሆነ መልኩ የማይዘጋጁ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና የቀረቡ ቃለ መጠይቆች ለማወቅ ተችሏል፡፡

በክልሎችና በከተማ አስተዳደሮች የሲሚንቶና የመሰረታዊ ሸቀጦች የሥርጭት ሂደትን በተመለከተ፤

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች የሲሚንቶና የመሰረታዊ ሸቀጦች ኮታ ሊደልደል፣ የፋብሪካዎች፣ የአስመጪዎች፣ እና አቅራቢ ድርጅቶች የሚያከፉፍሉባቸውን አካባቢዎች ሊወሰንና ሊያሳወቅ ይገባል፡፡

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች የመሰረታዊ ሸቀጦች መጠን/ኮታ 2001 ዓ.ም የተደለደለ ሲሆን ይህ የኮታ ድልድል ወቅታዊና ነባራዊ ሁኔታ በማገናዘብ ክለሳ ያልተደረገበት መሆኑ፤ ቢሆንም ግን በዚሁ የኮታ ድልድል መሰረት እየተከናወነ አለመሆኑ፤ የሲሚንቶ የኮታ መነሻ በግልፅ የተቀመጠበት ሁኔታ እንደሌለ እና ክልሎችና

ከተማ አስተዳደር መሰረታዊ ሸቀጦች ምርቶቹ ካለመኖራቸው የተነሳ በሚኒስቴር መ/ቤቱ እቅድ እና የአቅርቦት ጥያቄ ምላሽ የተሰጣቸው አለመሆኑ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሲሚንቶና መሰረታዊ ሸቀጦችን አቅርቦትና ስርጭትን ለመደገፍና ከአምራቾችና ከአቅራቢዎች ጋር መስራቱን በተመለከተ፤

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሲሚንቶና መሰረታዊ ሸቀጦችን በየዓመቱ ፍላጎት እያጠና የአምራቶችንና የአቅራቢዎች በእቅዱ የሚያካትትበት፣ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ስለሚሰራጩበት፣ ስለሚሸጡበትና ከቦታ ቦታ ስለሚዘዋወሩበት ሁኔታ ሊወሰንና ሸቀጦቹ ባለቀ ጊዜ እንዲተኩ የሚያደረግበት ስርዓት ሊዘርጋ ይገባል፡፡

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመሰረታዊ ሸቀጦች አስመጪዎች፣ አምራቾችና አከፋፋዮች/ ቸርቻሪዎችን እና የሲሚንቶ አምራቶች አሁን ካለው የምርት ከፍተኛ የአቅርቦት እጥረት፣ መቆራረጥና ፍላጎት አንፃር ምርቱ፣ አሰራሩና ስርጭቱ የማይጣጣም መሆኑ፤ የመሰረታዊ ሸቀጦች አስመጪዎች እና የሲሚንቶ አምራቶች የምርት አቅርቦት መነሻ ያደረገ ስርጭት እና በተዘረጋው ሰንሰለት መሰረት ምርቱን እየቀረበ አለመሆኑ እንዲሁም የሲሚንቶ ምርትም በየጊዜው አፈጻጸሙን እየተቆጣጠረ አለመሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

የመሰረታዊ ሸቀጦች አቅርቦት ስርጭትን ከከተማ አስተዳደሮች እና ከክልሎች ጋር የጋራ እቅድ ማዘጋጀቱን በተመለከተ፤

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሲሚንቶና የመሰረታዊ ሸቀጦች አቅርቦት ስርጭትን ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች በማሳተፍ እና ከሚመለከታቸው አካላት መረጃ ሊሰበስብ፣ የጋራ እቅድ ሊያዘጋጅ እና የአፈፃፀሙን ውጤታማነት ሊከታተልና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሲሚንቶና የመሰረታዊ ሸቀጦች አቅርቦት ስርጭትን ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች በማሳተፍ መረጃዎችን በመሰብሰብ እና በእቅዱ መሰረት በዓመት ሁለት ጊዜ የክትትልና የቁጥጥር ስራ እየሰራ አለመሆኑ፤ ከክልሎችና ከተማ አስተዳደሮቹ ኃላፊነትና ተጠያቂነት ያለው ጠንካራ የጋራ እቅድ ያልተዘጋጀ መሆኑ እና የክልሎችና የከተማ አስተዳደሮቹ እቅድና የአፈፃፀም ሪፖርቶች ልውውጥ ክፍተት መኖሩ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

የመሰረታዊ ሸቀጦችን አስመጪዎች/ አቅራቢ ድርጅቶች አመራረጥ ሂደት በተመለከተ

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመሰረታዊ ሸቀጦችን አስመጪዎች/አቅራቢ ድርጅቶች በመመሪያው መሰረት መመረጣቸውን የሚቆጣጠርበት እና ቅሬታዎችን የሚያስተናግድበት ስርዓት ሊዘረጋ እና ሊተገበር ይገባል፡፡

ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች፣ ሚኒስትር መ/ቤቶች፣ የመንግስት የልማት ድርጅቶች፣ የሲሚንቶና የዘይት ፋብሪካዎች አከፋፋዮቻቸውና ቸርቻሪዎች እንዲሁም ሌሎች የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ከተደረገ ቃለ መጠይቅ እና ከተከለሱ ማስረጃዎች እንደተገኘው፡-

- ❖ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሲሚንቶና መሰረታዊ ሸቀጦችን አስመጪዎች፤ አቅራቢ ድርጅቶች በመመሪያው መሰረት መመረጣቸውን የማያረጋግጥ እና የማይቆጣጠር መሆኑ፤

- ❖ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመሰረታዊ ሸቀጦች (የዘይት) ከ2013 ዓ.ም እና የሲሚንቶ ከ2014 ዓ.ም ጀምሮ አከፋፋዮች ሲመረጡ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች በአመራረጡ ላይ የማይሳተፉ መሆኑ፤ በአከፋፋይነት ተመርጦ እየሰሩ ያሉ አከፋፋዮች በመመሪያው መሰረት ስለመመረጣቸው በግልፅ የማያሳውቁ መሆኑ እና አከፋፋዮቹ ከሌላ አከባቢ በሚመጡ ጊዜ ከፍተኛ ቅሬታ መፍጠሩ እና ክልሎች ለመቆጣጠርም ክፍተት እየፈጠረባቸው መሆኑ፤ በሲሚንቶና በመሰረታዊ ሸቀጦች ስርጭት እና አከፋፋዮች አመራረጥና አመዳደብ ከክልል ክልል በየወቅቱ የሚለዋወጥ፣ ግልፅነትና ወጥነት የሌለው መሆኑ፣

- ❖ ክልሎች የተመደቡበት የስኳር ፋብሪካዎች ርቀት ፋብሪካዎቹ ያለማምረት ችግር ቢኖርም እያመረቱ ባሉ ፋብሪካዎች ሚዛናዊ በሆነ አመዳደብ ላይ ክፍተት መኖሩ ክልሎች ቅሬታ እያቀረቡ መሆኑ ለምሳሌ ለድሬዳዋ፣ ሃረር፣ ሱማሌ ክልሎች መተሃራ መመደብ ሲኖርባቸው ኦሞ ኩራዝ የተመደቡ መሆኑ፤ አዲስ አበባ መተሃራ ተመድቦ ትግራይ ኦሞ ኩራዝ መመደብ ሚዛናዊ አለመሆኑ እና ምርቱ ዘግይቶ እንዲደርስ፣ በየመንገዱ የደህንነት

ችግር እና በዋጋ ጭማሬና የምርት እጥረት ላይ ተፅእኖ እየፈጠረ መሆኑ በተከለሱ ማስረጃዎች የተገለፀ መሆኑ፣ ለማወቅ ተችሏል፡፡

የሲሚንቶ እና የዘይት ፋብሪካዎች የመሸጫ ዋጋ ቁጥጥርና ክትትል ማድረጉን በተመለከተ፤

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሲሚንቶ ፋብሪካዎች በየስድስት ወሩ የፋብሪካ የመሸጫ ዋጋ ሊወስን፤ ፋብሪካዎችም የጅምላና የችርቻሮዎች የዋጋ ጣሪያ ማውጣታቸው ሊቆጣጠር፤ የዘይት አቅራቢዎች በየሶስት ወሩ የፋብሪካ ዋጋ ሊያሳውቅ፣ አስመጪዎች /አቅራቢ ድርጅቶችና ለቸርቻሪ ነጋዴዎችም የመሸጫ ዋጋና የትርፍ ምጣኔን መወሰኑና የስርጭት እና የመሸጫ ዋጋ አፈፃፀሙን ሊከታተልና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡

በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሲሚንቶ ፋብሪካዎች በወጣላቸው ዋጋ መሰረት ተግባራዊ ስለመደረጉ በተከታታይና ቀጣይነት ባለው መልኩ ክትትል ባለመደረጉ ከተተመነ ዋጋ በላይ እየተሸጠ መሆኑና የሚሸጡበት ዋጋ ሲጠየቁ መረጃ የማይሰጡ ፋብሪካዎች መኖራቸው እንዲሁም በየስድስት ወሩ የፋብሪካ የሲሚንቶ የዋጋ ለውጥ መደረግ ቢኖርበትም ከአንድ ዓመት በላይ የዘገዩ መሆናቸው፤

- የዘይት ፋብሪካዎች በየሶስት ወሩ የፋብሪካ የመሸጫ ዋጋ ትመና እየተተገበረ ባለመሆኑ ዘይት ፋብሪካ ዋጋ ግንባታ እስከ እንድ አመት ሳይተመን፣ የዘይት ምርት አቅርቦቱ በወጥነት በተመሳሳይ ጊዜና መጠን ለአንድ ክልል፣ ዞንና ማህበራት እንዲቀርብ ከምርት አምራቾችና አቅራቢዎች ጋር በመሆን አለመሰራቱ፤
- ክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች የፓልም የምግብ ዘይት አስመጪ ድርጅቶች የሚያስመጡትን ዘይት አይነቱን፣ የጥራት ደረጃውን፣ መጠኑን እና በፓኬጅ መለየትና መወሰን እና የስኳር ምርት ጥራት ችግር ላይ እንዲሳተፉ እና እንዲከታተሉ አለመደረጉ፤
- በሲሚንቶ ስርጭት ላይ የሚፈጠሩ የስርጭት መዛባት እርምጃ አለመውሰድና ህግ አልባ ግብይት እየተደረገ እየታወቀ እርምጃ የሚወስድ አካል አለመኖሩ፣ በፍራንኮቫሎታ የገቡ ምርቶች የሚያከማቹ እና ከዋጋ በላይ በሚሸጡት ላይ እርምጃ እንዲወሰድ አለመደረጉ፣ በተጠኑ ጥናቶች የተገኙ ክፍተቶች ላይ

መፍትሄ እንዲሰጥ እና ቁጥጥርና ምርመራ እየተደረገ አለመሆኑና እንዲሁም እርምጃም እየተወሰደባቸው አለመሆኑ

በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

ከላይ ለተገኙት ክፍተቶች ለማሻሻል አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ተብሎ የታመነባቸው የማሻሻያ ሃሣቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመሰረታዊ ሸቀጦችና የሲሚንቶ የህግ ማእቀፎች ወቅታዊና ሁሉም አካታች በሆነ መልኩ ሊያዘጋጅ፤ የኮታ መመሪያ እና ያለአግባብ ምርቶች በሚያከማቹ አካላት ላይ እርምጃ የሚወሰድበት የህግ ማዕቀፍ ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች የመሰረታዊ ሸቀጦች 2001/2003 ዓ.ም የተደለደለው ኮታ ወቅታዊና ነባራዊ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ ሊያሻሻል እና ለክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች በተደለደለላቸው ኮታ የምርት አቅርቦት እንዲኖር ሊያደርግ እንዲሁም የሲሚንቶ ኮታ ድልድል በጥናት የተመሰረተ ግልፅ የሆነ ኮታ ሊያዘጋጅና ምርቱ እንዲሰራጭ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመሰረታዊ ሸቀጦች እና የሲሚንቶ የምርት አቅርቦት መነሻ ያደረገ ስርዓት በተለይ አሁን ካለው ፍላጎት፣ አቅርቦት፣ እጥረት እና የዋጋ ንረቱና የህብረተሰቡ የመግዛት አቅም ከፍተኛ ልዩነት አንፃር ምርቱ፣ አሰራሩና ስርጭቱ እንዲጣጣም በማድረግ ለሁሉም ተደራሽ ሊደረግበት የሚችል እና በጥናት የተለዩ የህገ-ወጥ ግብይት፣ ያለአግባብ ዋጋ መጨመር፣ ምርቶች በማከማቸት እጥረት እንዲፈጠር ማድረግ ወዘተ ግብይቱ/በስርጭቱ ላይ ያሉ ክፍተቶች የሚፈታበት ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመሰረታዊ ሸቀጦች እና የሲሚንቶ የምርት አቅርቦት መነሻ ያደረገ ስርዓት በተለይ አሁን ካለው ፍላጎት፣ አቅርቦት፣ እጥረት እና የዋጋ ንረቱና የህብረተሰቡ የመግዛት አቅም ከፍተኛ ልዩነት አንፃር ምርቱ፣ አሰራሩና ስርጭቱ እንዲጣጣም በማድረግ ለሁሉም ተደራሽ ሊደረግበት የሚችል እና በጥናት የተለዩ የህገ-ወጥ ግብይት፣ ያለአግባብ ዋጋ መጨመር፣ ምርቶች በማከማቸት እጥረት እንዲፈጠር ማድረግ ወዘተ ግብይቱ/በስርጭቱ ላይ ያሉ ክፍተቶች የሚፈታበት ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች እና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ጠንካራና የተደራጀ የጋራ የእቅድ ሰነድ ሊኖረው፤ ክልሎች የመሰረታዊ ሸቀጦች ዕቅድ እንዲያቅዱና በራሳቸው የፋይናንስ ምንጭ እንዲያገኙ ሊያበረታታ፣ ወጥነት ያለው ግምገማ ሊያካሂድና የግብረ-መልስ ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡
- የሚኒስቴር መ/ቤቱ የመሰረታዊ ሸቀጦችን እና የሲሚንቶ አስመጪዎች፣ አቅራቢ፣ አከፋፋይ ድርጅቶች በመመሪያው መሰረት መስፈርት አሟልተው መመረጣቸው በማረጋገጡና በመቆጣጠሩ እና ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች በአመራረጡና በሰንሰለት ዝርጋታው ላይ ተሳታፊ እንዲሆኑ በማድረግ የሲሚንቶና የመሰረታዊ ሸቀጦችን ስርጭት ክልሎች ምርት እና ዋጋ እንዲቆጣጠሩ እንዲሁም ምርቶቹ በተዘረጋላቸው ሰንሰለት ለህብረተሰቡ እንዲደርሱ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመሰረታዊ ሸቀጦች አስመጪዎች፣ አምራቶችና አከፋፋዮች/ቸርቻሪዎችን እና የሲሚንቶ አምራቶች አሁን ካለው የምርት ከፍተኛ የአቅርቦት እጥረት፣ መቆራረጥና ፍላጎት አንፃር ምርቱ፣ አሰራሩና ስርጭቱ እንዲጣጣም ማድረግ፤ የምርት አቅርቦት መነሻ ያደረገ ስርጭት እንዲካሄድ እና በተዘረጋው ሰንሰለት መሰረት ምርቱን መቅረቡን በየጊዜው አፈጻጸሙን መቆጣጠር ይኖርበታል፡፡

በገንዘብ ሚኒስቴር

የመንግስት ፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ስርዓት በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ኦዲት ሪፖርት ዘገባ

የመንግስት የፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ውጤታማ ሥርዓት መዘርጋቱን እንዲሁም ሥርዓቱ ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ መተግበሩን መገምገም፤

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመንግስት ፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ የሚመራበትን ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ የተዘረጋው ስርዓት ወጥነት እና ውጤታማ በሆነ መልኩ እየተተገበረ አለመሆኑ በዚህም ምክንያት የመንግስት ፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ዙሪያ የተለያዩ ችግሮች ይታያሉ እነሱም :-

- የፌዴራል መ/ቤቶች ሂሳብ አያያዝ አሰራርና አቀራረብ ወጥነትና ተመሳሳይነት እንዲኖራቸው ያለማድረጉ፤

- የሚኒስቴር መ/ቤቱ ማቋቋሚያ አዋጅ 648/2001 ማስፈፀሚያ ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀፅ 51 ንዑስ አንቀፅ 1 ላይ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የክልል መንግስታት የፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ሥርዓት ከፌዴራል መንግስት ጋር ተጣጣመ መሆን እንዳለበት የተገለፀ ቢሆንም ሁሉም የክልል መንግስት መ/ቤቶች፣ 43 ከፍተኛ የመንግስት ትምህርት ተቋማት እንዲሁም 7 የፀጥታ ተቋማት መ/ቤቶች ሪፖርት የሚያቀርቡት (IBEX- Integrated Budget Expenditure) ሲስተም መሆኑ፤
- በፌደራል እና በክልል መንግስት መ/ቤቶች የሚከናወኑ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች አጠቃሎ የስራ እና የገንዘብ አፈፃፀማቸውን ወቅቱን ጠብቆ ሪፖርቱ በተሟላ ሁኔታ ከመደበኛው በጀት አፈፃፀም ሪፖርት ጋር የማይቀርብ መሆኑ፤
- የጥሬ ገንዘብ ዕቅዶችን፣ መርሃ ግብሮች፣ የአፈፃፀም ሪፖርቶችን፣ የጥሬ ገንዘብ ፍላጎትን፣ የሂሳብ እና የኦዲት ግኝት ማስተካከያዎችን በወቅቱንና በጥራት በባለበጀት መ/ቤቶች በኩል ተዘጋጅቶ ዕርዳታና ብድር ሂሣብ ያለባቸው መ/ቤቶች የሚያቀርቡት ሪፖርት በተሟላ መልኩ ከመደበኛ የሂሳብ ሪፖርት ጋር አብሮ አለመቅረቡና ለማቅረብ ሙሉ ፍቃደኝነት የሌላቸው መኖራቸው፤ እንዲሁም በሚኒስቴር መ/ቤቱ የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ከመፃፍ ውጪ ችግሩን ለመቅረፍ ምንም አይነት አስተዳደራዊ እርምጃ እየወሰደ አለመሆኑ፤ በተጨማሪም መ/ቤቶቹ ያለባቸውን ብድርና እርዳታ ለገንዘብ ሚኒስቴር በሪፖርት ሳያቀርቡ በአዲስ አደረጃጀት ከሌላ መ/ቤት ጋር መዋሃድ እንዲሁም መበታተን ዕዳና እርዳታ ያላቸው መ/ቤቶች በመከታል የእርምት እርምጃ እየወሰደ አለመሆኑ፤ በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

ሚኒስቴር መ/ቤቱ በመንግስት ሂሳብ ሪፖርት አቀራረብ ዙሪያ ጥናት ማድረጉን በተመለከተ ፤

ሚኒስቴር መ/ቤቱ በመንግስት ሂሳብ ሪፖርት አቀራረብ ዙሪያ የታዩ ችግሮች በመለየት ጥናት በማካሄድ ለችግሩ መፍትሄ ሊሰጥ ይገባል፡፡

በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ እንደተቻለው ሚኒስቴር በመንግስት ሂሳብ ሪፖርት አቀራረብ ዙሪያ ለሚታዩ ችግሮች ለመፍታት የተጠና ጥናት ለኦዲቱ ያልቀረበ መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት በሪፖርቱ አፃፃፍ ዙሪያ የታዩ

ያልተቀረፉ ችግሮች መኖራቸው እነሱም ፡-

❖ በመንግስት ሂሳብ ሪፖርት ለመፃፍ የሚጠቅሙ መረጃ እጥረት መኖር እና የተገኘው መረጃ ጥራቱን የጠበቀ ያለመሆን፣

ማሳያ፡-

✓ ወጪዎችን በትክክለኛ ወጪ አርእስት ተመዝግቦ የማይቀርቡበት ሁኔታዎች መታየታቸው፣

✓ የሚፃፍ ሪፖርት በአንድ አካል ወይም በአንድ ግለሰብ ብቻ በመፃፉ የተሰሩ ስራዎች በአግባቡ በመረጃ መልክ ተመዝግቦ አለመያዝ፤

✓ የሚፃፈው የሪፖርቱ መረጃዎች በሚመለከታቸው ኮሚቴዎች የማይገመገሙ መሆናቸው፤

❖ ሥራዎች በተያዘው የጊዜ ገደብ መሰረት ያለመጠናቀቅ፣

❖ ከፋይናንስ ጋር የተያያዙ አዳዲስ ውሳኔ የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች የሚያጋጥም መሆኑና ውሳኔ በቶሎ ተሰጥቷቸው በሂሳብ ሪፖርት የማይደረጉ መሆናቸው ፣

❖ ከአንዳንድ የመንግስት መስሪያ ቤቶች የሚቀርበው የገቢ፣ የወጪ፣ የተሰብሳቢ፣ ተከፋይ፣ የሂሳብ ማመዛዘኛ ሪፖርት ጥራቱንና ወቅቱን ጠብቆ አለመቅረቡ፣

❖ በተለያዩ የአስተዳደር እርከን ያሉ መ/ቤቶች ወጥ የሆነ የበጀት አወቃቀር አለመኖሩ፣

❖ አንዳንድ የመንግስት መ/ቤቶች የኦዲት ግኝት ማስተካከያ መርሃ ግብሩን በጊዜ አስተካልሎ ያለማቅረብና በጊዜ ገደቡ የማስተካከያ እርምጃ ያለመውሰዱ

ከተከለሱ ማስረጃዎች ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

የመንግስት የሂሳብ አያያዝና የሪፖርት አቀራረብ ዓለምአቀፍ የፐብሊክ ሴክተር የሂሳብ ደረጃዎች (IPSAS) ለመተግበር የሚያስችል ጥናት ማድረጉን በተመለከተ፤

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመንግስት የሂሳብ አያያዝና የሪፖርት አቀራረብ ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን የሚያስችል ሥርዓት ሊዘረጋ እና ወደ ዓለምአቀፍ የፐብሊክ ሴክተር የሂሳብ ደረጃዎች(IPSAS) እንዲሸጋገር ለማደረግ በጥልቀት ጥናት ሊያጠና ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ የመንግስት የሂሳብ አያያዝና ሪፖርት አቀራረብ አለም አቀፍ

ደረጃውን ለመጠበቅ የሚያስችል ስራዎች ስለመሰራታቸው ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት ተገኝተዋል፡-

- ✓ ከዚህ ቀደም ከተለያዩ ሃገራት በ IPSAS ዙሪያ የተወሰዱ ረቂቅ የሆኑ አጫጭር ጥናቶች ቢኖሩም ተጠናክረው እና ከፍተኛ ትኩረት ተሠጥቷቸው ያልተሰራ መሆኑ፤
- ✓ በ IPSAS ዙሪያ የተሰሩ ረቂቅ የሆኑ አጫጭር ጥናቶች ቢኖሩም ተጠናክረው እና ከፍተኛ ትኩረት ተሠጥቷቸው ያልተሰራ መሆኑ፤
- ✓ የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር ስትራቴጂክ እቅድ ከ2010-2014 ዓ.ም ተግባራዊ ለማድረግ የታቀደ ቢሆንም ተግባራዊ አለመደረጉ፤ አፈፃፀሙ አለመገምገሙ እና ተግባራዊ ያልተደረገበት በቂ ምክንያት አለመቅረቡ፡ እንዲሁም በቀጣይ አመታት ከ2015 ዓ.ም ጀምሮ የመንግስት የፋይናንስ አስተዳደር ስትራቴጂክ እቅድ ያልተዘጋጀ/የሌለው/ መሆኑ፤
- ✓ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚቀርበው ሪፖርት በዓለምአቀፍ ደረጃ በሚከናወነው የመንግስት ወጪና የፋይናንስ ተጠያቂነት /PEFA/ ግምገማ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያለ መሆኑ፤
- ✓ ኢትዮጵያ ከ2010 ዓ.ም ጀምሮ በሂደት ወደ ዓለምአቀፍ የፐብሊክ ሴክተር የሂሳብ ደረጃዎች (IPSAS) ለመሸጋገር የተቀበለች ሲሆን በዚህ ዙሪያ የፀደቀ ፍኖተ ካርታ (Road Map) የሌለ መሆኑ፤
- ✓ የመንግሥት ፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብን ወደ ዓለምአቀፍ ፐብሊክ ሴክተር የሂሳብ ደረጃዎች (IPSAS) እንዳይሸጋገር ያደረጉትን ተግዳሮቶች ወይም ችግሮች በመለየት እንዲቀረፉ ለምክር ቤት ያልቀረበ መሆኑ፤
- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመንግስት የሂሳብ አያያዝና የሪፖርት አቀራረብ ስርዓቱን በሂደት ወደ ዓለምአቀፍ የፐብሊክ ሴክተር የሂሳብ ደረጃዎች (IPSAS) እንዲሸጋገር ወቅታዊ እና ችግር ፈቺ የሆነ ጥናት ከሚመለከተው አካላት ጋር በመሆን ያልተጠና መሆኑ፤

ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከተደረጉ ቃለ መጠይቆች ለመረዳት ተችሏል፡፡

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመንግስት ሂሣብ ሪፖርት ሙሉ በሙሉ የመንግስትን ሀብትና ዕዳ ለማካተት ጥናት ማድረጉን በተመለከተ፤

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመንግስት ሂሣብ ሪፖርት ሙሉ በሙሉ የመንግስትን ሀብትና ዕዳ ያካተተ እንዲሆን ጥናት በማድረግ የተሟላ ሪፖርት ሊያቀርብ ይገባል፡፡

በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ እንደተቻለው ሚኒስቴር መ/ቤቱ በመንግስት ሂሣብ ሪፖርት ላይ ሙሉ በሙሉ የመንግስትን ሀብትና ዕዳ ማካተት እንዳለበት ጥናት በማጥና ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፤

- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከ2010-2014 የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር ስትራቴጂክ ዕቅድ ላይ ጥናት ለማድረግ የታቀደ መሆኑና በታቀደው መሰረት ጥናቱ ያልተጠና መሆኑ፤ በዚህም ምክንያት ሃገሪቷ ያለባትን የውጭ እዳ እና የመክፈያ ጊዜ ገደብ የሚያሳይ የተጠቃለለ ሪፖርት የማይቀርብ መሆኑ፤ ሃገሪቷ ያላትን የሃብት መጠን የሚያሳይ ሪፖርት የማይቀርብ መሆኑ፤ለመረዳት ተችሏል፡፡

ሚኒስቴር መ/ቤቱ በልዩ ሁኔታ የተቋቋሙ ፈንዶች ሂሳብ ሪፖርት አቀራረብን በተመለከተ

ሚኒስቴር መ/ቤቱ በልዩ ሁኔታ የተቋቋሙ ፈንዶች ሂሳብ በዓመታዊ የመንግስት ሂሳብ ሪፖርት ውስጥ አጠቃሎ ሊያቀርብ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ፡-

- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ መደበኛ እና ካፒታል በጀት ተብሎ ሪፖርት ከማቅረብ ውጪ በልዩ ሁኔታ የተቋቋሙ ፈንዶች ሂሳብ በዓመታዊ የመንግስት ሂሳብ ሪፖርት ላይ አጠቃሎ የማያቀርብ መሆኑ፡
- ✓ በልዩ ሁኔታ የተቋቋሙ ፈንዶች አጠቃሎ የማቅረብ ተግባርን ለማከናወን የሚያስችል ጥናት በ2010 ዓ.ም - 2014 ዓ.ም Public Finance Management Strategy Plan (PFMP) የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር ስትራቴጂክ ላይ የታቀደ ቢሆንም አመታዊ ዕቅዳቸው ላይ ያልተካተተ እና ያልተከናወነ መሆኑ፤

<u>ማሳያ፡-</u>

- ✓ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ሂሣብ ለመዝጋትና ለማስመርመር እንዲሁም ከመዝገብ መሠረዝ የሚገባቸዉን ሂሳቦች አጣርቶ ለውሳኔ ለማቅረብ የሚያስችል የተሟላ መረጃ በአግባቡ ማግኘት አለመቻል፣ የተለያዩ ምክንያቶችን መነሻ

በማድረግ በአንዳንድ አስፈጻሚዎች በኩል ከልማት አጋሮች የተላለፈን በጀት በአግባቡ አለመጠቀም፣ ከተከለሱ ማስረጃዎችና ቃለ መጠይቅ በማድረግ ለመረዳት ተችሏል፡፡

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፌዴራልና የክልል የመንግሥት መ/ቤቶች ወርሃዊ ሪፖርታቸውን ማቅረባቸውን በሚጠበቅበት ደረጃ መዘጋጀቱን እና መቆጣጠሩን በተመለከተ፡-

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፌዴራልና የክልል የመንግሥት መ/ቤቶች ወርሃዊ ሪፖርታቸውን በሀገር ውስጥ ገቢ/እርዳታ/ብድር ሂሳብ፣ በመደበኛ በጀት ወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣ በካፒታል በጀት ወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣ በገንዘብ ዝውውር ሂሳብ ሪፖርት፣ በተሰብሳቢ ሂሳቦች፣ በተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት እና በሂሳብ ማመዛዘኛ ሪፖርት ማዘጋጀታቸውን ሊከታተልና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ

- ✓ የሚቀርቡ ሪፖርቶች ደረጃውን በጠበቀ መልኩ እና መመሪያው በሚያዘው መልኩ እየቀረቡ አለመሆን፤ ማሳያ፡-
    - ✓ ወጪዎችን በትክክለኛ ወጪ አርእስት ተመዝግቦ አለመቅረቡ፣
    - ✓ መ/ቤቶች የእርዳታና ብድር ሂሳቦች ሪፖርት ያለማድረግ በተጨማሪም በተከፋይ እና በተሰብሳቢ በማለት በመለየት ሪፖርት ያለመላክ፣
- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በዚህ መልኩ ማቅረባቸውን ለመከታተል የሚያስችለው እቅድ በማውጣት መርሃ ግብር በመንድፍ በተቀናጀ መልኩ የማይከታተል መሆኑ በተጨማሪም ፈፃሚ መ/ቤቶቹ በቃል በማውራት እንዲያስተካክሉ ከመንገር ውጪ በህግ የእርምት እርምጃ የማይወስድ መሆኑ፤ ከተከለሱ ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመንግስት የፋይናንስ ክንውንና የገንዘብ ይዞታን የሚያሳይ ሪፖርት ማቅረብን በተመለከተ፤

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመንግስት የፋይናንስ ክንውንና የገንዘብ ይዞታን የሚያሳይ ሪፖርት በየአመቱና ባስፈለገ ጊዜ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ሊያቀርብ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ

- ✓ በ2014/2015 በጀት ዓመት በጀት የተያዘላቸው ፕሮግራም እና ፕሮጀክቶች አፈፃፀም በየስድስት ወሩ ሪፖርት ውስጥ ተካትቶ ያልቀረበ መሆኑ፤
- ✓ በ2015 በጀት አመት በውጭ ቀጥተኛ ድጋፍ 20.9 ቢሊዮን ለማግኘት የታቀደ ቢሆንም የተገኘው 22.4% ብቻ መሆኑ እና ዝቅተኛ አፈፃፀም የሆነበትን ምክንያት ተለይቶ ለተወካዮች ምክር ቤት ያልቀረበ መሆኑ፤
- ✓ በ2014 በጀት ዓመት በሰሜኑ ጦርነት ምክንያት ጉዳት ለደረሰባቸው አካባቢዎች መልሶ ለማቋቋም በህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ተጨማሪ በጀት ያፀደቀ ቢሆንም በምን ያህል መጠን ስራ ላይ እንደዋለ በሪፖርት ያልተካተተ መሆኑ፤
- ✓ ለመልሶ ማቋቋም ግንባታ ፕሮግራም በ2015 በጀት ዓመት በምክር ቤቱ ከፀደቀው 20 ቢሊዮን በጀት ውሰጥ ምን ያህል ስራ ላይ እንደዋለ በሪፖርቱ ያቀረበ መሆኑ፤ ከተከለሱ ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

የመንግስት የፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ በፌዴራል፣ በክልልና መስተዳድሮች የተጣጣመ መሆኑን በተመለከተ

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የክልል መንግሥታትን የፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ሥርዓት ከፌዴራል መንግሥት ጋር የተጣጣመ እንዲሆን ሊያደርግ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ፡

- ✓ የተቀናጀ የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓትን በታቀደው መልኩ ወደ ክልሎችና ወረዳዎች ማዳረስ አለመቻሉ፣
- ✓ ከክልሎች እና የትምህርት ተቋማት በወቅቱ እና በተቀመጠው የጥራት መጠን ሪፖርት የማያቀርቡ መሆኑ፤
- ✓ ከፌዴራልና የክልል መንግስት መ/ቤቶች ሂሳብ አያያዝ አሰራርና አቀራረብ ወጥና ተመሳሳይነት እንዲኖራቸው ክትትል አለመደረጉ፤
- ✓ በፌዴራልና በክልል መንግስት መ/ቤቶች የሚቀርቡ የመንግስት ሪፖርቶች በሁለት አይነት ማለትም በኢፍ.ሚስ እና አይቢኤክስ መሆኑ ከተከለሱ ማስረጃዎች ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

ከላይ ለተገኙት ክፍተቶች ለማሻሻል አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ተብሎ የታመነባቸው የማሻሻያ ሃሣቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- ❖ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በመንግስት ሂሳብ ሪፖርት አቀራረብ አለም አቀፍና ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን ለማድረግ እንዲያስችለው ችግሮችን በመለየት እና ጥራቱን የጠበቀ ጥናት በማካሄድ በጥናቱ መሰርት ለታዩት ችግሮች የመፍትሂ ሃሳብ ሊስጥ ይገባል፡፡
- ❖ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመንግስት የሂሳብ አያያዝና የሪፖርት አቀራረብ ስርዓቱን በሂደት ወደ አለም አቀፍ የፐብሊክ ሴክተር የሂሳብ ደረጃዎች(IPSAS) እንዲሸጋገር ለማድረግ እና የፌዴራልና የክልል መንግስት መ/ቤቶች እንዲሁም የመንግስት ልማት ድርጅቶች የፋይናንስ ስርዓቱን ለመወሰን እና ለመቆጣጠር የሚችል   የስራ አመራር ቦርድ ሊያቋቁም ይገባል፡፡
- ❖ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመንግስት ሂሣብ ሪፖርት   የመንግስትን ሃብትና እዳን የያዘ ሂሳብ የያዘ ሪፖርት ለመፃፍ እና መንግስት ምንያህል ጥሬ ሃብት እና እዳ እንዳለው ለማወቅ የሚያስችል ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡
- ❖ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሀገር ውስጥም ሆነ ከውጭ ለተለያየ አላማ ለማዋል በልዩ ሁኔታ የተቋቋሙ የፈንድ ሂሳቦች ለታለመላቸው አላማና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ላይ መዋላቸውና ለማወቅና ለመቆጣጠር እንዲያሥችለው ከመደበኛ በጀት አፈፃፀም ጋር አጠቃሎ በሚያቀርበው በመንግስት ሂሳብ ሪፖርት ውስጥ ተካትቶ ሊያቀርብ ይገባል፡፡
- ❖ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በየአመቱ ለተለያዩ ለልማትና ለእድገት እንዲሁም ለኢኮኖሚ እድገት የሚመድበውን በጀት በአግባበቡ ለታለመለት አላማ መዋሉን እና ለቀጣይ በተሻለ መልኩ የሀገሪቷን ዕድገት ለመምራት እንዲያስችለው የፌዴራልና የክልል የመንግሥት መ/ቤቶች ወርሃዊ ሪፖርታቸውን በሀገር ውስጥ ገቢ/እርዳታ/ብድር ሂሳብ፣ በመደበኛ በጀት ወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣ በካፒታል በጀት ወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣ በገንዘብ ዝውውር ሂሳብ ሪፖርት፣ በተሰብሳቢ ሂሳቦች፣ በተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት እና በሂሳብ ማመዛዘኛ ሪፖርት አማካኝነት ሪፖርት ማዘጋጀታቸውን የሚከታተልበት ስርዓት በመዘርጋት ሊከታተልና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡
- ❖ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ግልፀኝነት እና ተዓማኒነትን ለሚመለከተው አካለት ለማስረፅ እንዲያስችል የመንግስት የፋይናንስ ክንውንና የገንዝብ ይዞታን የሚያሳይ ሪፖርት በየአመቱና ባስፈለገ ጊዜ ጥራቱና ወቅቱን ጠብቆ ያቀርብ ይገባል፡፡

❖ ሚኒስቴር መ/ቤቱ እንደ ሃገር ለኢኮኖሚ እና የልማት እድገት ለማምጣት በየአመቱ የሚመደበው በጀት ተዓማኒና ወጥነት እንዲኖረው ለማስቻል የክልል መንግሥታትን የፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ሥርዓት ከፌዴራል መንግሥት ጋር እንዲጣጣም ተገቢውን ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

❖ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰርት የመንግስት ፋይናንስ ሪፖርት እንዲቀርብ ለማድረግ የፌዴራልና የክልል መንግስት መ/ቤቶችን የሚቆጣጠርበት እና እንደአስፈላጊነቱ እርምጃ የሚወስድበት ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

❖ ሚኒስቴር መ/ቤቱ አለም አቀፍ የፐብሊክ ሴክተር የሂሳብ ደረጃዎች(IPSAS) ላይ ስርዓቱ በአግባቡ ተግባራዊ ሆኖ ለመፈፀም እና ለመገምገም እንዲያስችለው የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ግንዛቤ ሊፈጥር እና ስልጠና ሊሰጥ ይገባል፡፡

4. የአካባቢ ክዋኔ ኦዲት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር የ2015-16 ኦዲት አመት የተከናወኑ ኦዲት ሪፖርት ማጠቃለያ

በውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር የከተሞች የፍሳሽ ቆሻሻ አወጋገድ እና የሳኒቴሽን መሰረተ ልማት ግንባታ አፈጻጸም በተመለከተ

የሳኒቴሽን መሰረተ ልማት ፖሊሲ እና የሕግ ማዕቀፎች ዝግጅት በተመለከተ

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሳኒቴሽን መሰረተ ልማት ፖሊሲ እና የህግ ማዕቀፎች (ሳኒቴሽን የጥናትና ዲዛይን፣ የግንባታና የተቋማት አስተዳደር መስፈርቶች፣ ስታንዳርዶችና ማኑዋሎችን) ሊያዘጋጅና ተግባራዊነቱን ሊከታተል ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡

➢ የሳኒቴሽን መሰረተ ልማት የሚመራበት ፖሊስ ፣የሳኒቴሽን የጥናትና ዲዛይን፣ የግንባታና የተቋማት አስተዳደር እና የሳኒቴሽን መሰረተ ልማት ከተገነባ በኋላ የፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝ አወጋገድ ሥርዓት ዙሪያ/ያሉት ችግሮች ላይ ክትትል ለማድረግ የሚያስችል ማኑዋል በማዘጋጀት በክልልሎች ተግባራዊ እንዲያደርጉት ያልተላከ መሆኑ፣

የሳኔተሽን መስረት ልማት ፅንሰ-ሀሳብ እና የአዋጭነት ጥናቱ በገለልተኛ አካል ግምገማ መደረጉን በተመለከተ

ሚኒስቴር መ/ቤቱ በከተሞች ለሚገነቡት የሳኔተሽን መስረት ልማት ግንባታ ከመካሄዱ በፊት የፕሮጀክት ፅንሰ-ሀሳብ አዘጋጅቶ እንዲመረጥ ስለማድረጉና ወደ ተግባር ለመቀየር ያዘጋጀውን የአዋጭነት ጥናቱን በገለልተኛ አካል ግምገማ መደረጉን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡

- የሳኒቴሽን መሰረተ ልማት ፕሮጀክቶች ለአብነት (የደቡብ አቃቂ ፍሳሽ ተፋሰስ በቀን 60ሺ.ህ ሜትር ኩዩብ ፍሳሽ ማጣራት ለሚችል ፕሮጀክት ጥናቱን አጠናቆ መስከረም/2016 ያቀረበ ቢሆንም፤ጥናቱን ለፕላንና ልማት ሚኒስቴር አቅርቦ እንዲገመገም ያልተደረገ መሆኑ፤

የሳኒቴሽን መሰረተ ልማት ግንባታው በተያዘለት ጊዜና በጀት መከናወኑን በተመለከተ

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመከታተያ ቅፅ በማዘጋጀት በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት የከተሞች ሳኒቴሽን መሠረተ ልማት ግንባታ ሥራዎች በውሉ መሠረት የጥራት ደረጃቸውን ጠብቀው በተያዘላቸው ጊዜና በጀት መከናወናቸውን ለማረጋገጥ ወቅታዊ ወይም ተከታታይ የሆነ ክትትልና ግምገማ በማድረግ ግብረ-መልስ የሚልክበት ስርአት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡

- የ3 ከተሞችን (ጋምቤላ፣ አሶሳ፣ ሰመራ ሎጊያ) ጥናትና ዲዛይን ስራ ለማሰራት በአንድ አመት(በ300 የስራ ቀን) ውስጥ አጠናቆ ለማቅረብ በታህሳስ 2012 በጀት ዓመት ውል ተገብቶ ጥናቱ በጥር/2015 ዓ.ም የተጠናቀቀ ሲሆን፤ ጥናቱን በውሉ ላይ ከተጠቀሰው ጊዜ በላይ ሦስት አመት የዘገየ መሆኑን፤
- የምስራቅ ተፋሰስ ፍሳሽ ፕሮጀክት (በቀን 104 ሺ.ህ ሜትር ኪዩብ ፍሳሽ ማጣራት የሚችለው ፕሮጀክት) ከአማካሪ መሃንዲስ ከNicoholas o.dwer limited in Jv with ms concultancy plc ከሚባል የአየርላንድ ድርጅት ጋር የአዋጭነት ጥናት፣

ዝርዝር ጥናት እና የጨረታ ሰነዶችን ለማዘጋጀት በታህሳስ 2011 ውል የገባ ሲሆን፤ የአዋጭነት ጥናቱን በ7 ወር እንዲሁም ዝርዝር ጥናቱንና የሚዘጋጁት የጨረታ ዶክመንት አዘጋጅቶ ለማቅረብ በ14 ወር እንደሚያቀርብ በጠቅላላው በ21 ወር ውስጥ ስራውን አጠናቆ እንደሚያቀርብ የተዋዋለ ቢሆንም፤ ጥናቱን በሰኔ 2015 ዓ.ም አጠናቆ ያቀረበ ሲሆን፤ ጥናቱን ማቅረብ ከሚገባው ከተዋዋለበት ጊዜ (አንድ ዓመት ከስምንት ወር ዘግይቶ የተጠናቀቀ መሆኑ፣

- በ2015 በኦሮሚያ ክልል ስር ለሚገኙ ሶስት ከተሞች (አሰላ፤ ቢሾፍቱ እና ሻሸመኔ) የግንባታ ኮንትራክተር ቅጥር በማከናወን ስራውን ወደ 28% ለማድረስ ሙያዊ እገዛ መስጠት፡- እስከ አራተኛዉ ሩብ ዓመት 28% ለማከናወን ታቅዶ ሥራዉ ያልተከናወነ መሆኑ፤
- በኦሮሚያ ክልል ስር ለሚገኙ ሁለት ከተሞች (ጅማ እና ነቀምቴ) የግንባታ ኮንትራክተር ቅጥር በማከናወንና ሙያዊ እገዛ በመስጠት እስከ 2015 አራተኛዉ ሩብ ዓመት 28% ለማከናወን ታቅዶ፤ ሥራዉ ያልተከናወነ መሆኑ፤

የተገነቡት የሳኒቴሽን መሰረተ ልማት ተገቢውን ጥገናና እንክብካቤ መደረጉን በተመለከተ

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ቀድመው አገልግሎት በመስጠት ላይ ለሚገኙ የሳኒቴሽን መሰረተ ልማት ግንባታዎች ተገቢውን ጥገናና እንክብካቤ ሊያደርግና ሊከታተል ይገባል።

ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡

- በ2015 በጀት ዓመት በ8 ከተሞች 67 የህዝብና 95 የጋራ መፀዳጃ ቤቶች በአጠቃላይ 162 መጸዳጃ ቤቶችን የእድሳት ስራ ለማከናወን ታቅዶ የነበረ ቢሆንም፤ አፈጻጸሙ ግን በቁጥር 25 የመፀዳጃ ቤቶች ወይም 15% ብቻ ስለታደሱ አፈጻጸሙ ዝቅተኛ መሆኑ፤
- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተዘረጋውን የፍሳሽ ማስወገጃ መስመር በተመለከተ የኦዲት ቡድኑ በቅዱስ ጳውሎስ ሚኒሊየም ህክምና ኮሌጅ ሆስፒታል ባከሄደው መስክ ምልከታ ወቅት ከሆስፒታሉ ጀርባ ካላው ኮንዲሚኒም የሚወጣው ፍሳሽ በሆስፒታሉ ግቢ አቋርጦ የሚወጣ ሲሆን፤ በመንገድ ዳር ያለው ፍሳሽ ማስወገጃ ፈንድቶ በወቅቱ ጥገና ያልተደረገና

ፍሳሹ የአካባቢን ማኅበረሰብ ከመረበሽም አልፎ በጎርፍ ማስወገጃ ውስጥ በመግባት የአካባቢውን ወንዝ እየበከለ መሆኑ፤

- ከ2011 ጀምሮ ለጅማና ለነቀምት ከተማ መፀዳጃ ቤቶች ጥገና እንደተደረጋላቸው ቢገለጽም፤ በጅማ በፊት የተገነቡት ሌሎች መጸዳጃ ቤቶች በውሃ እጥረት ምክንያት አገልግሎት እየሰጡ አለመሆናቸው

የፍሳሽ ቆሻሻ ከማከማቻ/መሰባሰቢያ እስከ መልሶ መጠቀም/ማስወገድ ያለው የሰንሰለት አገልግሎት እየተሰጠ መሆኑን በተመለከተ

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የከተሞችን የፍሳሽ ቆሻሻ ከማጠራቀሚያ/መሰብሰቢያ እስከ መልሶ መጠቀም/ማስወገድ ያለውን አጠቃላይ የሳኒቴሽን ሰንሰለት ጥንቃቄ የተሞላበት የሳኒቴሽን አገልግሎትና አስተዳደር ሊያረጋግጥ ይገባል።

ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት

- በአቃቂ ቃሊቲ የፍሳሽ ቆሻሻ ማጣሪያ በመስክ ምልካታ ወቅት ለኦዲት ቡድኑ በቀን 100,000 ሜትር ክዩብ ፍሳሽ ቆሻሻ የማጣራት አቅም ያለው ቢሆንም፤ በየቀኑ እስከ 70,000 ሜትር ክዩብ (ከአቅም በታች) ፍሳሽ ቆሻሻ ብቻ እያጣራ መሆኑ፤
- የተጣራውን ፍሳሽ ውሃ መልሶ ለመጠቀም(ለመስኖ፤ ለከተማ አረንጓዴ ልማት ለአስፋልት እጥበትና ለመሳሰሉት) እንዲቻል የተጠና ጥናት የሌለ መሆኑ፤
- ከፍሳሽ ማጣሪው ሂዳት የሚወጣው ጋዝ 65 እስከ 75% ሚቴይን ጋዝ ስለሚሰጥ በመጠነኛ ማሻሻል ለሲሊንደርና ለጄኔሬተር መጠቀም እየተቻለ በቃጠሎ መልክ እየተወገደ ያለ መሆኑ እና
- ከፍሳሽ ማጣሪያው የሚወጣው ደረቅ ቆሻሻ (Sludge) ለማዳበሪያነትና ለተለያዩ ጥቅሞች ማዋል እየተቻለ፤ በማጣሪያው ግቢ ተከማችቶ ያለ መሆኑ፤
- የፍሳሽ ማጣሪያ ግቢ ዙሪያውን በከፊል ብቻ በአጥር የተሸፈነ ሲሆን፤ በግቢው የአትክልት/ደን ሽፋን የተወሰኑ የተተከሉ ቢኖርም፤ ከግቢው ስፋት አንጻር አነስተኛና ከተተከሉት ውስጥም የደረቁ የሚታዩ መሆኑ፤
- በተጨማሪ ደብረብርሃን ከተማ የፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ከከተማዉ በ13 ኪ.ሜ ርቀት ላይ በደረቅ ማስወገጃ ስፍራ አጠገብ በአጥር ታጥሮ ያለ ቢሆንም፤ የአካባቢዉ ህብረተሰብ እንስሳት ሞተዉባቸዉ ባቀረቡት ቅሬታ አሁን

አገልግሎት እየሰጠ እንዳልሆነና ከየመኖሪያ ቤቱና ሌሎች ድርጅቶች የሚፈሰው ፍሳሽ ቆሻሻ በቀጥታ ወደ ወንዝና በገበሬዉ ማሳ እየተደፋ ሲሆን፤ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፍሳሽ ማስወገጃ ግንባታውን ለመገንባት እስከሁንም በጥናት ደረጃ ያለ መሆኑ፤

- የሐረሪ ከተማ ፍሳሽ ቆሻሻውን የሚያስወግድበት ወይም የሚደፋበት ሳንድ ፊል የሌለው በመሆኑ ቀጥታ ከጎርፍ መውረጃ መስመር ጋር በመገነኘት ወደ አካባቢው ወንዝ እየተለቀቀ መሆኑ፤
- በጅግጅጋ ከተማ ባደረገው የከተማው ስታንዳርዱን የጠበቀ የፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ እንደሌለውና በከተማው በርቀት ላይ በተቆፈረ ጉድጓድ (land fill) ላይ ፍሳሹ የሚወገድ ሲሆን፣ ጉድጓዱ ሞልቶ ወደ አካባቢው ማህበረሰብና ወደ ወንዞች በመፍሰስ ወንዙም ወደ አራርሶ ከተማ፣ ደገ ሃቡር፣ ጎዴ ከተሞች ጋር በመድረስ የአካባቢው ማህበረሰብ እንደሚጠቀሙት እና እንስሳት እንደሚጠጡት፤ እንዲሁም ወደ ሸበሌ ወንዝ በመቀላቀል የአካባቢው ማህበረሰብ ለመጠጥ አገልግሎት እያዋለው ቢሆንም ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአፋጣኝ ወደ ግንባታ ገብቶ ችግሩን ለመቅረፍ የዘገየ መሆኑ፤

የከተሞች ፍሳሽ ቆሻሻ በአግባቡ እንዲጓጓዝ አስፈላጊ የሆኑ መሰረተ-ልማት አውታር መዘርጋቱን በተመለከተ

ሚ/ር መ/ቤቱ ከተለያዩ ተቋማት የሚፈሱት ፍሳሽ ቆሻሻ አስፈላጊ የሆኑ መሰረተ-ልማት አውታሮችን እንዲዘረጉ በማድረግ የፍሳሽ አወጋገድ ስርዓቱ እንዲጠናከር ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ ይገባል።

ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡-

- በአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን የአቃቂ ተፋሰስ፣ በቃሊቲ ተፋሰስ፣ በምስራቅ ተፋሰስ፣ በሦስት አመታት (ከ2013-2015 ዓ.ም) ከተጠናው ከ623.69 ኪ.ሜ የመስመር ዝርጋታ ጥናትና ዲዛይን ውስጥ ወደ ተግባር ወይም የፍሳሽ መስመር ዝርጋት የተከናወነው 392.31 ኪ.ሜ ወይም 63 ፐርሰንት ብቻ ሲሆን ቀሪው 231.38 ኪ.ሜ ወይም 37 ፐርሰንት ለጥናቱ ወጪ የወጣበት ቢሆንም፤ የፍሳሽ መስመር ዝርጋታ ጥናትና ዲዛይን ወደ መስመር ዝርጋታ ያልተቀየረ መሆኑ፡፡

በሰንጠረዥ የፍሳሽ መስመር ጥናት ዲዛይን እና መስመር ዝርጋታ አፈጻጸም በኪ.ሜ

በጀት ዓመት	የፍሳሽ መስመር ዝርጋታ ጥናትና ዲዛይን በኪ.ሜ		የፍሳሽ መስመር ዝርጋታ አፈጻጸም በኪ.ሜ			ተጠንቶ ወደ ፍሳሽ መስመር ዝርጋታ ያልተቀየረ በፐርሰንት
	ዕቅድ	አፈጻጸም (ሀ)	ዕቅድ	አፈጻጸም (ለ)	ከተጠናው ውስጥ ወደ ፍሳሽ መስ መር ዝርጋታ ያልተቀየረ በኪ.ሜ (ሀ)-(ለ)=ሐ ልዩነት	
2013	132.76	138.98	84.27	96.27	42.71	31%
2014	323.11	319.31	243.62	159.34	159.97	50%
2015	170.15	165.4	136.34	136.7	28.7	17.35%
ድምር	626.02	623.69	464.23	392.31	231.38	37

በቅዱስ ጴጥሮስ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል በአካባቢው በአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን የተገነባ ምንም አይነት የፍሳሽ ቆሻሻ መስመር ባለመኖሩ ተቋሙ የሚጠቀመውን ሲፕቲክ ታንከር በ23 ቀበሌ ባለው የወንዝ ፍሳሽ መሄጃ ጋር አገናኝተውት የሆስፒታሉ ፍሳሽ ቆሻሻ የአካባቢውን ማህበረሰብ ሽታው እየረበሸና ቀጥታ ወደ ወንዝ እየተለቀቀ ሲሆን፤ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአካባቢው የፍሳሽ መስመር እንዲዘረጋላቸው የሰራው ስራ የሌለ መሆኑ፤

በሳኒቴሽን ዘርፍ ለተሰማሩት ባለሙያዎች የአቅም ግንባታ ስልጠና መሰጠቱን በተመለከተ

ሚ/ር መ/ቤቱ በሳኒቴሽን ዘርፍ ለተሰማሩ ለፌዴራል እና ለክልል ባለሙያዎች ብቃታቸውን ለማጎልበት (በጥናት እና ዲዛይን፣ በፕሮጀክት፣ በግዥ እና በኮንትራት፤

በገንዘብ አስተዳደርና ተጠያቂነት)፤እንዲሁም ለግል ሴክተሩ ማለትም ለግንባታ ተቋራጮች፣አማካሪዎች፤በምርትና ዕቃ አቅራቢዎች ዘንድ የሚስተዋሉ ክፍተቶችን ለመቅረፍ ወቅታዊነት ያለው የአቅም ግንባታ ስልጠና ሊሰጥ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡-

- በ2015 በግንባታ ክትትልና ኮንትራት አስተዳደርና የዓለም ባንክ የግዥ መመሪያ/ Guide line/ ላይ ከፌዴራል፤ ክልሎች እና ከተሞች ለተወጣጡ ሰልጣኞች በአንድ ዙር ለ6 ቀናት ለ 60 ሰልጣኞች ሥልጠና ለመስጠት፡- እስከ አራተኛዉ ሩብ ዓመት 60 ባለሙያዎችን ለማሰልጠን ታቅዶ በዕቅዱ መስረት ያልተሰጠ መሆኑ፤
- በ2013 በጀት ዓመት በሳኒቴሽን ጽንሰ ሐሳብና ንጽህና አጠባበቅ ላይ ከክልሎችና ከከተማ አስተዳደሮች የተወጣጡ ለ80 ባለሙያዎች የአሰልጣኞች ስልጠና ለመስጠት ቢታቀድም የአቅም ግንባታው ስልጠና ያልተሰጠ እንዲሁም በ2014 እና በ2015 በጀት ዓመት ዕቅድ ውስጥም አካተው ያልተተገበረ መሆኑ፤

የህብረተሰብ ተሳትፎ በማምጣት ዘላቂነት ያለው የሳኒቴሽን አገልግሎት ፕሮግራሞች ማረጋገጡን በተመለከተ

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሳኒቴሽን ተቋማት ግንባታ በተጨማሪ የባህሪይ ለውጥና ተጠቃሚው ህብረተሰብ ተሳትፎ በማምጣት፣ ዘላቂነት ያለው የሳኒቴሽን አገልግሎት ፕሮግራሞችን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡-

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፍሳሽ ቆሻሻ ከማስወጋድ ጋር በተያዘ አገር አቀፍ ምክክር/ የውይይት መድረኮችን ፈጥሮ ግንዛቤ ማስጨበጫ ለመስጠት በ2013 ፕሮፖዛል የተቀረጸ ቢሆንም፤ በ2014 በጀት ዓመትም ግንዛቤ ማስጨበጫ ለመስጠት ዝግጅት አድርጎ እንደነበርና ይህ ኦዲት ሪፖርት እስከተጠናቀቀበት ድረስ የተሰጠ ግንዛቤ ማስጨበጫ የሌለ መሆኑ፤

በኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የእንስሳት ቁራዎች አደረጃጀት እና የስጋ ምርት አገልግሎት አሰጣጥ ውጤታማነት በተመለከተ

የእንስሳትንና የእንስሳት ውጤቶች ልየታ ምዝገባ ፣የኋልዮሽ ክትትል እና ደህንነት የሬጉላቶሪ ቁጥጥር ስርዓት የሚያግዙ የፖሊሲ የህግ ማዕቀፎችን መዘጋጀታቸውን በተመለከተ

ባለስልጣኑ የእንስሳትንና የእንስሳት ውጤቶች ልየታ ምዝገባ፣ የኋልዮሽ ክትትል እና ደህንነት የሬጉላቶሪ ቁጥጥር ስርዓት የሚያግዙ የፖሊሲ ሀሳቦች፣ ስትራቴጂዎችን፣ የህግ ማዕቀፎችን እንዲዘጋጅ እና እንዲጸድቅ ምክረ ሀሳብ ሊያቀርብና ሲጸድቁም ተግባራዊነቱን በበላይነት ሊመራ ይገባል፡፡

ነገር ግን ባለስልጣኑ የእንስሳትንና የእንስሳት ውጤቶች ልየታ ምዝገባ፣ የኋልዬሽ ክትትል ረቂቅ አዋጁ ከተዘጋጀበት ሰኔ 2009 ዓ.ም ኦዲቱ እስከ ተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ አዋጁ ያልጸደቀ መሆኑ፤

የእርድ እንስሳትን የምዝገባና ኋልዮሽ ክትትልና ቁጥጥር ሥርዓትን በተመለከተ

ባለስልጣኑ የእርድ እንስሳትን የምዝገባና ኋልዮሽ ክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በእንስሳት ምርት (ሥጋ) ጤንነትና ደህንነት ዙሪያ አስፈላጊ መረጃ ለማግኘት የሚያስችል ሥርዓት ባለመኖሩ፣ ለእርድ የሚቀርቡ እንስሳት የኋላ ታሪካቸዉን (የጤና ሁኔታ፤ የመጡበት አካባቢ፤ የእንቅስቃሴያቸዉ ሁኔታ፤ ዝርያቸዉ እና ሌሎች መረጃዎች) ለመከታተል የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ባለመኖሩ የዳልጋ ከብቶችም ሆኑ በጎችና ፍየሎች የእንስሳት ልየታ ምዝገባ እና ክትትል ስርአት ውስጥ ያልገቡ መሆኑ፣

የምዝገባና የኋሊዮሽ ስርአት ማረጋገጫ አሰጣጥና አጠቃላይ የእንስሳት ልየታና ምዝገባ ሥርዓት በተመለከተ

ባለስልጣኑ የምዝገባና የኋሊዮሽ ስርአት ተከትለው የመጡ የእርድ እንስሳትን አመሳክሮ ማረጋገጫ በመስጠትና በዚሁ ስርአት እንዲቀጥሉ በማድረግ አጠቃላይ የእንስሳት ልየታና ምዝገባ ሥርዓቱን በማጠናከር የምግብ ደህንነትን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ በናሙና ተመርጦ በታዩት 6 ኤክስፖርት ቄራዎች፣ ፍሪጎ ሪፌኮ የቦራን ምግቦች ኃላ/የተ/የግ/ማህበር ኤክስፖርት ያቆመ በመሆኑ ያልተካተተ ሲሆን ሉና የስጋ አምራችና ላኪ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር፣ አክሻከር ቄራ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር፣ አቢሲኒያ ኤክስፖርት ቄራ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር፣ ኤልፎራ ደብረዘይት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እና ኦርጋኒክ ኤክስፖርት ቄራ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር፣ ሁሉም ቄራዎች የሚያከናውኑት የቅድመ እርድ ምርመራ የእንስሳውን የኋላ ታሪክ መሰረት ያደረገ አለመሆኑ፣

ባለስልጣን መ/ቤቱ የመንግስት እና የግል የአገር ውስጥ ቄራዎች ምዝገባ ና የብቃት ማረጋገጫ መስጠቱን በተመለከተ

ባለስልጣን መ/ቤቱ የመንግስት እና የግል የአገር ውስጥ ቄራዎችን ከክልሎች ጋር በመሆን ሊመዝገብና የብቃት ማረጋገጫ ሊሰጥ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ ባለስልጣኑ፡-

- የመንግስት እና የግል የአገር ውስጥ ቄራዎችን ከክልሎች ጋር በመሆን መመዝገብና የብቃት ማረጋገጫ የመስጠት ስራን አለማከናወኑ፣
- በመንግስት እና በግል የአገር ውስጥ ቄራዎች የሚያቀርበውን ሥጋና የስጋ ተረፈ ምርት ጤንነት ጥራትና ደህንነት ቁጥጥር ሥራ አለመከናወኑ፣
- በ2015 በጀት አመት በ60 ከሥጋ መሸጫ ወይም ልኳንዳ ቤቶች በሚሰበሰበው የሥጋ ምርት ናሙናዎች ላይ የጥራትና ደህንነት ምርመራ ተግባራት ለማከናወን ታቅዶ መከናወኑን የሚያሳይ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፤

የመዳረሻ ገበያን ለማስፋት የሚያስችል ስርአት መኖሩንና ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ

ባለስልጣኑ የመዳረሻ ገበያን ለማስፋት በጥናት ላይ የተመሰረተ ባለሀብቱ ጥራቱን፣ ደህንነቱንና ጤንነቱን በጠበቀ መልኩ በህጋዊ መንገድ የስጋ ምርቱን ወደ ውጭ አገር እንዲልክ የሚያደርግ ስርአት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ፡-

- የመዳረሻ ገበያን በሚመለከት በባለስልጣኑ ጥናት ስለመጠናቱ ማስረጃ ለኦዲት ቡድኑ ያልቀረበ መሆኑ፤ ተጨማሪ የመዳረሻ ገበያዎችን ለማግኘት፤ እንዲሁም

አሁን ያሉትን ገበያዎች ቀጣይነት ለማረጋገጥ በሚያስችል መልኩ እንስሳት ልየታና ምዝገባ ስርዓትን በአለም ዓቀፍ ደረጃ ማስተዋወቅ አለመቻሉ፣

- እንደሀገር ከበሽታ ነፃ የሆነ ቀጠና መፍጠር ባለመቻሉና በተለይም አፈ-ተግር የተባለ በሽታ ዳልጋ ከብቶችም ሆነ በበጎችና ፍየሎች ላይ የሚከሰትና አፋቸውንና እግራቸውን በማቁሰል የሚያጠቃቸው በቫይረስ አማካኝነት የሚነሳ ሲሆን ከሰውነታቸው በሚወጣ ፈሳሽ የሚተላለፍ በመሆኑ በቀላሉ የሚዛመት ስለሆነ ይህንን በሽታ ማጥፋት ባለመቻሉ የመዳረሻ ገበያን ማስፋት አለመቻሉ፣
- እንደ ሀገር የርቢ ማቢያ /commercial ranch/ አለመኖሩ፣ የውጪ ገበያን ለማስፋፋት በባለስልጣኑ ደረጃ እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በሚፈለገው ደረጃ ተቀናጅቶ ያለመስራት፣ ለውጪ ገበያ የሚሆኑ የእርድ እንስሳትን በጥራትም ሆነ በብዛት በገበያ ላይ ባለመገኘቱ የመዳረሻ ገበያን ማስፋት እንዳልተቻለ ከተከለሱ መረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች ለማወቅ ተችሏል፡፡

ባለስልጣን መ/ቤቱ የመንግስት እና የግል የአገር ውስጥ ቄራዎች ምዝገባ ና የብቃት ማረጋገጫ መስጠቱን በተመለከተ

ባለስልጣን መ/ቤቱ የመንግስት እና የግል የአገር ውስጥ ቄራዎችን ከክልሎች ጋር በመሆን ሊመዝገብና የብቃት ማረጋገጫ ሊሰጥ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ ባለስልጣኑ፡-

- የመንግስት እና የግል የአገር ውስጥ ቄራዎችን ከክልሎች ጋር በመሆን መመዝገብና የብቃት ማረጋገጫ የመስጠት ስራን አለማከናወኑ፣
- በመንግስት እና በግል የአገር ውስጥ ቄራዎች የሚያቀርበውን ሥጋና የስጋ ተረፈ ምርት ጤንነት ጥራትና ደህንነት ቁጥጥር ሥራ አለመከናወኑ፣

በቄራዎች ውስጥ የሳኒተሪ፣ የምግብ ደህንነት እና የሰራተኞች ደህንነት መርሆች እንዲተገበሩ ስታንደርዶች ማውጣቱን በተመለከተ

ባለስልጣን መ/ቤቱ በቄራዎች ውስጥ የሳኒተሪ፣ የምግብ ደህንነት እና የሰራተኞች ደህንነት መርሆች እንዲተገበሩ የተለያዩ ስታንደርዶች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ውይይት በማድረግ ሊያወጣ ይገባል፡፡

- ይሁን እንጂ ለስጋ ምርት የንፅህና አጠባበቅ ደንብ (ES 1114_2005 Code of hygienic practice for processed meat products)፣ ፍሬሽ የስጋ ምርት የንፅህና አጠባበቅ ደንብ (ES 1115_2005 Code of hygienic practice for fresh meat) የኤክስፖርት ቄራ የንጽህና አጠባበቅ (ES 1134_2005 Abattoirs Code of hygienic practice) የቄራዎች መሰረታዊ መስፈርቶች (1118-2005 Abatiors besic requirmentes) የቁም እንስሳ ገበያ ላይ ያሉ መሰረታዊ መስፈርቶች (ES 1135-2005 besic requirments for alive stock market) የስጋና የቁም እንስሳ ደረጃ (ES 2789-2006 grading live animals and carcass) የተባለ ስታንዳርድ በባለስልጣኑ እና በኢትዮጵያ ደረጃዎች ኢንስቲትዩት የወጡ ሲሆን፤ በናመና ተመርጠው ከታዩት 6 ቄራዎች ውስጥ አንዱ ኤክስፖርት ያቆመ በመሆኑ፤ ያልተካተተ ሲሆን አምስቱ ቄራዎች ስታንዳርዶቹን የመተግባር ችግር ያለባቸው መሆኑ፣

ቄራዎች የፍሳሽና ደረቅ ቆሻሻዎች አወጋገድ የአካባቢ ጥበቃ መስፈርት አሟልተው መስራታቸው በተመለከተ

ባለስልጣኑ ቄራዎች የፍሳሽና ደረቅ ቆሻሻዎች አወጋገድ በተመለከተ የአካባቢ ጥበቃ መስፈርት አሟልተው እየሰሩ ስለመሆኑ ክትትል እና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡
ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ቀርቦ ከተከለሱ ማስረጃዎች ፣ የመስክ ምልከታዎች እና ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በቀረበው ቃለ መጠይቅ መሠረት፡-

- አልነጃም ኤክስፖርት ቄራ ኃ/የተ/የግ ማህበር የቆሻሻ ማከከማቻ ስፍራው ደረጃውን ያልጠበቀና ለአካባቢ ብክለት መንስኤ መሆኑ፣
- ሐላል ኤክሰፖርት ቄራ ኃ/የተ/የግ ማህበር የፍሳሽ ማስወገጃ የሌለው መሆኑ፣ ከተከለሱ መረጃዎች ለማወቅ የተቻለ ሲሆን፤ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት 5 ኤክስፖርት ቄራዎች እና አንድ የአገር ውስጥ ቄራ ኦርጋኒክ የኤክስፖርት ቄራ ኃ/የተ/የግ ማህበር የስጋ ተረፈ ምርቱ ለሌለ ጥቅም ማዋል ሲገባው ጉድጓድ በመቆፈር የሚቀበር መሆኑ ፈርሱን ያለምንም ማጣራት በቄራው ግቢ ውስጥ በአጥር ጥግ የሚጣል መሆኑ፣
- አቢሲኒያ ኤክስፖርት ቄራ ኃላ/የተ/የግ/ማህበር የደረቅ ቆሻሻው ከከተማ አስተዳደሩ ቆሻሻ ጋር አብሮ የሚወገድ መሆኑ፣

➢ ኤልፎራ ደብረዘይት አክሲዮን ማህበር የደረቅ ቆሻሻ ተረካቢዎች መጥተው እስከሚወስዱት ድረስ በክፍት ቦታ ተገቢ ባልሆነ መንገድ የሚከማች መሆኑ፣

➢ ኦርጋኒክ፣ አቢሲኒያ እና አልፎራ ቄራዎች የፍሳሽ ቆሻሻ ማከሚያ ስርአት የሌላቸው መሆኑ፤ እንዲሁም የአዲስ አበባ ቄራዎች ድርጅት የፍሳሽ ቆሻሻውን ሳያክም ቀጥታ ወደ ወንዝ የሚለቅ መሆኑ፣

በቄራዎች ውስጥ ለሚሰሩ ሠራተኞቹ ደህንነቱ የተጠበቀ የሥራ አካባቢን መፍጠሩንና የአደጋ መከላከያ ትጥቆችና አልባሳትን መቅረቡን በተመለከተ፡-

በቄራዎች ውስጥ ለሚሰሩ ሠራተኞቹ ደህንነቱ የተጠበቀ የሥራ አካባቢን ሊፈጥር እና የአደጋ መከላከያ ትጥቆችና አልባሳትን በወቅቱና በተፈለገ ጊዜ ስለመቅረቡና በስራ ላይ የሚጠቀሙት ስለመሆኑ ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ በናሙና በታዩት ቄራዎች ደብረዘይት አልፎራ ኤክስፖርት ቄራ አ/ማ፣ አቢሲኒያ ኤክስፖርት ቄራ አ/ማ፣ ሉና ኤክስፖርት ቄራ አ/ማ፣ አክሽከር ኤክስፖርት ቄራ አ/ማ፣ ኦርጋኒክ ኤክስፖርት ቄራ አ/ማ የበረዶ ልብስ፣ የእጅ ጓንት የአደጋ መከላከያ ኮፍያ እና ቦቲ ጫማ ያልተሟላ መሆኑ በቀረበ ቃለመጠይቅ እና የመስክ ምልከታ ለማወቅ ተችሏል፡፡

ለእርድ የሚቀርቡ እንስሳትን ለልየታና የኋልዮሽ ክትትል ሲባል የመለያ ቁጥሮችን ወደ ዳታ ቤዝ/መረጃ ቋት እንዲገባ መደረጉን በተመለከተ፡-

ባለስልጣኑ ለእርድ የሚቀርቡ እንስሳትን ለልየታና የኋልዮሽ ክትትል ሲባል የመለያ ቁጥሮችን ወደ ዳታ ቤዝ/መረጃ ቋት እንዲገባ ሊያደርግ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ፡-

➢ የእንስስሳት ልየታና ምዝገባ ስርዓት በሚተገበርባቸው ቦታዎች የኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ስራዎች በተገቢው ደረጃ መጠቀምና መለዋወጥ እንዲያስችል የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መሰረተ ልማትን ፍላጎት በማሟላት የኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን አጠቃቀምን በ2015 በጀት አመት እቅድ 100% አፈፃፀም ለማድረስ የተቀደ ቢሆንም፤ አለመከናወኑ፣

➢ የእንስሳት መለያ (ታግ) አቅርቦት መሸጫ ማእከላት በመክፈት፤እንዲሁም የአጠቃቀም ስርዓት መመስረት (ተጨማሪ የታግ መሸጫዎችን የበግና ፍየል

እንዲሁም ዳልጋ ከብት ገበያዎች እና በኳራንቲን ጣቢያች አካባቢ መከፈት) በ2015 በጀት ዓመት ታቅዶ፤ አለመከናወኑ፣

- ለባለድርሻ አካላት የኤክስቴንሽን አገልግሎትን ለመስጠት ይቻል ዘንድ የበግ እና ፍየል ልየታና ክትትል ስርዓት (ዳታ ቤዝ) መቅረፅ፤ የማስፈፀሚያ የስልጠና እና ግንዛቤ ማስፈፀሚያ ሰነድ ለማዘጋጀት በ2015 በጀት ዓመት ታቅዶ አለመከናወኑ፣
- ለዓለም አቀፉ የእንስሳት ጤና ድርጅት፣ ለአፍሪካ ሕብረት የእንስሳት ሀብት ልማት ቢሮና ለምስራቅ አፍሪካ የልማት በይነ መንግስታት የሀገራችን የእንስሳት ደህንነትና ጥበቃ መረጃ ማቅረብ የሚሉ ግቦች በ2015 በጀት ዓመት በእቅድ የተያዙ ቢሆንም፤ ያልተከናወኑ መሆኑ፣

የስጋ ምርት አገልግልግሎት ውጤታማነትን ለማረጋገጥ የአቅርቦት ሰንሰለቱን ችግሮች በጥናት በመለየት እንዲቀረፉ ከሚመለከተው አካል ጋር በቅንጅት መሰራቱን በተመለከተ፡-

ባለስልጣን መ/ቤቱ የስጋ ምርት አገልግልግሎት ውጤታማነትን ለማረጋገጥ የአቅርቦት ሰንሰለቱ ላይ ያሉትን ችግሮች በጥናት በመለየትና ችግሮቹ እንዲቀረፉ ከሚመለከተው አካል ጋር በቅንጅት ሊሰራ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ በግብርና ሚኒስቴር በ2012 በጀት ዓመት አነስተኛ የአመንዣጊ እንስሳት የአቅርቦት ሰንሰለት እና የግብይት አስተዳደር ስርዓት (SMALL RUMINANT SUPPLY CHAIN AND MARKETING MANAGEMENT SYSTEM) በሚል ርዕስ ጥናት ተጠንቶ ችግሮች የተለዩ ቢሆንም፤ በጥናቱ የተለዩትን ችግሮች በተቀመጠው መፍትሄ ሀሳቦች ከሚመለከተው አካል ጋር በቅንጅት ያልተሰራ እና የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት የድርሻቸውን እንዲወጡ ግንዛቤ የመስጠትና የስራ ክፍፍል የተደረገበት ማስረጃ አለመኖሩ፤

በጤና ሚኒስቴር የፌዴራል ሆስፒታሎች ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድን በተመለከተ

ከፌደራል ሆስፒታሎች የሚመነጨውን ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ክፍተት ለመለየት ጥናት መደረጉን በተመለከተ

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከፌዴራል ሆስፒታሎች የሚመነጨውን ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ በተመለከተ ክፍተቶችን ለመለየት እና መፍትሄ ለመስጠት የሚያስችል ጥናት ሊያጠና ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ፣ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጦ የታዩት የፌዴራል ሆስፒታሎች (በሀዋሳ ሪፈራል ሆስፒታል፣ በዲላ አጠቃላይ ሆስፒታል፣ በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊንየም የሕክምና ኮሌጅ፣ በጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል) የሚመነጨውን ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ በተመለከተ ከፍተኛ ክፍተቶች እና ችግሮች ቢኖሩም በየአመቱ በሪፖርት ከመግለጽ በዘለለ ክፍተቶችን መሰረት ያደረገ ጥናት የሌለ መሆኑ፣

የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ጥናት እና የአካባቢ አስተዳደር እቅድ ዝግጅትን በተመለከተ

በፌዴራል ሆስፒታሎች የሚሰጡትን አገልግሎት በአዋጅ 299/1995 አንቀጽ 5 መሰረት የአካባቢን እና ማህበረሰብን ሊጎዱ የሚችሉ አደገኛ ቆሻሻ ከሚያመነጩ ተቋማት የሚመደብ በመሆናቸው ፕሮጀክቶች/ ሆስፒታሎቹ ከመሰራታቸው በፊት የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ጥናት (Environmental Impact Assessment) እንዲያዘጋጁ ወይም ከአዋጁ ቀድሞ ያለ ጥናት የተቋቋሙ ከሆነ ደግሞ የአካባቢ አስተዳደር እቅድ ማዘጋጀት (environment management plan) እንዳለባቸው ይገልጻል፡፡

ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጦ ከታዩ ሆስፒታሎች መካከል፡-

- ጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታልን በተመለከተ ሪፈራል ሆስፒታል በመሆኑ የታካሚ ቁጥርና የሚሰጠው አገልግሎት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣ እንደመሆኑ መጠን በአካባቢው እና ህብረተሰቡ ላይ ሊያስከትል የሚችለው አሉታዊ ተፅዕኖ ያልተጠና ወይም የአካባቢ አስተዳደር እቅድ ያልተዘጋጀ መሆኑ፣

➢ ከአዋጁ በኋላ የተሰሩ የኤካ ኮተቤ ሆስፒታል፣ እንዲሁም አዳዲስ የማስፋፊያ ስራ ፕሮጀክት የሰሩ ሆስፒታሎች መካከል ዲላ ሆስፒታል፣ ሀዋሳ ሪፈራል ኮምፕሬሲቭ ሆስፒታል፣ የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሕክምና ኮሌጅ፣ ሕይወት ፋና ኮምፕሪንሲቭ ሆስፒታል እና አለርት ስፔሻላይዝድ ሆሰፒታል የአካባቢ ተፅእኖ ግምገማ ጥናት ወይም የአካባቢ አስተዳደር እቅድ ያላዘጋጁ መሆናቸው፤

ከፌዴራል ሆስፒታሎች የሚወጣውን ደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ አወጋገድ የድጋፍና የቁጥጥር ስርአትን ወጥነት በተመለከተ

ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፌዴራል ሆስፒታሎች የሚመነጨውን ቆሻሻ በተመለከተ ወጥነት ያለው የድጋፍና ቁጥጥር ስርዓት ዘርግቶ ሊከታተል ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ከፌዴራል ሆስፒታሎች የሚወጣውን ደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ አወጋገድን በተመለከተ የድጋፍና የቁጥጥር ሥርዓት ቢኖርም፤-

- ❖ ወጥ በሆነ መልኩ በታቀደው/ በስታንዳርዱ መሠረት ተግባራዊ አለመሆኑን በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጦ ከታዩት ከፌዴራል ሆስፒታሎች፤ ከአለርት ሆስፒታል፣ ከህይወት ፋና ሆስፒታል፣ ከድል ጮራ ሪፈራል ሆስፒታል፣ ከጥቁር አንበሳ እስፔሻላይዝድ ሆስፒታል፣ የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሕክምና ኮሌጅ፣ ከዲላ አጠቃላይ ሆስፒታል፣ ከሀዋሳ ሪፈራል ሆስፒታል እና ከጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ ሼክ ሀሰን የበሬ ኮምፕሬሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል በመጠይቅ ለመረዳት ተችሏል፡፡

አገልግሎት የማይስጡ መድኃኒትና ኬሚካሎች አካባቢንና ህብረተሰቡን በማይጎዳ መልኩ መቀመጡና መወገዱን በተመለከተ፡-

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፌዴራል ሆስፒታሎች አገልግሎት የማይስጡ መድኃኒትና ኬሚካሎች አካባቢንና ህብረተሰቡን በማይጎዳ መልኩ መቀመጡንና መወገዱን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡
ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፌዴራል ሆስፒታሎች ውስጥ ያለውን አገልግሎት የማይስጡ መድኃኒትና ኬሚካሎች አካባቢንና ህብረተሰቡን በማይጎዳ መልኩ የሚያስቀምጡና የሚያስወግዱ መሆኑን ስለመከታተሉ በተመለከተ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጦ ከታዩ ሆስፒታሎች የሚከተሉትን ነባራዊ ሁኔታዎች ተገኝቷል፡-

- በዲላ አጠቃላይ ሆስፒታል ጊዜ ያለፈባቸው መድኃኒቶችና ኬሚካሎች በስቶር ውስጥ የተቀመጠ ቢሆንም፤ ሆስፒታሉ ከ2012 ዓ.ም ጀምሮ የተበላሹ እና የአገልግሎት ዘመናቸው ያለፍ መድኃኒቶች የከተማው ደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ በተዘጋጀ ስፍራ ከመመሪያ ውጭ በሆነና የሚያስከትለው ጉዳት ባልተጠና መልኩ በመቅበር ያስወገዱ መሆኑ፣
- ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሕክምና ኮሌጅ ጊዜ ያለፈባቸው መድኃኒቶች ከዚህ በፊት አዳማ ማቃጠያ ቦታ የሚቃጠል ቢሆንም፤ አሁን ማስወገጃ ቦታ ባለማግኘት ሳይወገድ ለረጅም ጊዜ የተቀመጠ መሆኑ፣
- በህይወት ፋና ሆስፒታል ግቢ ውስጥ በሁለት ክፍል ውስጥ የአገልግሎት ጊዜያቸው/ ያለፈ መድኃኒቶች ከ2 አመት በላይ የተከማቹ መሆኑና በመድኃኒት አቅራቢ ኤጀንሲ በሚያደረገው የመድኃኒት ስርጭት ፕሮግራም የሚገኙ ቢሆንም፤ ኤክስፓየር ሊያደርግ አንድ፣ ሁለት ወይንም ሶስት ወር ሲቀረው ወደ ሆስፒታሉ ስለሚገባ ኤክስፓየርድ የሚበዛ መሆኑ በመጠይቅ መገለጹ፣
- በጅግጅጋ ሃስን የበሬ ሆስፒታል ኬሚካል ነክ የሆኑ ፍሳሽ መድኃኒቶች በላቦራቶሪ በተወስነ ደረጃ የኬሚካል ይዘታቸው ተቀንሶ የሚቀበር መሆኑን ቢገልጹም በአካባቢና በህብረተሰቡ ላይ በረጅምና በአጭር ጊዜ ውስጥ የሚያስከትለውን ጉዳት ሳይጠና የሚቀበር መሆኑ፣
- በተጨማሪ በጅግጅጋ ሃስን የበሬ ሆስፒታል የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው መድኃኒቶችን ከተለያዩ ተቋማት የተውጣጣ ኮሚቴ ተዋቅሮ በ2005 ዓ.ም የወጣውን ከሕክምና አገልግሎት የሚወጡ የቆሻሻ አስተዳደር መመሪያ (Health care waste management) መሰረት ሳይሆን ከከተማ ውጭ በሜዳ ላይ የሚቃጠሉ መሆን፣
- በአለርት ሆስፒታል የአገልግሎት ጊዜአቸው ያለፈ መድኃኒቶች የሚወገድበት ቦታ ባለመኖሩ ስቶር ውስጥ ከ3 አመት በላይ ሳይወገድ የተቀመጠ መሆኑ፤
- በጳጥሮስ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የአገልግሎት ጊዜ ያለፈባቸው መድኃኒቶች በብዛት የተከማቸ መሆኑ እና በተገቢው መንገድ ያልተቀመጠ መሆኑ፤ ከቆርቆሮ እና ከተሰባበረ ጣውላ በተሰራ እና ለዝናብ በተጋለጠ መልኩ የተቀመጠ መሆኑ፣

ለደረቅ ቆሻሻ የተገነቡ ማቃጠያዎች (incinerator) ደረጃቸውን የጠበቀ፣ ክትትልና ጥገና የሚደረግላቸው ስለመሆኑ በተመለከተ

ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፌዴራል ሆስፒታሎች ለደረቅ ቆሻሻ ማቃጠያ የተገነቡ ማቃጠያዎች (incinerator) ደረጃቸውን የጠበቁና አስፈላጊው ክትትልና ጥገና በየጊዜው የሚደረግላቸው ስለመሆኑ ሊቆጣጠር ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ የፌዴራል ሆስፒታሎች ለደረቅ ቆሻሻ ማቃጠያ የተገነቡ ማቃጠያዎች (incinerator) ደረጃቸውን የጠበቁና አስፈላጊው ክትትልና ጥገና በየጊዜው የሚደረግላቸው መሆኑን በሚኒስቴር መ/ቤቱ የቁጥጥር ሥራ መካሄዱን ለማረጋገጥ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠ ከታዩት ሆስፒታሎች የሚከተሉት ታይተዋል፡፡

- በሀዋሳ ሪፈራል ሆስፒታል የቆሻሻ ማቃጠያ ደብል ቻንበር (በሁለት ዙር የማቃጠል ሂደት) አለመሆኑ፣ ያልታጠረ መሆኑ፣ የሆስፒታሉን የቆሻሻ መጠን ያላማከለ እና ሙቀቱን ለማመቅና እና ፍንጣሪን ለመከላከል የሚያገለግል በር ያልተሠራለት መሆኑ፣
- በዲላ አጠቃላይ ሆስፒታል የቆሻሻ ማቃጠያ ደረጃውን የጠበቀ ባለመሆኑ የሚያመነጨው ሙቀት አነስተኛ እና ቆሻሻን ሙሉ በሙሉ ማቃጠል የማይችል መሆኑ፣
- በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሕክምና ኮሌጅ የቆሻሻ ማቃጠያ ተበላሽቶ ከ2013 ዓ.ም ጀምሮ ከጥቅም ውጭ በመሆኑ እስከ ሁለት ቀን ቆሻሻው ተጠራቅሞ ወደ የካቲት ሆስፒታል ተወስዶ የሚወገድ መሆኑ፤
- በቅዱስ ጴጥሮስ ስፔሻላይዝድ ሆሰፒታል ቆሻሻ ማቃጠያን በተመለከተ መታደስ የሚያስፈልገው፣ ሆስፒታሉ ከሚያመነጨው ቆሻሻ መጠን ጋር የማይመጣጠን፣ በመመሪያው መሰረት ያልታጠረና ለመኖሪያ ቤቶች ቅርብ አካባቢ መሆኑ፣
- ህይወት ፋና አጠቃላይ ሆስፒታል የቆሻሻ ማቃጠያ (incinerator) አጥር የሌለው እና ጭሱ ወደ ማህበረሰቡ የሚጨስ እና የሚበክል መሆኑ፤
- የአለርት ሆስፒታል ቆሻሻ የሚያስወግድበት መመሪያ ቢኖረውም፤ያልተሟላ ወይም ከስታንዳርድ በታች የሆነ የቆሻሻ ማቃጠያ መኖሩ፣
- የሼክ ሀሰን የበሬ ኮምፕሬሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ማቃጠያ ሲገነባ ሆስፒታሉ ከሚያመነጨው ቆሻሻ አንጻር ተመጣጣኝ ያልሆነ መሆኑን

ቅሬታዎች እና ጥቆማዎችን የማጣራት ስራ በመስራት፣ መፍትሄ መሰጠትን በተመለከተ

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከፌዴራል ሆስፒታሎች የሚመነጨውን ቆሻሻ አወጋገድ በተመለከተ ከህብረተሰቡ እና ከሌሎች ተቋማት የሚቀርቡ ቅሬታዎች እና ጥቆማዎችን የማጣራት ስራ በመስራት፣ ግብረ መልስ በመስጠት ተግባራዊቱን ሊከታተል ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ፡-

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከፌዴራል ሆስፒታሎች የሚመነጨውን ቆሻሻ አወጋገድ በተመለከተ ከህብረተሰቡ እና ከሌሎች ተቋማት የሚቀርቡ ቅሬታዎች እና ጥቆማዎችን አቀራረብ ሥርዓት እና የቀረቡትን ቅሬታዎች እና ጥቆማዎችን የማጣራትና ግብረ-መልስ አሰጣጥ ስርዓት መኖሩና ተግባራዊ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ማስረጃ ተጠይቆ ያልቀረበ መሆኑ እና
- በሃዋሳ ሪፈራል ሆስፒታል አካባቢ ያሉ ነዋሪዎችና በሃይቁ ላይ የአሳ ማስገር ስራ ላይ የተሰማሩ ማህበራት ከሆስፒታሉ የሚወጣው ፍሳሽ የተበከለና በሃይቁ ውስጥ ላሉ ብዝሀ-ህይወት አሳሳቢ መሆኑን ቢናገሩም ቅሬታው ያልታሰማ መሆኑ እና ከህብረተስቡ የሚነሳው ቅሬታ የሚያስተናግድበት የስልክ መስመር የማይሰራ በመሆኑ ቅሬታ ለማቅርብ የተቸገሩ መሆናቸውን ለመረዳት ተችሏል፡፡

ከሆስፒታል የሚወጡ ፍሳሽ ቆሻሻ የህብረተሰቡን ጤና እና አካባቢን በማይጎዳ መልኩ ስለመወገዳችው እና በአግባቡ መታከማቸውን በተመለከተ

ከሆስፒታሎች የሚመነጭ ፍሳሽ ቆሻሻ የህብረተሰቡን ጤና እና አካባቢን በማይጎዳ መልኩ ስለመወገዳቸው እና በአግባቡ ስለመታከማቸው የፍሳሽ ቆሻሻ ማጣሪያና ማከሚያ (Waste Water Treatment plant) ስለመኖሩ ሊቆጣጠር እና ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሆስፒታሎች የሚመነጭ የኬሚካል ፍሳሽ ቆሻሻ የህብረተሰቡን ጤና እና አካባቢን በማይጎዳ መልኩ ስለመወገዳችው እና በአግባቡ ስለመታከማቸው የፍሳሽ ቆሻሻ ማጣሪያና ማከሚያ (Waste Water Treatment plant) መኖሩን የቁጥጥርና የክትትል ሥራ እየሠራ ስለመሆኑ ለማጣራት በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጦ ከታዩት ሆስፒታሎች፡-

- የጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የፍሳሽ ቆሻሻ ማጣሪያና ማከሚያ (Waste Water Treatment plant) በቆይታ ብዛት ያረጀ ስለሆነ እድሳትም ስላልተደረገለት የማይሰራ በመሆኑ ከሆስፒታሉ የሚወጣው ፍሳሽ በአንድ በኩል የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን በዘረጋው መስመር ሳይጠራ ቀጥታ የተገናኘ ሲሆን፤ በሌላ በኩል ሴፕቲክ ታንክ ሞልቶ ቀጥታ ወደ ጎርፍ ማስወገጃ ቦይ የሚለቀቅ መሆኑ፣
- ሃዋሳ ሪፈራል ሆስፒታል የተገነባው የፍሳሽ ቆሻሻ ማጣሪያ ኩሬ/Waste water treatment pond/ መታደስ ያሚስፈልጋቸው እና ፍሳሽ ቆሻሻው ሳይጠራ ወደ ሃይቅ የሚሰርግ እና የሚፈስ መሆኑ፤ ሆስፒታሉ የፍሳሽ ማጣሪያ ገንዳዎች የገነባ ቢሆንም፤ ከተለያየ ቦታ የሚወጣን ፍሳሽ እየታከመ አለመሆኑ፤ በመስክ ምልከታ ታይቷል ፡፡ ከዚህም ጋር በተያያዘ ሆስፒታሉ የማጣራት ሂደቱን ጨርሶ የሚወጣው ፍሳሽ በተቀመጡት የልቀት ደረጃ ወስን መሰረት መሆኑን በተከታታይ የፍሳሽ ናሙና በላብራቶሪ በማስመርመር በተፈቀደው የልቀት መጠን ለመሆኑ ክትትል እንዲያደርግ የሚጠበቅበት ሲሆን፤ በመስክ ክትትል የምርመራ ውጤት ከፍተኛ ብክለት ያለው መሆኑን አስረድተዋል፡፡
- በ15/06/2015 ዓ.ም የአዋሳ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃና የአየር ንብረት ለውጥ ቁጥጥር ጽ/ቤት ለአዋሳ ዩኒቨርሲቲ ሪፈራል ሆስፒታል ባደረገው ቁጥጥር በሰጠው ግብረ- መልስ ሆስፒታሉ በቀን ከሚጠቀመው 45,000 ሊትር ውሃ ውስጥ 80%(36,000 ሊትር) ቆሻሻ ውሃ እንደሚያመነጩ፣ የWHO መመሪያ መሰረት የታሰበ ቢሆንም፤ ወደ አምስቱ ፍሳሽ ቆሻሻ ማብላያ ገንዳዎች (waste stabilizer pond) ምንም ፍሳሽ ቆሻሻ አለመግባቱ፤ እንዲሁም ጽ/ቤቱ ለዩኒቨርሲቲው ፍሳሽ መውጫ መስመሩ ባዶ መሆኑን ገልጸው እንዲስተካከል ግብረ-መልስ ቢሰጥም፤ ችግሩ ያልተስተካከለ መሆኑ፤
- በዲላ አጠቃላይ ሆስፒታል ደም የተቅላቀለበት ፍሳሽ ቆሻሻ በፕላስቲክ ጀሪካኖች ተሞልቶ ሳይወገድ ለረጅም ጊዜ የተቀመጠ መሆኑ፣
- ለዲላ ሪፈራል ሆስፒታሉ ከተለያዩ ክፍል የሚመነጩ ፍሳሽ ቆሻሻዎች ተሰብስበው ሴፕቲክ ታንክ ውስጥ በማጠራቀምና ምንም አይነት ማጣሪያና ማከሚያ ሂደት ሳያልፍ ተመጠ የከተማው ማዘጋጃ ባዘጋጀው ክፍት መድፊያ ቦታ (Open Land fill) ላይ የሚደፋ መሆኑ፣

➢ ከቅዱስ ጴጥሮስ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል፣ ለሚወጣው ፍሳሽ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ የተዘጋጀው ከ10 ዓመት በላይ ሳይወገድ የቆየ በወራጅ ወንዝ አጠገብ በመሆኑ ያልታከመ ፍሳሽ በስርገት ወደ ወንዙ የሚገባ እና ከፍተኛ ብክለት እያስከተለ መሆኑ፣

➢ የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሕክምና ኮሌጅ ፍሳሽ ቆሻሻ ሳይታከም ወደ ከተማው ፍሳሽ ማስወገጃ እንዲገባ እየተደረገ መሆኑ፣

➢ ህይወት ፋና አጠቃላይ ሆስፒታል፣ በጂግጂጋ ሃሰን የበሬ ሆስፒታል እና አለርት አጠቃላይ ሆስፒታለ የፍሳሽ ቆሻሻ ማጣሪያና ማከሚያ (Waste Water Treatment plant) ባለመኖሩ ቀጥታ ወደ ከተማ ፍሳሽ የሚወገድ መሆኑን፣

ከፌደራል ሆስፒታሎች የሚመነጨውን ቆሻሻ በአይነታቸው ተለይተው በአግባቡ መቀመጣቸው እና መወገዳቸውን በተመለከተ

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከፌዴራል ሆስፒታሎች የሚመነጨውን ቆሻሻ በአይነታቸው ተለይተው በቆሻሻ ማጠራቀሚያ ዕቃዎች በአግባቡ ስለመቀመጣቸውና አካባቢንና ህብረተሰቡን በማይጎዳ መልኩ ስለመወገዳቸው ሊቆጣጠር ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከፌደራል ሆስፒታሎች የሚመነጭውን ቆሻሻ በአይነታቸው ተለይተው በቆሻሻ ማጠራቀሚያ ዕቃዎች በአግባቡ ስለመቀመጣቸውና አካባቢንና ህብረተሰቡን በማይጎዳ መልኩ መወገዳቸውን ቁጥጥር ስለመደረጉ በተመለከተ በሃዋሳ ሪፈራል ሆስፒታል፣ በአለረት አጠቃላይ ሆስፒታል እና የቅዱስ ጳውሎስ ሚሊኒየም ሕክምና ኮሌጅ በተደረገ የመስክ ጉብኝት ቆሻሻ በአይነታቸው ተለይተው በቆሻሻ ማጠራቀሚያ ዕቃዎች በአግባቡ ከማስቀመጥ አንጻር የተሻለ ቢሆንም የሚከተሉት ችግሮች ታይተዋል፡-

➢ በኦዲቱ ወቅት ቅዱስ አማኑኤል የአእምሮ ስፔሳላይዝድ ሆስፒታል ውስጥ ከሚገኘው ፋርማሲ የሚወጣው ደረቅ ቆሻሻ አደገኛ ወይም አደገኛ ያልሆነ በመባል አለመለየቱ፣

➢ በሀዋሳ ሪፈራል ሆስፒታል የአመድ መቅበሪያ አለመኖሩ እና ከሰውነት ክፍል የሚወጡ ሊቀበሩ የሚገባቸውን ለመቅበር የሚሆን ጉድጓድ ያልታጠረ መሆኑ፡፡

- ለዲላ አጠቃላይ ሆስፒታል ከሰውነት ክፍል የሚወጡ ሊቀበሩ የሚገባቸውን ለመቅበር የሚሆን ጉድጓድ ቢኖርም፤ ከቆሻሻ ማቃጠያ የተሰበሰበ አመድ ግን ለረጅም ጊዜ የተከማች መሆኑ፣
- የቅዱስ ጳውሎስ ሚሊኒየም ሕክምና ኮሌጅ በተደረገ መጠይቅ መሠረት የአመድ መቅበሪያ የሌለ እና ወደ ከተማ የቆሻሻ ማስወገጃ የሚጣል መሆኑ፤ እንዲሁም ከሰውነት ክፍል የሚወጡ ሊቀበሩ የሚገባቸውን ለመቅበር የተዘጋጀው ጉድጓድ የሞላ መሆኑ፤
- በተመሳሳይም ቅዱስ ጴጥሮስ አጠቃላይ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የአመድ መቅበሪያ ባለመኖሩ በየማዳበሪያ ተሞልቶ ወደ ከተማው ቆሻሻ መጣያ የሚጣል መሆኑ፣
- አለርት አጠቃላይ ሆስፒታል የአመድም ሆነ የእንግዴ ልጅ(የፕላሴንታ) መቅበሪያ ቦታ ባለመኖሩ ምክንያት ፕላሴንታ በግቢ ውስጥ የሚገኘው ዛፎች ውስጥ ዝቅተኛ ቦታ ላይ ለእንስሳትና ለዝናብ ክፍት በሆነ መልኩ ተከማችቶ መኖሩና ከማቃጠያ የወጣውም አመድ በ5 የተለያዩ ቦታዎች ተከማችቶ ተገኝቷል፡፡

በኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎትና የአየር ጠባይ የማላመድ እና ስርየት አፈፃፀምን በተመለከተ

ኢንስቲትዩቱ የአየር ጠባይ ለውጥና የአየር ብክለት ቁጥጥር ማድረጉን በተመለከተ

ኢንስቲትዩቱ የአየር ጠባይ ለውጥና የአየር ብክለት ጥናትና ምርምር በማካሄድ ክትትል ሊያደርግ እና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡-ኢንስቲትዩቱ ለከፍታ አየር ሁኔታ መከታተያ የሚጠቅሙ 800 እና 30 ግራም ባሎኖችን ሃይድሮጂን አዘጋጅቶ በመሙላት በፓይለት ባሎንና በሬድዮ ሶንዴ በቀን ሁለት ጊዜ መረጃ ለመሰብሰብ በ2014 ዓ.ም በ12 ወራት 578 ለማከናወን በዕቅድ ይዞ የነበረ ቢሆንም 89 ወይም 15 ፐርሰንት ብቻ ያከናወነ ሲሆን በ2015 በጀት ዓመት ደግሞ በዕቅድም ያልተያዘና ያልተከናወነ መሆኑ፣

ኢንስቲትዩቱ ከአየር ጠባይ ጋር ቁርኝት ላላቸው በሽታዎች የጤና ሚቲዎሮሎጂ ገደቦችን ያዘጋጁ መሆኑን በተመለከተ

ኢንስቲትዩቱ የጤናውን ዘርፍ ለማገዝ የሚያስችሉ ከወባ እና ከበረሃ አንበጣ እንቅስቃሴ መስፋፋት ሁኔታ በተጨማሪ ከአየር ጠባይ ጋር ቁርኝት ላላቸው በሽታዎች በጊዜና በቦታ ለመቆጣጠር የሚያስችል የጤና ሚቲዎሮሎጂ ገደቦችን ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት የጤናውን ዘርፍ ለማገዝ የሚያስችሉ ከአየር ጠባይ ጋር ቁርኝት ላላቸው በሽታዎች (አስም፣ ሳምባ በሽታ፣ ፖሊዮ፣ ፈንጣጣ፣ ኮሌራ የመሳሰሉት) በጊዜና በቦታ መቆጣጠር የሚያስችል የጤና ሚቲዎሮሎጂ ገደቦችን ለማዘጋጀት በ2015 በጀት ዓመት በዕቅድ የተያዘው ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ

ሁሉም የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች አገልግሎት እየሰጡ መሆናቸውን በተመለከተ፡፡

ኢንስቲትዩቱ ያቋቋማቸው እና የሚያስተዳድራቸው ሁሉም የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች አገልግሎት እንዲሰጡ ሊያደርግ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ኢንስቲትዩቱ ካቋቋማቸው እና ከሚያስተዳድራቸው 1303 (210 አንደኛና ሳይኖፕቲክ እንዲሁም 1093 3ኛና 4ኛ ደረጃ) የተለያዩ የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል 124 የሚሆኑ (1ኛ ደረጃ፣ አውቶማቲክ፣ 3ኛ ደረጃ እና 4ኛ ደረጃ) ጣቢያዎች አገልግሎት የማይሰጡ ለምሳሌ በተቋቋሙ በጥቂት ጊዜ ውስጥ የተዘጉ ወይም በተቋቋሙበት ዓመት የተዘጉ ጣቢያዎች መካከል ከአንደኛ ደረጃ ጣቢያዎች ዋርዴር በ2009 ዓ.ም ፣ጉሊና በ2009 ዓ.ም ፣ባድሜ በ2010 ዓ.ም ፣ ከሶስተኛ ደረጃ ጣቢያዎች ደግሞ ስምንት አርሲ ነገሌ፣ አራጉሬ፣ ባናት፣ ዲማ፣ ፊናርዋ፣ ማይካድራ፣ እዳጋ ህብረት እና ኮኔ) እንዲሁም ከአራተኛ ደረጃ ጣቢያዎች ሶስት (አጉላዕ፣ሐይቅ መስሐል እና ማይቀይህ) አገልግሎት መስጠት ያቆሙ መሆኑ

የአየር ሁኔታና ጠባይ መሰረት ያደረገ የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎትን በማስፋፋት አርሶ አደሩንና አርብቶ አደሩን ተጠቃሚ ማድረጉን በተመለከተ

ኢንስቲትዩቱ የአየር ሁኔታና ጠባይ መሰረት ያደረገ የሰብልና የእንስሳት ሃብት ልማትን ያማከለ የመድህን ሽፋን በማስፋፋትና የግብርና ሚቲዎሮሎጂ የምክር አገልግሎት በመስጠት አርሶ አደሩንና አርብቶ አደሩን ለማገዝ በትኩረት ሊሰራ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡-

- ኢንስቲትዩቱ ስለሰብሎች የዕድገት ሁኔታ የሚገልፅ መረጃ እንዲሰበሰብ የሚጠበቅ ቢሆንም፤ እንዲህ አይነቱን መረጃ ለመሰብሰብ ምቹ ሁኔታ ያላቸው ጣቢያዎች ይህንን የጣቢያውን ይዞታ መሬት የሰብል የዕድገት ሁኔታ ክትትል ለማድረግ እየተጠቀሙበት እንዳልሆነ፣

- እንዲሁም ለግብርናው ምክር የሚያገለግሉ የሚቲዎሮሎጂ መሳሪያዎች በበርካታየሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች የሌሉ፤ እንዲሁም ያሉትም የማይሰሩ መሆኑ

የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች አስፈላጊው ጥበቃ የሚደረግላቸው መሆኑን በተመለከተ

ኢንስቲትዩቱ የሚቲዎሮሎጂ መረጃ አሰባሰብ ደህንነትን ለማረጋገጥ እና የሚቲዎሮሎጂ መሳሪያዎቹን ከጉዳትና ከጥፋት ለመታደግ በሁሉም የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች አስፈላጊው ጥበቃ እንዲደረግላቸው ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትብብር ሊሰራ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡- በሁሉም ጥበቃ በሚያስፈልጋቸው 1ኛ ደረጃ የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች አስፈላጊው ጥበቃ እንዲደረግላቸው የሚገባ ቢሆንም፤ በተለይ 1ኛ ደረጃ ጣቢያዎች ሰፊ ይዞታና በርካታ የሚቲዎሮሎጂ መሳሪያዎች ቢኖራቸውም ከመረጃ ሰብሳቢ ባለሙያ (ኦብዘርቨር) በስተቀር ጥበቃ የሌላቸው በመሆኑ መሳሪያዎቹ እና የአጥር ብረቶች ለስርቆት እየተዳረጉ መሆናቸውን፣

በኢትዮ ኢንጂነሪንግ ግሩፕ የፓወር ኢኪዩፕመንት ማምረቻ ኢንዱስትሪ የማምረቻ ፋብሪካዎች የሥራ አፈፃፀም እና የአካባቢ አያያዝ ሥርዓት ውጤታማነትን በተመለከተ

የኢንዱስትሪው የግብዓት ግዥ፣ የንብረት አያያዝና አወጋገድ ሂደት ህጎችን እና መመሪያዎችን የተከተለ ስለመሆኑ፤

ኢንዱስትሪው አቅርቦት ሰንሰለት በመከተል፤ የገበያ ጥናትና የግዥ ዕቅድ በወቅቱ በማዘጋጀት ለሁሉም ፋብሪካዎች የምርት ግብዓት በዕቅዱ መሰረት ሊያቀርብ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ፡-

- ኢንዱስትሪው የአቅርቦት ሰንሰለቱን ቀልጣፋና ዘመናዊ አለማድረጉ፤

- ኢንዱስትሪው የሚፈጽማቸው ግዥዎች የመንግስት ግዥ ህግና መመሪያን ያልተከተሉ መሆናቸው፤
- ኢንዱስትሪው ለምርት አገልግሎት የሚውሉ የግብዓት ግዥዎችን ሲፈፅም በዕቅድ መሠረት በተፈለገው ጊዜ፣ መጠን፣ ጥራት እና ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ ያልተከናወኑ መሆናቸው፤

የኢንዱስትሪው የውል አተገባበርን በተመለከተ፤

ኢንዱስትሪው በተደረገው ውል እና በተመላከተው ጊዜ ውስጥ ዕቃውን፣ አገልግሎቱን እና የግንባታ ሥራውን አጠናቆ ሊያስረክብ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ፡-

- ኢንዱስትሪው የማምረቻ ማሽን የምርት አቅም እና የሰው ኃይልን መሠረት በማድረግ ቀድሞ ገበያ በማፈላለግ የደንበኛ ትዕዛዝ ተቀብሎ ውል በመግባት ምርት አለማምረቱ፤
- ኢንዱስትሪው ከተለያዩ ድርጅቶች ጋር የገባውን የምርቶች አቅርቦት በገባው ውል መሰረት በወቅቱ ያልተፈፀሙ መሆናቸው፡፡

ኢንዱስትሪው ለቋሚ ንብረቶች የመድን ዋስትና መግባቱን በተመለከተ

ኢንዱስትሪው ማንኛውንም የውጭ አገር ቋሚ ንብረት ግዥ ሲፈፅም በቅድሚያ የመድን ኢንሹራንስ እንዲገባለት ሊያደርግ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ፡-

- ኢንዱስትሪው ለሰንዳፋ ሶላር ፓኔል ማምረቻ ፋብሪካ በቻፕተር ኢለቨን በብር 47,818,657.03 በ2007ዓ/ም የተገዛው የሶላር ፓኔል ማምረቻ ማሽን የግዥ ሂደት የተመራበት መንገድ የሚገልጽ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፤
- ኢንዱስትሪው ለተገዛው ማሽን ሊደርስ ለሚችል ማንኛውም ጉዳት የመድን ዋስትና ባለመግባቱ ለኪሳራ መዳረጉና ኦዲቱ እስከ ተጠናቀቀበት የተገዛው የሶላር ፓኔል ማምረቻ ማሽን ወደ ሥራ ያላስገባ መሆኑ፤
- ኢንዱስትሪው የንብረት የኢንሹራንስ ሂሳብ መከታተያ መዝገብ የሌለው መሆኑ፤

የኢንዱስትሪው ንብረት አያያዝ እና ተረፈ ምርት አወጋገድ በተመለከተ፤

ኢንዱስትሪው ዘመናዊ፣ቀልጣፋና ውጤታማ የንብረት አስተዳደር ስርዓት እንዲሁም አገልግሎት ሊሰጡ የማይችሉ ንብረቶችን እና ተረፈ ምረቶችን በወቅቱና በተገቢው መንገድ ሊያስወግድ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ፡-

- ኢንዱስትሪው አገልግሎት ሊሰጡ የማይችሉ ንብረቶችን እና ተረፈ ምርቶች አገልግሎታቸው ሲያበቃ ወይም አገልግሎት ላይ የማይውሉበት ደረጃ ሲደርሱ በየወቅቱ በሚመለከተው አካል እንዲወገድ የማያደርግ መሆኑ፤
- በኢንዱስትሪው ስር በሚገኙ ፋብሪካዎች ብዙ ሊወገዱ የሚችሉ የተለያዩ ንብረቶች በሚመለከተው አካል ተጠንቶ የሚወገዱ ንብረቶች ያልተለዩና የዋጋ ግምት ያልወጣላቸው መሆኑ፣ ለአብነት በሞጆ ዋየርና ኬብል ማምረቻ ፋብሪካ 74,725 ቶን የአንዱ ቶን ዋጋ 102,323.27 ብር በጠቅላላ ብዜት የ7,646,106,350.75 የኬብል ፕላስትክ መስሪያ ኬሚካል ግብዓት (MV cable material polyetien compound KL-XL-09) የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈበት ኬሚካል ሳይወገድ በመጋዝን ተከማችቶ የሚገኝ መሆኑ፣

የሚመረቱት ምርቶች ዘመናዊ የአመራረት ቴክኖሎጂን የሚጠቀም እና የጥራት ደረጃቸውን ያሟሉ መሆኑን በተመለከተ

ኢንዱስትሪው በሥሩ በሚገኙ የማምረቻ ፋብሪካዎች የሚመረቱ ምርቶች የጥራት ደረጃቸውን ያሟሉና ዘመናዊ የአመራረት ቴክኖሎጂን በመጠቀም ሊያመርት ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ፣

- ኢንዱስትሪው የምርት ፍተሻና ጥራት ቁጥጥር ሥራን በመስራት የአገር አቀፍም ሆነ የአለም አቀፍ የጥራት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ያላገኘ መሆኑ፤
- ኢንዱስትሪው በሥሩ በሚገኙ የማምረቻ ፋብሪካዎች የሚመረቱ ምርቶች የጥራት ደረጃቸውን ያላሟሉና ዘመናዊ የአመራረት ቴክኖሎጂ የማይጠቀሙ መሆኑ፤

የማምረቻ ፋብሪካዎች ለሚያመርቷቸው ምርቶች የደረጃ ምልክት፣ የአጠቃቀም ምልክት ያላቸው መሆኑን በተመለከተ፤

ኢንዱስትሪው በሥሩ የሚገኙ የማምረቻ ፋብሪካዎች ለሚያመርታቸው ምርቶች የደረጃ ምልክት፣ የአጠቃቀም ምልክት እና ደረጃውን የጠበቀ የምርት ማሸጊያ ሊኖረው ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ ፡-

- ፋብሪካዎች ለሚያመርቷቸው ምርቶች ደረጃ በኢትዮጵያ ደረጃዎች ኢንስቲትዩት (እስታንዳርድ) ያልተቀመጠላቸው፤የምርት ሰርተፊኬሽን ያላገኘ እና አለምቀፍ ደረጃን መሰረት ያላደረገ መሆኑ፤
- ኢንዱስትሪው በትራንስፎርመር ምርት ዝቅተኛ መለኪያ ከኢትዮጵያ ደረጃዎች ኢንስቲትዩት የምርት ሰርተፊኬሽን ያላገኘ መሆኑ፤

የፋብሪካዎቹ የአካባቢ፣የጤና እና ደህንነት አያያዝ ስርዓት ተግባራዊ ስለመሆኑ፤

ኢንዱስትሪው በስሩ የሚገኙ የማምረቻ ፋብሪካዎች የአካባቢ አያያዝ ስርዓት መተግበራቸውን የሚከታተል የአካባቢ ባለሙያ እንዲመደብ ሊያደርግ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ፡-

- ኢንዱስትሪው በማምረቻ ፋብሪካዎቹ ውጤታማ የሆነ የአካባቢ አስተዳደር ደህንነት ስርዓት (Environmental Management System) ISO 14001፡2015 ሂደት ተግባራዊ ያላደረገና ሠርትፊኬት ያላገኘ መሆኑ፤
- በማምረቻ ፋብሪካዎቹ የአካባቢ አያያዝ ስርዓት መተግበራቸውን የሚከታተል የአካባቢ አያያዝ ባለሙያ በኢንዱስትሪ ደረጃ ያለ ቢሆንም፤በፋብሪካዎቹ ያልተመደበ መሆኑ፣
- ፋብሪካው የሙያ ደኅንንትና ጤንነት ሥርዓት ISO 45001፡2018 (Occupational Safety and Health Management)ን በስታንዳርዱ መሰረት ያልተገበረ በመሆኑ፤የሙያ ደኅንነትና ጤንነት ሥርዓት ISO 45001፡2018 (Occupational Safety and Health Management)ን የምስክር ወረቀት ያላገኘ መሆኑ፤

በኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የሠብል ምርምር እና ተደራሽነት ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ

ዘመናዊ የምርምር ፋሲሊቲዎች መሟላቱን በተመለከተ፡-

ኢንስቲትዩቱ ውጤታማ የሆነ የምርምር ሥራዎች ለማከናወን የሚያግዙ ዘመናዊ የእርሻ መሣሪያዎች፣ የምርምር ቤተሙከራዎች እና የግሪን ሀውስ ፋሲሊቲዎች በማደራጀትና በማዘመን ሊሠራ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ በኢንስቲትዩቱ ምርምር ማዕከላት ውጤታማ የሆነ የምርምር ሥራዎች ለማከናወን የሚያግዙ ዘመናዊ የእርሻ መሣሪያዎች፣ የምርምር ቤተሙከራዎች እና የግሪን ሀውስ ፋሲሊቲዎች በአብዛኛው የምርምር ማዕከላት አልተሟሉም፡፡

የምርምር መነሻ ዘር ማከማቻ ፋሲሊቲዎች በማዕከላት መሟላቱን በተመለከተ፡-

ኢንስቲትዩቱ የምርምር መነሻ ዘር ማከማቻና ማደራጃ ፋሲሊቲዎች በምርምር ማዕከላት፣ በልቀት ማዕከላት እና በክላስተር ደረጃ እንዲሟሉ በማድረግ የምርምር ሥራዎች ዘመኑ በደረሰበት ሣይንሳዊ አሠራር የጥራት ደረጃውን በጠበቀ መልኩ ሊተገበር ይገባል፡፡

በኢንስቲትዩቱ የምርምር መነሻ ዘር ማከማቻና ማደራጃ ፋሲሊቲዎች በምርምር ማዕከላት ደረጃ እንዲሟሉ በማድረግ የምርምር ሥራዎች ዘመኑ በደረሰበት ሣይንሳዊ አሠራር የጥራት ደረጃውን በጠበቀ መልኩ እንዲተገበር አልተደረገም፡፡

የምርምር ኬሚካሎች አያያዝ፣ አስተዳደር እና አወጋገድን በተመለከተ፡-

ኢንስቲትዩቱ የምርምር ኬሚካሎች አያያዝ፣ አስተዳደር እና አወጋገድ ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርገው ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ በኢንስቲትዩት፡-

- የደብረዘይት የግብርና ምርምር ግቢ ውስጥ ባለቤትነቱ የግብርና ሚኒስቴር ነው የተባለ በሁለት ቤት ውስጥ ተዘግቶበት ከተቀመጠ ከ15 ዓመት በላይ እንደሚገመት ባለሙያዎች የሚገልጹትና የኬሚካል ዓይነቱ የማይታወቅ በአካባቢው ላይ ከፍተኛ ሽታ የፈጠረ ኬሚካል መኖሩ፣ ጊዜያቸው ያለፈባቸው

ኬሚካሎች፣ የአፈር ማዳበሪያዎች እና ፀረ አረም ኬሚካሎች በወቅቱ የማይወገድ መሆኑን ከተከለሱ ሰነዶች ለማወቅ መቻሉ፣

- በሆለታ ግብርና ምርምር ማዕከል በስንዴ ምርምር መጋዘን ውስጥ ምንነቱ የማይታወቅ ከ30 ዓመት በላይ የተቀመጠ 50 ሊትር ኬሚካል መኖሩ፤ በመስክ ምልከታ ወቅት የተገኘ መሆኑ፣

ለቤተሙከራ የሚያስፈልጉ ኬሚካሎች፣ ሪኤጀንቶች እና ኪቶች አቅርቦትን በተመለከተ፡

ኢንስቲትዩቱ ለምርምር ቤተሙከራ የሚያስፈልጉ ኬሚካሎች፣ ሪኤጀንቶች እና ኪቶች በዕቅድ በመያዝ በዕቅዱ መሠረት ቀርቦ ለምርምር ሥራ እንዲውሉ ሊያደረግ ይገባል፡፡ በኢንስቲትዩቱ ግብርና ምርምር ማዕከላት ለምርምር ቤተሙከራ የሚያስፈልጉ ኬሚካሎች፣ ሪኤጀንቶች እና ኪቶች በወቅቱ አይቀርቡም፡፡

በአዝዕርት፣ በአትክልትና ፍራፍሬ፣ በቡናና ሻይ እና በቅመማ ቅመም ምርምር መከናወኑን በተመለከተ፡

ኢንስቲትዩቱ በሰብል ምርምር ዘርፍ በአዝዕርት፣ በአትክልትና ፍራፍሬ፣በቡናና ሻይ እና በቅመማ ቅመም ሰብሎች አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች በማውጣት ለህብረተሰቡ ተደራሽ ሊያደረግ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ በኦዲት ወቅት፡-በሰብል ምርምር ዘርፍ በአዝዕርት፣ በአትክልትና ፍራፍሬ፣ በቡናና ሻይ እና በቅመማ ቅመም ሰብሎች አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች አባዝቶ ለህብረተሰቡ ተደራሽ የሚያደርግ አካል የለም፡፡

የግሉን ዘርፍ ቴክኖሎጂ የማባዛት አቅም እንዲጎለብት መደረጉን በተመለከተ፡-

ኢንስቲትዩቱ የግሉን ዘርፍ ቴክኖሎጂ የማባዛት አቅም እንዲጎልበት በማድረግ በሰብል ብዜት ቅንጅታዊ የትስስር ሥርዓት በመዘርጋት ሊሰራ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ

- ✓ ኢንስቲትዩቱ የግሉን ዘርፍ ቴክኖሎጂ የማባዛት አቅም እንዲጎልበት በማድረግ በሰብል ብዜት ቅንጅታዊ የትስስር ሥርዓት በመዘርጋት በምርምር የተገኙ ቴክኖሎጂዎች (በሆርቲ ካልቸር፣ በቡና፣ በቅመማ ቅመም፣ ሰሊጥ እና በጥጥ

ሰብሎች) ላይ መነሻ ዘሮቹን እያባዛ ለተጠቃሚ ተደራሽ የሚያደርግ አካል እንዲፈጠር አልተሠራም፡፡

ኢንስቲትዩቱ ባወጣቸው የሰብል ውጤቶች ላይ የዳሰሳ ጥናት መደረጉን በተመለከተ፡-

ኢንስቲትዩቱ በምርምር የወጡ የሰብል ውጤቶች ያስገኙትን ለውጥ ለማወቅ ተጠቃሚዎችን በማሳተፍ በየጊዜው የዳሰሳ ጥናት በማከናውን ሊገመግም ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ

- ✓ በኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት በምርምር የወጡ የሰብል ውጤቶች ምን ያህሉ በምርት ሂደት ላይ እንደሚገኙ፣ ምን ያህሉ ከምርት እንደወጡ በአጠቃላይ እስከ አሁን በተከናወኑ የምርምር ውጤቶች የተገኙትን ለውጥ ለማወቅ ተጠቃሚዎችን ያሳተፈ የዳሰሳ ጥናት በየወቅቱ በመከናወን አልተገመገመም፣

በግብርና ሚኒስቴር የእንስሳት መኖ አቅርቦትና ስርጭት አፈፃፀም በተመለከተ

የእንስሳት መኖ ልማትን ለማከናወን የሚስችሉ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ ደንብና መመሪያዎች ተዘጋጅተው ተግባራዊ መደረጋቸውን በተመለከተ

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የእንስሳት መኖ ልማትና አጠቃቀም ውጤታማ እና ቀጣይነት እንዲኖረው የሚረዱ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ ደንብና መመሪያዎችን ሊያዘጋጅ እና በሚመለከተው አካል አፀድቆ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል።

ይሁን እንጂ፡-

- ➢ በሚኒስቴሩ የተዘጋጀው አገር አቀፍ የመኖ ስትራቴጂ (2020-2035) ቢኖርም፣ በተለያዩ ቋንቋዎች ተተርጉሞ ለክልሎች እና ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርስ ያበ2015 ዓ.ም የእንስሳት መኖና ግብዓት ግብይት የሚል መመሪያ በረቂቅ ደረጃ የተዘጋጀ ቢሆንም፣ ፀድቆ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፣
- ➢ የእንስሳት መኖ ልማትና አጠቃቀም ውጤታማነት እና ቀጣይነት እንዲኖረው የሚረዳ የተዘጋጀ ደንብ አለመኖሩ፣

የእንስሳት መኖ ቴክኖሎጂዎችን የሚያሰራጭበትን ስርአት ዘርግቶ ተግባራዊ ስለማድረጉ

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የእንስሳት መኖ ቴክኖሎጂዎችን ከሀገር ውስጥና ከውጭ ሀገር የሚያሰባስብበትን፣ የሚያጠናቅርበትን፤ እንዲሁም ለየሥነ-ምህዳሩ እና ለተጠቃሚው በሚስማማ ደረጃ የሚያሰራጭበትን ስርአት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ በተጨማሪም ሚኒስቴር መ/ ቤቱ የእንስሳት መኖን በተመለከተ የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችንና አሰራሮችን ለይቶ ለተጠቃሚው እንዲደርስ ሊያደርግ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ

- የመኖ ምርታማነትን ለመጨመር የሚያስችሉ አዳዲስ የመኖ የመነሻ/የመኖ ዘሮች የሚሰራጩበት እና ግብይት የሚደረግበት ወጥ የሆነ የአሰራር ስርዓት የሌለ መሆኑ፤
- የመነሻ ዘር በመውሰድ መኖን የሚያባዙ ድርጅቶች የማይታወቁ በመሆኑ፤ ክትትል እና ቁጥጥር ለማድረግ አስቸጋሪ መሆኑ፤
- የመኖ መነሻ ዘር ለሚያባዙ ከምርምር ማዕከላት እንዲሁም ለመኖ ዘር ተጠቃሚ የመኖ ዘር ከሚያባዙ ድርጅቶች የመኖ ዘር በብዛትና በዓይነት የማይቀርብ መሆኑ፤

የግብዓት አመራረት፣ ክምችት፣ የአጓጓዝ ሂደት ውጤታማ እና ቀልጣፋ እንዲሆን የአሰራር ሥርዓት ስለመዘርጋቱ

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የግብዓት(የመኖ ዘር እና መኖ) አመራረት፣ ክምችት፣ የአጓጓዝ ሂደት ውጤታማ እና ቀልጣፋ እንዲሆን የአሰራር ሥርዓት እንዲዘረጋ ሊያደርግ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ

- የኦዲት ቡድኑ ባደረገው የመስክ ምልከታ ተመርተው የታሸጉ የመኖ ምርቶች የተመረቱበትና መጠቀሚያ ጊዜው የሚያበቃበት የሌለው መሆኑ፤ በናሙና ከታዩ 10 ድርጅቶች በ8ቱ የመኖ ማቀነባበሪያዎች የመኖ አመራረት፣ ክምችት፣ እና የአጓጓዝ ሂደት በተመለከተ መመሪያ የሌላቸው እና መመሪያ መኖር እንዳለበትም እውቀቱ የሌላቸው መሆኑ፤
- የእንስሳት መኖ እና የመኖ ጥሬ ዕቃዎች አምራች አስመጪ ጅምላ አከፋፋይ፣ ላኪ እና ችርቻሮ ንግድ ድርጅቶች የምዝገባና የስራ ፈቃድ የብቃት ማረጋገጫ

መስፈርትን ለመወሰን የወጣው መመሪያ 02/2010 ክፍል 2 ተራ ቁጥር 2 የመኖ ያለቀለት ምርት መደርደርያ ጣውላ ወይም ፕላስቲክ ፓሌት ላይ መቀመጥ እንዳለበት የሚገልፅ ቢሆንም፤ በናሙና ካየናቸው ሚዛን የእንስሳት መኖ ማቀነባበሪያ፣ ህብረት የወተት ከብት አርቢዎች የገበያ አገልግሎት ህብረት ስራ ማህበር፣ ደራሮ የእንስሳት መኖ ማቀነባበሪያ ያመረቱት ምርት ለአፍላ ቶክሲን (ሻጋታ) በሚያጋልጥ መልኩ መሬት ላይ ተቀምጦ መገኘቱ፤

የምጥን መኖ ቀመር በማዘጋጀት፣ የአመጋገብ ሥርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የእንስሳት መኖ ማቀነባበሪያ ተቋማት እንዲቋቋሙ፣ እንዲስፋፉ፣ የተለያዩ የእንስሳት ዓይነቶችና የምርት ባህርያትን መሰረት ያደረገ የምጥን መኖ ቀመር በማዘጋጀት፣ የአመጋገብ ሥርዓት (Nutrition) ሊዘረጋ ይገባል።

ይሁን እንጂ ፡-

- በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የምጥን መኖ ቀመር ለማዘጋጀት የሚያስችሉ ዋና ዋና ግብአቶች ዝርዝር የያዘ እና የተለያዩ የመኖ ግብዓቶች በመጠቀም ምጥን መኖ ሊያገኙት የሚችሉ ጥቅም በጥናቱ የተጠቀሰ ቢሆንም፤ የመኖ አምራች ድርጅቶች እንዲያውቁትና የመኖ ቀመር ሲያዘጋጁ እንዲጠቀሙበት ያልተደረገ መሆኑ፤
- በናሙና ካየናቸው 9 የእንስሳት መኖ ማቀነባበሪያ የመኖ ቀመር የሚያዘጋጁት በመንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች መሆኑን እና በግብርና ሚኒስቴር የመኖ ቀመር (Ratio formulation) ተዘጋጅቶ እንደማያውቅ የመኖ ግብዓት ዕጥረት ሲያጋጥም በሌላ በመተካት ወይም በመኖ ቀመር ከተቀመጠው ውጪ የሚያመርቱበት ጊዜ መኖሩን ይህም በመኖው ላይ የጥራት ጉድለት የሚያመጣ መሆኑን፤
- ለአምራች ኢንዱስትሪዎች/ካምፓኒዎች የመኖ ቀመርን በተመለከተ በዕቅድ ተይዞ ስልጠና የማይሰጥ መሆኑ፤

ጥራትና ደረጃውን የጠበቀ የመኖ ግብዓት ለሚመለከታቸው እየቀረበ መሆኑን ማረጋገጡን በተመለከተ

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ጥራትና ደረጃውን የጠበቀ የመኖ ግብዓት ለአርሶና አርብቶ አደሩ፣ ለባለሀብቶችና ለተደራጁ የማህበረሰብ አካላት እየቀረበ መሆኑን ሊያረጋግጥ፣ሊከታተል እና ችግር ያለባቸውን በመለየት ለበለጠ ሙያዊ ጥራት ቁጥጥር ለሚመለከታቸው ላብራቶሪ እንዲያሳውቁ ሊያደርግ፤ እንዲሁም አፈጻጸሙን ሊከታተል ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ጥራትና ደረጃውን የጠበቀ የመኖ ግብዓት ለአርሶና አርብቶ አደሩ፣ ለባለሀብቶችና ለተደራጁ የማህበረሰብ ክፍሎች እየቀረበ መሆኑን ክትትል በማድረግ የማያረጋግጥ መሆኑ፤

የእንስሳት መኖ ኢንቨስትመንት ላይ ለተሰማሩ ባለሀብቶች ድጋፍ መደረጉም በተመለከተ፤

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የእንስሳት መኖ ኢንቨስትመንት ላይ የተሰማሩ ባለሀብቶች የመሬት እጥረት ባለባቸው አካባቢዎች በሚፈቀድላቸዉ ብድር በኮንትራት እርሻ አሰራር የአካባቢው አርሶና አርብቶ አደሮች ጋር እንዲተሳሰሩ የተቀናጀ ድጋፍ ሊሰጥና አፈጻጸሙን ሊከታተል ይገባል፡፡በተጨማሪም ለመኖ ኢንቨስትመንትና ግብይት የሚያስፈልጉ የመሰረተ ልማት እና ሌሎች ግብአቶች አቅርቦት በወቅቱና በተፈለገው መጠንና ጥራት እንዲቀርብ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ሁኔታዎችን ሊያመቻች ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የእንስሳት መኖ ኢንቨስትመንት ላይ የተሰማሩ ባለሀብቶች የመሬት እጥረት ባለባቸው አካባቢዎች በኮንትራት እርሻ አሰራር የአካባቢው አርሶና አርብቶ አደሮች ጋር እንዲተሳሰሩ እስካሁን መሬት ላይ የወረደ አሰራር አለመኖሩ እና ይህን ስራ ለመስራት የተመቻቸ ብድር የሌለ መሆኑ፤

የመኖ ግብዓትን እና መኖን በተመለከተ የገበያ ትስስር እንዲኖር ስለመደረጉ በተመለከተ

ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአርሶ አደርና በተደራጁ ወጣቶችና ሴቶች፤በመኖ አምራቾች ድርጅቶች እና በእርሻ ምርምር መካከል የመኖ ዘር እና መኖ በበቂ መጠንና በተፈለገው

ጊዜ ማግኘት እንዲችሉ የተጠናከረ የገበያ ትስስር በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲኖር ሊያደርግ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ፡-

- በዘርፉ ለተሰማሩ የእንስሳት አርቢዎችና አድላቢዎች አስተማማኝ የመኖ አቅርቦት በሚፈለገው ጥራትና መጠን ለገበያ የማይቀርብላቸው መሆኑ፤
- የግብይት ስርዓት ባለመኖሩ ምክንያት የእንስሳት መኖ አምራቾችና አቀነባባሪዎች የእንስሳት መኖ ገበያውን በሚፈለገው መጠን ማረጋጋት ያልቻሉ መሆኑ፣
- እንደሀገር የመኖ መነሻ ዘር በመውሰድ መኖ አምርቶ ወደ ገበያ የሚያቀርብ ድርጅቶች የሌለ መሆኑን፤

የእንስሳት መኖ ዘር ለሚያመርቱ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት መሰጠቱን በተመለከተ፡-

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከአንድ ክልል በላይ የዕፅዋት ዘር(የእንስሳት መኖ ዘር) በማከፋፈል ለሚሰማሩ አምራቾች ወይም አከፋፋይ ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ሊሰጥና ክትትልና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ፡-

- የዕፅዋት ዘር ግብዓት ማስፈፀሚያ መመሪያ ቁጥር 464/2013 ክፍል 1 ገፅ-3) እና አዋጅ ቁጥር 782/2005 አንቀፅ 20 ንኡስ አንቀፅ 1 ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከአንድ ክልል በላይ የዕፅዋት ዘር(የእንስሳት መኖ ዘር) በማከፋፈል ለሚሰማሩ አምራች ወይም አከፋፋይ ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ሊሰጥና ክትትልና ድጋፍ ሊያደርግ እንደሚገባ የሚገልፅ ቢሆንም፤ በናሙና ተመርጠው ከታዩ ባለድርሻ አካላት ለማወቅ እንደተቻለው በአንድ ክልል ላይ የመኖ ዘር የሚያመርቱ ድርጅቶች በተለያዩ አካላት የብቃት ማረጋገጫ የሚሰጣቸው(ለምሳሌ፡- ኤደን ፊልድ፣ አናቶሊ፣ መንግስቱ ተሰማ፣ ማትያስ፣ በየነ ኦላኖ) መሆኑ፤ ይህም በክልሉ ግብርና ቢሮ፣ በግብርና ሚኒስቴር እና በግብርና ባለስልጣን የሚሰጥ መሆኑን በተደረገው ቃለ መጠይቅ የተገለፀ መሆኑ፤ በተጨማሪም ክልሉ ክትትል በሚያደርግበት ወቅት የብቃት ማረጋገጫ ሳይሰጣቸው ከኢንቨስትመንት ቢሮ ፈቃድ በማግኘት የመኖ ዘር

ማምረት ስራ ላይ የተሰማሩ የመኖ ዘር አምራቾች መኖራቸውን፣ ይህም ተቀናጅቶ የመስራት ችግር መኖሩን እና በመኖ ዘር ማምረት ስራ ላይ የሚሰጡ ፈቃዶች ወጥነት የሌላቸውና ለመከታተል አመቺ አለመሆናቸውን ፤

የግብርና ግብዓትና ምርትን ፣ጥራት፣ ውጤታማነት፣ ደህንነት በመስፈርቶችና በግብርና ደረጃዎች መሰረት በመገምገም የጥራት ማረጋገጫ ወረቀት መስጠቱን በተመለከተ

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የግብርና ባለስልጣን የግብርና ግብዓትና ምርትን ፍቱንነት (ጤንነቱ የተረጋገጠ)፣ ጥራት፣ ውጤታማነት፣ የደህንነት በመስፈርቶችና በግብርና ደረጃዎች መሰረት በመገምገም የጥራት ማረጋገጫ ወረቀት መስጠቱን እና ጥቅም ላይ እንዲውል ክትትል ማድረጉን ሊቆጣጠር ይገባል፡፡ እንዲሁም ሚኒስቴር መ/ቤቱ የምጥን መኖ ምርት ሀገሪቱ በአፀደቀቻቸው ወይም በተቀበለቻቸው የጥራት ደረጃዎች መሠረት እንዲመረት ከሚመለከታቸው ተቆጣጣሪ አካላት ጋር በቅንጅት ሊሰራ ይገባል።

ይሁን እንጂ ፡-

- የመኖ ደረጃዎች በደረጃዎች ኢንስቲትዩት የፀደቁ 45 የመኖ ደረጃዎች መኖራቸው ነገር ግን በናሙና የታዩ የመኖ አቀነባባሪዎች የመኖ ደረጃዎችን እንደማያውቋቸው እና ያልደረሷቸው መሆኑ፤
- በደረጃዎች ኢንስቲትዩት የተዘጋጀውን የመኖ ደረጃዎች በሚመለከታቸው አካላት ወደ ታች በማውረድ እንዲተዋወቁ እና እንዲተገበሩ ያልተደረገ መሆኑ፤

ከምርምር ማዕከላትና ከግብዓት አቅራቢ ማዕከላት ጋር ተፈላጊ እና ውጤታማ የሆኑ የመኖ ግብዓቶች በምርምርና በጥናት እንዲቀርቡ በቅንጅት መሰራቱን በተመለከተ

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከምርምር ማዕከላትና ከግብዓት አቅራቢ ማዕከላት ጋር ተፈላጊ እና ውጤታማ የሆኑ የመኖ ግብዓቶች በምርምርና በጥናት እንዲቀርቡ በቅንጅት ሊሰራ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ፡-

- ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከምርምር ማዕከላትና ከግብዓት አቅራቢ ማዕከላት ጋር ተፈላጊ እና ውጤታማ የሆኑ የመኖ ግብዓቶች በምርምርና በጥናት እንዲቀርቡ በቅንጅት የማይሰራ መሆኑ፤

ሴቶች እና ወጣቶች በተለያዩ የእንስሳት መኖ ልማት አማራጭ ቴክኖሎጂዎችን መሰረት በማድረግ የሚደራጁበትን የአሰራር ስልትና ስትራቴጂ መቀረፁን በተመለከተ

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሴቶች እና የወጣቶች በተለያዩ የእንስሳት መኖ ልማት አማራጭ ቴክኖሎጂዎችን መሰረት በማድረግ የሚደራጁበትን የአሰራር ስልትና ስትራቴጂ ከሌሎች አካላት ጋር በመሆን፤ በማጥናትና በማፀደቅ ተግባራዊ እንዲደረግ የስልጠና፤የምክርና የቴክኒክ ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ፡-

- ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሴቶች እና የወጣቶች ተደራጅተው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ሞላሰስ በተመለከተ ጥናት ያጠና ቢሆንም፤ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፤
- የመኖ ዘር እጥረት ለመቅረፍ ተደራጅተው የሚሰሩ ወጣቶች እና ሴቶች የሌሉ መሆኑ፤

ቅንጅታዊ አሠራር በመፍጠር በወቅቱ የመኖ ግብዓት ለአርሶ አደሩ/አርብቶ አደሩ እንዲደርስ መድረጉን በተመለከተ

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ቅንጅታዊ አሠራር ለማጎልበትና ለማጠናከር የሚያስችሉ ስልቶችን በመቀየስ በወቅቱ ግብዓት ለአርሶ አደሩ/አርብቶ አደሩ እንዲደርስ ሊያደርግ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ፡-

- ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ መኖን የተመለከተ እና የመኖ ግብዓቶች ለአርሶ አደሩ/አርብቶ አደሩ እንዲደርስ በቅንጅት እንዲሰራ የተቀየሰ ስልት እና የተሰራ ስራ ስለመኖሩ ማስረጃ አልቀረበም፡፡

በእንስሳት መኖ ዙሪያ ዓለምአቀፍ መልካም ተሞክሮዎችን በመውሰድ ስለመተግበሩ እና አምራቾች ንግድ ትርኢቶች ላይ እንዲሳተፉ መደረጉን በተመለከተ

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከሚመለከታቸው ጋር በመቀናጀት የመኖ ኢንቨስትመንትና ምርት ግብይት የተመለከቱ የሀገር ውስጥና የውጭ ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመር ሊያስፋፋ፣ እንዲሁም አምራቾች በሀገር አቀፍና በዓለም አቀፍ ንግድ ትርዒቶች እንዲሳተፉ ሁኔታዎችን ሊያመቻች ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ-

- በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከሚመለከታቸው ጋር በመቀናጀት የመኖ ኢንቨስትመንትና ምርት ግብይት የተመለከቱ የሀገር ውስጥና የውጭ ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመር ሊያስፋፋ እንዲሁም አምራቾች በሀገር አቀፍና በዓለም አቀፍ ንግድ ትርዒቶች እንዲሳተፉ የተመቻቸ ሁኔታ ስለመኖሩ ማስረጃ አልቀረበም፡፡

የእንስሳት መኖ ግብዓቶች በተመለከተ ለሚመለከታቸው አካላት ትምህርት እና ስልጠና ስለመስጠቱ

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተለያዩ የእርሻና የኢንዱስትሪ መኖ ጥሬ ዕቃ ወይም ግብዓቶች ጥራታቸውን ጠብቀው እንዲሰባሰቡ፣ እንዲከማቹና ፣ ለተጠቃሚው እንዲደርሱ ለማድረግ የሚያስችሉ አሰራሮችንና የኤክስቴንሽን አገልግሎት ተደራሽነትን የሚያሳልጡ የሥልጠናና የሙያ አገልግሎት በየደረጃው እንዲዘረጋ ሊያደርግ እና ተግባራዊነቱን ሊከታተል ይገባል።

ይሁን እንጂ፡-

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተለያዩ የእርሻና የኢንዱስትሪ መኖ ጥሬ ዕቃ ወይም ግብዓቶች ጥራታቸውን ጠብቀው እንዲሰባሰቡ፣ እንዲከማቹና፣ ለተጠቃሚው እንዲደርሱ ለማድረግ የሚያስችሉ አሰራሮችንና የኤክስቴንሽን አገልግሎት ተደራሽነትን የሚያሳልጡ የሥልጠናና የሙያ አገልግሎት በየደረጃው እንዲዘረጋ ያላደረገ መሆኑ፤

የመኖ የዘር ምርት መረጃ ቋት መዘጋጀቱን (መደራጀቱን) በተመለከተ

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የመኖ ዘር ምርት መረጃ ቋት ሊያዘጋጅ (ሊያደራጅ) ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የመኖ ዘር ምርት መረጃ ቋት ያልተደራጀ መሆኑ፤

በኢትዮጲያ ብዝሀ ህይወት ኢንስቲትዩት የወራሪ መጤ ዝርያዎችን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር እና ለማጥፋት የተዘረጋው ስርአት ውጤታማነትን በተመለከተ

ወራሪ መጤ ዝርያዎች ከመከሰታቸው በፊት የቅድመ መከላከል ስራዎችን በተመለከተ

ኢንስቲትዩት ወራሪ መጤ ዝርያዎች ከመከሰታቸው በፊት የቅድመ መከላከል ስራዎች በየደረጀው የሚተገበሩበትን የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ሊያደረግ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ፡-

- ወራሪ መጤ ዝርያዎች በሀገሪቱ ከመከሰታቸው በፊት የቅድመ መከላከል ስራዎች በየደረጃቸው የሚተገበሩበት የአሰራር ስርአት መመሪያ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፣
- ወራሪ መጤ ዝርያዎችን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር በየኬላዎቹ የሚወጡትንና የሚገቡትን ብዝሀ-ህይወት የሚቆጣጠር ባለሙያ የሌለ መሆኑ፤

ወራሪ መጤ ዝርያዎችን ለመከላከል፡ለመቆጣጠር እና ለማጥፋት የሚያስችል ምቹ የህግ ማዕቀፍ ተዘርግቶ ተግባራዊ ማደረጉን በተመለከተ፡-

ኢንስቲትዩቱ ወራሪ መጤ ዝርያዎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያግዙ የሕግ ማእቀፍ በማዘጋጀት ሲፈቀድም ስራ ላይ መዋላቸውን ሊከታተል ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ ኢንስቲትዩቱ ወራሪ መጤ ዝርያዎችን ለመከላከል ለመቆጣጠር እና ለማጥፋት የሚያስችል ከፌዴራል እስከ ክልሎች ድረስ የተዘረጋ የህግ ማዕቀፍ መመሪያ ደንብ እና አዋጅ በማውጣት ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፤

ወራሪ መጤ ዝርያዎችን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠርና ለማጥፋት የሚያስችል የተቀናጀ ብሔራዊ ዕቅድ መዘጋጀቱን በተመለከተ፡-

ኢንስቲትዩቱ ወራሪ መጤ ዝርያዎችን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠርና ለማጥፋት የሚያስችል የተቀናጀ ብሔራዊ ዕቅድና ፕሮግራም/ፕሮጀክት አዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ይሁን እንጂ ወራሪ መጤ ዝርያዎችን ለመከላከል፣ለመቆጣጠር እና ለማጥፋት የተቀናጀ ብሄራዊ ዕቅድ፣ፕሮጀክት እና ፕሮግራም ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑን፣ ለምሳሌ፡- እንደአረንጓዴ አሻራ ፕሮግራም እና የተቀናጀ የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ ትኩረት አግኝቶ ሀገራዊ አጀንዳ እንዲሆን አለመደረጉ፣

የሀገሪቱን ቁልፍ የብዝሀ ሕይወት ሀብቶች እና የሚጠበቁ የማህበረሰብ ደኖችን በወራሪ መጤ ዝርያዎች እንዳይጠቁ መጠበቃቸውን በተመለከተ

ኢንስቲትዩቱ የሀገሪቱን ቁልፍ የብዝሀ ሕይወት ሀብቶች (ብሔራዊ ፓርኮች፣ ትላልቅ ወንዞች፣ ሐይቆችና የውሃ ግድቦችን) እና ሌሎች ወሳኝ ቦታዎች በወራሪ መጤ ዝርያዎች እንዳይጠቁ የሚጠበቁበትን ሁኔታ ሊያመቻች ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ፡-

- ኢንስቲትዩቱ ብሄራዊ ፓርኮች፣ትላልቅ ወንዞች፣ሀይቆች፣ የውሃ ግድቦች እና ደኖች እና በውስጡ የሚገኙ ብዝሀ ህይወቶች በወራሪ መጤ ዝርያዎች እንዳይጠቁ የሚጠበቁበት የአሰራር ስርአት የሌለው መሆኑ፣

በወራሪ መጤ ዝርያዎች የተወረሩ አካባቢዎችን በመለየትና በማፅዳት መልሶ ማልማት የሚያስችል ስርዓት ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፡-

ኢንስቲትዩቱ በወራሪ መጤ ዝርያዎች የተወረሩ አካባቢዎችን በመለየት አካባቢን በማይጎዳ መልክ በማፅዳት ከወራሪ ዝርያዎች የፀዳውን መሬት መልሶ ማልማት የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ፡-

- በወራሪ መጤ ዝርያዎች የተወረሩ አካባቢን በመለየት አካባቢን በማይጎዳ መልኩ በማጽዳት የጸዳውን መሬት መልሶ የማልማት ተግባር ያልተከናወነ መሆኑን፣

ጠቀሜታ ያላቸው ወራሪ መጤ ዝርያዎችን በጥናት በመለየት ጥቅም ላይ እንዲውሉ መደረጉን በተመለከተ፡-

ኢንስቲትዩቱ ጠቀሜታ(ፋይዳ) ያላቸው ወራሪ መጤ ዝርያዎችን ጥናት ላይ የተመሰረተ ስልት በመቀየስ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ሊያደርግ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ፡-

- ወራሪ መጤ ዝርያዎች ከሚሰጡት ጠቀሜታ አንጻር በጥናት በመለየት ጥቅም ላይ እንዲውሉ የተደረገ ጥናት የሌለ መሆኑን፤

ኢንስቲትዩቱ ከሌሎች ተቋማት ጋር በመተባበር የመጤ ዝርያዎችን ሽፋንና ስርጭት ለመለየት በየወቅቱ መረጃ መሰብሰብን በተመለከተ፡-

ኢንስቲትዩቱ ከሌሎች የሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በመተባበር በሀገሪቱ የወራሪ መጤ ዝርያዎችን ሽፋንና የስርጭት መጠን ለመለየት የሚያስችሉ ስልቶችን በመጠቀም በየወቅቱ መረጃ ሊሰበስብ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ፡-

- ኢንስቲትዩቱ ወራሪ መጤ ዝርያዎችን ለመከላከል ለመቆጣጠርና ለማጥፋት በሀገሪቱ የሚገኙ ዝርያዎችና ሽፋንና የስራጭት መጠን ለመለየት የሚያስችል የመረጃ መሰብሰብ ስልቶች የማይጠቀም መሆኑ፤
- የወራሪ መጤ ዝርያ የስርጭት መጠናቸውን በየወቅቱ ለመለየት አስፈላጊውን ቴክኖሎጂ በመጠቀም መረጃዎችን የመሰብሰብና የማሰራጨት ስራ ያልተሰራ መሆኑን፤
- ወራሪ መጤ ዝርያዎች በሀገሪቱ የስርጭት መጠን እና ሽፋን ወቅታዊ መረጃ የሌለ መሆኑን፤

በሀገሪቱ ወራሪነታቸው የተረጋገጡ ዝርያዎችን በሚመለከት ብሔራዊ መረጃ ክምችት መዘጋጀቱን በተመለከተ፡-

ኢንስቲትዩቱ በሀገሪቱ መኖራቸው የተደረሰበት እና በዓለምአቀፍ ደረጃ ወራሪነታቸው የሚታወቁ ዝርያዎችን በሚመለከት የተቀናጀና የተደራጀ ብሔራዊ መረጃ ክምችት (ዳታ ቤዝ) አዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል ተደራሽ ሊያደርግ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ፡-

- ኢንስቲትዩቱ ወራሪ መጤ ዝርያዎችን ለመከላከል፡ለመቆጣጠር እና ለማጥፋት የተቀናጀ እና የተደራጀ ብሄራዊ መረጃ ክምችት(ዳታ ቤዝ) አዘጋጅቶ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑን፡
- ወራሪ መጤ ዝርያዎችን በተመከተ በሀገሪቱ ባሉ ክልሎች ወራሪነታቸው የተረጋገጡ አረሞችን የሚለይበት መረጃ የሌለ መሆኑን፤
- በሀገሪቱ በሚመለከታቸው ተቋማት ወራሪ መጤ ዝርያን በተመለከተ ወቅታዊ የሆነ መረጃ የሚገኝበት ዳታ ቤዝ የሌለ መሆኑን፤

ወራሪ መጤ ዝርያዎችን በሚመለከት ለማህበረሰቡ፣ ለመንግስት እና ለሚመለከታቸው አካላት ግንዛቤ መስጠትን በተመለከተ፡-

ኢንስቲትዩቱ ወራሪ መጤ ዝርያዎችን በሚመለከት ስለሚገኝበት ሁኔታ፣ እያደረሰ ያለውን ተጽዕኖ እና መቋቋም የሚቻልበትን ስልት ለማህበረሰቡ፣ ለመንግስት እና ለሚመለከታቸው አካላት ግንዛቤ ሊሰጥ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ፡-

- ወራሪ መጤ ዝርዎችን በተመለከተ ስለሚገኙበት ሁኔታ፡ስለጉዳታቸው እና መከላከያ መንገዶች ለሚመለከተው አካል የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ በችግሩ ስፋት ልክ ያልተሰራ መሆኑን፡

ወራሪ መጤ ዝርያዎችን ፣ ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር ከፌዴራል እስከ ወረዳ መዋቅር በመዘርጋቱን በተመለከተ፡-

ኢንስቲትዩቱ ወራሪ መጤ ዝርያዎችን፣ የመከላከል፣ የመቆጣጠር እና የማጥፋት ስራን በባለቤትነት መምራት የሚያስችል መዋቅር ከፌዴራል እስከ ወረዳ እንዲኖር ወይም ኃላፊነት የሚወስድ አካል እንዲወሰን ሊደረግ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ፡-

- ኢንስቲትዩቱ ወራሪ መጤ ዝርያዎችን ለመከላከል፣ለመቆጣጠር እና ለማጥፋት ከፌዴራል እስከ ወረዳ/ቀበሌ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት ያልሰራ መሆኑን፤

- ወራሪ መጤ ዝርያዎችን በሀገሪቱ ትኩረት ተሰጥቶበት በጀት፣ፖሊሲና ስትራቴጂ ተነድፎለት በሁሉም ክልሎች ዞኖችና ወረዳዎች በመንግስት ባለው መዋቅር ውስጥ በባለቤትነት መምራት የሚችል አካል የሌለ መሆኑን፤

ወራሪ መጤ ዝርያዎች ዙሪያ የጥናት ውጤቶች ወደ ባለድርሻ አካላት ወርደው ተግባራዊ መሆናቸውን በተመለከተ፡-

ኢንስቲትዩቱ በወራሪ መጤ ዝርያዎች ዙሪያ የሚደረጉ የጥናት ውጤቶች ወደ ባለድርሻ አካላትና ማህበረሰቡ ወርደው ተግባራዊ የሚደረጉበትን እና ተግባራዊ መሆናቸውን የሚከታተልበት የአሰራር ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ ፡-

ወራሪ መጤ ዝርያን በተመለከተ በተለያዩ አካላት የተደረጉ የጥናት ውጤቶች ወደ ባለድርሻ አካላት ወርደው ተግባራዊ ያልተደረጉ መሆኑ፤

?? ??? ??? ??? ???????

?2015/ 2016 ??? ?? ? ???? ??? ? ?? ?? ?? ????
? ? ? ?? ?? ??

የ2015/16 በጀት ዓመት የድጋፍና ድጎማ ኦዲት ዳይሬክቶሬት

ዕቅድና ክንውን ማጠቃለያ ሪፖርት

ተ.ቁ	የወኪል መ/ቤቱ ስም	ዕቅድ (በቁጥር)				ክንውን (በቁጥር)					ክንውን በመቶኛ (%)
		ተከታታይ ኦዲት	የማረጋገጫ ኦዲት	ዓመታዊ ኦዲት (ገንዘብ ሚ/ር)	ድምር	ተከታታይ ኦዲት	የማረጋገጫ ኦዲት	ዓመታዊ ኦዲት (ገንዘብ ሚ/ር)	ልዩ ኦዲት	ድምር	
1	ምሥራቅ	34	11	0	45	62	11	0	0	73	162
2	ምዕራብ	60	2	1	63	72	2	1	3	75	119
3	ሰሜን	89	1	0	90	34	1	0	0	38	42
4	ደቡብ	79	3	0	82	93	3	0	0	96	117
5	ማዕከላዊ	51	6	0	57	56	8	0	0	64	112
	ድምር	313	23	1	337	317	25	1	3	346	103

መግለጫ፣

1. የ IPF ኦዲት ለብቻው ያልታቀደና በተወሰኑ የፌዴራል አስፈጻሚ መ/ቤቶች፣ ዞኖችና ክልሎች ናሙና ተወስዶና ተሰርቶ በዓመታዊ ኦዲት ውስጥ ስለተጠቃለለ ለብቻው ተለይቶ አልቀረበም፡፡

2. የማረጋገጫ ኦዲት ከተባሉ 25 ኦዲቶች ውስጥ፣

2.1 በ7 ክልሎች (ኦሮሚያ፣ ሶማሊ፣ ቤኒ/ጉ፣ደቡብ፣ ሲዳማ፣ ጋምቤላ፣ ሀረሪ.) እና በ2 ከተማ

አስተ/ሮች (አ/አ/ እና ድሬዳዋ) የ250 ወረዳዎች/ከተማ አስተዳደሮች የ2014 በጀት ዓመት የዜጎች የበጀት መመሪያ ዝግጅት (preparation of citizen budget guideline) የማረጋገጫ ኦዲትን /DLR 7.13/ በተመለከተ ከተጠቀሱ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች 281 ወረዳዎች/ከተማ አስተዳደሮች በናሙና ተወስደው ሥራዉ ተሠርቷል፡፡

2.2 የየክሎች የ2013 በጀት ዓመት ወጪ 60%ቱ የመሠረታዊ አገልግሎት ሰጪ ሴክተሮች ወጪ መሆኑን ማረጋገጥን /DLR 1(a).2/ በተመለከተ ከአ/አበባ ከተማ አስተዳደር እና ትግራይ ክልል በስተቀር በወቅቱ በነበሩ 9 ክልሎች (አማራ፣ ኦሮሚያ፣ ደቡብ ብሄር-ብሄረሰብ፣ ቤኒሻንጉል-ጉሙዝ፣ ጋምቤላ፣ ሶማሊ፣ ሀረሪ፣ ሲዳማ፣ አፋር) እና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ላይ ሥራዉ ተሠርቷል፡፡

2.3 በተመረጡ ክልሎች እና ከተማ አስተ/ሮች ካሉ ወረዳዎች 50%ታቸው በ2013 በጀት ዓመት መጨረሻ ቋሚ ዕቃ ቆጥረውና ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር አመዛዝነው ለየክልሎቻቸው ገንዘብ ቢሮ ሪፖርት ማድረጋቸውን ማረጋገጥን /DLR 8.11/ በተመለከተ በኦሮሚየ፣ በአማራ፣ በደቡብ (የቀድሞ)፣ በቤኒሻንጉል-ጉሙዝ፣ በሶማሊ፣ በጋምቤላ፣ በአዲስ አበባ እና በድሬ ሬዳዋ 363 ናሙና (ወረዳዎች/ከተማ አስተዳደሮች) ተወስዶ ሥራዉ ተሠርቷል፡፡

በበጀት ዓመቱ በአጠቃላይ 337 የተከታታይ፣ የማረጋገጫ (Verification) እና ዓመታዊ ኦዲቶችን ለመሥራት የታቀደ ሲሆን በበጀት ዓመቱ የ346 ኦዲቶች ተከናውኖ ሪፖርቱ ማለትም፡-

- የ317 ወረዳዎች፣ ከተማ አስተዳደሮች እና ሴክተር ቢሮዎች ለየብቻ ተዘርዝሮ በሪፖርት ተጠቃሏል፡፡ (317 ኦዲቶች) ፣
- የ11 ክልሎች እና የ2 ከተማ አስተዳደር የ2015 ዓመታዊ ኦዲት በ2015 በጀት ዓመት የገንዘብ ሚ/ር የመደበኛና የ IPF ዓመታዊ ኦዲት ተጠቃሏል፡፡ (1 ኦዲት)፣
- ለክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች 25 የማረጋገጫ (Verification) ኦዲቶች፣
  - ✓ በ7 ክልሎች እና 2 ከተማ አስተዳደሮች በ2014 በጀት ዓመት ከየክልሎቹ በጀት ቢያንስ 60% ለመሠረታዊ አገልግሎት ሰጪ ሴክተሮች በጀት መመደቡን ማረጋገጥ፣

- ✓ በ7 ክልሎች (ኦሮሚያ፣ ሶማሊ፣ ቤኒ/ጉ፣ደቡብ፣ ሲዳማ፣ ጋምቤላ፣ ሀረሪ) እና በ2 ከተማ አስተ/ሮች (አ/አ/ እና ድሬዳዋ) የ250 ወረዳዎች/ከተማ አስተዳደሮች የ2014 በጀት ዓመት የዜጎች የበጀት መመሪያ ዝግጅት (preparation of citizen budget guideline) የማረጋገጫ ኦዲትን /DLR 7.13/ በተመለከተ ከተጠቀሱ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች 281 ወረዳዎች/ከተማ አስተዳደሮች በናሙና ተወስደው፣

- ✓ በተመረጡ ክልሎች እና ከተማ አስተ/ሮች ካሉ ወረዳዎች 50%ታቸው በ2013 በጀት ዓመት መጨረሻ ቋሚ ዕቃ ቆጥረውና ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር አመዛዝነው ለየክልሎቻቸው ገንዘብ ቢሮ ሪፖርት ማድረጋቸውን ማረጋገጥን /DLR 8.11/ በተመለከተ በኦሮሚየ፣ በአማራ፣ በደቡብ (የቀድሞ)፣ በቤኒሻንጉል-ጉሙዝ፣ በሶማሊ፣ በጋምቤላ፣ በአዲስ አበባ እና በድሬ ሬዳዋ 363 ናሙና (ወረዳዎች/ከተማ አስተዳደሮች) ተወስዶ፣

በሚባሉ የማረጋገጫ ኦዲቶች ርዕስ ተጠቃሏል፡፡

- ➢ ሰሜን ወኪል ላይ ከጣና ትራንስፖርት ድርጅት፣ ከፈለገ-ህይወት ሆስፒታል እና አዲሱ የአባይ ድልድይ አስፓልት ግንባታ ጋር በተያያዘ የካሳ ልኬታ ላይ 3 ልዩ ኦዲቶች ተሠርተዋል፡፡

- በተጨማሪም፣
  - የ2015 በጀት ዓመት የተጠቃለለ ዓመታዊ ኦዲት ከክልሎች እስከ ገንዘብ ሚኒስቴር ባሉ ደረጃዎች የተከናወነ ሲሆን ለዚህም ለመደበኛ (ፕሮግራም) በጀት ከ11 ክልሎች እና የድሬ ዳዋ ከተማ አስተዳደር፣ ለ IPF ደግሞ ከ11 ክልሎች እና 2 ከተማ አስተዳደሮች የ2015 በጀት ዓመት የተጠቃለለ ሂሳብ ኦዲት ከወረዳ እስከ ክልል ሴክተር ቢሮዎች እና ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮዎች 68 (ወረዳ/ከተማ አስተዳደር፣ ዞንና ክልል ፋይናንስ ጽ/ቤቶች እንዲሁም ሴክተር ቢሮዎች) እንዲሁም ከፌዴራል አስፈጻሚ መ/ቤቶች 6፣ በድምሩ 74 ናሙናዎች ተወስደው ኦዲቱን በማከናወን ሪፖርቱ በገንዘብ ሚኒስቴር ላይ በፕሮጀክት (IPF) እና በፕሮግራም ተጠቃልሎ በወቅቱ ለገንዘብ ሚኒስቴር ቀርቧል፡፡

6. የተከናወኑ የ'ESPES AF ፕሮጀክት ተከታታይ እና የማረጋገጫ ኦዲቶች ዋና ዋና ግኝቶች ማጠቃለያ ሪፖርት

1. በድጋፍና ድጕማ ኦዲት ይሬክቶሬት ሥር ከተከናወኑ የ2015/16 የ'ESPES ፕሮጀክት የተከታታይ ኦዲቶች የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶችና ጉልህ የሆኑ የኦዲት ግኝቶች ማጠቃለያ ሪፖርት

መግቢያ፣

ዳይሬክቶሬቱ በአሁኑ ወቅት የሚያከናውነው ኦዲት የኢትዮጵያ መንግሥትና የዓለም ባንክ ባደረጉት ስምምነት መሠረት የፍትሃዊነት መሠረታዊ አገልግሎት ለሁሉ ዓቀፍ የዕድገት ተጠቃሚነት ፕሮግራም (Enhancing Shared Prosperity through Equitable Service-ESPES) የተከታታይ እና የማረጋገጫ ኦዲት ሲሆን፣ የተከታታይ ኦዲት በየሩብ ዓመቱ፣ የማረጋገጫ ኦዲት ደግሞ በገንዘብ ሚኒስቴር በተጠየቀ ጊዜ እየተከናወነ በስምምነቱ መሠረት ሪፖርቱ ለገንዘብ ሚኒስቴር እና ለዓለም ባንክ በወቅቱ እንዲደርስ ተደርጓል፡፡ ይህ ኦዲት የሚሸፍናቸው ሴክተሮች የመሠረታዊ አገልግሎት አቅራቢ የሆኑትን በወረዳና በክልል ደረጃ የሚገኙ የጤና፣ የትምህርት፣ የግብርናና ተፈጥሮ ሀብት፣ የንጹህ ውሃ አቅርቦት እና የገጠር መንገድ ሴክቶሮችን ነው፡፡

ስለሆነም የፍትሃዊነት መሠረታዊ አገልግሎት ለሁሉ ዓቀፍ የዕድገት ተጠቃሚነት ፕሮግራም (Enhancing Shared Prosperity through Equitable Service-ESPES) የተከታታይ እና የማረጋገጫ ኦዲት ዋና ትኩረት በእነዚህ መሠረታዊ አገልግሎት አቅራቢ መ/ቤቶች (በወረዳና በክልል ደረጃ) የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ላይ በመሆኑ፣ እየተጠቃለለ የሚላከው ኦዲት ሪፖርት ግኝቶች የሚያተኩረው በገንዘብ መጠን (quantitative amount) ላይ ሳይሆን በዓይነት ላይ (Qualitative) በመሆኑ፣ ዋና ዋና ግኝቶች የሚባሉት በዓይነት እንጂ በመጠን አለመሆናቸውን እንገልፃለን፡፡

በመሆኑም በ2015/16 የኦዲት ዘመን ለተከናወኑት ተከታታይ ኦዲቶች የተሰጡት የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት የኦዲት አስተያየቶችና በየመሠረታዊ አገልግሎት አቅራቢ መ/ቤቶች የሚታዩት የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች በአብዛኛው ተመሣሣይነት ያላቸው

በመሆኑ፣ ዋና ዋና የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶቹ በአንድ ላይ ተጠቃልለው በሚከተለው ሁኔታ ለዓይነት ቀርበዋል፡፡

ሀ/ **በ2015/16 የኦዲት ዘመን የታዩ ዋና ዋና የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች**

በአሁኑ ወቅት የተወሰነ መሻሻል ቢታይም፣ ቀጥሎ የተመለከቱት ዋና ዋና የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች በበርካታ የመሠረታዊ አገልግሎት አቅራቢ መ/ቤቶች ውስጥ በመታየት ላይ ናቸው፡፡

እነሱም;-

ጥሬ ገንዘብና ባንክ፤

- በየወቅቱ የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ የማይደረግና ከመዝገብ (ሌጀር) ከወጪ ቀሪ ጋር የማይመሳከር መሆኑ፣ አንዳንድ ጊዜ የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ የሚደረግ ቢሆንም ቆጠራዉ ከመዝገብ (ሌጀር) ከወጪ ቀሪ ጋር የማይመሳከር መሆኑ፣ በተጨማሪም አልፎ አልፎ የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ በተደረገባቸው መ/ቤቶች በቆጠራውና በጥሬ ገንዘብ ምዝገባ ሚዛን መካከል ልዩነት (አንዱ ከፍ ወይም ዝቅ) የሚታይ መሆኑ፣
- አልፎ አልፎ የገንዘብ ያዥ የጥሬ ገንዘብ መቆጣጠሪያ መዝገብ ያልተቋቋመ ሲሆን በተቋቋበት ደግሞ ምዝገባ የተቋረጠ መሆኑ፣
- አልፎ አልፎ ለጥቃቅን ክፍያዎች (petty cash system) በሳጥን መያዝ ያለበት ጥሬ ገንዘብ ሥርዓት ያልተዘረጋ ሲሆን በተዘረጋባቸውም ቢሆን በአግባቡ የማይሠራበት መሆኑ፣ በዚህም ምክንያት አልፎ አልፎ በሣጥን/ካዝና ውስጥ እንዲቀመጥ በመመሪያ ከተፈቀደው የገንዘብ መጠን በላይ ገንዘብ የሚቀመጥ መሆኑ፣
- በፋይናንስ መመሪያ መሠረት ከባንክ በቼክ መከፈል ያለበት ጥሬ ገንዘብ አልፎ አልፎ ከሣጥን/ካዝና በጥሬ ገንዘብ የሚከፈል መሆኑ፣
- አልፎ አልፎ በካዝና/ሣጥን እና በባንክ ያለ ጥሬ ገንዘብ በሂሳብ ሙከራ ሚዛን (Trial Balance) ላይ መደበኛ ባልሆነ የሂሳብ ሚዛን (በዴቢት መሆን ሲገባ በክሬዲት) የሚታይ መኖሩ፣
- በአንዳንድ መ/ቤቶች የቆየና ያልተተከ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ያለ መሆኑ፣ ከዚህም ውስጥ ካለፉት ዓመታት ዞሮ የመጣ ከቀድሞ ገንዘብ ያዥ የሚፈለግ መኖሩ፣

- የባንክ ሂሣብ ማስታረቂያ አልፎ አልፎ በየወሩ የማይዘጋጅ መሆኑ፣ በተዘጋጀባቸውም በሌጀርና በባንክ ሂሳብ ማስታወቂያ መካከል የታየው ልዩነት ያልተጣራ መሆኑ፣
- አልፎ አልፎ በባንክ ሌጀር ሚዛን እና በባንክ ማስታወቂያ ሚዛን መካከል ልዩነት ያለ መሆኑ፣
- በአንዳንድ መ/ቤቶች ቀሪ ቼክ (Cheque stub) ላይ የሂሳብ ሚዛኑም ወደቀጣይ ቀሪ ቼክ (Cheque stub) ያልዞረ መሆኑ፣
- ከከዝና (ከሳጥን) በተንጠልጣይ የተከፈሉ የቅድሚያ ሂሣብ ክፍያዎች በወቅቱ የማይወራረዱ፣ አሊያም ወደ ሂሳብ ክፍል ዞረው በተሰብሳቢ የማይያዙ መሆኑ፣
- አልፎ አልፎ ገንዘብ ያዦች ለሚያንቀሳቅሱት ጥሬ ገንዘብ መዝገብ ያልተቋቋመ መሆኑ፣ በአንዳንድ መዝገቡ በተቋቋመባቸው ደግሞ ተገቢ ምዝገባ ያልተደረገ ወይም ምዝገባው የተቋረጠ መሆኑ፣

<u>**ተሰብሳቢ እና ተከፋይ ሂሳብ፤**</u>

- የቅድሚያ ሂሣብ ክፍያዎች እና ተከፋይ ሂሳቦች በወቅቱ አለመወራረዳቸው፣ በተለይ በተሰብሳቢ በተያዘው ሂሳብ ውስጥ፡-
  - የጥሬ ገንዘብ ጉድለት የሚገኝ መሆኑ እና ከዚህም እርምጃ ሳይወሰድበት የዘገየ እና ባለቤቱ የማይታወቅ መኖሩ፣
  - ከተከፈሉ ረዘም ያለ ጊዜ የሆናቸው ተሰብሳቢ ሂሳቦች መኖራቸው እና ተሰብሳቢ ሂሳብ እያለባቸው ሲሠሩበት የነበረውን መ/ቤት የለቀቁ ሠራተኞች መኖራቸው፣
- ግንባታው/ሥራው የተቋረጠ ቢሆንም ለግንባታ/ሥራ በቅድሚያ ክፍያ የተሰጠና ያልተተካ ተሰብሳቢ መኖሩ፣
- አልፎ አልፎ ተሰብሳቢ እና ተከፋይ ሂሳቦች መደበኛ ባልሆነ ሚዛን (ተሰብሳቢ በዴቢት መያዝ ሲገባ በክሬዲት፣ ተከፋይ ደግሞ በክሬዲት መያዝ ሲገባ በዴቢት) የተያዙ መሆኑ፣
- አልፎ አልፎ ለተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሣቦች ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ተቀጽላ ሌጀር ያልተቋቋመ መሆኑ፣

- አልፎ አልፎ ለተሰብሳቢ እና ተከፋይ ሂሣቦች የቆይታ ጊዜያቸውን የሚያሳይ የዕድሜ ትንተና (Age analysis) ያልተሠራ መሆኑ፣
- አልፎ አልፎ ደጋፊ ማስረጃ የሌላቸው እና ባለቤታቸው የማይታወቅ ተሰብሳቢዎች መኖራቸው ፣

<u>**ወጪዎች፡**</u>

- የተወሰኑ ክፍያዎች በበቂና አግባብ ባላቸው ማስረጃዎች አለመደገፋቸው፣
- የውሎ አበል፣
    - አልፎ አልፎ ሠራተኞች በቢሮ መደበኛ ሥራቸው ላይ እያሉ (መስክ ሳይሄዱ) የውሎ አበል የተከፈላቸው መሆኑ፣
    - በድጋሚና በብልጫ የተከፈለ ውሎ አበል መኖሩ፡
    - በአብዛኛው የውሎ አበል የመስክ ሥራ ከመሠራቱ በፊት ቀጥታ (በቅድሚያ) በወጪ የተመዘገበና ሪፖርት የተደረገ መሆኑ፣
    - ያለ የውሎ አበል ፎርም እና የተሠራው የመስክ ሥራ ዓይነት ሳይጠቀስ የተወራረዱ ዉሎ አበሎች መኖራቸው፣
    - መስክ የሄዱበት መነሻና መድረሻ ቀንና ቦታ በውሎ አበል ማወራረጃ ቅጽ ላይ ሳይጠቀስ የተወራረደ ውሎ አበል መኖሩ፣
    - በውሎ አበል ማወራረጃ ቅጽ 2 ላይ የሠራተኞች ደመወዝ አለመጠቀስ፣ በዚህም የተነሳ ውሎ አበሉ መከፈል በሚገባው ተመን የተከፈለ መሆኑን ለማረጋገጥ አዳጋች መሆን፣
    - መስክ ላይ የሄዱበት ቦታ በውሎ አበል ማወራረጃ ቅጽ ላይ ሳይጠቀስ የተወራረደ ውሎ አበል መኖሩ፣
    - አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች በውሎ አበል ቅጽ ላይ ሳይሞሉ የተወራረዱ ውሎ አበሎች መኖራቸው፣
    - የውሎ አበል ሂሳብ ሲወራረድ አልፎ አልፎ እንዲሁም ቁርስ፣ ምሳ፣ እራት እና መኝታ የተጠቀሙባቸው ቦታዎች በውሎ አበል ፎርም ላይ ያልተጠቀሰ መሆኑ፣
- አልፎ አልፎ መከፈል ከሚገባው በላይ እና በድጋሚ የተከፈሉ ሂሳቦች መኖራቸው፣
- በነዳጅ ፍጆታ ላይ ተገቢ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት የሌለ መሆኑ፣ ለምሳሌም፣

- ነዳጁ ገቢ የተደረገበት የንብረት ገቢ ደረሠኝ ያልቀረበለት የነዳጅ ወጭ መኖሩ፣
- ጌጁ ለማይሠራ ተሽከርካሪ ነዳጅ የሚቀዳ መሆኑ፣
- ገንዘቡ የተከፈለበት ደረሰኝ ያልቀረበለት የነዳጅ ወጪ መኖሩ፣
- አልፎ አልፎ የነዳጅ ወጪ የተጠቃሚውን መ/ቤት ስም፣ ነዳጁ የተቀዳለት መኪና ታርጋ ቁጥር እና ቀን በሌለው ማስረጃ ተመዝግቦ ሪፖርት የተደረገ መሆኑ፣
- በአንዳንድ መ/ቤቶች ተሽከርካሪዎች በተወሰነ ነዳጅ መጠን የሚሄዱት ርቀት /ኖርማላይዘሽን/ ሥራ ላይ ያልዋለ መሆኑ፣

* ገቢ ለመደረጉ የንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞዴል 19) ያልቀረበለት የንብረት ግዥ ወጪ መኖሩ፣ በንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞዴል 19) ላይ ዝርዝር ሁኔታዎቹ ያልተጠቀሰ ግዥ መኖሩ፣
* የሀገር ውስጥ ሥልጠና ወጪዎች አልፎ አልፎ የሥልጠናውን ዓይነት፣ ቦታ፣ የሰልጣኞች ሁኔታ የሚገልጽ ቅድመ-ሀሳብ (proposal) ሳይቀርብላቸው የሚፈጸሙ መሆኑ እንዲሁም በተሳታፊዎች መቆጣጠሪያ ዝርዝር /ሊስት/ ያልተደገፉ መሆኑ፣
* አልፎ አልፎ ወጪዎች ከሻጭ ወይም አገልግሎት ሰጪ በተሰጠ ደረሰኝ ያልተደገፉ መሆኑ፣
* ሥራ ለለቀቀ ሠራተኛ የተፈጸመ የደመወዝ ክፍያ መኖሩ፣
* በስሌት ስህተት በብልጫ የተከፈለ እንዲሁም በሰዓት መቆጣጠሪያ ያልተደገፈ የጤና ባለሙያዎች የማታ ተረኝነት (night duty) ክፍያ መኖሩ፣
* አልፎ አልፎ ወጪዎች ያልተመዘገቡና ሪፖርት ያልተደረጉ መሆኑ፣
* ከክፍያ ላይ መቀነስ ሲገባ ያልተቀነሰ የቅድሚያ ገቢ ግብር (withholding tax) እና የተጨማሪ እሴት ታክስ (value added tax) የቅድሚያ ገቢ ግብር (withholding tax) ሂሳብ መኖሩ፣
* አንዳንድ የውል ስምምነት የሚያስፈልጋቸው ክፍያዎች ያለ የውል ስምምነት የተፈጸሙ መሆኑ፣
* አልፎ አልፎ ግዥዎች ከደንብና መመሪያ ውጭ የተፈጸሙ መሆኑ፣ ለምሳሌ፣
  - አልፎ አልፎ ግዥዎች በተጠየቀው ዝርዝር (specification) መሠረት ለመፈጸማቸው በቴክኒክና ሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸው የማይረጋገጡ መሆኑ፣

- ያለ ተጠቃሚው ጥያቄ የተፈጸመ ግዥ መኖሩ፣
- የአቅራቢዎች ውድድርና የአሸናፊ መረጣ ሳይደረግ የተፈጸመ ግዥ መኖሩ፣
- የተጠቃሚው መ/ቤት ስምና ቀን የሌለው ማስረጃ የቀረበለት ግዥ መኖሩ፣

- አልፎ አልፎ ወጪዎች ትክክለኛ ባልሆነ የሂሳብ መደብ የተመዘገቡና ሪፖርት የተደረጉ መሆኑ፡
- አልፎ ደጋፊ ማስረጃ የሌላቸው ወጪዎች መኖራቸው፣

<u>የሂሳብ ሪፖርት፡</u>

- አልፎ አልፎ ወርሃዊ የሂሣብ ሪፖርቶች በወቅቱ ያልተዘጋጁና ለሚመለከተው አካል ያልተላኩ መሆኑ፣

<u>ንብረት፡</u>

- የአላቂና ቋሚ ዕቃዎች መቆጣጠሪያ መዝገብ በአንዳንድ ኦዲት ተደራጊዎች አለመቋቋም፣ በተቋቋመባቸውም በአንዳንዶቹ ምዝገባው በአግባቡ አለመከናወን እንዲሁም በአንዳንዶች ደግሞ የንብረት ምዝገባ መቋረጥ፣
- በአንዳንድ መ/ቤቶች በተወሰነ ወቅት በተለይ ደግሞ በበጀት ዓመት መጨረሻ የንብረት ቆጠራና ምዘና የማይደረግ መሆኑ እና በአንዳንድ ቆጠራው በተደረገባቸው ደግሞ ምዘና የማይደረግ መሆኑ፣
- አልፎ አልፎ መጻህፍትና የልዩ ትምህርት መገልገያ መሣሪያዎች አለመመዝገባቸው፣
- አልፎ አልፎ ለቋሚ ዕቃዎች መለያ ቁጥር ያልተሰጣቸው መሆኑ፣
- ለንብረቶች ተገቢው አያያዝ ያልተደረገ መሆኑ (ለምሳሌ ተገቢ የንብረት መጋዘን ካለመኖሩ፣ መጋዘን ባለበት ደግሞ በቂ የዕቃ መደርደሪያ ባለመኖሩ ንብረቶች ሜዳ ላይ እንዲሁም መጋዘን ውስጥ ባዶ ወለል ላይ ተበታትነው የተቀመጡ መሆኑ)፣
- አገልግሎት የማይሰጡ ዕቃዎች በወቅቱ ያልተወገዱ መሆኑ እና አገልግሎት ከሚሰጡ ዕቃዎች ጋር ተቀላቅለው የተቀመጡ መሆኑ፤
- አልፎ አልፎ አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ንብረቶች ያለሥራ መቀመጣቸው፣

- በአብዘኛው የተሽከርካሪ ፕሮፋይል እና የባለቤትነት ደብተር ያለመኖር እና አልፎ አልፎ ታርጋ ቁጥር/ሰሌዳ ቁጥር የሌላቸው ተሽከርካሪዎች (መኪኖች እና ሞተር ሳይክሎች) መኖራቸው፣
- አልፎ አልፎ ዕቃዎች በዓይነት ሳይለዩ ተደባልቀው የተመዘገቡ መሆኑ፣
- በአብዘኛው ኦዲት ተደራጊዎች በተጠቃሚዎች እጅ ላይ ለሚገኙ ቋሚ ዕቃዎች መቆጣጣሪያ ካርድ አለመኖሩ፣ ካርዱ ባለበት ደግሞ አልፎ አልፎ ምዝገባ አለመኖሩ፣
- በአንዳንድ ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ንብረቶች ላልታወቀ አገልግሎት በውሰት በሚል ወጪ የተደረጉና ለመ/ቤቶቹም ተመላሽ ያልተደረጉ መሆኑ፣
- አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶችና የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው መድኃኒቶች አልፎ አልፎ ያልተወገዱ መሆኑ፣
- አልፎ አልፎ በንብረት ክፍል በቂ የሰው ኃይል ያልተመደበ መሆኑ፣ በዚህ ምክንያት በተለያዩ ሠራተኞች መሠራት ያለባቸው ሥራዎች በአንድ ሠራተኛ የተሠሩ ስለመሆኑ፣

<u>የክትትል ኦዲት</u>

- ለኦዲት ሥራ ድጋሚ በሚከድበት ወቅት ባለፈው ኦዲት ወቅት በታዩ ድክመቶች ላይ በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ የማሻሻያ እርምጃ አለመወሰዱ፣ ከዚህ ጋር ተያይዞ በተለያ ተመላሽ መደረግ ያለባቸው ሂሳቦች ተመላሽ አለመደረጋቸው፣

ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ከላይ ለተመለከቱት ድክመቶች አለመሻሻልና በወቅቱም እርምጃ ላለመወሰዱ ኦዲት ተደራጊዎች ሲጠየቁ የሰጧቸው መልሶች (Management Responses) ሲጠቃለሉ የሚከተለውን ይመስላሉ፡፡

- ከፍተኛ የሰለጠነና ልምድ ያለው የሰው ኃይል እጥረት መኖር፣
- ከፍተኛ የሥራ ጫና መኖር፣
- የግንዛቤ ማነስ፣
- ተገቢውን ትኩረት አለመስጠት
- የኃላፊዎችና የሥራ ሂደት ባለቤቶች ቶሎ ቶሎ ከቦታቸው መነሳት፣

ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

2. <u>የማረጋገጫ ኦዲት</u>

በኦዲት በጀት ዓመቱ፣

- በ7 ክልሎች (ኦሮሚያ፣ ሶማሊ፣ ቤኒ/ጉ፣ደቡብ፣ ሲዳማ፣ ጋምቤላ፣ ሀረሪ.) እና በ2 ከተማ አስተ/ሮች (አ/አ/ እና ድሬዳዋ) የ250 ወረዳዎች/ከተማ አስተዳደሮች የ2014 በጀት ዓመት የዜጎች የበጀት መመሪያ ዝግጅት (preparation of citizen budget guideline) የማረጋገጫ ኦዲት /DLR 7.13/፣
- ከአ/አበባ ከተማ አስተዳደር በስተቀር ከየክልሎች የ2013 በጀት ዓመት ወጪ 60%ቱ የመሠረታዊ አገልግሎት ሴክተሮች ወጪ መሆኑን ማረጋገጥ /DLR 1(a).2/፣ እና
- በተመረጡ ክልሎች እና ከተማ አስተ/ሮች ካሉ ወረዳዎች 50%ታቸው በ2013 በጀት ዓመት መጨረሻ ቋሚ ዕቃ ቆጥረውና ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር አመዛዝነው ለየክልሎቻቸው ገንብ ቢሮ ሪፖርት ማድረጋቸውን ማረጋገጥ /DLR 8.11/፣

የሚሉ የማረጋገጫ ኦዲቶች ተሠርተዉ በገንዘብ ፍሰት አመላካቾች (Disbursement Linked Results) የተቀመጠላቸው መስፈርት መሟላት አለመሟላቱ ተረጋግጧል፡፡

3. <u>ለመሠረታዊ አገልግሎቶች ድጋፍ ዓመታዊ የሂሳብ ኦዲት የተሰጠ አስተያየት እና በሥራ አመራር አንቀጽ ሥር የተገለጹ ዋና ዋና ጉዳዮች</u>

የፍትሀዊ መሠረታዊ አገልግሎት ለጋራ ብልጽግና ፕሮግራም (ESPES) እና የፍትሀዊ መሠረታዊ አገልግሎት ለጋራ ብልጽግና ውጤት ተኮር ፕሮግራም (ESPES-AF) የ2015 በጀት ዓመት የተጠቃለለ ሂሳብ ሪፖርት ኦዲት ላይ የተሰጠው የኦዲት አስተያየት ከተወሰኑ ሁኔታዎች በስተቀር የሚል “ነቀፌታ ያለበት” (qualified, Except for) ሲሆን፣ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች እና በስራ አመራር አንቀጽ ሥር ከተገለጹ በርካታ ጉዳዮች መካከል ዋና ዋና ጉዳዮች ከዚህ ቀጥሎ ተዘርዝረዋል፡፡

3.1 ትኩራት የሚሹ ጉዳዮች፣

3.1.1 የፕሮጀክት ሂሳብ (IPF)

- ከክልሎች የሂሳብ ሪፖርቶች በተዘዋዋሪ ለማረጋገጥ የተቻለ ቢሆንም በገንዘብ ሚኒስቴር ቻናል አንድ ከሚተዳደረዉ የብር አካዉንት ላይ ተቀንሶ ለክልሎች የተላከ እና የባንክ አድቫይሶች የቀረቡለት ብር 540,233,782.00 የተቀባይ መ/ቤት ስም እና የባንክ ሂሳብ ቁጥር በባንክ አድቫይሶቹ ላይ አለመጠቀሱ፣
- ወደ የገንዘብ ሚ/ር ቻናል አንድ የባንክ ሂሳብ ለገባ ብር 20,000,000.00 የባንክ አድቫይስ ላይ ብሩ የመጣበት የባንክ ሂሳብ ባለመጠቀሱ ምንጩ የማይታወቅ መሆኑ፣
- ToPCOM computer Training ከተባለ ድርጅት በብር 2,135,599.91 የተገዙ 20 HP ላፕቶፕ ኮምፒዉተሮች በሞዴል 19 ገቢ ሲደረጉ ለክትትል ያመች ዘንድ ሴሪ ቁጥራቸዉ ያልተገለጸ መሆኑ፣
- በብር 17,962,793.73 ተገዝተዉ ለኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን ለተሰጡ 80 GIS፣ 108 ኮምፒዉተሮች፣ 16 ፕሪንተሮች እና 11 plotters የንብረት ገቢ ደረሰኝ አለመቅረቡ፣

3.1.2 በ**ፕሮግራም ሂሳብ (ESPES_AF P4R) እና የፕሮጀክት ሂሳብ (IPF)**

የሥራ አመራር ከተገለጹት በርካታ ጉዳዮች መካከል ዋና ዋናዎቹ፣

- በአንዳንድ መ/ቤቶች ያልተተከ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ያለ መሆኑ፣
- በጣም ጥቂት ከሆኑት በስተቀር በሁሉም ክልል ወረዳዎች፣ ከተማ አስተዳደሮች እና የክልል መሰረታዊ አገልግሎት ሰጪ ሴክተር ቢሮዎች ከፍተኛ መጠን ያላቸው ተሰብሳቢ እና ተከፋይ ሂሳቦች በወቅቱ ሳይወራረዱ ለረጅም ጊዜ ተወዝፈው መቀመጣቸው፣
- የወጪ ሂሳብ አመዘጋገብና ሪፖርት አደራረግ ህጉን ያልተከተለ መሆኑ፣ ለምሳሌም የውሎ አበል የመስክ ሥራ ከተጠናቀቀ በኋላ ተወራርዶና በወጪ ተመዝግቦ ሪፖርት መደረግ ሲገባ በብዙ መ/ቤቶች በቅድሚያ ክፍያ በወጪ የተመዘገበና ሪፖርት የተደረገ መሆኑ፣ ለመጪ ሂሳቦች የተሟላ ደጋፊ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፣

- በወረዳዎች እና ከተማ አስተዳደሮች ለመንግስት ተሽከርካሪዎች የሚቀዳው ነዳጅ ተሽከርካሪዎች በተወሰነ ነዳጅ መጠን የሚሄዱት ኪሎ ሜትር ባልተሰላበት ሁኔታ መሆኑ፣
- በክልል ወረዳዎች፤ ከተማ አስተዳደሮች እና የክልል መሰረታዊ አገልግሎት ሰጪ ሴክተር ቢሮዎች የግዥ አፈጻጸም መንግስት ባወጣው የግዥ ደንብና መመሪያ መሠረት የማይፈጸም መሆኑ፣
- ለንብረቶች ተገቢው አያያዝ ያልተደረገ መሆኑ፣ ለምሳሌ፣

➢ ተገቢ የንብረት መጋዘን ካለመኖሩ፣ መጋዘን ባለበት ደግሞ በቂ የዕቃ መደርደሪያ ባለመኖሩ ንብረቶች ሜዳ ላይ እንዲሁም መጋዘን ውስጥ ባዶ ወለል ላይ ተበታትነው የተቀመጡ መሆኑ፣

➢ አልፎ አልፎ አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ንብረቶች ያለሥራ መቀመጣቸው፣

➢ አገልግሎት የማይሰጡ ዕቃዎች በወቅቱ ያልተወገዱ መሆኑ እና አገልግሎት ከሚሰጡ ዕቃዎች ጋር ተቀላቅለው የተቀመጡ መሆኑ፤

በ2015/16 የኦዲት ዘመን በተከናወኑ ተከታታይ ኦዲቶች ላይ ወጭ ተደርጎ ለሚመለከተው አካል የተላከ የስራ አመራር ሪፖርት ማጠቃለያ

በ2015/16 የኦዲት ዘመን 317 የተከታታይ፣ 25 የማረጋገጫ (Verification)፣ 1 ዓመታዊ ኦዲት (ገንዘብ ሚ/ር) እና 3 ልዩ ኦዲቶች፣ በድምሩ 346 ኦዲቶች የተከናወኑ ሲሆን፣ በኦዲቱ ወቅት በውስጥ ቁጥጥር ላይ የተለዩት (የተገኙት) ድክመቶች/ ግድፈቶች እና የተሰጡት የማሻሻያ ሀሳቦች /አስተያየቶች (Recommendation) እንደሚከተለው በቁጥር ተጠቃልሎ በሠንጠረዥ ቀርቧል፡፡

ተ.ቁ	ወጭ ተደርጎ ለሚመለከተው አከል የተላከ የስራ አመራር ሪፖርት	የኦዲቱ ብዛት (በቁጥር)				
		ተከታታይ ኦዲት	የማረጋገጫ ኦዲት	ዓመታዊ ኦዲት (ገንዘብ ሚ/ር)	ልዩ ኦዲት	ድምር

1	በስራ አመራሩ የተገለጹት፣ የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች/ ግድፈቶች እና የማሻሻያ ሀሳቦች	317	25	1	3	346
	ድምር	**317**	**25**	**1**	**3**	**346**

7. <u>ልዩ ኦዲት</u>

በበጀት አመቱ ካለን የሰዉ ሃይል አንጻር በእቅድ ለመስራት የተያዘዉ 11 የልዩ ኦዲት ስራ ቢሆንም የልዩ ኦዲት በበጀት አመቱ 26 ኦዲት ይደረግልን ጥያቄ በመቅረቡ የመደበኛ ኦዲት ዳይሬክቶሬቶችን ጨምሮ በማሳተፍ 23 የልዩ ኦዲት ማከናወን ተችሏል ፡፡ የተሰራዉ የኦዲት ሪፖርትም ለሚመለከታቸዉ እና ኦዲቱ እንዲሰራላቸዉ ለጠየቁ አካላት እንዲደርሳቸው ተደርጓል፡፡ ዝርዝሩም እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

<u>የኦዲት ስራቸዉ የተጠናቀቁ ኦዲቶች</u>

1. ድል በትግል የገበያ አ.ማ
2. የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
3. የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን
4. የኢትዮጵያ ልማት ባንክ አዳማ ቅርንጫፍ
5. የኢትዮጵያ ፓራ ኦሎምፒክ ኮሚቴ
6. የሰላሌ ዩኒቨርሲቲ የ2011 በጀት ዓመት የተለያዩ ግዢዎች
7. የኢትዮጵያ ክፍያ መንገዶች ኢንተርፕራይዝ
8. የኢትዮጵያ መድን ድርጅት
9. ግዮን ሆቴል ድርጅት
10. አንድ ኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ
11. የትምህርት ሚኒስቴር
12. የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ

13.የአዲስ ትውልድ ፓርቲ

14.የመቱ ዩኒቨርሲቲ

15.የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ

16.እንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት

17.ህብረት ሥራ ኮሚሽን

18.የጣና ሐይቅ ትራንስፖርት ድርጅት

19.ፈለገ ህይወት ሆስፒታል

20.የትራንስፖርትና ሎጂስቲክ ሚኒስቴር

21.ዋቸሞ ዩኒቨርስቲ

22.የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት

23.ቢኤም ኢትዮጵያ ስፌት እና ጨርቃ ጨርቅ አክስዮን ማህበር ናቸው፡፡

8. <u>የሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን የ2015 በጀት ዓመት የሥራ ክንውን</u>

1 <u>መግቢያ</u>

ሁለተኛው የተቋሙ ስትራቴጂክ ዕቅድ ዝግጅት ከ2014 በጀት ዓመት ጀምሮ በትግበራ ሂደት ላይ የሚገኝ ሲሆን ' የ2015 በጀት ዓመት ዕቅድ በኮርፖሬሽኑ የስራ አመራር ቦርድ በመጸድቅ ተተግብሯል ፡፡ በእዚህ ስትራቴጂክ ዕቅድ ኮርፖሬሽኑ ራዕዩን ' ተልዕኮውን እና እሴቶችን ለይቶ በመተግበር ላይ ሲሆን ' ዝርዝር ጉዳዮችም እንደሚከተለው ይታያሉ፡፡

2 <u>የኮርፖሬሽኑ ራዕይ</u>

"በአፍሪካ ውስጥ ታዋቂና ግንባር ቀደም የሆነ የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ኦዲት የሚያደርግ የኦዲት ተቋም ሆኖ መገኘት"፡፡

3 <u>የኮርፖሬሽኑ ተልዕኮ</u>

"የሙያ ነጻነቱ የተጠበቀ የኦዲትና ተያያዥ ሥራዎችን በመንግስታዊ የልማት ድርጅቶች ላይ የሚሰራ የኦዲት ተቋም መሆን"፡፡

4 የኮርፖሬሽኑ ስትራቴጂክ ምሰሶዎች

የስትራቴጂክ እቅድ ማዕቀፋችን ኮርፖሬሽኑ የተጣለበትን ተልዕኮ ለመወጣት እና ራዕዩን እውን ለማድረግ አስፈላጊ የሆኑት አራት ቁልፍ ምሰሶዎች ያሉት ሲሆን፣ የእነዚህ አራት ምሰሶዎች መጎልበት እና ቀጣይነት ለተቋሙ ግንባታ እና ቀጣይ ስኬት መሰረት ከመጣል ባሻገር ኮርፖሬሽኑ በውጫዊ ከባቢያዊ ሁኔታ ላይ ለሚደረጉ ለውጦች ተገቢ ምላሽ ለመስጠት እና እንዳስፈላጊነቱም በጎ ተጽእኖ ለማሳረፍ በሚቻልበት ሁኔታ ላይ ሰፊ አወንታዊ ተፅእኖ ያለው የድርጅት ባህልን ለመፍጠር ያስችላል። እነዚህም አራት ምሰሶዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

ተፈላጊነት፡- የደንበኞቻችንን፣ የሰራተኞቻችንን እና የሌሎች ባለድርሻ አካለት ፍላጎት እና ተልዕኳችንን ለማሳካት እንቅስቃሴያችን በሙሉ ደንበኛ ተኮር ይሆናል፤

ተስማሚነት፡- በማያቋርጥ የለውጥ ሑደት ውስጥ የሚገኘውን ውጫዊ የከባቢ ሁኔታዎችን የዋጀ ተቋማዊ ተስማሚነት በመፍጠር የሚከሰቱ መልካም አጋጣሚዎችን ወደ ውጤት መቀየር፤

ዘላቂነት፡- በፋይናንሳችን፣ በሰራተኞቻችንና በአጠቃላይ በህዝብ ሀብት ላይ አዎንታዊ ተጽእኖ ለማሳደር፣ የምናበረክታቸውን ጠቃሚ አገልግሎቶችን በዘላቂነት ለመስጠት እና የላቀ ውጤት ለማምጣት የሚያስችሉንን አሰራሮች እንከተላለን፤

ገለልተኛነት እና መልካም ስም፡- ደንበኞቻችን እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት በኮርፖሬሽኑ ላይ የሚያሳድሩትን አመኔታ ለመጨመር የሙያ ነጻነታችንን እና ገለልተኝነታችንን በማንኛውም ሁኔታ እንጠብቃለን& ጠንካራ ስም ለመገንባትም አበክረን እንሰራለን፡፡

5 የኮርፖሬሽኑ ስትራቴጂክ ግቦች

ኮርፖሬሽኑ ተልኮውን ለማሳካት ሁለት አበይት ግቦችን ያስቀመጠ ሲሆን፤ እነሱም፡-

ሀ) የተጠናከረ የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር

ውጤታማና ገለልተኛ የኦዲት አገልግሎት በመስጠት የመንግስት የልማት ድርጅቶች የፋይናንስና ሀብት አስተዳደር ቁጥጥር፣ ተጠያቂነት እና መልካም የድርጅት አመራር እንዲጠናከር ማገዝ፤

ለ) የተሳካ የሀብት አጠቃቀምና ዝግጁነት

እሴት የሚጨምር የማማከር አገልግሎት በመስጠት የመንግስት የልማት ድርጅቶች የፋይናንስና ሀብት አስተዳደር አመች እና ስኬታማ እንዲሆን ሙያዊ እገዛ ማድረግ ናቸው፡፡

6 የምንሰጣቸው አገልግሎቶች

ከላይ የተጠቀስቱን ግቦች ለማሳካት ኮርፖሬሽኑ የሚሰጣቸው አገልግሎቶች ሁለት ሲሆኑ እነሱም፡-

ሀ) የማረጋገጥ አገልግሎት

ለውሳኔ ሰጭ አካላት የሚቀርቡ የፋይናንስ ሪፖርቶች እና/ወይም የመረጃ አውዱን ጥራት የሚያሻሽሉ ገለልተኛ የፋይናንሺያል ኦዲት እና ሌሎች የማረጋገጥ አገልግሎቶችን በመስጠት በመንግስት የልማት ድርጅቶች እና የመንግስት ፕሮጀክቶች ውሰጥ የተጠናከረ የፋይናንስና የሀብት አስተዳደር ቁጥጥር እና ተጠያቂነት እንዲሰፍን ማገዝ፡፡

ለ) የማማከር እና ማረጋገጥ ያልሆኑ አገልግሎቶች

የመንግስት የልማት ድርጅቶች እና የመንግስት ፕሮጄክቶች ያለማቋረጥ ተለዋዋጭ ከሆነው የንግድ እና የቁጥጥር ከባቢ ለሚመነጩ ተግዳሮቶች የተዘጋጁና ውጤታማ መፍትሄ ለመስጠት የሚያስችል አቅም ለመፍጠር የሚያግዙ እሴት የሚጨምሩ የማማከር አገልግሎቶች (ለምሳሌ፡- የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ መስፈርቶች፣ ድርጅታዊ የስጋት አስተዳደር፣ ታክስ እና ቴክኖሎጂ ነክ ስጋቶች) መስጠት ናቸው ።

በመሆኑም በበጀት ዓመቱ ዓመታዊ ዕቅድ ከንውን ከአምስት ዓመቱ ስትራቴጂክ ኢንሼቲቭ እና ከመደበኛው የሥራ እንቅስቃሴ አንጻር እንደሚከተለው ይታያል፡-

ሀ) ነቀፌታ የሌለበት የኦዲት ሪፖርት ላይ የመድረስ ኢኒሼቲቭ

የሚጠበቅና የተገኘ ውጤት ፡-

- የኦዲት ውዝፍ ሥራዎች በ2015 ሙሉ በሙሉ (100%) ለማጠናቀ ተብሎ የታቀደ ቢሆንም ፣ ተቋማት ሂሳባቸውን በተለያዩ ምክንያቶች ዘግተው ማቅረብ ባለመቻላቸው በ2015 በጀት ዓመት መጨረሻ ላይ በአማካይ ለማጠናቀቅ የተቻለው 77% በመሆኑ አፈጻጸሙ የዕቅዱን 77% ነው (አባሪ ተያይዟል-5) ፣
- የደንበኞችን የኦዲት ሪፖርቶች ወቅታዊ ለማድረግ የውዝፍ ሂሳቦችንን ከመቀነስ በተጓዳኝ ዝግጁ በሆኑ ተቋማት ላይ ቅድመ ኦዲት (Preaudit) በአራት ደንበኞች ላይ ተጀምሮ በመሰራት ላይ የሚገኝ ሲሆን ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል፣
- በስትራቴጂክ ዘመኑ ማብቂያ (2018) ላይ በኮርፖሬሽኑ የሚሰሩ ኦዲቶች ቢያንስ ሰማንያ አምስት በመቶ (85%) የኦዲት ሪፖርቶቹ ነቀፌታ የሌላቸውና ጉልህ ስህተት የሌለባቸው ይሆናሉ ተብሎ የታቀደ ሲሆን፣ ደንበኞች በ2013 ላይ አግኝተውት ከነበረው የኦዲት አስተያየት በ2014 በጀት ዓመት እና በተጠናቀቀው 2015 በጀት ዓመት ያገኙት የኦዲት ሪፖርት ውጤት እየተሻሻለ መምጣቱን እና በተጠናቀቀው በጀት ዓመት መጨረሻ ካሉን የድርጅት ደንበኞቻችን ውስጥ 67.3% ነቀፌታ የሌለበት (Clean) ፣ 14.14% ነቀፌታ ያለበት አስተያየት ኳሊፋይድ (Qualified) ፣9.27% የተቃውሞ አስተያየት (Adverse) እና 2.44% ደግሞ አስተያየት ያልተሰጠባቸው (Disclaimer) ሆነዋል (አባሪ ተያይዟል-6)፡፡ በመሆኑም በስትራቴጂክ እቅዱ በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረት ጉልህ መሻሻል እየታየ በመሆኑ የተቀመጠውን ግብ ለማሳካት ድጋፍና ክትትሉ ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል፡፡

ለ) የተሻሻለ የኦዲት ዘዴዎች እና የኦዲት ሥራ-አመራር (practice management) የምንተገብርበት ኢኒሼቲቭ

የሚጠበቅና የተገኘ ውጤት፡-

- የኦዲት አደራረግ ዘዴያችን ሙሉ በሙሉ ኢንተርናሽናል የኦዲት ስታንደርድን (IAS) የጠበቀ እንዲሆን የሚሰራውን ሥራ በተመለከተ በአብዛኛው የኦዲት ስራዎች ስታንደርዱን ጠብቀው እየተሰሩ ቢሆንም ፣ በአፍሮ ሳይ የተዘጋጀውን የኦዲት ማኑዋል

ሙሉ ለሙሉ ለመተግበር የኦዲት ስራ ወረቀቶቹን ኮርፖሬሽኑ ኦዲት ከሚያደርጋቸው የልማት ድርጅቶች አንጻር የመከለስ ስራ በመጠናቀቅ ላይ ነው’

- የኦዲት ሥራችን በኮምፒተር የታገዘና ኦዲት ሶፍትዌሮችን የሚጠቀም ለማድረግ የሚሰራውን ሥራ በተመለከተ ከፌደራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤት ጋር በጋራ ለመስራት ምክክር የተደረገ ሲሆን ፣ ኮርፖሬሽኑ ለሚያከናውናቸው ኦዲቶች ተስማሚ የሆነ ሶፍትዌር የማፈላለግ ስራ እየተሰራ ነው’
- በስትራቴጂክ ዘመን ማብቂያው ላይ (2018) የኦዲት ሪፖርታችን በውጪ የጥራት ገምጋሚ አካል ሲፈተሽ ጉልህ የጥራት ችግር የሌለበት እንዲሆን የሚሰራውን ሥራ በተመለከተ የሚወጡ የኦዲት ሪፖርቶች በአብዛኛው የጥራት ደረጃቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ ለማስቻል የኦዲት ጥራት ክለሳና ግምገማ በየደረጃው እየተካሄደ ይገኛል ፡፡ የተዘጋጁ የስልጠና ሰነዶችም በመከለስ ላይ ናቸው፡፡

ሐ) የኮርፖሬሽኑን ህንጻ ለስራ ምቹና ዘመናዊ ለማድረግ (Office Renovation and Improved Working Environment) **የምንተገብርበት ኢኒሼቲቭ**

የሚጠበቅና የተገኘ ውጤት ፡-

- የኮርፖሬሽኑ ህንጻና ክፍሎቹ ጥሩ የስራ ከባቢ እንዲፈጥሩ ማድረግና ሰራተኛው በደስታና በፍላጎት እንዲሁም ጤንነቱ በተጠበቀ የመስሪያ ቦታ እንዲሰራ በማድረግ ለስራ ምቹና ሳቢ የማድረግ ሥራን በተመለከተ የሪኖቬሽን ሥራው የመጀመሪያ ጥናት ተካሂዶ ለእድሳቱ የሚያስፈልገው የወጪ መጠን የታወቀ እና የተጠየቀው ወጪ ከፍተኛ በመሆኑ ወጪውን ለመሸፈን የሚያስችሉ አማራጮች እየታዩ ናቸው፡፡

መ) ወረቀት ያልበዛበት የስራ ሁኔታ መፍጠር (Paperless Working Environment) **የምንተገብርበት ኢኒሼቲቭ**

የሚጠበቅና የተገኘ ውጤት ፡-

- ውጤታማነትን መጨመር በተመለከተ ጅምር ስራዎች በመካሄድ ላይ ናቸው፣
- የወረቀት ፍጆታን በመቀነስ ወጪን ለመቀነስ ጅምር ስራዎች በመሰራት ላይ ናቸው፣

- አላስፈላጊ እንቅስቃሴዎችን ለመቀነስ የሚያስችል ጅምር ሥራዎች በመካሄድ ላይ ይገኛሉ፣
- የአካባቢ ብክለትን በመቀነሱ በኩል የድርሻችንን መወጣት በተመለከተ የግንዛቤ ሥራዎች በመሰራት ላይ ናቸው::

በዚህም መሰረት ለኦዲት ሥራ ከደንበኞች የሚመጡና ወደ ደንበኞች የሚላኩ አንገብጋቢ የሆኑ ደብዳቤዎች የመረጃ ልውውጡ ፈጣን እንዲሆን በተከፈተ የመረጃ መለዋወጫ ፎልደር ውስጥ ገብተው የሚፈለጉ መረጃዎች ወዲያውኑ እንዲገኙና እርምጃም እንዲወሰድባቸው ተደርጓል ፡፡

ሠ) የኮርፖሬሽኑን የሥራ ዘርፍና የሥራ ክፍሎችን ማስፋፋት (Expanding Business Portfolio) **የምንተገብርበት ኢኒሼቲቭ**

የሚጠበቅና የተገኘ ውጤት፡-

- የገበያ ዕድልን የማስፋት ስትራቴጂ (Going to Market strategy) በመንደፍ ነባሮቹን የማስቀጠልና አዳዲስ ደንበኞችን የማበራከት ሥራን በተመለከተ የሥራ ክፍሉ ውዝፍ የኦዲት ሥራና በማጥራት ላይ ስለነበረ ይህ ሥራ ያልተሰራ ሲሆን፣ በቀጣዩ በጀት ዓመት ጀምሮ ለመስራት (የምንሰጣቸው የአገልግሎት ፓኬጆች እና ዋጋቸው እንዲሁም ተያያዥ ጉዳዮች) ተሰርተው እንዲቀርቡ ይደረጋል፣

- በስትራቴጂክ ዕቅዱ ማብቂያ ላይ (2018) ከኦዲት ውጪ የሚገኘውን ገቢ ከጠቅላላው ገቢ ሃምሳ በመቶ (50%) የማድረስ ሥራን በተመለከተ የልዩ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ክፍሉን በባለሙያ ከማጠናከር አንስቶ ወደ ሥራ ከመግባት ጀምሮ ክፍሉ በኮርፖሬሽኑን ውዝፍ የኦዲት ሥራን በማጥራት በኩል ዕገዛ ላይ ስለነበረ በዚህ ረገድ የተሰሩ ሥራዎች የሉም ፡፡

ዝርዝር አፈጻጸሙ በአባሪ ተያይዟል (አባሪ 1)

7. የኮርፖሬሽኑ የኦዲት ሥራዎች ዕቅድና ክንውን

7.1 የኦዲት ሥራዎች ዕቅድና ክንውን

በ2015 በጀት ዓመት በኮርፖሬሽኑ ተይዞ የነበረው የኦዲት ሥራ ዕቅድና የተገኘው አፈጻጸም ቀጥሎ ተመልክቷል:-

የዕቅዱ ዓይነት	የ2015 በጀት ዓመት ዕቅድ	የ2015 በጀት ዓመት የአፈጻጸም	የ2014 በጀት ዓመት አፈጻጸም	በ2015 በጀት ዓመት የታየው የአፈጻጸም ልዩነት ንጽጽር በመቶኛ (%)	
				ከ2015 ዕቅድ አንጻር (%)	ከ2014 አፈጻጸም አንጻር (%)
የተጠናቀቀ የኦዲት ሪፖርቶች ብዛት	270	274	318	1	(14)

ከላይ በሠንጠረዡ እንደተመለከተው በ2015 በጀት ዓመት በኮርፖሬሽኑ የኦዲት ሥራ ዕቅድ መሰረት 270 የኦዲት ሪፖርት ለማውጣትና ለማጠናቀቅ ዕቅድ የተያዘ ሲሆን ' ተጠናቅቀው ወጪ የተደረጉ 205 ' ከረቂቅ ሪፖርት ጀምሮ በተለያዩ የአፋጻጸም ደረጃዎች የሚገኙ የኦዲት ሥራዎች አፈጻጸም ስሌት መሰረት በድምሩ 69 የኦዲት ሥራዎች የተጠናቀቁ በሚል በተከፋፈለ አፈጻጸም በድምሩ 274 የወጡና የተጠናቀቁ የኦዲት ስራዎች ተመዝግቧል ፡፡ በዚህም መሰረት የበጀት ዓመቱ አፈጻጸም ከዕቅዱ በ4(1%) የኦዲት ሥራ በብልጫ ቢታይም አፈጻጸሙ ተመጣጣኝ ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል ፡፡ ይህ አፈጻጸም ከ2014 በጀት ዓመት 263 የወጣ የኦዲት ሪፖርትና 55 የተጠናቀቁ የኦዲት ሥራዎች ክንውን አንጻር ሲነጻጸር በ44(14%) የወጡ እና

የተጠናቀቁ የኦዲት ሥራዎች አፈጻጸም በማነስ ታይቷል :: ይህ ውጤት ሊመዘገብ የቻለበት ዋንኛ ምክንያት፡-

- በ2014 በጀት ዓመት ውስጥ በርከት ያሉ ወጪ የተደረጉ ሪፖርቶች (263) መሆናቸው እና በኦዲት ሂደትም የነበሩት ቢሆን አነስተኛ (75 ብቻ) መሆናቸው ከፍተኛውን ክብደት የሚይዝ ነው፣
- በተጠናቀቀው 2015 በጀት ዓመት ውዝፍ የኦዲት ሥራዎችን መቶ በመቶ ለመቀነስ ታቅዶ በክፍተኛ ርብርብና ጥረት በመሰራት ውዝፍ የኦዲት ስራውን 77% ለማድረስ የተቻለ ቢሆንም፣ ይህ አፈጻጸም ከኮርፖሬሽኑ ውጤታማነት ማነስ ሳይሆን ደንበኞች ሂሳባቸውን በወቅቱ ዘግተው አለመቅረብ'ቀርበው በተሰሩ የኦዲት ስራዎች ላይ በርከት ያሉ የምልልስ ግንኙት መፈጠር እንዲሁም ለአስተያየት የተላኩ ረቂቅ የኦዲት ርፖርቶችን ለመመለስ ብዙ ጊዜ መፍጀት የሚጠቀሱ ምክንያቶች ናቸው፣
- በ2014 በጀት ዓመት መጨረሻ ላይ በተለያየ የኦዲት ሂደት ላይ ከነበሩት 75 የኦዲት ስራዎች ውስጥ '57'ቱ ሁሉንም ሂደት ጨርሰው ሪፖርቶቹ ወጪ ቢደረጉም 18 ያህሉ ግን እስከዚሁ በጀት ዓመት መጨረሻ ድረስ አሁን በሂደት ላይ የሚገኙ ናቸው፣
- በአጋጣሙ ችግሮች ዙሪያ ከደንበኞች ጋር በተደረገው ውይይትና መግባባት ችግሮቹ እየተፈቱ በመምጣታቸው የኦዲት ሪፖርቶች ከቀድሞ በተሻለ በፍጥነት እየወጡ መምጣታቸው የሚጠቀስ ቢሆንም አሁንም በሚፈለገው ፍጥነት ደረጃ ላይ አለመገኘቱ የሚጠቀስ ነው፣

- በሌላ በኩል ደግሞ በ2015 በጀት ዓመት መጨረሻ ላይ በኮርፖሬሽኑ የኦዲት ፖርትፎሊዮ ቡድኖች ሥር በተለያየ የኦዲት አፈጻጸም ደረጃ ላይ የነበሩ የኦዲት ሥራዎች (WIP) ብዛት በድምሩ 89 ሲሆኑ' ከነዚህ ውስጥ 29 ያህሉ ረቂቅ የኦዲት ሪፖርታቸው ለኦዲት ተደራጊዎች ተልኮ ምላሽ በመጠባበቅ ላይ የነበሩ ሲሆን' የእነዚህ አፈጻጸም በተጠናቀቀ የኦዲት ስራዎች አንጻር 26 ሪፖርቶች ይሆናሉ፡፡ በተመሳሳይ 44 የኦዲት ሥራዎች በተለያየ ደረጃ የክለሳ ሂደት (Audits Under Reviews) ላይ የሚገኙ ሲሆን' የእነዚህ አፈጻጸም በተጠናቀቀ የኦዲት ሥራዎች አንጻጻር 35 የተጠናቀቁ የኦዲት ስራዎች ይሆናሉ፡፡ 16 የሚሆኑ የኦዲት ሥራዎች

የመስክ ሥራቸው በመካሄድ ላይ (Audits at field work level) ያሉ እና የእነዚህ አፈጻጸም በተጠናቀቀ የኦዲት ስራዎች አንጻር 8 ይሆናሉ፡፡

7.2 የኮርፖሬሽኑ የኦዲት ሥራዎች የሪፖርቶች ዓይነትና ስርጭት

7.2.1 የኦዲቱ ሪፖርት

ከላይ እንደተመለከተው ኮርፖሬሽኑ ከተቋቋመበት ዓላማ አንጻር አንዱና ዋነኛው ተግባሩ ለመንግስታዊ የልማት ድርጅቶች የኦዲት አገልግሎት መስጠት ነው ፡፡ በዚህም መሰረት ኮርፖሬሽኑ ተመርማሪ ድርጅቶች በየበጀት ዓመቱ መጨረሻ የሚያዘጋጁትን የየዘመኑን የሥራ ክንውን እንቅስቃሴዎቻቸውንና ውጤቱን የሚያመላክት የኃብትና ዕዳ መግለጫ ' የገቢና የወጪ ሂሳብ መግለጫ እንዲሁም የጥሬ ገንዘብ ፍሰት መግለጫና የድርጅቱ የኃብት ለውጥ (Equity) የሚያሳይ የሂሳብ መግለጫዎችን መሰረት በማድረግ እንደ ድርጅቱ ሁኔታ ተቀባይነት ባለው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት የተዘጋጁና ትክክል ስለመሆናቸው አጠቃላይ አስተያየት ለመስጠት የሚያስችል የሂሳብ ምርመራ ያከናውናል::

7.2.2 የሪፖርት ስርጭት

ኮርፖሬሽኑ የእያንዳንዱን ድርጅት ሂሳብ ከመረመረ በኋላ እንደሁኔታው ሪፖርቱን በቀጥታ ለድርጅቱ የበላይ ተቆጣጣሪ መ/ቤት ወይንም ቦርድ ሲልክ በግልባጭ ደግሞ ለተመርማሪው ድርጅት ያሳውቃል፡፡ በተጨማሪም ፡-`

ለፌደራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤት፣

ለመንግስት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ፣

ለገንዘብ ሚኒስቴር እና የሚመለከታቸው ሌሎች መ/ቤቶች፣

ሪፖርቱን ተመልክተው የሚያስፈልጋቸውን መረጃ እንዲያገኙና ክትትል እንዲያደርጉ የሪፖርቱን ግልባጭ ይልካል ::

7.2.3 የሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን የሚያወጣቸው ሪፖርቶች

ኮርፖሬሽኑ የሚያወጣቸው የኦዲት ሪፖርቶች ሁለት አይነት ሲሆኑ፣ እነሱም

1. የኦዲተሩን አስተያየት የሚይዘው የኦዲት ሪፖርት (Auditor's Opinion)'
2. የኦዲት ግኝቶችንና የማሻሻያ ሃሳቦችን የሚይዘው ዝርዝር የሥራ አመራር ሪፖርት (Management letter) ናቸው::

7.2.3.1 ከላይ በተራ ቁጥር 1 የተጠቀሰው ሪፖርት የሚያመለክተው በአንድ ድርጅት ተዘጋጅተው የቀረቡትን የሂሳብ መግለጫዎች ኦዲት በማድረግ ከዚህ በሚገኘው ውጤት መሰረት ጠቅላላ የሂሳቡ ይዘት በኦዲተሩ አስተያየት ትክክለኛውን ሁኔታ ማሳየት ወይም አለማሳየቱን የሚገለጽበት የኦዲት ሪፖርት ነው፡፡

7.2.3.2 ላይ በተራ ቁጥር 2 የተመለከተው ሪፖርት ደግሞ በተራ ቁጥር 1 በተጠቀሰው አጭር ሪፖርት ውስጥ ከተመለከቱት ነጥቦች በተጨማሪ በሂሳብ ምርመራ ወቅት የተደረሰባቸው የአሰራርና የውስጣዊ ቁጥጥር ድክመቶች ካሉ ይህንኑ በመጠቀም እንዲወገዱ ለማድረግ ወይንም ለማሻሻል የሚያስችሉ የኦዲተሮችን አስተያየት ጭምር የሚያካትት ዝርዝር ሪፖርት ነው ::

7.3 በበጀት ዓመቱ የወጡ የኦዲት ሪፖርቶች አይነት፣ እንዲሁም ከ2014 በጀት ዓመት አፈጻጸም ጋር ሲነጻጸር ቀጥሎ ተመልክቷል:-

ከላይ በተራ ቁጥር 7.1 እንደተመለከተው በ2015 በጀት ዓመት ኮርፖሬሽኑ 205 የኦዲት ሪፖርቶች የወጡ ' 69 የኦዲት ሥራዎች የተጠናቀቁ በድምሩ 274 የኦዲት ሥራዎች አፈጻጸም የተገኘ ሲሆን ' የወጡትን ሪፖርቶች ከተሰጣቸው የኦዲት አስተያየት አይነት (Type of audit opinion) አንጻር እንደሚከተለው ተጠቃልሎ በየኦዲት አስተያየቱ አይነት ተመልክቷል፡-

	የተሰጡ የኦዲት አስተያየቶች ማጠቃለያ በየአይነቱ (Summary of Types of Audit Opinions)	የ2015 የወጡ ብዛት (በቁጥር)	የ2014 የወጡ ብዛት (በቁጥር)	ልዩነት የ2015 በጀት ዓመት ከ2014 በመብለጥ (በማነስ)	
				በቁጥር`	በመቶኛ (%)
1	አጥጋቢ ሆነው በመገኘታቸው ነቀፌታ የሌለበት አስተያየት የተሰጠባቸው (Unqualified / Clean audit opinion) የኦዲት ሪፖርቶች	138	158	(20)	(13)
2	አልፎ አልፎ ሊጠቀሱ ከሚችሉ ጥቂት ጉድለቶች ወይም ስህተቶች በስተቀር በአጠቃላይ ሲታይ አጥጋቢ ሆነው በመገኘታቸው ነቀፌታ ያለበት አስተያየት የተሰጠባቸው (Qualified / Except for audit opinion) የኦዲት ሪፖርቶች	29	41	(12)	(29)
3	አቋም ለመውሰድ እንደማይቻል በመግለጽ የኦዲት አስተያየት ያልተሰጠባቸው (Disclaimer of opinion) የኦዲት ሪፖርቶች	19	55	(36)	(65)

4	አጥጋቢ ሆነው ባለመገኘ ታቸው የተቃውሞ አስተያየት የተሰጠባቸው (Adverse Audits Opinion) የኦዲት ሪፖርቶች	5	4	1	25
5	አስተያየት የማይሰጥባቸው የኦዲት ሪፖርቶች እና ሌሎች (Interim and Special Audits Reports) and Others	14	5	9	180
	ጠቅላላ ድምር	**205**	**263**	**(58)**	**(22)**

ከላይ በሠንጠረዡ የተመለከቱት የኦዲት ሪፖርት ዓይነቶች ዝርዝራቸው በአባሪ ተያይዟል (አባሪ 3)፡፡

8. <u>የኮርፖሬሽኑ የፋይናንስ ዕቅድና ክንውን</u>

ኮርፖሬሽኑ የገቢ ምንጭ በዋናነት የተመሰረተው ለተለያዩ የመንግስት የልማት ድርጅቶችና ሌሎች መንግስታዊ ተቋማት (ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች) ከሚሰጠው የኦዲት አገልግሎት ከሚያስከፍለው የአገልግሎት ዋጋ በተጨማሪ ከልዩ አገልግሎቶች ማለትም ከማማከርና ከልዩ ኦዲት ሥራ እንዲሁም ከሕንፃው ቢሮዎች ከሚገኝ የኪራይ ገቢ ገቢውን የሚያዳብር ሲሆን ፣ በዚህም መሠረት የኮርፖሬሽኑ የ2015 በጀት ዓመት የፋይናንስ እንቅስቃሴ እንደሚከተለው ተመልክቷል:-

8.1 የኮርፖሬሽኑ የ2015 በጀት ዓመት የገቢ ዕቅድና ክንውን

መግለጫ	የ2015 በጀት ዓመት ዕቅድ	የ2015 በጀት ዓመት የአፈጻጸም	የ2014 በጀት ዓመት አፈጻጸም	የ2015 የአፈጻጸም ግምት የታየው ልዩነት ንጽጽር በመቶኛ (%)	
				ከ2015 ዕቅድ አንጻር (%)	ከ2014 አፈጻጸም አንጻር (%)`
ከኦዲት ሥራና ከማማከር አገል ግሎት የተገኘ ገቢ	74,696,458	96,990,570	72,961,579		21
ከቤት ኪራይ የተገኘ ገቢ	996,985	996,985	996,985	-	-
በዕቅድ የማይ ያዙ ልዩ ልዩ የውስጥ ገቢዎች	-	56,000	38,680	-	-
የገቢ ድምር	75,693,443	98,043,555	73,997,243	30	20

<u>ማብራሪያ</u>

- የ2015 በጀት ዓመት የኦዲት ሥራ ገቢ ከዕቅዱ ጋር ሲነጻጸር አፈጻጸሙ በብር 22,294,112 (30%) እና ይህ አፈጻጸም ከ2014 አፈጻጸም ጋር ሲነጻጸር ደግሞ በብር 24,028,991 (33%) በመብለጥ የታየበት ዋንኛ ምክንያት ከላይ በ'7.1' ሥር የተመለከተው ማብራሪያ ሲሆን ' በሌላ በኩል ደግሞ ከዚህም በተጨማሪ ከ"IFRS" ትግበራ እና ከህጋዊነት (Compliance) ኦዲት ጋር በተገናኘ ተጨማሪ ሥራ የተሰራ

በመሆኑ ለእነዚህ ሥራዎች ደግሞ ተጨማሪ የኦዲት ሥራ ክፍያ መከፈል ስለሚኖርበት በኦዲት አገልግሎት ገቢ ላይ መጠነኛ ጭማሪ በመደረጉ ነው ፡፡

8.2 የወጪ ሂሳብ

8.2.1 የኮርፖሬሽኑ የ2015 በጀት ዓመት የወጪ ዕቅድና ክንውን

መግለጫ	የ2015 በጀት ዓመት ዕቅድ	የ2015 በጀት ዓመት አፈጻጸም	የ2014 በጀት ዓመት አፈጻጸም	የ2015 አፈጻጸም የታየው ልዩነት ንጽጽር በመቶኛ (%)	
				ከ2015 ዕቅድ አንጻር (%)	ከ2014 አፈጻጸም አንጻር (%)
የደመወዝ አበልና የፐርሶኔል ወጪ	57,709,102	49,328,197	34,745,503	15	(42)
የሥራ ማስኬጃ ወጪ	13,978,487	13,134,134	5,451,996	6	(141)
የወጪ ድምር	**71,687,589**	**62,462,331**	**40,197,499**	**13**	**(55)**

ማብራሪያ፡-

ከላይ በሠንጠረዥ እንደተመለከተው የ2015 በጀት ዓመት የወጪ የአፈጻጸም ከበጀት ዓመቱ ዕቅድ አንጻር ሲነጻጸር አፈጻጸሙ ከዕቅዱ በብር 9,225,258 (13%) በማነስ ታይቷል ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በዚሁ በሠንጠረዥ ላይ እንደተመለከተው የ2015 በጀት ዓመት የአፈጻጸም ካለፈው የ2014 በጀት ዓመት አፈጻጸም ጋር ሲነጻጸር የ2015 አፈጻጸም በብር 22,264,832 (55%) በልጦ ታይቷል ፡፡

ለዚህ ልዩነት ዋንኛው ምክንያት እንደሚከተለው ቀርቧል:-

ሀ) የ2015 በጀት ዓመት ዕቅድ ከ2015 በጀት ዓመት የአፈጻጸም አንጻር ጋር ሲነጻጸር

¾ ደመወዝ፣ አበልና የፐርሶኔል ወጪ በጀት ልዩነትን በተመለከተ፡-

የ2015 በጀት ዓመት የወጪ በጀት ከ2015 በጀት ዓመት የአፈጻጸም ጋር ሲነጻጸር የደመወዝ ' አበልና የፐርሶኔል ወጪ በብር 8,380,905 (15%) አንሶ ታይቷል ፡፡ ይህም የሆነበት ዋንኛ ምክንያት፡-

- አዳዲስ የኦዲት ባለሙያዎችን በየደረጃው ለመቅጠር ዕቅድ ቢያዝም መቅጠር የተቻለው ግን በከፊል ሲሆን & ከተቀጠሩትም መካከል በርካታዎቹ በራሳቸው ምክንያት ሥራ በመልቀቃቸው በደመወዝ ፣ በጡረታ መዋጮና በመጓጓዣ አበል ክፍያ ላይ የወጪ አፈጻጸሙ ከበጀቱ በብር 5,208,329 በማነስ ሥራ ላይ ባለመዋሉ፣
- በበጀት ዓመቱ ለማበረታቻ የሚከፈለው ገንዘብ አፈጻጸሙ ከበጀቱ በብር 169,951 በማነሱ'
- በ2015 በጀት ዓመት የተጠራቀመ የአንድ ዓመት ፈቃድ ያልወሰዱ የኮርፖሬሽኑ ሰራተኞች በገንዘብ ተለውጦ በመሰጠቱ የወጪ አፈጻጸሙ ከበጀቱ በብር 433,989 በመብለጡ'
- በበጀት ዓመቱ የተያዙት ስልጠናዎች በውዝፍ ሂሳብ ኦዲት ምክንያት ስልጠናዎቹ በወቅቱ ባለመሰጠታቸውና አብዛኛው ስልጠናዎች ደግሞ በመንግስት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ ወጪ በመከናወናቸው ' የውጪ አገር ትምህርት በተልዕኮ የሚማሩ ባለሙያዎችም ቁጥራቸው እየቀነሰ በመምጣቱ '

በአጠቃላይ ለትምህርትና ስልጠና የወጣው ወጪ ከበጀቱ በብር 1,775,242 በማነስ ሥራ ላይ በመዋሉ'

- የትርፍ ሰዓት ሥራ ክፍያ አፈጻጸሙ ከበጀቱ በብር 1,188,364 ሊያንስ የቻለው ለ `IPSAS` ትግበራ ተብሎ ሥራውን ለሚሰሩ ባለሙያዎች የተያዘው በጀት ባለሙያዎቹ በአስቸኳይ ውዝፍ ኦዲት ሥራዎች ላይ በመሆናቸው የትግበራ ሥራው በመዘግየቱና ክፍያው ባለመፈጸሙ፤
- የሙያ አበል ፤ ተጨማሪ የቤትና የሀላፊነት አበል የሚገባቸው ባለሙያዎች ቁጥራቸው እየጨመረ በመምጣቱና በ2015 በጀት ዓመት የወጣው የወጪ አፈጻጸም ከበጀቱ በብር 461,399 መጨመሩ'
- ከቤቶች ኮርፖሬሽን ለኮርፖሬሽኑ ኃላፊዎች የተሰጡ ቤቶች የኪራይ ዋጋቸው ከበፊቱ የጨመረ በመሆኑ የወጪ አፈጻጸሙ ከበጀቱ በብር 179,367 በመጨመሩ'
- ለዩኒፎርም የተያዘው በጀት የወጪ አጠቃቀሙ ከበጀቱ በብር 173,476 ሊያንስ በመቻሉ'
- የሌሎች ጥቃቀንና ልዩ ልዩ አነስተኛ የአበልና የፐርሶኔል ወጪዎች በጀት አንዳንዱ በማነስና አንዳንዱም በመብለጥ ወጥተው የ2015 በጀት ዓመት የእነዚህ ጥቃቅን ወጪዎች ድምር አፈጻጸም ከተመሳሳይ በጀት ዓመት ዕቅድ በብር 940,298 ያህል በማነስ ስራ ላይ በመዋሉ፣

የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ምክንያቶች ናቸው ፡፡

የሥራ ማስኬጃ ወጪ በጀት ልዩነትን በተመለከተ ፡

የሥራ ማስኬጃ ወጪን በተመለከተ ዕቅዱ የ2016 ዕቅድ ከ2015 የክንውን ግምት በብር 844,353 (6%) በማነስ የታየበት ዋና ዋና ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፡-

- ለውጪ አገር ትምህርታዊና የልምድ ልውውጥ የተያዘውን በጀት አፈጻጸም በተመለከተ የወጣው ወጪ ከበጀቱ በብር 768,265 ሊያንስ በመቻሉ'
- የጽዳት ዕቃዎች ግዢ አፈጻጸሙ ከበጀቱ በብር 114,571 በማነሱ'

- ኮርፖሬሽኑ ከውጭ አገር ለሚያስመጣው ለሥራ ማጣቀሻ መጽሐፍት (IFRS Packages) በውጭ ምንዛሪ እጥረት ምክንያት በ2015 በጀት ዓመት ሊመጣ ባለመቻሉ አፈጻጸሙ ከበጀቱ ብር 600,000 በማነሱ'
- የጽህፈት መሳሪያ የወጪ አፈጻጸም ከበጀቱ በብር 162,754 በማነሱ'
- የኮርፖሬሽኑ ተሽከርካሪዎች እያረጁ መምጣታቸውና የወጋ ጭማሪም በመኖሩ የነዳጅና ቅባት የወጪ አፈጻጸም በከበጀቱ በብር 192,461 በመብለጡ'
- በበጀት ዓመቱ ለኮርፖሬሽኑ ከፍተኛ ኃላፊዎች በኪራይ የተሰጡ ቤቶችን ለኑሮ ምቹ የማድረግ ሥራ ስለተሰራ የወጪ አፈጻጸሙ ከበጀቱ በብር 852,440 መብለጡ'
- ከባለድርሻ አካላት ጋር የሚደረገውን የምክክር መድረክ በተመለከተ አፈጻጸሙ ከበጀቱ በብር 1,522,410 በማነሱ'
- ኮርፖሬሽኑ በመንግስት ትዕዛዝ የአክሰስ ሪል እስቴት የልዩ ኦዲት ስራ ተሰርቶ ገቢው አጠራጣሪ በመሆኑ እና የማይሰበሰበው ገንዘብ በተጠባባቂ የወጪ አርስት መያዝ ስላለበት የወጪ አፈጻጸሙ ከበጀቱ በብር 2,323,749 በመብለጡ'
- የቋሚ ዕቃዎች እርጅና ቅናሽ አፈጻጸሙ ከበጀቱ በብር 779,359 ሊያንስ የቻለው ይገዛሉ የተባሉት ሶስት ተሽከርካሪ መኪናዎች ባለመገዛታቸውና የእርጅና ቅናሽ በእነዚህ ተሽከርካሪዎች ላይ ባለመሰላቱ'
- የሌሎች ጥቃቅንና ልዩ ልዩ አነስተኛ የሥራ ማስኬጃ ጪዎች በጀት አንዳንዱ በማነስና አንዳንዱም በመብለጥ ወጥተው የ2015 በጀት ዓመት የእነዚህ ጥቃቅን ወጪዎች ድምር የወጪ አፈጻጸም ከበጀቱ በብር 265,937 ያህል በማነሱ'

የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ምክንያቶች ናቸው፡፡

ለ) የ2015 በጀት ዓመት የወጪ አፈጻጸም ከ2014 በጀት ዓመት የወጪ አፈጻጸም ጋር ሲነጻጸር የደመወዝ'አበልና የፐርሶኔል ወጪ በጀት ልዩነትን በተመለከተ:-

የ2015 በጀት ዓመት የውጪ አፈጻጸም ግምት ከ2014 በጀት ዓመት ክንውን ጋር ሲነፃፀር የደመወዝ'አበልና የፐርሶኔል ወጪ በብር14,582,694 (42%)በልጦ ታይቷል፡፡ ይህም የሆነበት ዋንኛ ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፡-

- በ2015 በጀት ዓመት የደረጃ ዕድገት ለሚገባቸው ሠራተኞች ዕድገት በመሰጠቱ ፤ ለሁሉም ሠራተኞች ከመስከረም ወር 2015 ጀምሮ የደመወዝ ጭማሪ በመደረጉ፤

ተጨማሪ ባለሙያዎች በመቀጠራቸውና ሠራተኞች ጠዋትና ማታ የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲያገኙ ከፐብሊክ ሰርቪስ የትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት ጋር ከህዳር 2014 ዓ.ም ጀምሮ ውለታ በመገባቱ ምክንያት በደመወዝ ፣ በጡረታ መዋጮና አበል ላይ የ2015 በጀት ዓመት የወጪ አፈጻጸም በብር 13,780,043 ከ2014 ተመሳሳይ ወቅት በልጠ ሥራ ላይ በመዋሉ፣

- በሥራ መብዛት የተነሳ የተጠራቀመ የዓመት ፈቃድ ያላቸው ባለሙያዎች በገንዘብ ተለውጦ እንዲሰጣቸው በመደረጉ የ2015 በጀት ዓመት የአፈጻጸም ከ2014 በብር 311,655 መብለጡ'
- የማበረታቻ (ቦነስ) ክፍያ በደመወዝ ጭማሪ የተነሳ የ2015 አፈጻጸም ከ2014 አፈጻጸም በብር 1,232,157 በመብለጡ'
- በአገር ውስጥ ለሚሰጥ ስልጠና እና በተልዕኮ ለሚማሩ የኮርፖሬሽኑ ሰራተኞች የ2015 በጀት ዓመት የወጪ አፈጻጸም ከ2014 በጀት ዓመት አፈጻጸም በብር 952,784 በማነሱ'
- የሌሎች ጥቃቀንና ልዩ ልዩ አነስተኛ የአበልና የፐርሶኔል ወጪዎች በጀት አንዳንዱ በማነስና አንዳንዱም በመብለጥ ወጥተው የ2015 በጀት ዓመት የእነዚህ ጥቃቅን ወጪዎች ድምር አፈጻጸም ከ2014 በጀት ዓመት ከነውን በብር 211,623 ያህል በመብለጥ ስራ ላይ በመዋሉ'

የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ምክንያቶች ናቸው፡፡

የሥራ ማስኬጃ ወጪ በጀት ልዩነትን በተመለከተ፡-

የሥራ ማስኬጃ ወጪን በጀት በተመለከተ የ2015 የአፈጻጸም ግምት ከ2014 አፈጻጸም በብር 7,682,138 (141%) በልጦ የታየበት ዋና ዋና ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፡-

- ከአገር ውጪ በሚሰጥ ትምህርት ' ስልጠና እና ወርክ ሾፖች ላይ ለመሳተፍ በ2015 ከተያዘው በጀት የወጣው ወጪ ከ2014 በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት የወጪ አፈጻጸም በብር 1,731,735 ሊበልጥ የቻለው በ2015 በጀት ዓመት ውስጥ የኮርፖሬሽኑ ከፍተኛ ባለሙያዎች የውጪ አገር ትምህርታዊ ኮንፍረንስ ላይ ለመሳተፍ ለሄዱበት የወጣ ወጪ ሲሆን ' በ2014 በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት

ግን ለዚህ ጉዞ በጀት ቢያዝም የዚህ አይነት የውጪ አገር ትምህርታዊ ጉዞ ባለመደረጉ፤

- በበጀት ዓመቱ የተቀጠሩ ባለሙያዎች በ2015 ዓ.ም ጀምሮ በተደረገው የደመወዝ ጭማሪ የተነሳ ለተቀጠሩት ባለሙያዎች ኢንሹራንስ ስለሚከፈል የ2015 የወጪ አፈጻጸም ከ2014 የወጪ አፈጻጸም በብር 456,343 በመብለጡ '
- በዋጋ መጨመር የተነሳ የጽህፈት መሳሪያዎች የ2015 የወጪ አፈጻጸም ከ2014 አፈጻጸም በብር 413,666 በመብለጡ '
- በዋጋ መጨመርና በመኪናዎች እርጅና የተነሳ ፍጆታ መጨመር የ2015 የነዳጅና ቅባት የወጪ አፈጻጸም ከ2014 አፈጻጸም በብር 441,964 በመብለጡ'
- በዋጋ መጨመርና በመኪናዎች እርጅና የተነሳ የመኪናዎች ጥገና ወጪ የ2015 የጥገና ወጪ አፈጻጸም ከ2014 አፈጻጸም በብር 456,736 በመብለጡ'
- በበጀት ዓመቱ ለኮርፖሬሽኑ ከፍተኛ ኃላፊዎች በኪራይ የተሰጡ ቤቶችን ለኑሮ ምቹ የማድረግ ሥራ ስለተሰራ የ2015 የወጪ አፈጻጸሙ ከ2014 አፈጻጸም በብር 817,595 መብለጡ'
- በ2015 በጀት ዓመት ከባለድርሻ አካላት ጋር የተደረገው የምክክር መድረክ ጋር በ2014 በጀት ዓመት ባለመኖሩ የ20115 አፈጻጸም ከ2014 አፈጻጸም በብር 177,590 በመብለጡ '
- ኮርፖሬሽኑ በመንግስት ትዕዛዝ የአክሰስ ሪል እስቴት የልዩ ኦዲት ስራ ተሰርቶ ገቢው አጠራጣሪ በመሆኑ እና የማይሰበሰበው ገንዘብ በተጠባባቂ የወጪ አርስት መያዝ ስላለበት የወጪ አፈጻጸሙ ከ2014 አፈጻጸም በብር 2,323,749 በመብለጡ'
- በ2015 በጀት ዓመት ዓመታዊ የሰራተኞች ስብሰባ በመደረጉ እና ተመሳሳይ ስብሰባ በ2014 በጀት ዓመት ባለመኖሩ የ2015 የወጪ አፈጻጸም ከ2014 አፈጻጸም በብር 287,173 በመብለጡ'
- በ2015 በጀት ዓመት በርከት ያሉ አዲስ የተገዙ ቋሚ ዕቃዎች በመገዛታቸው (ኮምፒተሮች ' ጄነሬተር ወዘተ) እና በዚሁ በጀት ኣመት የተደረገው የእርጅና ቅናሽ ከ2014 አፈጻጸም በብር 682,743 በመብለጡ'
- የሌሎች ጥቃቅንና ልዩ ልዩ አነስተኛ የስራ ማስኬጃ ወጭዎች በጀት አንዳንዱ በማነስና አንዳዱም በመብለጥ ወጥተው የ2015 በጀት ዓመት የእነዚህ ጥቃቅን

ወጪዎች ድምር ካለፈው የ2014 በጀት ዓመት አፈጻጸም በብር 107,156 ያህል በማነስ ስራ ላይ ሊውል እንደሚችል በመገመቱ'

የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ምክንያቶች ናቸው ፡፡

8.3 የ2015 በጀት ዓመት የትርፍ (Surplus) ዕቅድ ክንውን

መግለጫ	የ2015 በጀት ዓመት ዕቅድ	የ2015 በጀት ዓመት አፈጻጸም	የ2014 በጀት ዓመት አፈጻጸም	የ2015 አፈጻጸም የታየው ልዩነት ንጽጽር በመቶኛ (%)	
				ከ2015 ዕቅድ አንጻር (%)	ከ2014 አፈጻጸም አንጻር (%)
ያልተጣራ ትርፍ (ከታክስ በፊት)	4,005,854	35,581,224	33,799,743	788	5
የተጣራ ትርፍ (ከታክስ በኋላ)	2,804,098	24,906,857	23,659,820	788	5

<u>ማብራሪያ፡-</u>

ከላይ በሠንጠረዥ እንደተመለከተው የ2015 በጀት ዓመት የትርፍ ክንውኑ ከበጀት ዓመቱ እቅድ እና ከ2014 የትርፍ ክንውን ጋር ሲነጻጸር የ2015 የትርፍ ክንውን በማነስ ሊታይ

የቻለበት ዋና ምክንያት ከላይ በገቢ አፈጻጸም '8.1' እና በወጪ '8.2' ሥር እንደተመለከተው ነው ፡፡

8.4 የ2015 በጀት ዓመት የካፒታል በጀት ዕቅድና ክንውን

በ2015 በጀት ዓመት ለካፒታል በጀት ከተያዘው በጀት ብር 35,650,000 ውስጥ በሥራ ላይ የዋለው ብር 7,934,328 ለላፕ ቶፕ እና ዴስክ ቶፕ ኮምፒተሮች 'የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ጀነሬተር' ድንገተኛ የኤሌክትሪክ ኃይል መቋረጥ መከላከያ (UPS) 'ወንበር እና ጠረጴዛዎች ግዢ ለመፈጸም ሥራ ላይ ውሏል፡፡ ቀሪው ብር 27,715,672 በሥራ ላይ አልዋለም ፡፡ ለዚህም ዋንኛው ምክንያት፡-

- ይገዛሉ ተብለው በዕቅድ የተያዙት ሶስት አውቶሞቢሎች ማለትም ብር 12,500,000 በመንግስት የግዢ አገልግት በኩል እንዲፈጸም የተደረገው ጥረት ባለመሳካቱ'
- የኮርፖሬሽኑን ቢሮ ለማዛመን (Office Renovation Works) የተያዘው በጀት ብር 15,000,000 የግንባታው ግዢ ጥናት (የቴክኒካልና የፋይናንሻል) መሰረት ግንባታው የሚያስወጣው ወጪ አጅግ ከፍተኛ በመሆኑና ይህም ከኮርፖሬሽኑ አቅም በላይ በመሆኑ አማራጭ መፍትሄ በመፈላለግ ላይ በመሆኑ'
- ለገመድ አልባ ኢንተርኔት ዝርጋታ ' የደህንነት ካሜራ ተከላ እንዲሁም ዲጂታል የሰራተኞች የሰዓት መቆጣጠሪያ ስርዓት መሳሪያዎች ግዢ የተያዘው በጀት ብር 1,800,000 የቢሮ ዕድሳት የማዘመን ሥራ (Office Renovation Works) ሁኔታው እስከሚታወቅ ድረስ እንዲዘገይ በመደረጉ በጀቱ ሥራ ላይ አልዋለም'

የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ምክንያቶች ናቸው፡፡

9) የኮርፖሬሽኑ የሰው ኃይል

1) በ2015 በጀት ዓመት በኮርፖሬሽኑ የነበረው የሰው ኃይል እንቅስቃሴ ቀጥሎ በሠንጠረዥ ተመልክቷል:-

የሰው ኃይል እንቅስቃሴ	የሰው ኃይል ብዛት		ድምር
	ወንድ	ሴት	
በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ የነበሩ	93	54	147
አዲስ የተቀጠሩ	18	4	22
ንዑስ ድምር	**111**	**58**	**169**
በተለያዩ ምክንያቶች ከኮርፖሬሽኑ የለቀቁ ሰራተኞች ድምር	**(19)**	**(10)**	**(29)**
ሰኔ 30 ቀን 2015 ዓ.ም (በበጀት ዓመቱ መጨረሻ) ላይ የነበሩ ሠራተኞች ብዛት	**92**	**48**	**140**

2) ሰኔ 30 ቀን 2015 የነበረው የሰው ኃይል ብዛት በሥራ መደብና በጾታ ሲተነተን፡-

የባለሙያ ብዛት በሙያ ዘርፍ	በሥራ ላይ ያለው የሰው ኃይል ብዛት (በቁጥር)		
	ወንድ	ሴት	ድምር
የኦዲት ባለሙያዎች	65	24	89

የድጋፍ ሰጪ ባሙያዎች	27	24	51
ጠቅላላ ድምር	**92**	**48**	**140**

ዝርዝር የሰው ኃይል እንቅስቃሴው በአባሪ 2 ተያይዟል::

10. <u>የተመርማሪ ድርጅቶች አጠቃላይ የሂሣብ አያያዝ፣ የንብረት አጠባበቅና የፋይናንስ አስተዳደርን በተመለከተ የታዩ ዋና ዋና ደክመቶችና የተሰጡ የማሻሻያ ሃሳቦች</u>

<u>የሂሣብ አያያዝና የንብረት አጠባበቅ</u>

10.1.0 ቋሚ ንብረት (Fixed Assets)

ባለፉት ዓመታት ሪፖርቶች እንደተጠቆመው ሁሉ በ2015 በጀት ዓመት ውስጥ በተደረገው ምርመራም አንዳንድ ድርጅቶች የቋሚ ንብረት መቆጣጠሪያ ዝርዝር መዝገብ የሌላቸው፤ ያላቸውም ቢኖሩ አንዳንዶች ደግሞ መዝገባቸው ያልተሟላ፣ እንዳንዶቹ ደግሞ የተለያዩ ቋሚ ንብረቶችን በአንድ ላይ መዝግበው ተገኝተዋል፡፡ በቋሚ ንብረት ላይ ሊኖር የሚገባው ቁጥጥር ለማጠናከር እንዲረዳ የቋሚ ንብረት ዝርዝር መዝገብ መያዙ አስፈላጊ ከመሆኑም ሌላ ይኸው መዝገብ ቢያንስ ከዚህ የሚከተሉትን አስፈላጊ መረጃዎች መያዝ እንደማገባው በተደጋጋሚ አስተያየት ተሰጥቶበታል፡፡

- የቋሚ ንብረቱ የተገዛበት ቀንና ዋጋ መግለጫና ንብረቱ ገቢ የሆነበት ደረሰኝ ማጣቀሻ
- የአገልግሎት ቅናሽ (Depreciation)
- መለያ ቁጥር
- ንብረቱ የሚገኝበት ክፍልና በማን ኃላፊነት ሥር እንደሚገኝ፡፡

10.1.1 አንዳንድ ተመርማሪ ድርጅቶች የቋሚ ንብረት መዝገብ ቢይዙም ግገርን፣ ሽያጭንና ዝውውርን በተመለከተ የተሟላ መረጃ በየጊዜው ካለመመዝገባቸውም ሌላ በዝርዝር መዝገቡ ውስጥ ያለው የዋጋና የአገልግሎት ቅናሽ ሂሣብ ከሂሳብ መዛግብት (accounting records) ጋር በየወቅቱ ባለመመሳከሩ በሁለቱ መዛግብት መካከል

ልዩነቶች አጋጥመዋል፡፡ ስለዚህ የቋሚ ንብረት ዝርዝር መዝገብ በመያዝ ሊገኝ የሚገባውን መረጃ በሙሉ ለማግኘት ዝርዝር መዝገቡ ከሂሣብ መዛግብት ጋር በየጊዜው እየተመሳከረ መስማማት እንደሚገባው ተመልክቷል፡፡

10.1.2 በመዝገብ ላይ የሰፈሩት ንብረቶች በእውን መኖራቸውንና ተገቢውን እንክብካቤ የሚደረግላቸው ስለመሆኑ ለማረጋገጥ የሚያስችል የቋሚ ንብረት ቆጠራ አድርገው የማያውቁ ድርጅቶች መኖራቸው ሌላው ችግር ነው፡፡ አንዳንድ ድርጅቶች ደግሞ ከፊል ቆጠራ ብቻ ማድረጋቸውና ሌሎች ድርጅቶች ደግሞ ቆጠራ ቢያካሂዱም የቆጠራው ውጤት ከቋሚ ንብረት እና ከሂሣብ መዛግብት ጋር ስለማይመሳከር ቆጠራውን ማካሄድ ትርጉም እንዳይኖረው አድርጎታል፡፡

10.1.3 ቋሚ ንብረቶች ከአንድ ድርጅት ወደ ሌላ በማናቸውም መልክ ሲዛወሩ ርክክቡ በተገቢው ሥነ-ስርዓት ባለመፈፀሙና በሰነድ ያልተደገፈ በመሆኑ ምክንያት ቋሚ ንብረቶቹ በተረካቢውም ሆነ በአስረካቢው ድርጅት የሂሣብ መዝገብ ውስጠ በአንዳንድ ድርጅቶች በትክክል አይመዘገቡም ወይም ከመዝገብ አይሰረዙም፡፡ ስለዚህ ርክክቡ በሥነ-ሥርዓት እንዲጠናቀቅና መዛግብቱም ይህንኑ ርክክብ እንዲያንፀባርቁ ይደረግ ዘንድ አሰፈላጊው ማሳሰቢያ ተሰጥቷል፡፡

10.1.4 አንዳንድ ድርጅቶች ለቋሚ ንብረቶቻቸው ደህንነት የገዙት የመድን ዋስትና በቂ ያልሆነና በአደጋ ጊዜ ሊደርስ የሚችለውን ጥፋት ሙሉ በሙሉ ሊሸፍን የማይችል ሲሆን፣ ሌሎች ደግሞ ለንብረቶቻቸው ምንም የመድን ዋስትና ያልገቡ መሆኑ ታውቋል፡፡ በመሆኑም እነዚህ ድርጅቶች በአደጋ ወቅት ሊደርስ ከሚችል ኪሣራና በቂ የመተኪያ ገንዘብ በማጣት ከሚፈጠረው የሥራ መተጓጐል ለመዳን እንዲችሉ ተመጣጣኝ የመድን ዋስትና መግዛት እንዳለባቸው ተጠቁሟል፡፡

10.1.5 በቋሚነት መመዝገብ ያለባቸው ዕቃዎች ዋጋ ከስንት ብር በላይ መሆን እንዳለበት ወይም የትኞቹ ንብረቶች በቋሚነት መያዝ እንዳለባቸው በውል ያልተገለፀባቸው ድርጅቶችም አጋጥመዋል፡፡ ይህ ችግር የተከሰተው የካፒታላይዜሽን ፖሊሲ (Capitalization Policy) ባለመኖሩ ስለሆነ ድርጅቶች ለቋሚ ንብረት አንድ ወጥ የሆነ አያያዝ እንዲኖራቸውም ተገቢውን እንክብካቤና ጥበቃ መደረጉን ለማረጋገጥ ሆነ ተገቢው የአገልግሎት ቅናሽ እንዲሰላና የዓመቱ ወጪ በአግባቡ እንዲተመን

ማድረግ የቋሚ ንብረት አመዘጋገብ መመያ (Capitalization) Policy) እንዲኖራቸው ምክረ ሀሳብ ተሰጥቷል፡፡

10.1.6 በአንዳንድ ድርጅቶቹ ሥር የሚገኙ እንደ መኪና የመሳሰሉት ቋሚ ንብረቶች የባለቤትነት ደብተር ቀደም ብለው በባለቤትነት በያዟቸው ድርጅቶች ስም ተመዝግበው እንደሚገኙ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይህ አሠራር ትክክለኛ ስላልሆነ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ድርጅቶች በአስቸኳይ ተሽከርካሪዎችን በስማቸው አስመዝግበው የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር እንዲያወጡ ማሳሰቢያ ተሰጥቷል፡፡

10.1.7 አንዳንድ ቋሚ ንብረቶች በተለይ ተሽከርካሪዎች በእርጅናም ይሁን መለዋወጫ ዕቃዎች ባለመኖሩ ለአመታት ለፀሃይና ለዝናብ በተጋለጠ ሁኔታ በአንዳንድ መ/ቤቶች ቅጥር ግቢዎች ውስጥ ቆመው ይታያሉ፡፡እነዚህ ሊጠገኑ ከቻሉ መጠገን ፣ ካለበለዚያ ደግሞ በጨረታ በመሸጥ ከተጨማሪ ብክነት መከላከል እንደሚገባ አስተያየት ተሰጥቷል፡፡

10.1.8 ከድርጅቶች ግዢ ጋር በተያያዘ ተገቢ ያልሆኑ የሂሳብ አመዘጋገብ ሂደቶች የተስተዋሉ ሲሆን፣ በተለይ የግዢው ዋጋ ከሚገዛቸው ድርጅት ጋር የነበረን የባንክ ብድር የሚያጠቃልል ሆኖ እያለ ዕቃውን መዝገብ ላይ ያለማስፈር እና የተገዙት ድረጅቶችና ንብረቶች በገቢያ ዋጋ ባለመመዝገባቸው የተነሳ ከግዢው ጋር በተያያዘ የሚፈጠሩትን ግዙፋዊ ሕልዎት የሌላቸው ንብረቶች (Intangible assets /goodwill) ያለመመዝገብ ወይም በተዛባ ዋጋ መመዝገብ፣ የግዢና የሽያጭ ስምምነቶችን ያለማቅረብ ወይንም ለማቅረብ ፍላጎት ያለመኖር ሁኔታዎች ታይተዋል፡፡

10.1.9 በሂሣብ መግለጫዎች ውስጥ የሚታዩ ግዙፋዊ ህልዎት የሌላቸው ንብረቶች እንዴት እንደተፈጠሩ ዋጋቸው እንዴት እንደተተመነ የሚያሳዩ ማስረጃዎች ያለመገኘት ሁኔታዎች ተሰተውለዋል፡፡

10.2.0 በመጋዘን ያሉ ዕቃዎች (Stocks)

10.2.1 አንዳንድ ድርጅቶች በበጀት በዓመቱ መጨረሻ በቆጠራ የተገኙት ዕቃዎች በሂሣብ መዛግብት ውስጥ ከሚታዩት ጋር አመሳክረው በጉድለት ወይም በብልጫ የሚገኙትን ልዩነት የጉድለቱ ወይንም የብልጫው መንስኤ ምን እንደሆነ ለማወቅና ወደፊትም ቢሆን ተመሳሳይ ስሕተት እንዳይፈፀም በማድረግ የእርምት እርምጃ ከመውሰድ ይልቅ በቀጥታ እንደ ዓመታዊ ወጪ ወይም ገቢ ይመዘግቡታል፡፡ ከፊሎቹ ደግሞ በተሰብሳቢ ወይም በተከፋይ ሂሣብ ውስጥ በተንጠልጣይ ሂሳብ (Suspense) እንደሚይዙና ከዓመት ወደ ዓመት እንደሚዘዋወር ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ዕቃዎቹን በዓመቱ መጨረሻ ቆጥሮ የዕቃዎችን እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር ከተያዘው የክምችት ወይም የሂሣብ መዝገብ ጋር ማወዳደሩ ብቻውን ምንም ጥቅም ስለማይሰጥ ልዩነት ካለ የልዩነቱን መንስኤ መርምሮ ማወቅና አስፈላጊውን የእርምት እርምጃ መውሰድ የሚገባ መሆኑ ተገልጿል፡፡

10.2.2 በአንዳንድ ድርጅቶች በብልሽትና በተለያዩ ምክንያቶች ጥቅም ላይ ሳይውሉ ለረዥም ጊዜያት የቆዩ ዕቃዎች እንዳሉ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ለእንደዚህ ያሉ ዕቃዎች መጠባበቂያ መያዝ እንደሚገባቸው ማሳሰቢያ ከመስጠቱም በላይ ጥቅም ላይ የማይውሉ መሆኑ ከተረጋገጠ የበላይ ኃላፊዎችን በማስፈቀድ በሽያጭ ማስወገድ እንደሚገባ አስተያየት ተሰጥቷል፡፡ በተጨማሪም አንዳንድ ድርጅቶች ለረዥም ጊዜ የቆዩ ዕቃዎችን በዓመታዊ ቆጠራ ወቅት በዝርዝር ባለመያዛቸው ለነዚህ መጠባበቂያ ተብሎ በየመዝገባቸው የሚታየው ሂሣብ በቂ መሆን አለመሆኑን ለመገመት አልተቻለም፡፡ ስለዚህ በዓመታዊ ቆጠራ ጊዜ የዕቃዎቹ ሁኔታ በትክክል በቆጠራ መዝገቡ ላይ እንዲገለጽ የሚያስፈልግ መሆኑን ተጠቁሟል፡፡

10.2.3 ከውጪ አገር ለሚገዙ ዕቃዎች የሚደረገው ወጪ ዕቃዋቹ እስከሚደርሱ ድረስ በጉዞ ላይ ያሉ ዕቃዎች በሚል ሂሣብ ውስጠ ይመዘገባሉ፡፡ ዕቃዎቹ ከታዘዙና ዋጋው ከተከፈለ በኋላ እጅግ ቢዘገይ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ እንደሚደርስ የሚገመት ቢሆንም በአንዳንድ ድርጅቶች እንደታየው ግን በጉዞ ላይ የሚገኙ ዕቃዎች ተብሎ ከዓመትና ከሁለት ዓመት በላይ የቆዩ ሂሣቦች ሲኖሩ አንዳንዶቹ ደግሞ በሰነድ የተደገፉ ሆነው አልተገኙም፡፡ ከላይ ለተጠቀሱት ድክመቶች መንስኤ ከሚሆኑት

መካከል የገዥ ትዕዛዝ ከተላለፈበት ጊዜ ጀምሮ ሥርዓት ባለው ሁኔታ ክትትል ተደርጐ ዕቃዎቹ መጋዘን መግባታቸውን አለማረጋገጥ፤ የተበላሹ ወይም የጠፉ ዕቃዎች መኖራቸውን ለማወቅ ተገቢውን ጥረት አለማድረግና ለጠፉም ሆነ ለተበላሹ ዕቃዎች በጊዜው የመድን ካሣ አለመጠየቅ በመሆናቸው በዚህ ረገድ ያለው አሠራር እንዲሻሻልና ያጋጠሙ ድክመቶችም እንዲታረሙ የሙያ ምክር ተሰጥቷል፡፡

10.2.4 በአንዳንድ ድርጅቶች ዕቃዎች ለምርት ሂደት ወይም ለሌላ አገልግሎት ያልዋሉና በየጊዜው እንቅስቃሴ ሳያሳዩ ለረዥም ጊዜ ከመቆየታቸው የተነሳ ጥቅም ላይ ወይም ለምርት ተግባር ስለማይውሉ በቆይታ ሂደት የሚያጋጥማቸውን የጥቅም መቀነስ (Impairment) የሚያሳይ የሂሣብ መጠባበቂያ (Provision) እንዲያዝላቸው አልተደረገም፡፡ በዚህም ምክንያት በግምጃ ቤት ያለ ንብረት ዋጋ ሥራ ላይ ሊውሉ የማይችሉ ንብረቶችን በመጨመሩ የንብረቱ ዋጋ በዚያኑ መጠን ስለሚንር አያያዙ እንዲስተካከል ምክር ተሰጥቷል፡፡

10.3.0 ተሰብሳቢ ሂሣቦች (Receivables)

10.3.1 አንዳንዶቹ ድርጅቶች በብዙ መቶ ሺህ እና በሚሊዮን የሚቆጠሩ ተሰብሳቢ ሂሣቦች ሳይሰበሰቡ ከዓመት ወደ ዓመት እንደሚሸጋገሩና ጊዜው እየረዘመ በሄደ ቁጥር ባለዕቃዎችን በውዴታ ወይም በሕጋዊ መንገድ ለማስከፈል ችግር መፍጠሩ ታይቷል፡፡ ይህ ችግር ያለባቸው ድርጅቶች ሁሉ ተገቢውን ጥረት በማድረግ በውዝፍ ያሉትን ሂሳቦች ገቢ እንዲያደርጉና ለወደፊቱም ለተሰብሳቢ ሂሣቦች ተገቢውን ትኩረት በመስጠት ሂሣቦችን በወቅቱ በመሰብሰብ ከኪሳራ ለመዳን አስፈላጊውን ጥረት ማድረግ እንዳለባቸው ተገልጾላቸዋል፡፡ ተሰብሳቢነታቸው አጠራጣሪ ለሆኑም ሂሣቦች በቂ መጠባበቂያ (Provision) ሊያዝላቸው የሚገባ መሆኑም ተገልጿል፡፡

10.3.2 አንዳንድ ድርጅቶች ተሰብሳቢ ብለው ከያዙት ሂሣብ ውስጥ ከማን መሰብሰብ እንዳለባቸው የማይታወቁ ሂሣቦች መኖራቸው ተደርሶበታል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ በቂ ዝርዝር ያለመያዝ ሁኔታ ለምዝበራ መንገድ ስለሚከፍት ተገቢውን ጥረት በማድረግ

የባለዕዳዎቹ ዝርዝር ወጥቶ ገንዘቡ እንዲሰበሰብ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን እንዲገነዘቡ ማሳሰቢያ ተሰጥቷል፡፡

10.3.3 አንዳንድ ተመርማሪዎች የሂሣብ ግንኙነት ካላቸው መንግሥታዊ ' የግል ድርጅቶችንና የግለሰቦችን የተሟላ አድራሻ ባለመያዛቸው በምርመራው ወቅት ለተመረጡት ድርጅቶችና ግለሰቦች በሙሉ በዓመቱ መጨረሻ የነበረውን ሂሣብ በቀጥታ ለሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን በመግለጽ እንዲያረጋግጡ መጠየቅ ያልተቻለ ሲሆን፣ የሚጠየቁትም ቢሆን ከበርካታዎቹ ምላሽ ማግኘት ሳይቻል ቀርቷል፡፡ መልስ ከተገኘላቸው መጠይቆች መካከልም አንዳንዶቹ የሂሣብ ማረጋገጫው ከተመርማሪው ድርጅቶች የሂሣብ መዛግብት ጋር ልዩነት እንዳላቸውም ታይቷል፡፡ ስለዚህ ድርጅቶቹ የተሰብሳቢ ሂሣቦችን በሚመለከት የድርጅቶችንና የግለሰቦችን የተሟላ አድራሻ እንዲይዙ፣ የሂሣብ ማረጋገጫ መጠይቅ ሲቀርብ መልስ የመስጠት ልምድ እንዲዳብርና የሂሣብ ማስታወቂያዎችም በየጊዜው ከድርጅቶች ጋር በመለዋወጥ ሂሣቦችን ማስታረቅና ማስማማት አስፈላጊ መሆኑን እንዲያውቁ ሙያዊ ምክር ተሰጥቷል፡፡

10.3.4 በአብዛኛዎቹ ድርጅቶች ለሠራተኞች ብድርና ደመወዝ ቅድሚያ መስጠት የተለመደ ቢሆንም አንዳንድ ድርጅቶች ስለብድርም ሆነ ስለቅድሚያ ደመወዝ ክፍያ አወሳሰን፣ አፈ.ቃቀድና አሰባሰብ በሚመለከት መመሪያ የሌላቸው ናቸው፡፡ መመሪያው ያላቸውም ቢሆኑ በትክክል በተግባር ላይ ባለማዋላቸው መጠኑ አነስተኛ የማይባል የመንግሥት ገንዘብ በሠራተኞች ስም በተሰብሳቢ ሂሣብ ይታያል፡፡ ከዚህ ሌላ በተለይ ብድር ያለባቸው ሠራተኞች ከመሥሪያ ቤቱ ሲሰናበቱ ወይም ወደሌላ ድርጅት ሲዛወሩ አስቀድመው ያለባቸውን ዕዳ እንዲከፍሉ ስለማይደረግ ለረዥም ጊዜ የቆዩ ብድሮች ከዓመት ዓመት ሲንከባለሉ ይታያሉ፡፡ እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉትን ችግሮች ለማስወገድ ድርጅቶች ለሠራተኛ ብድር የሚሰጡበትንና የሚሰበስቡትን ዝርዝር መመሪያ እንዲያወጡና መመሪያውን በትክክል ሥራ ላይ እንዲያውሉት አሳስበናል፡፡

10.4.0 <u>በባንክና በካዝና ያለ ገንዘብ</u>

10.4.1 አንዳንድ ድርጅቶች የሚሰበስቡትን ገንዘብ በወቅቱ እንደተሰበሰበ ወደ ባንክ ገቢ እንደሚያደርጉና ከዚህም ገንዘብ ላይ ክፍያዎች እንደሚፈፀሙ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ የዚህ ዓይነት አሠራር ለቁጥጥር የማያመችና ለስህተትም የሚጋብዝ ስለሆነ፤ በየዕለቱ የሚሰበሰብ ገንዘብ ሁሉ ምንም ሳይነካለት ወዲያውኑ ወይም በሚቀጥለው የሥራ ቀን ባንክ ገቢ እንዲደረግ ማሳሰቢያ ተሰጥቷል፡፡

10.4.2 አንዳንድ ድርጅቶች በባንክ ያላቸውን ሂሣብ በየወሩ ከባንክ ከሚላከው የሂሣብ ማስታወቂያ ጋር በወቅቱ በማገናዘብ አያስታርቁም፡፡ በዚህም የተነሳ የየድርጅቱቶቹ መዛግብት የማያውቋቸው የገንዘብ መጠኖች በመኖራቸው ምክንያት መናልባት ከባንክ ሂሣብ አላግባብ ወጭ ቢሆኑ እንኳን በወቅቱ ለማወቅና ለማረም አይቻልም፡፡ በተጨማሪም በርከት ያሉ የሂሣብ ማስታወቂያዎች ላይ ከጊዜ ወደ ጊዜ የተንከባለሉ ረዘም ላለ ጊዜ በድርጅቶቹ በኩል ያልተመዘገቡ የባንክ ገቢና ወጪዎች ይታያሉ፡፡ ስለዚህ በባንክ ያለውን ሂሣብ በትክክል ለመቆጣጠር ከባንዝ የሚላከውን ወርሃዊ የባንክ ሂሣብ ማስታወቂያ የሂሣብ መዝገብ ጋር በየወሩ ማስታረቅና ማስማማት፤ ልዩነቶችንና ስሕተቶችን እንዲሁም አላግባብ ወጪ የሆኑ ሂሣቦች ሲገኙ ወዲያውኑ ተከታትሎ አስፈላጊውን የእርምት እርምጃ መውሰድና መዝገቡንም ማስተካከል የሚያስፈልግ መሆኑን ለሚመለከታቸው ድርጅቶች ተገልያላቸዋል፡፡

10.4.3 አንዳንድ ድርጅቶች በሂሣብ ዘመኑ መጨረሻ በካዝና የነበረውን ጥሬ ገንዘብ አይቆጥሩም፣ ቢቆጥሩም በዓመቱ መጨረሻ የሚደረገው የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ከመዛግብቱ ጋር ስለማይመሳከር ቆጠራውን ጥቅም አልባ ስለሚያደርገው መታረም እንደሚኖርበትና ተመሳክሮ ልዩነት ካለም የልዩነቱን መንስኤ አውቆ አስፈላጊውን የእርምት ርምጃ እንዲወሰዱ ማሳሰቢያ ተሰጥቷል፡፡

10.4.4 በባንክ ያለ ገንዘብ በሚመረመርበት ወቅት ተመርማሪ ድርጅቶች በሂሣብ ዘመኑ መጨረሻ ያላቸውን የገንዘብ መጠን ባንኮቻቸው እንዲያረጋግጡና ሌሎች የተዛመዱ ጉዳዮችንም እንዲያሳውቁ ሲጠየቁ ከባንኮቹ የሚገኘው መልስ አንዳንድ ድርጅቶች

አለን ብለው ከሚያሳዩት የገንዘብ መጠን የተለየ እንደሆነ ማወቅ ስለተቻለ የታዩትን ልዩነቶች ከባንኮቻቸው ጋር በመነጋገር እንዲያስተካክሉ ምክር ተሰጥቷል፡፡

10.5.0 <u>ተከፋይ ሂሣቦች</u> (Payables)

10.5.1 አንዳንድ ድርጅቶች ለመንግሥት መክፈል የሚገባቸውን ግዴታዎች ማለትም ከሠራተኞች ደመወዝ የተቀነሰ የሥራ ግብር፣ የጡረታ መዋጮ እንዲሁም የሽያጭና የንግድ ትርፍ የታክስ ሕጉ በሚያዘው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለግብር ሰብሳቢው መ/ቤት ክፍያ በወቅቱ እንደማይከፍሉ የሂሣብ መዝገባቸው ያሳያል፡፡ ይህ ሁኔታ ማንኛውም ግብር በወቅቱ እንዲከፈል በመንግሥት የተደነገገውን ደንብና ሥርዓት ባለማክበር በድርጅቶች ላይ መቀጫን ሊያስከትል ስለሚችል የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ምክር ተሰጥቷል፡፡

10.5.2 አንዳንድ ድርጅቶች ተከፋይ ብለው ከያዙት ሂሣብ ውስጥ ረዘም ላለ ጊዜ ሳይከፈሉ የቆዩና መክፈል እንዳለባቸው የማይታወቁ ሂሣቦች እንዳሉት ለማወቅ ተችሏል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ በቂ ዝርዝር ያለመያዝ ሁኔታ ለምዝበራና ብኩንነት መንገድ ስለሚከፍት በተከፋይ ሂሣቦች አኳያ ሊኖር የሚገባውን የውስጥ ቁጥጥር የሚያላላ በመሆኑ አስፈላጊውን ጥረት በማድረግ የተከፋይ ድርጅቶችን ወይም የግለሰቦችን ዝርዝር በማውጣት ክፍያዎችን በወቅቱ እንዲፈጽሙ ተገልጿል፡፡

10.6.0 በዋና መ/ቤቶችና በሥሩ በሚገኙ ቅርንጫፍ /ቤቶች ወይም ድርጅቶች መካከል ስላሉ ሂሳቦች

10.6.1 በአንዳንድ መ/ቤቶችና በስራቸው በሚገኙ ቅርንጫፎች ወይም ድርጅቶች መካከል ባሉ ሂሳቦች ላይ አጥጋቢ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓትን ተገቢ የአሰራር ስርዓቶች ባለመዘጋታቸው ምክንያት የሂሣብ ያለመታረቅ ችግሮች ከመከሰታቸውም በተጨማሪ ለሙስና እና ስርቆት የሚያጋልጡ ሁኔታዎች በመሆናቸው አግባብ ያለው ስርዓት እንዲዘረጋና ሂሳቦች በየጊዜው እንዲታረቁ አስተያየት ተሰጥቷል፡፡

10.7.0 ልዩ ልዩ

10.7.1 በአንዳንድ ድርጅቶች የሚታየው የሂሣብ ሰነዶች ቁጥጥርና ጥበቃ አጥጋቢ አይደለም፡፡ በዚህም የተነሳ በምርመራ ጊዜ አንዳንድ ደጋፊ ሰነዶች ሊቀርቡ አልቻሉም፡፡ ሂሣቡን በሚገባ ለማስመርመርና ሂሣቡን በሚመለከት ወደፊት ሊነሱ የሚችሉ ጥያቄዎችን በማስረጃ ለመመለስ፣ የሂሣብ ሰነዶች በስርዓት፣ በእንክብካቤና ሲፈለጉም በቀላሉ ሊገኙ በሚችሉበት ሁኔታ መያዝ እንዳለባቸው ምክር ተሰጥቷል፡፡

10.7.2 በአንዳንድ ድርጅቶች ውስጥ ጆርናል ቫውቸሮች በሂሣብ ሠራተኞች ከተዘጋጁ በኋላ ተገቢው የሥራ ኃላፊ ተመልክቶትና ትክክለኛነታቸውን መርምሮ ሳያፀድቅ በሂሣብ መዝገብ እንደሚመዘገቡ ታውቋል፡፡ ማናቸውም የሂሣብ ማስተካከያዎች በጆርናል ቫውቸሮች አማካይነት ስለሚፈፀሙ በቫውቸሮቹ አጠቃቀም ላይ ያለው ቁጥጥር ካልተጠናከረ ለማጭበርበርና የሂሣብ መዛባት መንገድ ስለሚከፍት ጥንቃቄ እንዲደረግ ሐሳብ ተሰጥቷል፡፡

10.7.3 በአንዳንድ ድርጅቶች ከክፍያ ሰነድ ጋር የተያያዙ የወጪ ደጋፊ ደረሰኞች የተወራረዱ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ምንም ዓይነት ምልክት አይደረግባቸውም፡፡ እንዲህ ዓይነቱ አሠራር አግባብ ባለመሆኑ የወጪ ማረጋገጫ ደረሰኞች በተደጋጋሚ ለሂሣብ ማወራረጃነት እንዳይውሉ ቀደም ብሎ አገልግሎት ላይ የዋሉ መሆናቸውን የሚገልጽ ተከፍሏል ወይም ተወራርዷል የሚል መለያ እንዲደረግላቸው አስተያየት ተሰጥቷል፡፡

10.7.4 አልፎ አልፎ የሠራተኞችን የግል ማህደር በተሟላ ሁኔታ ያልያዙ ድርጅቶች አጋጥመዋል፡፡ የትምህርት፣ የደረጃ ዕድገት፣ የደመወዝ ጭማሪ፣ የዝውውርና ሌሎችንም ሠራተኛውን የሚመለከቱ ማስረጃዎች ተሟልተው እንዲያዙ አስተያየት ተሰጥቷል፡፡

10.7.5 አንዳንድ ግብይቶች (Transactions) በተሳሳተ የሂሣብ መለያ የተመዘገቡ ወይም በትክክለኛው የሂሣብ ቋት ውስጥ ያልተመዘገቡ (Coding and Posting Error) ሆነው በመገኘታቸው የሂሣብ መለያዎች በትክክል ስለመፃፋቸውና በትክክለኛው

ሂሣብ ቋት ስለመመዝገባቸው ካዘጋጀው ሰው የተለየ ከፍ ያለ የሥራ ኃላፊነት ባለው ሰው መረጋገጥ እንደሚገባው አስተያየት ተሰጥቷል፡፡

10.7.6 አብዛኛውን ጊዜ ረቂቅ የሂሣብ መግለጫዎች በጥንቃቄ ባለመዘጋጀታቸው ምክንያት በሂሣብ ምርመራ ወቅት ስህተቶችን ለማረም ተደጋጋሚ ማስተካከያዎች (Adjustment) የሚደረጉ ስለሆነ ፤ እነዚህ ሁኔታዎች ደግሞ የኦዲት ባለሙያዎችን ጊዜ የሚሻሙና የሂሣብ ምርመራውን ጊዜ የሚያራዝሙ መሆናቸው ተገልፆ የሂሣብ መግለጫዎች በጥንቃቄ እንዲዘጋጁ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቷል፡፡

10.7.7 ማስረጃ የሌላቸው በሚሊዮን የሚቆጠሩ ገንዘቦችን የያዙ የሂሣብ ማስተካከያዎች (Adjustments) በአንዳንድ ድርጅቶች የሂሣብ መዛግብት ውስጥ ታይተዋል፡፡

10.7.8 በአንዳንድ ድርጅቶች የቦርድ ሰብሳቢ ቃለ ጉባኤዎች እንዳይመረመሩ ወይም እንዳይታዩ ክልከላ የተደረገባቸው ሁኔታዎችም አጋጥመዋል፡፡

10.8.0 <u>የፕሮጀክቶችና የፕሮግራሞች ሂሣብን በተመለከተ</u>

ከላይ የተጠቀሱት አንዳንዶቹ የሂሣብ አያያዝና የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች በአበዳሪና በለጋሽ አገሮች ድጋፍ የሚካሄዱ ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞችንም የሚመለከት ቢሆንም ፤ ከዚህ በተለየ መልኩ በአንዳንድ መ/ቤቶች ላይ ያጋጠሙ ጎላ ጎላ ያሉ ችግሮች ከዚህ እንደሚከተለው ጠቅለል ተደርገው ቀርበዋል፡-

- በክልል ቢሮዎች በሚገኙ የወጪ ደጋፊ ሰነዶች ላይ የሚታዩት የገንዘብ መጠኖችና ለአስፈፃሚ የፌደራል መንግሥት ተቋማት በሚቀርቡ የወጪ ሪፖርቶች (Statements of expenditure-SOEs) ላይ የተመለከቱት የገንዘብ መጠኖች መለያየት፣
- የሥልጠና እና የወርክ ሾፕ ተሳታፊዎች ማንነታቸውን የሚያሳይ መታወቂያና ስልጠናውንና ወርክሾፑን ለመሳተፍ የሚያስችል ውክልና ደብዳቤ ሳይኖራቸው የውሎ አበል ክፍያዎችን መፈፀም፣

- ስልጠና እና ወርክሾፕ ተሳታፊዎች መሳተፋቸውን የሚያረጋግጥ በተሳታፊዎቹ የተፈረሙ የጊዜ መቆጣጠሪያ (attendance sheet) ከክፍያ ሰነዶች ጋር ያለማያያዝ፣
- የስልጠና እና የወረክ ሾፕ ተሳታፊዎች በፈረሙት የጊዜ መቆጣጠሪያ ላይ ከተመለከቱት ቀናት በላይ የውሎ አበል ክፍያዎችን መክፈል፣
- ከሥልጠና እና የወርክ ሾፕ ፕሮግራሞች ጋር በተያያዘ አስፈላጊ መረዳዎች ማለትም ስልጠናው ወይንም መርክሾፑ ለምን ያህል ጊዜ እንደቆየ፣ የት ቦታ እንደተካሄደ የሚገልጽ ማስረጃ ከክፍያ ሰነዶች ጋር ያመለያያዝ፣
- ለአንዳንድ ወጪዎች ደጋፊ ሰነዶች ያለመገኘት፤ ወይም ከክፍያ ሰነዶች ጋር ያለመያያዝ፣
- ወጪዎችን በትክክለኛው ጊዜ ያለመመዝገብ (ለምሳሌ ያለፈውን ዓመት ወጪ በዚህኛው ዓመት መመዝገብ)፣

የሚሉት ጎላ ጎላ ያሉት በፕሮጀክቶችና ፕሮግራም ሂሳቦች ላይ የታዩ የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች ሲሆኑ ከላይ የተዘረዘሩት ችግሮች በተለይ በክልል ፣ በዞንና በወረዳ አፈፃፀም ቢሮዎች የሚታዩ በመሆናቸው ለሚመለከታቸው የክልሎች እና የፌደራል አስፈፃሚ ተቋማት ድክመቶችን ለማስወገድ አሰፈላጊውን ጥረት እንዲደረግ ማሳሰቢያ ተሰጥቷል፡፡

9. <u>**አባሪዎች**</u>